# የብልጽግና ወንጌል

ግርማዊ

"የብልጽግና ዶክትሪን የካሪዝማቲክ ሪቫይቫል እጅግ ከፍተኛው አዲስ አሳብ ሆኗል፤ ይህም በመሆኑ ከዚህ ቀደም በፈውስ ላይ ይደረግ የነበረውን አጽንኦት ወደ መተካቱ ተቃርቦአል" (ዴቪድ ሐረስ)።

የሽፋን ሥዕል ጆን ሮዝ

cover design by John Rose


የድርሰት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

All Rights Are Reserved

© 2000 Girmawi



የመጀመሪያው እትም 1990 ዓ.ም

ሁለተኛው እትም 1992 ዓ.ም

(ታርሞና ተሻሽሎ የቀረበ)

አድራሻ

ፖ.ሣ.ቁ. 127

አዲስ አበባ።

ሀብት ጊዜያዊ አቫንጉሊት ነው። ለጊዜው ያጫውተናል። የኋላ ኋላ ግን ባዶ እጃችንን እንደመጣን ባዶ እጃችንን ተመልሰን እንሄዳለን። ስለሆነም ደስ ልንሰኝ የሚገባን ከሞት ጥቁር ጥላ በስቲያ ብሩኅ የሕይወት መንግሥት እንዳለ በመረዳታችንና በክርስቶስ አማካኝነት የዚያ መንግሥት ነዋሪዎች በመሆናችን እንጂ አልፎ ሂያጅ በሆነው ቁሳዊ ሀብት ሊሆን አይገባም። ብዙ ምሁራን ሀብታቸውን፥ ዝናቸውን፥ ትዳራቸውን... ጥለው በመድኃኒት ራሳቸውን ይገላግላሉ – ሞትን ስለፈሩት ዛሬ ነገ መጣ እያሉ ከመስጋት ራሳቸውን ገድለው ያርፋሉ። እናም ደስታ ከሀብት በላቀ መሠረት ላይ መደገፍ አለበት።

ከገንዘብ ይልቅ ልንከታተላቸው የሚገቡንን ዘላለማዊ በረከቶች ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡11–16 ገልጾአል። እነዚህም ጽድቅ–እግዚአብሔርን መምሰል–እምነት–ፍቅር–መጽናናት–ደስታ–የዋህነት ናቸው። እነዚህ በዐለቱ ላይ ስንመሠረት የሚፈልቁ ውብ ፍሬዎች ናቸው! በመንፈስ ቅዱስ አምራችነት እየተሸለቀቁ የክርስቶስን የሕይወት ንጉሥነት የሚያውጁ ማለፊያ በረከቶች! እናም ክርስቲያን ሊያተኩር የሚገባው እዚህ ላይ ነው።

*(ከውስጥ ገጾች...)*

"... ከመስመር የወጡትን ወገኖች መስመር ያስይዛል፤ ሚዛን እንዲጠብቁ ይረዳቸዋል የሚል እምነት አለኝ። እውነተኛ ክርስቲያኖችም በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚቀርብላቸውን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሆኑን ሳይመረምሩ በጭፍን ተቀብለው ከማስተናገድ ያድናቸዋልና መጽሐፉን በእርጋታ ያንብቡት።"

(ሽመልስ አድማሴ – እንጦጦ መካነ ኢየሱስ ቤ/ክ)

"... የዘመኑን አወዛጋቢና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጭብጥ የሌላቸውን የእምነት እንቅስቃሴዎች በሚገባ በማጤን ምርቱን ከገለባው ለመለየት በጽሞና ያንብቡት... "

(ወንጌላዊ ሽፈራው ፈይሳ – ጌጃ ቃ/ሕ/ቤ/ክ)

"... ይህን መጽሐፍ በመደናገር ላይ ያሉ እውነተኛ አማኞች ሁሉ ሊያነቡት ይገባል... "

(ወርቅአገኘሁ ገረመው– ኢቫንጄሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ-ETC)

"... በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በመረጃ ተደግፈው የቀረቡ እውነቶች የብዙዎችን እግሮች ከመሰናከል እንደሚጠብቁ ተስፋ አደርጋለሁ።"

(ጌቱ ግዛው ከአዲስ አበባ ገነት ቤ/ክ)

# ማውጫ

## ምዕራፍና ርእስ–ጉዳይ


ገጽ

መግቢያ ......................................................................... 6

1. ከዊነርስ ቻፕል መጋቢ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ............ 10

2. የነ ሐገን ሬማ ስንክሳራዊ ገጽታዎች ................................ 16

3. ኢየሱስ በሲኦል ዳግም ተወልዶአል? ................................ 22

4. እምነት በእምነት ላይ .................................................... 46

5. ፈውስና ተአምራት ......................................................... 55

6. ብልጽግና ....................................................................... 77

7. የእምነት እንቅስቃሴ የሐገን ወይስ የኬንየን? ...................... 97

8. የእምነት እንቅስቃሴ ኑፋቄያዊ መሠረቶች ........................ 101

9. ኬነት ሐገንና የእምነት እንቅስቃሴ .................................. 109

10. የመገለጥ እውቀት ....................................................... 120

11. የእምነት እንቅስቃሴ ከኒውኤጅ ጋር ሲነጻጸር .................... 125

12. የእምነት እንቅስቃሴና የሳቅ ሪቫይቫል ............................ 133

13. የማጠቃለያ መልእክቶች .............................................. 143

14. የግንዛቤ ማጠናከሪያዎች .............................................. 151

ሜታፊዚክስ ................................................................... 151

ክርስቲያን ሳይንስ ............................................................. 152

ዩኒቲ ........................................................................... 153

ቲዎሶፊ ......................................................................... 155

የአሳብ ሥርቆት ................................................................ 156

የግርጌ ማስታወሻዎች ........................................................ 162

ዋቢ መጻሕፍት .................................................................. 170

ለዚህ እትም ዝግጁነት የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። የኤስ-አይ-ኤም የሚድያ ሠራተኞች ለሥራው ውጤታማነት ላበረከቱት ቅን አገልግሎት ሊመሰገኑ ይገባል።

***

እንደ ምድረ ዓለም ነዋሪ፥ ያለኸው እግዚአብሔር፥ ሰዎችና ቁሳቁሶች ባሉበት ክልል ነው። ስለሆነም እግዚአብሔርን ልታመልክ፥ ሰዎችን ልትወድና ቁሳቁሶችን ልትጠቀም ይገባል። በራስ-ወዳድነት ተገፋፍተህ ይህንኑ ጤናማ ቅደም-ተከተል ብታዛባና ቁሳቁሶችን (ገንዘብን ጨምሮ) ማምለክ ብትጀምር፥ እግዚአብሔርን እንደ ዕቃ ከመጠቀሙ አደገኛ ጫፍ ትደርሳለህ። (ዌርዝቢ - ያሰፈርሁት በራሴ አገላለጽ ነው።)

***

# ውድ ተደራሲያን

"የእምነት እንቅስቃሴ መሠረቶችና መዘዞች" እንደገና "የብልጽግና ወንጌል" በሚል ስያሜ ለኅትመት መብቃቱ የጉዳዩን አሳሳቢነት የሚያስገነዝብ ነው። የመጀመሪያውን ርእስ መቀየር ያስፈለገው በሁለት ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፥ "የእምነት እንቅስቃሴ መሠረቶችና መዘዞች" የሚለው ስያሜ የመጽሐፉን ጭብጥ ፍንትው አድርጎ የማሳየት ብቃት ቢኖረውም፥ ከርዝመቱ የተነሣ ለአጠራር አመች አልሆነም። "የብልጽግና ወንጌል" የሚለው ምንም እንኳ የእንቅስቃሴውን ጠቅላላ ገጽታ ባያንጸባርቅም፥ አሁን አሁን ጎልቶ የሚሰማ ጉዳይ በመሆኑ አጠር ከማለቱ ጋር ተስማሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በሁለተኛ ደረጃ፥ "የብልጽግና ወንጌል" ተብሎ የቀረበው ይኼኛው መጽሐፍ ከአንባብያን አስተያየቶች በመነሣት እንደ ሜታፊዚክስና ክርስቲያን ሳይንስ በመሳሰሉት ጽንሰ–አሳቦች ላይ መጠነኛ ማብራሪያ አካቷል። ስለ ሰው ተፈጥሮም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲወሱ የኖሩትን አመለካከቶች ለመዳሰስ ተሞክሮአል። የዊነርስ ቻፕል አገልጋይ ከሆኑት ከፓስተር ግርማ አሰፋ ጋር ያደረግሁትም ቃለ ምልልስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቃልሎአል። በአንጻሩ ደግሞ ብዙም አስፈላጊዎች አይደሉም የተባሉት ነጥቦች ከዚህኛው ሁለተኛ እትም ውስጥ ተወግደዋል።

በሌላ በኩል፥ ቀደም ሲል በዚህ እንቅስቃሴ ላይ ለተዘጋጀው መጽሐፍ ብዙ ምላሾች እንደደረሱኝ ለመግለጽ እፈልጋለሁ። ደብዳቤዎቼን እየጠቀሱ ዝርዝር ነጥቦችን ማንሣቱ ገጾቹን እንዳይፈጅብኝ በመስጋት ብተወውም፥ በአጠቃላይ ገንቢ አስተያየቶች እንደደረሱኝ በመግለጽ ለጻፉልኝ ወገኖች ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አስተያየታችሁም ሆነ በዚህ መጽሐፍ ዙሪያ ስለተነሡት ጉዳዮች ያደረሳችሁኝ መረጃ ሁሉ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው። ወደፊትም ተመሳሳይ ድጋፋችሁን እጠብቃለሁ።

ከደረሱኝ አስተያየቶች የጸጋ ስጦታ እንዳበቃና በአሁኑ ዘመን የማይሠራ መሆኑን የገለጹልኝም ነበሩ። ይህ ግን ከእኔ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ ጋር አብሮ የሚኼድ አሳብ አይደለም። እኔ እንደማምነው መንፈስ ቅዱስም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ካሪዝማቲክ አብያተ ክርስቲያናት አስፈላጊዎች ናቸው። ምክኮነል "ሌላ ወንጌል" (A Different Gospel) በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው፥ "ካሪዝማቲክ ተሐድሶን መቃወም ይህንኑ እንቅስቃሴ ያስገኘውን መንፈስ ቅዱስ ከመቃወም ተለይቶ እንደማይታይ" እንደገለጹ ሁሉ፥ እኔም ለአንባቢዎቼ ይህንኑ ለመድገም እሻለሁ። _ትናንት በክርስቶስና በሐዋርያቱ ዘመን የሠራው መንፈስ ቅዱስ ዛሬም የክርስቶስን አካል በማነጽ ላይ እንደሚገኝ በእጅጉ አምናለሁ።_ የጽሑፌ ዓላማም በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ ዙሪያ የሚከሰቱትን ህፀፆች መንቀስ እንጂ ቤተ ክርስቲያን ሕያው ሆና እንድትንቀሳቀስ የሚያደርገውን የሕይወት መንፈስ መጋፋት አይደለም።

ይህንንም ለማለት ያስደፈረኝ በመናፍቅነት ጎራ ያጎርሁት ዘመነኛው የእምነት እንቅስቃሴ (Faith Movement) በአንዳንድ ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ጎልቶ በሚታይባቸው አካባቢዎች በሰፋት ተቀባይነትን እያገኘ መምጣቱን መረዳቴ ነው። ምንም እንኳ ብዙዎች የእምነት ሥነ-መለኮት ከፔንተኮስታል ካሪዝማቲክ እንቅስቃሴዎች እንደመነጨ ቢገምቱም፥ ይኼ ግምት በታሪክ ምስክርነት ሊረጋገጥ አይችልም... ታሪካዊ መሠረቱ ኑፋቄያዊ ነው - ከውስጥ ገጾች እንደምንመለከተው። የእምነቱ መሥራች የሆኑት ኢ. ደብልዩ ኬንየን ራሳቸው የሚታፊዚክስ "ምሩቅ" ነበሩ። ይህም ሚታፊዚክስ ጥንታዊው የነ አርስቶትል ፍልስፍና አካል ሲሆን፥ በቀደምት መመሪያዎች በተለይም በኑባሬና በእውቀት ላይ የሚመሠረትና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የጎደለው አስተሳሰብ ነው። (ማብራሪያውን ከውስጥ ገጾች ያገኛሉ።)

ምክኮነል ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፋቸው እንዳረጋገጡት፥ የካሪዝማ መጽሔት "የእምነት እንቅስቃሴ አባት" እያለ የሚያንቆለጳጵሳቸው ኬነት ሐገን፥ የኬንየንን አሳቦች ወስደው የራሴ ናቸው ሲሉ አውጀዋል። ይህ ደግሞ በሥነ-ጽሑፍ ዓለም እጅግ አሳፋሪ ሥርቆት እንደሆነ ግልጽ ነው።

"ክርስትና በቀውስ ውስጥ" (Christianity in Crisis) የሚል መጽሐፍ ያሳተሙት ሐንክ ሐንግራፍ ካሪዝማቲኮችና ወንጌላውያን በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አጠቃቀም ላይ እንደሚለያዩ ከገለጹ በኋላ፥

*"የእምነት እንቅስቃሴ ግን እንዲህ አይደለም... የእምነት እንቅስቃሴ የክርስትናን ዓይነተኛ ባህርይ በማጣመም የተጭበረበረ ክርስትናና የተጭበረበረ ክርስቶስ ያቀርብልናል። ስለሆነም፥ የእምነት እንቅስቃሴን ሥነ-መለኮት መቃወም አማኞችን ከመከፋፈል ይልቅ አንድ የማድረግ ሚና ይኖረዋል። በአሁኑ ወቅት ክርስቲያኖች የሚጋፈጡት የእምነት እንቅስቃሴ ቀውስ፥ በካሪዝማቲኮችና ካሪዝማቲኮች ባልሆኑት መካከል በሚደረግ የቃላት ጨዋታ የሚታለፍ ሳይሆን፥ <u>የሞትና የሕይወት፥ የትክክለኛ እምነትና የኑፋቄ፥ ብሎም የክርስቶስ መንግሥትና የመናፍቃን መንግሥት ጉዳይ ነው</u>"* ብለዋል።

የዚህን አሳብ እውነተኛነት ደግሞ ካለፈው መጽሐፍ ልምድ በግብር ልመለከት ችያለሁ። ፔንተኮስታሎችም ሆኑ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይህንኑ መጽሐፍ በመጠቀም ምእመኖቻቸውን ሲያስተምሩ እንደነበር ተገንዝቤአለሁ። እናም በአንድነት ተባብረን ለእውነት መቆማችን አስደስቶኛል።

የኑፋቄ ትምህርት ዓይነተኛው ችግር እውነተኛ መስሎ መቅረቡ ነው። ቋንቋቸው የእኛን ቋንቋ ይመስላል። ለምሳሌ፥ "የእምነት እንቅስቃሴ" ሲባል ለጆሮአችን የሚጥም ይመስላል። "የእምነት ቃል" የሚለው የዚህ እንቅስቃሴ መሪ ሐረግም ራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ መሆኑ ግልጽ ነው (ሮሜ 10፡8)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው "የእምነት ቃል" ስለ ክርስቶስ አዳኝነት የሚሰበከውን ወንጌል የሚያመለክት ሲሆን፥ የነ ሐገን የእምነት ቃል ግን የአዎንታዊ አስተሳሰብን ፍልስፍና (Positive confession) የሚከተል

መሆኑን መለየት የሚቻለው እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን አስተውለው ሲያጠኑ ብቻ ነው።

*"የኑፋቄ ተማሪ የሆነ ሰው የቃላትን የቋንቋ ግርኛ ለመመዘን መዘጋጀት አለበት። መጀመሪያ የዚህ ዓይነቱ ግርዶሽ እንደሚኖር መገንዘብ አለበት! ቀጥሎም፥ ቃላቱ ካልተፍታቱ በመናፍቃኑ አስተምህሮና በእውነተኛ ክርስትና መካከል ያለው ልዩነት እንደሚደበቁበት መገንዘብ አለበት።"*

ሬይንሃርድ ቦንኬም "ሆልማርክስ ኦፍ ፔንተኮስት" ለሚለው መጽሐፍ በጻፉት መቅደም ውስጥ የሚከተለውን እውነት አስቀምጠዋል።

*"አደገኛው ነገር የሚከሰተው የሰይጣን ማታለያዎች የጌታን ድንቆች ሊመስሉ ስለሚችሉ ነው። እነዚህም የአስመሳዮች ምልክቶችና ድንቆች በአማኞች ከግልጋሎት ሊውሉ ይችላሉ። የተመረጡትን እንኳ ሳይቀር ለማታለል የውሸት ምልክቶችና ድንቆች እየተደረጉ ናቸው።"*

በመሆኑም፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች ላይ ላዩን "እምነት፥ ፈውስ፥ ብልጽግና" እያሉ ውስጥ–ውስጡን ምን እንደሚያደርጉ የቃላትን የተመሳሳይነት ድንበር ዘልቀን እንመለከታለን።

ብዙዎቹ የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች የክርስቲያን ካባ ደርበው በመቅረብ፥ የበርካታ ወገኖችን ሕይወት ለአደጋ ሲዳርጉ አይቶ ዝም ማለቱ ከክፋት ጋር የመተባበርን ያህል የከበደ ነገር ነው። በውጭው ዓለም ይኼ እምነት ያስከተላቸውን በርካታ መዘዞች ከውስጥ ገጾች ያገኙታል። በአዲስ አበባችንም ተመሳሳይ ችግሮች መከሰታቸው በግልጽ እየታየ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ባጠቃላይ የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ግራ ተጋብተው ብዙዎችን ግራ በማጋባት ላይ መሆናቸውን ይህንኑ ጥናት በማከናውንበት ወቅት ለመታዘብ ችያለሁ። ለአእምሮ መታወክ የተጋለጡም እንዳሉ ይሰማል። ይህንን ስንመለከት፥ ጂም በከር ንስሐ ከገባ በኋላ "እግዚአብሔር ባይገናኘኝ ኖሮ እብድ እሆን ነበር" ያለው አሳብ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

ለማንኛውም፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለዚሁ የዘመኑ የእምነት እንቅስቃሴ ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጽታ ቀጥለን እንመለከታለን። ተደራሲያንን አደራ የምለው ይህ ፍልስፍናን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚያዳብል ከባድ ጉዳይ በመሆኑ የመሰላቸውን ከመናገር ወይም ሌሎች በተናገሩት አስተያየት ከመስጠት እንዲታቀቡና መጽሐፉን ራሳቸው እንዲያነቡት ነው። ካነበቡት በኋላ ለማንም ሳያዳሉ እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ እንዲወስዱ በአክብሮት እጠይቃለሁ። ሁላችንም መከተል የሚኖርብን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተቀመጠውን የእግዚአብሔርን እውነት እንጂ የእኔን ወይም የብልጽግና ሰባኪዎችን ፍልስፍና ሊሆን አይገባም።

በሌላ በኩል፥ ከእኛ አሳብ የሚቃረን እውነት ሲቀርብ በጥሞና አመዛዝኖ እንደመፍረድ፥ በችኮላ ነገሮችን ልናበላሽ አይገባም። ይህንንም የምለው ሰዎች እነርሱ የሚደግፉአቸውን አገልጋዮች ስህተት የሚያሳዩ ወይም እነርሱ የሚያምኑበትን አሳብ መሠረተ–ቢስነት የሚጠቁሙ ጽሑፎችን አጥብቀው

እንደሚያጥላሉ ከራሴም ሆነ ከሌሎች ገጠመኞች ያየሁት እውነት በመሆኑ ነው። ከክርስቲያን በማይጠበቅ ሁኔታ ለስድብና ለድብድብ የሚነሣሡ ሰዎችም አጋጥመውናል።

ይህም ሆኖ፥ ቢል ኮስቢ እንደሚለው፥ "የውድቀት ቁልፉ ሁሉንም ሰው ለማስደሰት የሚደረግ ጥረት" እንደሆነ ስለማምን፥ የነዚህን ወገኖች ነቀፋ ወደ ጎን ትቼ ብዙዎችን ከጥፋት ለመመለስ ይረዳል ያልሁትን አሳብ በዚህ መጽሐፍ አካትቼ አቅርቤአለሁ። እርስዎም እንደ ቤሪያ ሰዎች (የሐዋ. 17፡11) በጽሞና አንብበው ለእውነት እንዲወስኑ በአክብሮት እጠይቃለሁ። ለማንኛውም ጥያቄና አስተያየት ልባችን ክፍት ነው።

ጸሐፊው

# 1

# ከዊነርስ ቻፕል ፓስተር ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

*"ኢየሱስን ወደ ሕይወትህ ባስገባህ ቅጽበት ከድህነት፥ ከበሽታና ከመንፈሳዊ ሞት ትድናለህ!" (የኬነት ሐገንን የቪድዮ ካሴት ለማሻሻጥ ከ"Word of Faith" መጽሔት ጀርባ የወጣ ማስታወቂያ – ጃንወሪ 1996።)*

***

*"በፊት በእግሬ እሄድ ነበር። አሁን ግን ኮንትራት ታክሲ እጠቀማለሁ" (ፓስተር ግርማ አሰፋ)።*

***

በመጀመሪያ ደረጃ ወደ ዊነርስ ቻፕል በመሄድ ከፓስተሩ ጋር የተወያየሁት ስለ ሃይማኖቱ አመሠራረትና ዶክትሪን ለትምህርት ቤት ጥናታዊ ዘገባ እንዳቀርብ በታዘዝሁት መሠረት ነበር። በታህሣሥ 1992 (በእኛ አቆጣጠር) ይህንኑ ጥናት ለኢትዮጵያ የድኅረ ምረቃ ሥነ–መለኮት ትምህርት ቤት (Ethiopian Graduate School of Theology - EGST) 'Independent Churches in Africa' ለተባለው ክፍል አቅርቤ ውይይት ተካሂዶአል። አሁን ደግሞ ከዚህ የሁለተኛ እትም ሥራ ውስጥ ማካተቱ ለሥራው ተጨባጭነት ጠቃሚ ሚና እንደሚኖረው በማሰብ እንደሚከተለው አጠር አድርጌ አቅርቤአለሁ።

## የዊነርስ ቻፕል አመሠራረት

"The Apostle" በሚል ርእስ ስለ ዴቪድ ኦዬዴፖ የገለጸ አንድ በራሪ ወረቀት እንደሚለው፥

*"ዶ/ር ዴቪድ ኦዩዴፖ በአንድ ሆቴል ውስጥ እንግዳ ሆነው ሳሉ ጌታ እጅግ በርካታ አፍሪካውያን በጉስቁልና፥ በበሽታ፥ በተስፋ መቁረጥና በምስኪንነት እየማቀቁ መሆናቸውን አሳያቸው። በዚህም ኀዘን ገብቶአቸው ሲያዝኑ ጌታ፥ 'የእምነትን ቃል (Word of Faith) በመስበክ ዓለምን ከዲያብሎስ ጭቆናዎች*

ሁሉ የምታድንበት ሰዓት ደርሶአል። እኔም የዚህ ተግባር ተካፋይ ትሆን ዘንድ አልክሃለሁ' ሲል ተናገራቸው።

"በዚህ ዓይነት ነበር ወደ ሚያዝያ 1981 አካባቢ 'የእምነት ነጻነት ሰዓት' (Faith Liberation Hour) በሚል ስያሜ ይህ አገልግሎት የተጀመረው... "[1]

አገልግሎቱ በዚህ መልክ ተጀምሮ እየተስፋፋ መምጣቱንና ብዙዎችን "ከመዋዕለንዋያዊ፥ አእምሮአዊና መንፈሳዊ" እስራቶች መፍታቱን ይኸው በራሪ ወረቀት ያስረዳል። ስለዚሁ አገልግሎት ከቀረቡት መረጃዎች መካከል አንዱ የሚከተለው ነው።

"ከናይጀሪያ በስተምዕራብ በምትገኝ አንዲት ከተማ [የከተማይቱ ስም አልተጠቀሰም] አንድ እብድ ከመጻሕፍት መደብር አጠገብ ቆሞ የዴቪድ ኦዩዴፖን ካሴት ያዳምጥ ጀመር። የካሴቱ አንደኛው ጎን ሲያልቅ እብዱ፥ 'ሁለተኛውን ጎን ክፈቱልኝና ልስማ' ሲል ተናገረ። በዚህም ጊዜ ሰውዬው ሙሉ ለሙሉ ከእብደት ነጻ ወጣ።"[2]

ኢትዮጵያዊው ፓስተር ግርማ አሰፋም ስለ ኦዩዴፖ አገልግሎት የሚከተለውን መስክረዋል።

«አገልግሎታቸው ልክ እንደ ሙሴ፥ ኢያሱና ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኸውም የእምነትን ቃል በመስበክ በዲያብሎስ ጭቆና ውስጥ ያሉትን ነጻ ማውጣት ነው።"[3]

የእምነቱ ተከታዮች እንደሚሉት፥

"ዶ/ር ዴቪድ ኦዩዴፖ እጅግ አስደናቂ ምስክርነቶችን ወዳስከተለ ትንቢታዊ ቅባት መግባታቸው ግልጽ ነው። ብዙዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል እውነት የሆነውን ቃላቸውን በማመን በንግዳቸው፥ በቤተሰባቸው፥ በሥራቸው፥ በሰውነታቸው፥ ወዘተ. . . ውጤቶችን በማግኘት ላይ ናቸው። ድንቅ ነው!... "[4] (ያተለቅሁት ነጥቦቹን ለማጉላት ያህል ነው።)

ይኸው የኦዩዴፖ አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ የተሻገረበትን ሁኔታ ፓስተር ግርማ እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል።

"በ1995 ሁለት ፓስተሮች ማለትም ቱንጂና ኬዚ 'አፍሪካን በወንጌል መውረር' (Africa Gospel Invasion Program - AGIP) የሚል ተልእኮ ይዘው ወደ አዲስ አበባ መጡ።"[5] ይህም "ሌጎስ የሚገኘው 'የዓለም ሚሲዮን ድርጅት' (World Mission Agency - WMA) አካል ሲሆን፥ የእምነትን ቃል በመስበክ አፍሪካን ከኃጢአት፥ ከጉስቁልናና ከጭቆና ነጻ ለማውጣት የተደራጀ ነው።"[6]

ሁለቱ ሚሲዮናውያን ከየአብያተ ክርስቲያናቱ ያሰባሰቡዋቸውን ሰዎች በማስተማር ሥራ ጀመሩ። አብያተ ክርስቲያናት ግን ተቃውሞአቸውን ከማሰማት አልታቀቡም።

ይህንኑ ውዝግብ አንሥተው ፓስተር ግርማ፥

*"እኛ ከሚተባበሩን ጋር አብረን ለመሥራት ፈቃደኞች ነን። በተልእኮአችን አንቀልድም። 'ኤፍ.ኤ.' ማለትም 'እምነት ሠራዊት' የራሱ ተልእኮ አለው። እኛ ግን ገንዘብ ስላለን ገንዘብ እንሰጣቸዋለን። ገንዘብ ከውጭ አይመጣም። እዚሁ ከአባላት እንሰበስባለን። በገንዘባችን የማይቃወሙንን ሰዎች እንረዳለን"*[7] ብለዋል።

ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አስመልክተው ፓስተሩ ሲናገሩ፥

*"ጊዜ ካለን አብረናቸው ለመሥራት ዝግጁዎች ነን። የምናስቀድመው ግን የራሳችንን ሥራ ነው። አንዳንድ ጊዜ ለአገልግሎት ሲጠሩን እንሄዳለን። ብዙውን ጊዜ እኔን ይጠሩኛል። የጸጋ ቃለ ሕይወት፥ ሙሉ ወንጌልና ሌሎችም ይጋብዙናል። በምናገለግልበት ጊዜ እጅግ ይገረሙና 'እንዲህ ዓይነት አገልጋይ እዚህ አገር አለ ወይ?' ብለው ይጠይቃሉ። ነገር ግን ከዊነር መሆናችንን ሲሰሙ ቅር ይላቸዋል"*[8] ብለዋል።

ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር ተስማምቶ መሥራቱ ጠቃሚ መሆኑን ለማሳሰብ በሞከርሁበት ወቅት ፓስተሩ ኢየሱስ እርሱ ዘንድ የመጡትን እንዳገለገለ በመግለጽ ዊነርም ከዚህ የተለየ አሠራር እንደሌለው አስረድተዋል።

በውይይታችን መሀል ለኬነት ሐገን አገልግሎት ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው ፓስተሩ፥ "ከኬነት ሐገን ትምህርቶች የምንጥለው ምንም ነገር የለም። ከመጻሕፍቶቻቸው አንዱም እንዲያመልጠን አንፈልግም"[9] ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህ ጊዜ ኬነት ሐገን ክርስቶስ በመንፈሱ እንደሞተ ስለሚያስተምሩበት ሁኔታ ጠይቄአቸው ፓስተሩ በሰፊው ተንትነውልኛል።

*"ኃጢአት በመሥራቱ ምክንያት አዳም በመንፈሱ ሞቷል። ስለዚህም ኢየሱስ በመንፈሱ ሞተ። በሽታ መንፈስ ነው። በመገረፉ ቁስል ተፈውሰናል። መንፈሳዊ ሞት ባይሞት ኖሮ በመስቀሉ ላይ የሞቱት ሌሎች ሰዎች ሊያድኑን ይችሉ ነበር። ይህንን ለማብራራት ግልጽ የሆነ ጥቅስ ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር። አሁን ግን አልመጣልኝም..."*[10]

(ከሥሩ የተሰመረበት በቀጥታ ከኢ. ደብልዩ. ኬንየን መጽሐፍ የተወሰደ አሳብ መሆኑን ስለ አንድነት ሥነ-መልኮት ከምናብራራበት ክፍል ይመልከቱ።)

# ብልጽግና

ፓስተር ግርማ አሰፋ ወደዚህ እምነት ከመጡ በኋላ በኢኮኖሚው ረገድ ሕይወታቸው እንዴት እንደተሻሻለ ሲገልጹ፥ ቀደም ሲል በእግራቸው ይመላለሱ እንደነበርና አሁን ግን የኮንትራት ታክሲ እንደሚጠቀሙ አስረድተዋል። ከዚያም ስለ ብልጽግና ሰፊ አሳብ እንዳገኝ የፓስተር ቱንጂን የንግግር ካሴት (Fundamental Issues About Financial Addition by Rev. Tunji Adeyinka) በአሥራ ሁለት ብር ሸጠውልኛል። ከካሴቱ ያገኘሁትን አሳብ አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ።

## ስለ ገንዘብ መጨመር ሊታወቁ የሚገባቸው ዓበይት ጉዳዮች

ፓስተር ቱንጂ በፈጣን አስተርጓሚያቸው በኩል በሚናገሩበት በዚያ ካሴት ውስጥ ስለ ብልጽግና የሚከተለውን ብለዋል።

*"... የትኛውም ዘር ከመዘራቱ፥ የትኛውም ስኬት ከመቀመሱ በፊት የእግዚአብሔር ቃል መቅደም አለበት (ኢሳ. 66)... ቃል ኪዳኑ ከማንኛውም ቅድመ-ሁኔታ የላቀ ነው። ንግዱ እየተንቀሳቀሰ አልነበረም (ስለ አንዲት ሴት ምስክርነት እየተናገሩ ነበር)። ነገር ግን መንፈሳዊ ኃይላትን ማሠራት ጀመረች። 'ሊያሽቆለቁል አይችልም! ይህ መንፈሳዊ ሕግ ነው! ይኼኔ ሌላ አማኝ ቢሆን 'ሁሉም ነገር እያሽቆለቆለ ነው' ይል ነበር። መንፈሳዊ ኃይልን እንዴት እንደሚታሰሩ ማወቅ አለባችሁ። የመንፈሳዊ ቃል ኪዳንን በረከት ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሁለት ደረጃዎች አሉ።*

*"የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝ። 'ፈቃድህን ላደርግ መጣሁ።' መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል። እርሱን በምትታዘዙበት ጊዜ ሁልጊዜም እርሱ ከናንተ ጋር እንደሆነ የሚያረጋግጥ ዋስትና አላችሁ። ብትወዱና ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ (ኢሳ. 1፡19)። ሁለተኛ መስጠት። ብልጽግና ከመስጠት አይጀምርም። ሳይታዘዙ መስጠት ገንዘብን ማባከን ነው።*

*"የምታገኙት ስለምትሰጡ አይደለም። መስጠት የሚከተሉትን ነገሮች ያከናውናል።* ***መስጠት ለመለኮታዊ ሞገስ የቃል ኪዳን መሣሪያ*** *ነው። የምንሰጠው ሞገሱን ለማግኘት ነው። አንድ ነገር በሕይወታችሁ ውስጥ ሊሠራ የሚችለው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ለገንዘብ ዕድላችን ዋስትና የሚሰጠው የእግዚአብሔር ሞገስ ነው።* ***መስጠት ሞገስን ያመጣል፤ ሞገስ ሁሉም ነገር እንዲሠራልህ ያደርጋል። የገንዘብ መጨመር የመለኮታዊ ሞገስ ተግባር ነው። ይኸውም እግዚአብሔር ሞገሱን እንደሰጠህ ነው...*** *"[11] (በትልቁ የተጻፈው ለአጽንኦት ነው።)*

## የዊነርስ ቻፕል እንቅስቃሴ ከቃሉ አንጻር ሲገመገም

ከፍ ብለን እንደተመለከትነው፥ የዊነርስ ቻፕል የተመሠረተው በኦዬዴፖ ራእይ ላይ ነው። ኦዬዴፖ ይህንኑ አገልግሎት ለመጀመር መለኮታዊ ጥሪ እንዳገኙ ይናገራሉ። የሚገርመው ግን ሁሉም የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች መለኮታዊ ራእይ ማግኘታቸውን ከመናገር አይታቀቡም። ኬነት ሐገን ወደ መንግሥተ ሰማይና ሲዖል ሲመላለሱ እንደኖሩና ከኢየሱስ ክርስቶስ፥ ብሎም ከመላእክት ጋር ሲወያዩ እንደነበር በመጽሐፎቻቸው ሁሉ ገልጸዋል። (ይህንን ኬነት ሐገን በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ ስላከናወኗቸው ተግባራት ከምናብራራበት ክፍል ይመልከቱ።)

እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ የእስልምናው መሥራች የሆኑት መሐመድ፥ የክርስቲያን ሳይንስ መሥራች የሆኑት ሜሪ ቤከር፥ የሞርሞኒዝም መሥራች የሆኑት ጆሴፍ እስሚዝ... ሁሉ መለኮታዊ ጥሪ እንደተሰጣቸው በመግለጽ ተከታዮችን አፍርተዋል። ሃይማኖታውያኑ ቀርቶ እንደ ኮንስታንቲንና ይኩኖ አምላክ የመሳሰሉ የፖለቲካ መሪዎች ሳይቀሩ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያከናወኑ እንዳሉ በመግለጽ የበላይነትን ለመቀዳጀት በቅተዋል።

የነ ኦዬዴፖም አካሄድ ከዚህ የተለየ ለመሆኑ ከነርሱ ብዕሮችና ካሴቶች በቀር ሌሎች መረጃዎች ሊገኙ አልቻሉም። እንዲያውም አካሄዳቸው ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ያፈነገጠ መሆኑን የሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎች አሉ። ከነዚህም መካከል ገንዘብ ለመሰብሰብ ሲባል የሚጠቀሙባቸው ስልቶች መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ጋር አብረው የማይሄዱ መሆናቸው ነው። የት ስፍራ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የእግዚአብሔርን ሞገስ ለማግኘት ገንዘብ እንዲሰጥ የሚጠይቀው? የት ስፍራ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን መንፈሳዊ ሞት ያስተማረው? የቱ ጋ ነው እግዚአብሔር ሰዎች እርሱን በማመን ከማናቸውም ዓይነት ምድራዊ ችግሮች፥ ከረሃብና ከበሽታ ነጻ እንደሚሆኑ የተናገረው?

ፓስተር ግርማ በመስቀል ላይ መሞት የኃጢአትን ይቅርታ የሚያስገኝ ቢሆን ኖሮ ማንም ሰው ይህንኑ ሊያደርግ እንደሚችል ተናግረዋል። ይህም "ቁሳዊው የኢየሱስ ደም በተረገመው እንጨት ላይ በፈሰሰበት ወቅት በደም ሥሮቹ ውስጥ ይፈስ ከነበረበት ጊዜ የላቀ ዋጋ አልነበረውም" ከሚለው የክርስቲያን ሳይንስ ዶክትሪን የተጨለፈ መሆኑ ግልጽ ነው።

ይህ አስተሳሰብ በበኩሉ ክፋት በምድር ላይ እንደሌለ ከሚያስተምረው የክርስቲያን ሳይንስ የተወሰደ ነው። ይህም ማለት ክርስቲያን ሳይንስ ክፋት እንደሌለ ስለሚያምንና ኃጢአትም ክፉ ነገር ስለሆነ፥ ይህንኑ ለማስወገድ ክርስቶስ እንደሞተ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስለማይቀበል ነው። *የዊነርስ ቻፕል፥*

*"ክፋትን አታዩም። ከክፋት ነጻ ወደሆነ ሕይወት ደርሰናል። ከእንግዲህ ክፋትን ስለማታዩ እግዚአብሔርን አመስግኑ። ያ ዕጣ ክፍላችሁ ነው።"*[12]

ምንም እንኳ ይህ አሳብ በሶፎንያስ 3፡14-15 ላይ እንደተመሠረተ ቢነገርም፥ እውነተኛው ምንጭ ክርስቲያን ሳይንስ ነው። ለምን ቢባል ክፋትን ሳያይ የሚኖር ክርስቲያን በዓለም ስለሌለ ነው። ጌታችንም ተስፋ የገባልን ከክፋት የጸዳ ሕይወት ሳይሆን በሚያጋጥመን መከራ ሁሉ አብሮን እንደሚሆን ነው። "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ። ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16፡33)።

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈሳዊ ሞት ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደታጠብን ይናገራል። በ1ኛ ዮሐንስ 1፡7 እንደተጠቀሰው፥ "የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።"

ፓስተር ቱንጂ «መንፈሳዊ ኃይላትን ስለማሠራት» ይሰብካሉ። ስለ ሴቲቱ ምስክርነት በሚያስረዱበት ስፍራ፥ «ይህ መንፈሳዊ ሕግ ነው» እያሉ ይናገራሉ። «መንፈሳዊ ሕግ» ተብሎ የታወጀው ደግሞ ምንም ሳይሆን አዎንታዊ ቃል ነው። ('ንግዱ አያሽቆለቁልም!' የተሰኘው መሆኑ ነው።) ይህ ደግሞ ምን ያህል ከኬነት ሐገን ስብከት ጋር እንደተቆራኘ በሚከተሉት ምዕራፎች ውስጥ የምንመለከተው ይሆናል።

# 2

# የነ ሐገን "ሬማ" ስንክሳራዊ ገጽታዎች

ኬነት ሐገን በኦክላሆማ ቱልሳ ያቋቋሙት ሬማ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል(Rhema Bible Training Center) ከተመሠረተበት ከ1974 እስከ 1988 ያስመረቃቸው በርካታ ተማሪዎች "የሐገንን ሥነ-መለኮት" ለማስፋፋት በየስፍራው ተበትነዋል። በመዲናችንም የሐገንን ትምህርትና "ሬማ ፌይዝ ሚኒስትሪ" "ሬማ የእምነት አገልግሎት" የሚል ስያሜ ያነገተ ተቋም (በነርሱ ግንዛቤ ቤተ ክርስቲያን) ከአንዲት ፔንተኮስተል ቤተ ክርስቲያን የገነጠላቸውንና ሌሎች ከየቤተ ክርስቲያናቸው ያፈነገጡትን ግለሰቦች አስከትሎ ውክቢያ በመፍጠር ላይ ይገኛል።

የዚሁ እምነት ዋንኛ ተዋናይ የሆኑት የኬነት ሐገን "የእምነት ቃል" መጽሔት ወደ 190,000 ቤቶች የሚበተን ሲሆን፥ በርሳቸውና ኬን ሐገን በተሰኙት ልጃቸው አማካኝነት የሚዘጋጁ 20,000 ያህል የካሴት ክሮችም ይሰራጫሉ። ኬነት ሐገን 229 ሠራተኞችና ወደ 20 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ንብረት እንዳላቸውና ለ200 ሺህ ደጋፊዎቻቸው የደብዳቤ መልእክት እንደሚያስተላልፉ ይናገራሉ። 126 መጻሕፎቻቸውና በራሪ ወረቀቶች 33 ሚሊዮን ቅጂዎች እንደተሸጡላቸው ይተርካሉ[1]።

ይሁንና፥ በዚሁ የነ ሐገን የእምነት ትምህርት ላይ ይፋዊ ተቃውሞዎች መሰንዘራቸው አልቀረም። ከነዚህም ተቃውሞዎች ፕሮፌሰር ቻርልስ ፋራህ በ1979 "From the Pinnacle of the Temple" በሚል ርእስ ያሳተሙትና የእምነት አስተማሪዎች እንኳንስና ሊቀበሉት ሊያነቡ ያልደፈሩት መጽሐፍ አንዱ ነው። ለምሳሌ፥ ቻርልስ ካፕስ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለውን ጽፈው ነበር።

*"መጽሐፉን ስላላነበብሁት አስተያየቴን የምሰነዝረው ከሰማሁት በመነሣት ነው... ይህ ሰው ክርስቲያን ስለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለኝም... ይሁንና፥ የመገለጥን እውቀት ተቃውሟል... ሰዎች ብዙ ሊያውቁ የሚሆነው ይኸው ነው..."*[2]

በዚሁ በ1979 ፔንተኮስታል የሆኑት የአሴምብሊስ ኦፍ ጎድ አባል ዶ/ር ጎርደን ፊ "በዘመኑ በሽታ ላይ አንዳንድ ትምህርቶች"[3] በሚል ርእስ ተከታታይ የመጽሔት ላይ ጽሑፎችን ያጎርፉ ጀመር። በተለይም "የብልጽግና ኑፋቄ" እና "የጤንነት ወንጌል" በሚሉ ርእሶች ጠንከር ያሉ ጽሑፎች አሳትመዋል።

በተለይ ደግሞ የእምነትን ትምህርት የፈውስ ዶክትሪን አንገት ያስደፋው "ልጃችን ሲሞት ዝም ብለን አየን" (We Let Our Son Die) በሚል ርእስ አንድ አባት የልጃቸውን አሟሟት የተረኩበት መጽሐፍ ነው። የእምነት ትምህርት ወንጌላዊው ዌስሊ ፓከር ለተባለው ልጃቸው የፈውስ ጸሎት ካደረጉለት በኋላ፥ ሌሪና ባለቤታቸው (ወላጆቹ) በስኳር በሽታ ለሚሠቃየው ልጃቸው መድኃኒት ላለመስጠት ወሰኑ። በልጁ ላይ በሽታው እየጸና መጥቶ በጣዕረ-ሞት ሲያጣጥር፥ ወላጆቹ በተማሩት መሠረት ሰይጣን ውሸተኛ የሞት ምልክት በማሳየት የሚፈትናቸው መሰላቸው። በመሆኑም፥ በኦገስት 23፥ 1973 ልጃቸውን በሞት እስኪነጠቁ ድረስ አዎንታዊ የፈውስ ቃል (positive confession) መናገራቸውን ቀጠሉ።

ልጃቸው ከሞተም በኋላ የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ሊካሄድ አልቻለም፤ ዌስሊ ከሞት ይነሣል በሚል *እምነት* አባቱ "የትንሣኤ ፕሮግራም" አዘጋጁ። ከሞት ይነሣል በሚል እምነት የሌላቸውን ሰዎች ሁሉ ልጃቸው ከሞት አልነሣ ሲል፥ የልጁ አባት እምነት የሌላቸውን ሰዎች ሁሉ ከፕሮግራሙ ስፍራ አባረሩ። ከዚያም የልጃቸውን ትንሣኤ ለአንድ ዓመት ያህል *በእምነት* ሲጠባበቁ ቆዩ።

በዚህ መሀል ለልጃቸው ሞት ምክንያት በመሆናቸው (child abuse)፥ ፍርድ ቤት ተከሰሱ። የዚህ ዓይነቱ ጥፋት እስከ 25 ዓመታት ድረስ ሊያሳስራቸው ይችል ነበር። ይሁንና፥ ፍርድ ቤቱ ወላጆቹ በአሳሳች ሃይማኖት ተታለው ያደረጉት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ክሱን ሊያነሣላቸው ችሏል።[4]

ይህን መሰል አሳዛኝ ታሪኮች በዚህ የእምነት ትምህርት ውስጥ በርካታ ይህን መሰል አሳዛኝ ታሪኮች በዚህ የእምነት ትምህርት ውስጥ በርካታ ይሰብኩ ናቸው። ሌላው ቀርቶ መድኃኒት መጠቀሙ ተገቢ እንዳልሆነ ይሰብኩ የነበሩት ዶ/ር ሆበርት ፍሪማንም የሰበካቸውን ጦስ ተቀብለው ዲሴምበር 8፥ 1984 በልብ ድካም ለህልፈተ-ሕይወት በቅተዋል[5]።

ይህንን ሁሉ ከተመለከቱ በኋላ፥ የአሴምቢልስ ኦፍ ጎድ አገልጋዮች የእምነቱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆን የሚገልጽ ይፋዊ ደብዳቤ ኦገስት 19፥ 1980 አዘጋጅተው በትነዋል[6]።

ቻርልስ ፋራህም፥ "ሂሳዊ ግምገማ - የእምነት ቀመር ሥነ-መለኮት ሥሮችና ፍሬዎች" (A Critical Analysis: The Roots and Fruits of Faith Formula Theology) በሚል ርእስ በኖቬምበር 1980 ጥናታዊ ጽሑፍ አቀረቡ። በዚሁ ለበርካታ ምሁራንና ተማሪዎች ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ፥ ፋራህ ይህንኑ የእምነት ትምህርት "ካሪዝማቲካዊ ሰብአዊነት"፥ "አዲሱ ኖስቲሲዝም"፥ ብሎም "ኑፋቄ" እያሉ በመጥራት ደጋፊዎቹን አበገኑ። ይህም ጥናታዊ ጽሑፍ በብዙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ታትሞ ወጣ። በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት ያለው "ክርስቲያኒቲ ቱዴይ" ጽሑፉን እንደሚከተለው ዘግቦት ነበር።

*"የፋራህ ጥናታዊ ወረቀት በእምነት-ቀመር አስተምህሮ ላይ ጠርነት አወጀ። የነ ሐገን-ኮፕላንድ-ፕራይስን ትምህርት ለሚቃወሙ ሁሉ የፋራህ ጽሑፍ እንደ መመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል አይጠረጠርም።"*[7]

ቀደም ሲል በዓለም-አቀፍ ደረጃ የአሴምብሊስ ኦፍ ጎድ ወንጌላዊ ሆነው ያገለግሉ የነበሩት ጂሚ ስዎገርት፥ በዲሴምበር 1980 "ሚዛናዊ የእምነት ሕይወት" በሚል ርእስ ተከታታይ ጽሑፎች ማሳተም መጀመራቸው ፋራህ ያቀጣጠሉትን እሳት አባባሰው። ሚስተር ጂሚ በመጀመሪያው ጽሑፋቸው "እኔም ብሆን የእምነት እንቅስቃሴን አንዳንድ ስህተቶች በመስበኬ አጥፍቻለሁ" ካሉ በኋላ፥ እግዚአብሔር አሁን ሌላ አቅጣጫ እንዳሳያቸው ገልጸዋል[8]።

በሁለተኛው ጽሑፋቸው፥ ሚስተር ጂሚ የሚከተለውን አሳብ አስቀምጠዋል።

*"ቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተ ክርስቲያን አካል አንድን ነገር ከጠቅላላው የእግዚአብሔር ትምህርት የተለየ ሆኖ ሲያገኙት፥ ትምህርቱ በራሱ እውነት ሊሆን ቢችልም እንኳ የኑፋቄ አደጋ እንዳለበት እሙን ነው፤ ሰዎች ለኑፋቄ የሚሰጡት ፍች የተለያየ ቢሆንም፥ ብዙዎቹ ኑፋቄ የክርስትናን እምነት በአጅጉ መበከል እንደሆነ ያምናሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፥ ኑፋቄ አንድን መሠረታዊ እውነታ ነጥሎ በመውሰድ በመጠኑ ማጣመም ነው። የዚህ ዓይነቱ ኑፋቄ የተለመደ ሲሆን፥ ዛሬ ተወዳጅነት በማግኘት ላይ የሚገኙ የክርስትና ትምህርቶች ወደዚሁ አቅጣጫ እያመሩ ናቸው ብዬ እፈራለሁ።"*[9]

ጂሚ በ1982 "ቅጥ ያጣ እምነት - አዲሱ ኖስቲሲዝም?" (Hyper-Faith: A New Gnosticism" የሚል መጽሐፍ አሳተሙ። በዚህ መጽሐፋቸውም፥ የእምነትን እንቅስቃሴ "ቅጥ ያጣ እምነት" (ገጽ 2)፥ "የዶክትሪን ስህተት" (ገጽ 4)፥ "የሰይጣን ሥራ" (ገጽ 5)፥ "ሳይንቲዝም" (ገጽ 10)፥ "ሕግ" (ገጽ 24)፥ "አዲሱ ኖስቲሲዝም" (ገጽ 11፥ 42) ሲሉ ተቃውመዋል። ሚስተር ጂሚ በመጨረሻም፥ የራሳቸውን ስህተት በመናዘዝና "[የእምነት እንቅስቃሴ] ስህተት ሁሉ ወደ ጥፋት እንደሚመራ"[10] በማስጠንቀቅ መጽሐፋቸውን አጠቃለዋል።

ዲ.አር. ምክኮንል "ሌላ ወንጌል"(A Different Gospel) በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ የነ ሐገንን እምነት አሳዛኝ ገጽታዎች ይፋ አውጥተዋል። ይህ መጽሐፍ በጴንተኮስተሎችም ሆነ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን፥ ካሪዝማቲኮቹ ግን ማስታወቂያውን በማስፈራቸው እንኳ እንደተጸጸቱ "ሚኒስትሪስ ቱዴይ" የሚባለው መጽሔታቸው ይገልጻል።

*"የኪነት ሐገንንና የሌሎችን እውነተኛ የወንጌል አገልጋዮችን አገልግሎት ለማውደም የተዘጋጀ የሚመስለውን መጽሐፍ ማስታወቂያ በማውጣታችን*

*ተጸጽተናል...በመሆኑም ምንም ዓይነት ቀጣይ ማስታወቂያ የማናወጣለት መሆናችንን እንገልጻለን።"*[11]

ይሁንና፥ ይህ የመጽሔት ዝግጅት ክፍሉ ጸጸት በአንባብያን ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ለምሳሌ፥ አንድ መጋቢ የሚከተለውን አስተያየት ሰንዝረው ነበር።

*"በእናንተ ዘንድ የጋዜጠኛነት ሥነ-ምግባር ባለመኖሩ በጣም አዝኛለሁ። የሥነ-መለኮት ተቋሞችና እንደእናንተ ዓይነት መጽሔቶች እንዲህ ያለ የተከላካይነት አቋም በመውሰዳቸው እንዲህ ዓይነት የሥነ-መለኮት አክራሪ አቅጣጫዎች ወደ ሚዛናዊነት ይመጡ ይሆን? ከዚህ የሚሻለው አቀራረብ የደራሲውን ጥሩ ነጥቦች ተመልክቶ በይፋዊ የክርክር መድረክ እውነቱ እንዲያሸንፍ ማድረግ ነው።"*[12]

ይህንን ከመሳሰሉ የአንባብያን አስተያየቶች የተነሣ የመጽሔቱ አዘጋጆች፥ "ሌላ ወንጌል" የተባለውንና እጅግ የፈሩትን መጽሐፍ ዋና ዋና ነጥቦች አሳጥረው ለማቅረብና ይፋዊ ውይይት ለማድረግ ተገደዱ። ራሳቸው ምክኮንልም ተጋብዘው የበኩላቸውን አስተያየት ሊሰጡ ቻሉ።

ምክኮንል ሃያሲያኑ መጽሐፉን በተመለከተ፥ "የከረረ ጥቃት" (polemic) እንደሰነዘሩ በመግለጽ ያቀረቡትን አስተያየት በአዎንታ ነበር የተቀበሉት።

*"አዎን፥ 'ሌላ ወንጌል' የከረረ ጥቃት ነው። ለዚህም ደግሞ ይቅርታ አይጠይቅም። ሕይወት በአደጋ ላይ ሲሆን፥ እምነት በመናጋት ላይ ሲገኝ፥ አብያተ ክርስቲያናትም በመከፋፈል ላይ ሲሆኑ፥ [ይህንኑ ችግር በሚፈጥሩት ላይ] የከረረ ጥቃት መሰንዘሩ ተገቢ ነው። እዚህ ላይ የምንነጋገረው የሥነ-መለኮት ምሁራን ለምእተ-ዓመታት ሲከራከሩ በኖሩባቸው ጉዳዮች ላይ አይደለም። የምንነጋገረው ስለ ሰዎች ሕይወት ነው። በእምነት ሥነ-መለኮት ጦስ አንዲት ነፍስ ብትጠፋ ነገሩ በዋዛ የሚታለፍ አይሆንም። ለአንዲት ነፍስ መጥፋት እንኳ የከረረ ጥቃት ሊሰነዘር ይገባል። ነገር ግን ለእምነት ሥነ-መለኮት የተሠዋችው ነፍስ አንዲት ብቻ አይደለችም። በመቶ የሚቆጠሩ ጥሩ ጥሩ ሰዎች ተሠውተዋል"*[13]

በማለት ከላይ የተመለከትነውን የዌስሊ ፓከር፥ ሌሎች መድኃኒት ተነፍገው የሞቱትን በመቶ የሚቆጠሩ ልጆች፥ በእንዲያና ስቴት ሆባርት ፍሪማን ከዚህ እምነት ጋር በተያያዘ ያስከተለውን ጥፋት ዘርዝረዋል። ምክኮንል በማከልም፥

*"ይህ የፖለቲካ፥ የሕዝባዊ ግንኙነቶች ወይም የመንፈሳዊ ትክክለኛነት ጉዳይ ሳይሆን፥ ዶክትሪን ነው - ገዳይ ዶክትሪን- በመቶ የሚቆጠሩትን ሰዎች ሕይወት ያጠፋና በሺህ የሚቆጠሩትን እምነቶችና አብያተ ክርስቲያናት ያወደመ ዶክትሪን"*[14] ብለዋል።

እኚህ ጸሐፊ የእምነት ትምህርትን አደገኛነት በተጨባጭ ለማሳየት ካቀረቧቸው ሕያው ምስክሮች መካከል ባኗ የዚህ እምነት ጦስ ሰለባ የሆነባት ሴት የጻፈችው ደብዳቤ ይገኝበታል።

*"ውድ ምክኮንል፥*

*"ሌላ ወንጌል' የሚለውን መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል ጨርሼ መነሣቴ ነው። ይህንን ደብዳቤ የምጽፈው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ላካተትኸው የጥናት ውጤት ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ ያህል ነው። እንዲሁም ደግሞ ከራሴ ታሪክ በመጠኑ ለማወቅ ትፈልግ ይሆናል የሚል አሳብ አለኝ...*

*"ከአሥራ አንድ ዓመታት በፊት የሬማ ምሩቃን ከሚያንቀሳቅሷት ቤተ ክርስቲያን ራሴን አግልያለሁ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ለሰባት ዓመታት በአባልነት ቆይቼ ነበር። በ1981 እዚያ መሄድ ጀመርሁና በ1983 ባል አገባሁ። በዚያን ጊዜ ለአሥራ አራት ዓመታት ዳግም ተወልዶ ይመላለስ ከነበረ ክርስቲያን ጋር ነበር ጋብቻችንን የፈጸምነው፤ እኔ ግን ካመንሁ ገና አራት ዓመቴ ነበር። ባለቤቴ ከዚህ በፊት የሐገንን መጻሕፍት ያነበበ ቢሆንም እስከ ጋብቻችን ዕለት በእምነት እንቅስቃሴ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ አያውቅም ነበር።*

*"በመስከረም ወር አንድ የሁለት ዓመት ወንድ ልጅ አስታቅፎኝና የሦስት ወራት ነፍሰጡር ሳለሁ ለዘላለሙ ተለየኝ። አየህ፥ ለአያሌ ዓመታት የትርፍ አንጀት በሽታ ነበረበት። ሐኪሞቹ ለካንሰር በሽታ እንዳይጋለጥ በ30 ዓመቱ ትርፍ አንጀቱ እንዲወጣለት ይነግሩት ነበር። (ገና በሽታ ሲጀማምረው በውትድርና ተግባር ላይ ሳለ ሐኪም ቤት ሂዶ ነበር።)*

*"በጋብቻችን ወቅት፥ ከሚሰማው የእምነት ትምህርት ሳቢያ እንደ ተፈወሰና የሕመም ምልክቶቹ የውሸት እንደሆኑ ይነግረኝ ነበር። ይሁንና፥ በ30 ዓመት ዕድሜው በጉበት ካንሰር ሞተ...*

*"አሁን አሁን ሐኪሞች የውሸት ዘገባ የሚሰጡን ጠላቶች ሳይሆኑ እውነተኛ ወዳጆቻችን እንደሆኑ ተረድቻለሁ። አሁን እንግዲህ ተስፋዬ በሮሜ 8:28 ላይ በመጽናት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለበጎነት እንደሚለውጥ መጠባበቅ ብቻ ነው።*

*"በነዚያ ዓመታት ኢየሱስን የምንከተል መስሎኝ ነበር። አሁን ግን እዚያ የቀሩትን ጓደኞቼን በማሰብ አለቅሳለሁ... አሁን ሰይጣን ቤተ ክርስቲያናቸውን እየከፋፈለ ነው። ነገሩ ሁሉ በጣም ያሳዝናል።"*[15]

የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ሰዎች በእንዲህ ዓይነቱ አደገኛ ዶክትሪን ላይ የሚሰነዘረውን አሳብ ጆሮ አውሶ እንደማድመጥና "እውነት ይሆንን?" (የሐዋ ሥራ 17:10) ብለው እንደማረጋገጥ ቀና የሆነውን ምክር በደፈናው "የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ" ብለው መደምደማቸው ነው። ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስን የሚቃወም ሰው "መንፈስ ቅዱስ መሥራት አቁሟል!" በሚል አጭር ዓረፍተ ነገር መገላገል ሲችል፥ ለምን ይሆን የእምነት ሥነ–መለኮትን ኑፋቄያዊ ገጽታዎች ሲፈትሽ የሚደክመው?

በርግጥ ግለሰቡ ከቤተ ክርስቲያን ደመወዝ የሚያገኝ ከሆነና የሚሰነዝረው አሳብ ከሥራ የሚያፈናቅለው ከመሰለው በእጅ አዙር ሊናገር ይችላል።

ብዙዎቹ ግን እውነት ነው ብለው ያመኑበትን ግንዛቤ ለማስፋፋት ወይም ውሸት ነው ብለው የኮነኑትን አሳብ ለማውገዝና ከላይ እንደተመለከተው የብዙዎችን ሕይወት ከአደጋ ለመታደግ ሲሉ ይጽፋሉ።

♣

# 3

# ኢየሱስ በሲኦል ዳግም ተወልዷልን?

**(Identification)**

*"በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 እግዚአብሔር በሥጋ እንደ ተገለጠና በመንፈስ እንደ ጸደቀ ይናገራል። አንድ ነገር መጀመሪያ ርኩስ ካልሆነ በቀር በመንፈሱ ጻድቅ እንደማይሆን ግልጽ ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ ኃጢአት ተደርጎ ነበር። [ኢየሱስ] በመንፈሱ የሰይጣንን የኃጢአት ባህርይ ተቀብሎ በሞተ ጊዜ፥ 'አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?' ሲል ጮኸ።*

*"በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ነገር አታውቁም። ሙሴ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተቀብሎ በግን ሳይሆን እባብን በዓላማ ላይ የሰቀለው ለምን ይመስላችኋል? ይኼ ነገር ያሳስበኝ ነበር። 'ካልጠፋ ነገር የሰይጣን ምልክት የሆነውን እባብ ለምን ከዓላማው ላይ ሰቀልህ? ለምን በግ አልሰቀልህም?' ብዬ ስጠይቅ ጌታ እንዲህ ሲል መለሰልኝ። 'ምክንያቱም በመስቀሉ ላይ የተሰቀለው የሰይጣን ምልክት ስለሆነ ነው። በገዛ መንፈሴ መንፈሳዊ ሞት በመቀበሌ ዕዳው ተከፈለ።'*

*"እንግዲህ ልብ ልትሉ የሚገባችሁ ኢየሱስ እንደሞተ ነው፤ ኃጢአትን እንዳደረገ ሟች ሰው ወደ ጥልቁ ወርዷል። ግን እዚያ ስላልቀረ እግዚአብሔርን አመስግኑ። እዚያ በሲኦል ዳግም ተወልዶ ተነሣ። "(ኬነት ኮፕላንድ "What Happened from the Cross to the Throne?"* በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ)።

የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆቹ ኑፋቄያዊ የአንድነት (Identification) ዶክትሪን የስርየቱን ሥጋዊ ባህርይ በመካድ፥ ክርስቶስ ወደ አጋንንታዊ አምሳል ተለውጠ በሲኦል "ዳግም – እንደተወለደ" ያስተምራል፤ አማኞችም ወደ ሥጋ ለባሽ አምላክነት ወይም ትስእብት (Incarnation) ሊለወጡ እንደሚችሉ ይገልጻል። ይህም የኬነት ሐገንና የኬንየን አንዱ ትምህርት ነው።

ምክኮነል እንደዘገቡት፥ 'አንድነት' (identification) የእምነት ሥነ–መለኮት ትምህርት መሠረት በመሆኑ፥ እጅግ አስፈላጊያቸው ነው። ለዚህም ነው ኬነት ኮፕላንድ ይህንኑ ትምህርት አጥብቆ ስለተቃወመው ሰው ሲናገሩ፥ "ያ ሰው ዛሬ ሙት ነው፤ ይህንን የምላችሁ እናንተን ለማስጠንቀቅ ነው። ሰዎች ይህንን ትምህርት አስተምረዋል ብላችሁ አትተቹ። ካልገባችሁ አፋችሁን ዘግታችሁ ጸልዩ" ያሉት።[1]

ምክኮነል የኬንየንን መጽሐፍ ጠቅሰው እንዳስፈሩት፥ ስርየት ለክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ያልታወቀ እውነት ነበር፤ ደቀመዛሙርቱ "የመንፈሳዊ ሞቱንም" ሆነ በሲኦል ያሳለፈውን የሦስት ቀናት ሥቃይ ምሥጢር አያውቁም።

ኬንየን ሰው "በእግዚአብሔር የኑባሬ ምድብ" ውስጥ እንደሚገኝ፥ መላእክት፥ ሰውና እግዚአብሔር መንፈስ እንደመሆናቸው፥ አንድ ዓይነት ባሕርይ እንዳላቸው ተናግረዋል። ኬነት ሐገን፥ "ሰው ሥጋዊ ኑባሬ አይደለም - መንፈስ እንጂ" እስከ ማለት ይደርሳሉ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ልዩነት የዓይነት ሳይሆን የደረጃ ብቻ ነው። በእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ዘንድ የሚታወቀው የሥነ-ሰብእ (Anthropology) ድንጋጌ፥ "ሰው ነፍስን ይዞ በሥጋ ውስጥ የሚኖር መንፈስ ነው" የሚል ነው። ኬንየን፥ "የሰው መንፈስ ትክክለኛ ሰው ነው" ብለዋል። ሐገንም አክለው፥ "እኛ በሥጋ ውስጥ ብንኖርም መንፈስ ነን" ብለዋል። በተጨማሪም፥ "እናንተ 'እኔ' ብላችሁ የምትጠሩት ሥጋችሁን ከሆነ ያ ትክክል አይደለም። ነገር ግን 'እኔ' የምትሉት የውስጥ ሰውነታችሁን ከሆነ ያ ትክክል ነው" ሲሉ አስረድተዋል።[2]

ይህንኑ ዶክትሪን ተቀብሎ የሚንቀሳቀሰውና እዚሁ አዲስ አበባችን የሚገኘው ሬማ የእምነት አገልግሎት፥ "ሰው መንፈስ እንደሆነ ነፍስ እንዳለው በሥጋ ውስጥ እንደሚኖር እናምናለን" ሲል በእምነት መግለጫው ተራ ቁጥር "ከ" ሥር አውጇል።

ዳግማዊው ኬነት ሐገን በመባል የሚታወቁት የኬነት ሐገን ልጅ፥ ጃኑዌሪ 1996 በየወሩ በሚታተመው የ"ወርድ አፍ ፌይዝ" መጽሔት ውስጥ፥ "ለክርስቲያን አንድ የስኬታማነት ቁልፉ በክርስቶስ አንተ ማን እንደሆንህ መገንዘቡ ነው" ካሉ በኋላ አሳባቸውን በምሳሌ ሲያብራሩ፥ "ለምሳሌ፥ አንተ መንፈስ እንደሆንህ፥ ነፍስ እንዳለህና በሥጋ ውስጥ እንደምትኖር መገንዘብ አለብህ"[3] ብለዋል።

እንደሚታወቀው፥ ሜታፊዚካል ኑፋቄዎች ሁሉ እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ውስጥ ስላለ ሁሉም ነገር በተለይም ሰው አምላክ ነው የሚል የፓንቴይስቲክ (pantheistic) አሳብ አላቸው። (ኒው ኤጅም በዚህ ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ እንዳለው ልብ ማለቱ ተገቢ ይሆናል - ዕፀዋቶችን፥ ቀንድ-አውጣዎችን፥ መጻሕፍትን፥ ሰዎችንና የመሳሰሉትን ጨምሮ ነገሮች ሁሉ አንዱን አምላካዊ ባህርይ እንደሚጋሩ የሚሰብክ። የእምነት እንቅስቃሴ ከኒው ኤጅ ጋር ስላለው ቁርኝት የምናብራራበትን ምዕራፍ ይመልከቱ።)

ሜሪ ቤከር ኤዲ በበኩላቸው፥ "መንፈስ ትክክለኛና ዘላለማዊ ነው፤ ቁስ አካል ግን ትክክለኛ ያልሆነ ጊዜያዊ ነገር ነው። ስለሆነም፥ ሰው መንፈሳዊ እንጂ ቁሳዊ አይደለም" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ግን ለዘመናት የቆየ የኖስቲሲዝም ጽንሰ-አሳብ እንጂ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው እውነት አይደለም።

## *ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ ከመለኮትነት*

## *ወደ አጋንንትነት እንደተቀየረ*

በውድቀቱ ምክንያት ሰው ፍጥረትን እንዲገዛ የተሰጠውን ሥልጣን ለሰይጣን አስተላልፎአል። እናም አዳም እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠውን ለሰይጣን በማስተላለፍ እግዚአብሔርን ከዱ፡። ይህም በእምነት ሥነ–መለኮት "ከፍተኛ ክህደት" (High Treason) በመባል ይታወቃል። ስለሆነም፥ ሰይጣን በሰው ዓመፅ ብቻ ሳይሆን፥ አምላክ በመሆኑ ባለው "ሕጋዊ መብት" ፍጥረትን ይገዛል። እግዚአብሔርም ዓለምን መልሶ ከእጁ ለማስገባት፥ ለሰይጣን ቤዛ ይከፍላል።

## *መንፈሳዊ ሞትና የኢየሱስ ዳግም ልደት*

ኬንየን እንደሚሉት፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሁለት ሞት ሞቷል – የመጀመሪያው መንፈሳዊ፥ ቀጣዩ ሥጋዊ። የክርስቶስ መንፈሳዊ ሞት ያስፈለገው ሕመምም ሆነ ኃጢአት በመነሾነት መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ ባለመሆናቸው ነው። እንደ ኬንየን፥ "ኃጢአትና በሽታ ከአንድ ምንጭ የሚቀዱ ሲሆኑ፥ ደራሲያቸውም ሰይጣን ነበር።"[4] ኬንየን በመቀጠልም፥

*"ክርስቶስ በቤዛነቱ ያስገኘው ሁሉ ከመንፈሱ የመጣ ነው። ኃጢአት የተደረገው መንፈሱ ነበር። በሰው ልጅ ምትክ የፍርድን ሥቃይ የተቀበለው በመንፈሱ ነበር። ጻድቅ ተብሎ የታወጀው መንፈሱ ነበር... ለሰው ልጅ ደኅንነትን ያስገኘውም የመንፈሱ ትንሣኤ ነበር። ሰው በስሜት ሕዋሳት እውቀት (Sense Knowledge) ስለታሰረ የተመለከተው የክርስቶስን ሥጋዊ ሥቃይና ሥጋዊ ትንሣኤ ብቻ ነው። ጉዳዩ ግን ከዚያ እጅግ የላቀ ነው"*[5] ብለዋል።

በእኚህ ግለሰብ መገለጥ መሠረት፥ የክርስቶስ ሥጋዊ መከራና ሞት ምንም ዋጋ የለውም። እውነተኞቹ የማዳን ተግባራት መንፈሳዊ ሞቱና መንፈሳዊ ትንሣኤው ናቸው። ከራሳቸው እንስማ።

*"የኃጢአትን ዋጋ የከፈለው [ሥጋዊ] ሞቱ ከሆነ፥ እንግዲያው ማንም ሰው ስለ ራሱ ሊሞት ይችል ነበር። ኃጢአት ያለው በመንፈሳዊው ስፍራ ነው። ሥጋዊ ሞቱ ለመንፈሳዊ ፍጻሜ መሣሪያ ብቻ ነበር።"*[6]

ከዊነርስ ቻፕሉ ፓስተር ግርማ አሰፋ ጋር በተነጋገርሁ ጊዜ ይህንኑ አሳብ በመዋስ፥ «በሥጋ መሞት የኃጢአትን ይቅርታ ሊያስገኝ ከቻለ ማንም ሰው ይህንኑ ተግባር ሊያከናውን ይችል ነበር» ሲሉ ገልጸውልኛል። ከወደ የይሆዋ ምስክሮች መንደር እንደመጡ የሚነገርላቸው ፍሬድሪክ ፕራይስም እንዲህ ሲሉ ይሟገታሉ።

*"ለኃጢአታችን የተበየነው ቅጣት በመስቀል ላይ መሞት ይመስላችኋል? ይኼማ ቢሆን ኖሮ፥ ሁለቱ ሌቦች የኃጢአታችሁን ዋጋ በከፈሉላችሁ ነበር። የለም!*

*ቅጣቱ ወደ ራሱ ሲኦል በመዝለቅ ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር ነበር... ሰይጣንና የሲኦል አጋንንት ሁሉ በኢየሱስ ላይ መረብ አኑረው ዕዳችንን እንዲከፍል እስከ ሲኦል ጫፍ ድረስ ጎተቱት።"[7]*

ኬነት ኮፕላንድ እንደሚሉት፥ ስርየትን ያስገኘው የክርስቶስ ደም ሳይሆን፥ ወደ ሲኦል መውረዱ ነው።

*". . . ደም በፈሰሰ ጊዜ ስርየት አላስገኘም ነበር . . . ኢየሱስ ያንተንና የእኔን መብቶች በእግዚአብሔር ዘንድ ለመመለስ፥ ሦስት አስጨናቂ ቀናትና ሌሊቶች በዚህች ምድር እምብርት ውስጥ አሳልፎአል።"[8]*

ኬነት ሐገንም፥ "«መንፈሳዊ ሞት ከእግዚአብሔር ከመለየት የላቀ ነው... ይህም የሰይጣንን ባህርይ መውረስ ማለት ነው"[9] ሲሉ አስረድተዋል።

በሜታፊዚካል መናፍቅነታቸው የሚታወቁት ሜሪ ቤከር ኤዲም ተመሳሳይ አቋም አላቸው።

*"ቁሳዊው የክርስቶስ ደም በተረገመው እንጨት ላይ በተረጨ ጊዜ፥ በደም ሥሮቹ ውስጥ ይፈስ ከነበረበት ጊዜ የበለጠ ከኃጢአት የማንጻት ብቃት አልነበረውም።"[10]*

ይህ መቼም ወንጌላችን ከሚናገረው እጅጉን የራቀ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው። "...ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴዎስ 26፡28)። "የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል" (1ኛ ዮሐንስ 1፡7) . . . የወንጌሉ አስኳል የሆነው የክርስቶስ ደም "*ሥጋዊ*" ተብሎ ከተንቋሸሸ ምን ወንጌል ተረፈን!

ከዚህም ሌላ፥ ኬንየን ኢየሱስ መንፈሳዊ ሞት በሞተ ጊዜ በባህርዩ ውስጥ ውስጣዊ ለውጥ እንደተካሄደ አስተምረዋል – የሰው ኃጢአትና መንፈሳዊ ሞት ወደ እርሱ ሲዞር፥ ኢየሱስ "አዲስ ሰይጣናዊ ፍጥረት" ሆነ። ከዚህም የተነሣ፥ "ኢየሱስ ኃጢአት ሆነ። መንፈሱም ከእግዚአብሔር ተለየች።"[11] በእምነት ሥነ–መለኮት፥ ኢየሱስ የኃጢአት ምትክ አይደለም – ወደ አጋንንት ተቀየረ እንጂ።[12]

ኢየሱስ የሰውን ቅጣት ተቀብሎ ከተሠቃየና የሰውን ሕጋዊ ግዴታ ሁሉ ለሰይጣን ካሟላ በኋላ፥ እግዚአብሔር የፍትሕን መከወን አወጀ። ኢየሱስ መንፈሳዊ ሞት ስለሞተና ወደ ሰይጣናዊ ፍጥረትነት ስለተቀየረ፥ "ኢየሱስ ከሞት ከመነሣቱ በፊት ዳግም ተወልዶ ነበር።"[13] ለኬንየን፥ አንድነት ክርስቶስ በወደቀ አጋንንታዊ ደረጃችን ከእኛ ጋር ሙሉ ለሙሉ መተባበሩንና እኛም "በምትካዊ መሥዋዕት" ከእርሱ ጋር ሙሉ ለሙሉ መተባበራችንን ያመለክታል[14]።

በዚህ ትምህርት መሠረት፥ ከሰው ልጅ የሚፈለገው እንግዲህ "ዴፊኬሽን" (Deification) ማለትም ወደ አምላክነት መለወጡ ነው። ኬንየን

እንደሚሉት፥ ከመለኮታዊ ባህርይ ጋር የተፈጠረው ሰው ኃጢአት በመሥራቱ በሰይጣን ባህርይ ተሞልቷል፤ ይሁንና፥ በአዲስ ልደት አማካኝነት መለኮታዊ ባህርይ አግኝቷል። "ዳግም መወለድ ማለት በመንፈስ የእግዚአብሔርን ባህርይና ሕይወት መቀበል ማለት ነው"[15] ብለዋል ኬንየን።

ኬንየን ዶፊኬሽን የሜታፊዚካል ኑፋቄዎች ትምህርት እንደነበር ማወቃቸውን ዶክተር ምክኮንል ከሚከተለው ጽሑፋቸው ውስጥ መዝዘው በማውጣት አጋልጠዋል።

*"ክርስቲያን ሳይንስ፥ ቲዎሶፊ፥ አዲሱ አሳብና አዲሱ ዩኒቴሪያኒዝም አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ስለ ሰው ልጅ ተሠግዎ ያስተምራሉ፤ ይህም ማለት ሁሉም ሰው በውስጡ አምላክ አለው ብለው ይናገራሉ። አንድ ሰው በውስጡ አምላክ ካለውማ እንግዲህ እርሱና አምላክ ተጣምረዋል – ከተጣመሩም ሥጋ–ለባሽ አማልክት ሆነዋል።"[16]*

ይህ ጽሑፍ ከድሮዎቹ የኬንየን በራሪ ወረቀቶች የተገኘ ሲሆን፥ ኬንየን የሰውን ሥጋ–ለባሽ አምላክነት እንደሚቃወሙ ያሳያል። የሚያሳዝነው በመጨረሻው እርሳቸውም ይህንኑ የተቃወሙትን ትምህርት ተቀብለው ማስተጋባታቸው ነው።

ዛሬ ኬነት ሐገን የሰውን ሥጋ–ለባሽ አምላክነት በግልጽ ያስተምራሉ። ሐገን እንደሚሉት፥ "በአዲስ ልደት ውስጥ ትክክለኛ ተሠግዎ አለ!"[17] በዚህ አዲስ ልደት፥ እግዚአብሔር "ዓይነተኛ ባህርዩን፥ እርሱነቱንና ኑባሬውን ለእኛው ሰብአዊ መንፈስ"[18] ያስተላልፋል። ስለሆነም፥ "ማንም ዳግም የተወለደ ሰው ሥጋ ለባሽ አምላክ ነው። እንዲሁም አማኝ ሁሉ የናዝሬቱ ኢየሱስን ያህል ሥጋ ለባሽ አምላክ ነው።"[19]

የሚከተሉትም የኬነት ሐገን አባባሎች ናቸው።

*"እኛ እንዲህ ነን፤ እኛ ክርስቶስ ነን!"[20] "እንዲያውም፥ በመልእክቶች ውስጥ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ እንደሆነች ተገልጾአል። ቤተ ክርስቲያን ግን ክርስቶስ መሆናችንን ገና አላወቀችም። ይህንን ስናውቅ፥ የተመደበልንን ሥራ መሥራት እንጀምራለን።"[21]*

*"ክርስቶስ ራስ ነው – እኛ አካል ነን – የክርስቶስ አካል ክርስቶስ ነው።"[22]*

ሚካኤል ብሩኖ "ክርስቲያኒቲ ኢን ክራይሲስ" የተባለውን መጽሐፍ በመቃወም "ክርስቲያኒቲ ኢን ፓወር" ሲሉ ባሳተሙት መጽሐፋቸው፥ "አዳም የተፈጠረው እንደ ሌላ ኑባሬ አይደለም። የተፈጠረው ከመንፈስ ጋር ነው። ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተለየ አይደለም"[23] ብለዋል።

አንድ ለኅትመት ያልበቃ ጽሑፍ እንደገለጸው ኬነት ኮፕላንድ የሚከተለውን ተናግረዋል።

*"እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረበት ምክንያት ራሱን ለማባዛት ስለፈለገ ነው። በውስጣችሁ የሚኖር አምላክ የለም። ራሳችሁ አምላክ ናችሁ።"*[24]

ጆን አቫንዚኒ ከሞሪስ ሴሩሎ ጋር በመተባበር ባሳተሙት "The Endtime Manifestation of the Sons of God" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለው አሳብ ሰፍሮአል።

*"እግዚአብሔር በምድር ላይ ራሱን እያባዛ ነው።"*[25]

በ"ሕይወት" ጋዜጣ ቅጽ 2፥ ቁ. 17 "ታላቅ መንፈሳዊ ወታደር" ተብለው በፈውስ አገልጋይነታቸው የተሞገሱት ሞሪስ ሴሩሎም ከመድረክ ላይ ቆመው፥ "እዚህ የምታዩት ሞሪስን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው" ሲሉ የሰዎችን አምላክነት እንደሚከተለው አጉልተው አስተጋብተዋል።

*"ከመጀመሪያው የእግዚአብሔር አጠቃላይ ዓላማ ራሱን ለማባዛት እንደነበረ ታውቃላችሁ?... እስቲ ተናገሩት፥ የእግዚአብሔር ልጆች በሉ ተናገሩት... እዚህ ስቆም የምታዩት ሞሪስ ሴሩሎን አይደለም፤ እግዚአብሔርን ነው የምታዩት...*"[26]

ትራይን እንደሚሉት፥ "ለዚህ መለኮታዊ ብርሃን ራሳችንን ክፍት ባደረግን መጠን ከተራ ሰውነት ወደ አምላካዊ ሰውነት እንለወጣለን።"[27] ትራይንና ኪንየን እንደሚያስተምሩት፥ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት የፈጠሩ አማኞች አማልክት ናቸው። እንዲሁም፥ አማኞች ሁሉ ክርስቶስ በሲኦል ዳግም ከመወለዱ ጋር ከተባበሩ ቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም ዓይነት በሽታ፥ ሥቃይ፥ ሁኔታና ጉድለት እንደምትላቀቅ ኪንየን አስተምረዋል። እነዚህ ችግሮች የሚመጡት አማኞች ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን አንድነት ለመገንዘብ ባለመቻላቸው ብቻ ነው። እንደ ትራይን አገላለጽ፥ መንፈስ መሆኑን ያወቀ አማኝ ከእነዚህ ሁሉ የሥጋ ውስንነቶች ነጻ ነው።

## *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ*

"ሰው ምንድን ነው?" ብለን ብንጠይቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጣቸው መልሶች አሉት።

*"እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔርም መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" (ዘፍ. 1፡26-27)።*

## የእግዚአብሔር መልክ-ምሳሌ

*"እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፤ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥ የፈጠረውን ምሳሌ እንዲመስል የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል... " (ቆላ. 3፡9-10)።*

*"እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ… " (ኤፌ. 4፡24)።*

*"ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን። በእርሱም ይህንን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል" (1ኛ ዮሐ. 3፡2-3)።*

ከዚህኛው የዮሐንስ መልእክት ምንባብ እንደምንመለከተው፥ በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራችንና እርሱን መምሰላችን የንጽሕና ወይም የቅድስና ጉዳይ ነው። ሌሎችን የእግዚአብሔር አምሳል እንድምታዎች ጥቂት ገጾች አልፈን የምንመለከት ሲሆን፥ እዚህ ላይ፥ "ሰብአዊ ማንነታችን እንዴት ይገለጻል?" ለሚለው ጥያቄ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተሰጡትን የተለያዩ ምላሾች ማሰሱ ተገቢ ይሆናል።

## 1. ሦስትነት (Trichotomism – ትራይኮቶሚዝም)

ዶ/ር ኤሪክሰን በመጽሐፋቸው ውስጥ እንደጠቀሱት፥ ይህ የአጥባቂ ወንጌል አማኞች አመለካከት ነው። በዚህ አመለካከት መሠረት፥ ሰው ከሦስት ጥንተ ነገሮች ማለትም ከሥጋ፥ ከነፍስና ከመንፈስ እንደተሠራ ይታመናል። ነፍስ የአመክንዮ፥ የስሜት፥ የማኅበራዊ መስተጋብርና የመሳሰለው ሁሉ መሠረት የሆነች ሥነ-ልቦናዊ አካል ናት። ሰውና እንስሳት ከዕፅዋት የሚለዩት ነፍስ ስላላቸው ነው። መንፈስ ደግሞ ሰውን ከእንስሳት ይለየዋል። ይህ ሰው መንፈሳዊ ጉዳዮችን የሚያስተናግድበት አካል ነው። ባህርይ ከነፍስ ላይ፥ መንፈሳዊነት ደግሞ ከመንፈስ ላይ ይመሠረታል።[28]

የግሪክ ፈላስፎች ሥጋ የሰው ልጅ ቁሳዊ ገጽታ፥ ነፍስ ደግሞ ቁሳዊነት እንደሌላትና መንፈስ ሁለቱንም ወደ አንድነት እንደሚያመጣቸው ገልጸዋል። የአሌክሳንደሪያ የእምነት አባቶች ትራይኮሚስቶች እንደነበሩ ኤሪክሰን 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡23ን በመጥቀስ አስረድተዋል።[29]

## 2. ሁለትነት (Diachotomism - ዳያኮቶሚዝም)

ይህ አብዛኛው ክርስቲያን ማኅበረሰብ የሚከተለው አመለካከት ነው። በዚህ አመለካከት፥ ሰው ሥጋና ነፍስ አለው። ሥጋዊ አካል የሚሞትና ወደ አፈር የሚመለስ ሲሆን፥ ነፍሱ ግን ሕያው ናት። ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየውም ነፍስ ያለው በመሆኑ ነው።[30]

ዳያኮቶሚስቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነፍስና መንፈስ አንድ ዓይነት እንድምታ እንዳላቸው ይገልጻሉ። ዶ/ር ኤሪክሰን ይህንኑ አመለካከት በግልጽ ለማሳየት የሚከተሉትን ጥቅሶች ተጠቅመዋል። በሉቃስ 1፡46-47፥ "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች" የሚለው፥ "መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሤት ታደርጋለች" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ይናገራሉ።[31] በማቴዎስ 6፡25 ሰው ነፍስና ሥጋ እንዳለው ተገልጾአል፤ በ1ኛ ቆሮንቶስ

5፡3፥ 5 ግን ሥጋና መንፈስ እንዳለው ተመልክቷል፤ በዘፍጥረት 35፡18፤ 1ኛ ነገሥት 17፡21... ሞት የነፍስ መውጣት እንደሆነ ተጠቅሶአል።[32] በመዝሙር (31)፡5 እና በሉቃስ 23፡46 በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነፍስን ስለመስጠት የሚናገረው በሌሎች ትርጉሞች መንፈስን ስለመስጠት ይናገራል።

አንዳንድ ጊዜ "ነፍስ" የሚለው ቃል ከሰው ሕይወት ጋር በተዛመደ መልኩ አገልግሏል፤ "ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?" (ማርቆስ 16፡26)። ስለ መንፈስ መታወክ (ዮሐ. 13፡21) እና ስለ ነፍስ መታወክ [መዝ. (42)፡6] ዮሐ. 12፡27) የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ።

ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ምሁራን ሰው ከሥጋ የተለየ መንፈስ ወይም ነፍስ እንደሆነ ያስተምራሉ። ከነዚህ ግለሰቦች አንዱ የሆኑት ዊልያም ኒውተን ክላርክ፥ «የራስ-ንቃትን ግብረገባዊነት የተላበሰው ሰው ሰውነት ሳይሆን ሰውነትን ሊገዛ የሚገባው ነው» ብለዋል።[33]

የዚህ አመለካከት አራማጆች፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «አባት ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል» ሲል የተናገረውን ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጥቀስ የሥጋን አላስፈላጊነት ያስረዳሉ። እንደነርሱ አስተምህሮ፥ ሰው ያለ ሥጋ ሊኖር የሚችል ፍጡር ነው። ይህም ከእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች አሳብ ጋር አብሮ የሚሄዝ መሆኑ ሊጤን ይገባል።

## 3. ነጠላነት (Monism - ሞኒዝም)

ሰው እንደ አንድ አካል እንጂ የአካላት ጥርቅምቃሚ መታየት እንደሌለበት ያስተምራል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን እንደ ሥጋ፥ ነፍስ፥ መንፈስ እንደማይገልጽና እንደ ወጥ አካል የሚያስተምር መሆኑን ያስረዳሉ። በሞኒዝም አመለካከት ሰው ማለት ሥጋዊ አካል ያለው ነው።[34]

መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን ቁሳዊ (ሥጋ ያለው) እና ቁሳዊ ያልሆነ (ነፍስና መንፈስ) ያለው አካል አድርጎ የሚመለከት መሆኑ ከብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በግልጽ የሚታይ ነው። ይሁንና፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሰውን ከቁሳዊ አካል ውጭ የሚመለከቱ ይመስላል። ለምሳሌ፥ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ ለተማጸነው ሰው "ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ" (ሉቃ. 23፡43) ብሎታል። ይሁን እንጂ በሰማይ ስለሚኖረው ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ልብ ማለቱ ተገቢ ነው። ምድራዊ አካል እንዳለ ሁሉ ሰማያዊ አካልም እንዳለ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ገልጾታል። ይህም ሰው መንፈስ ወይም ነፍስ ብቻ የሚሆንበትን ሁኔታ ያጠበዋል።

የእምነት አስተማሪዎች እንደሚሉት ሰው በአካል ውስጥ የሚኖር መንፈስ ብቻ ሳይሆን፥ በትክክለኛው ማንነቱ ሰው ከመንፈስ፥ ከነፍስና ከሥጋ የተገነባ ፍጡር ነው (1ኛ ተሰ. 5፡23)።

የእምነት አስተማሪዎች፥ "ሰው መንፈስ ነው" ለሚለው "መገለጣቸው" ከሚያቀርቧቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 እና 4 ይገኙባቸዋል። እነዚህ ሰዎች ጌታ ለኒቆዲሞስ፥ "ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው" ሲል ስለ ዳግም ልደት የተናገረውንና እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ልናመልክ እንደሚገባን የተጠቀሰውን በመውሰድ፥ መንፈስ ነን ሲሉ ይናገራሉ።

ለመሆኑ፥ ጌታ ለኒቆዲሞስ ዳግም ልደት ከመንፈስ መወለድ እንደሆነ ሲናገር፥ በቀጥተኛ ፍችው ነበር መልእክቱን ያስተላለፈው? እንግዲያው፥ ጌታ ራሱ ለምን ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ባዩ ጊዜ፥ "መንፈስ ይሆን?" ሲሉ ለሰነዘሩት ጥያቄ፥ "አዎን፥ እኔ መንፈስ ነኝ፤ እናንተም ዳግም ስትወለዱ ልክ እንደ እኔው መንፈስ ትሆናላችሁ?" በማለት አልመለሰም? ይልቁንም ጌታ፥ "እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ <u>መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና</u>" (ሉቃስ 24፡39) ሲል ነበር የመለሰው።

ጌታ የዳግም ልደት ትምህርትን በገለጸበት ወቅት ኒቆዲሞስ አሳቡን በቀጥታ ወስዶ ከሥጋዊ ልደት ጋር እንዳዛመደው ግልጽ ነው። "ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ዳግም ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለዳል?" ሲል ነበር የጠየቀው። የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆችም እንዲሁ መልእክቱን በማዛባት መንፈስ ነን ብለዋል። ጌታችን ግን ለኒቆዲሞስና ለእኛም ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት፥ ከሚታየው ቁሳዊ ዓለምና ሕይወት ባሻገር እግዚአብሔር ለልጆቹ ያዘጋጀው መንፈሳዊ ዓለም እንዳለ ነው።

ነገር ግን የዚሁ የመንፈሳዊ ዓለም እውነታም ሆነ የእኛ ከመንፈሱ መወለድ፥ ሰብአዊ ማንነታችንን አይሽረውም። ዛሬ ክርስቲያኑም እንደሌላው ሰው ሁሉ፥ ነፍስ፥ ሥጋ፥ መንፈስ አለው። ይበላል፥ ይጠጣል፥ ያገባል፥ ይጋባል፥ ሌላም ሌላም ሰብአዊ ተግባር ያከናውናል። በሚመጣው ዓለም ግን "አያገቡም አይጋቡምም፥ እንደ መላእክት ናቸውና" (ሉቃስ 20፡35)። በዚህም ጊዜ እንኳ ሰው መንፈስ ብቻ ሳይሆን አካል የሚኖረው መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን።

*"ሰማያዊ አካል አለ፤ ምድራዊም አካል አለ"* (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡40)።

ብዙዎች እንደሚሉት፥ ሰው መንፈስ ነው የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ በቀጥታ ወስደን አማልክት ነን የምንል ከሆነ፥ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር የሚያሳያቸውን ልዕለ–ተፈጥሮአዊ ባህርያት ሁሉ ማሳየት ሊጠበቅብን ነው። ይህንን ግን በውስንነት የሚኖረው የሰው ልጅ ሊወጣው እንደማይችል የሰው ልጆች የጋራ ተሞክሮ ያሳያል።

ለመሆኑ፥ ሰው መንፈስ እንደሆነና በሥጋ ውስጥ እንደሚኖር የሚያስረዳው ዶክትሪን አደገኛ የሚሆነው እምኑ ላይ ነው? አደገኛነቱ በብዙ መልኩ ቢሆንም፥ ለአንባቢዎቼ ላስገነዝብ የምፈልገው ሁለቱን ብቻ ነው። ይህ አስተሳሰብ ከጥንቱ የኖስቲሲዝም ትምህርት የመነጨ ሲሆን፥

እንደሚታወቀው የኖስቲሲዝም መምህራን መልካሚ የሰው ነፍስ ክፉ በሆነው ሥጋ ውስጥ ታስራ እንደምትኖር ያስተምሩ ነበር። ስለሆነም፥ ሰዎች ከፈጣሪ ጋር ለመገናኘት ከዚሁ ክፉ ሥጋ መገላገል ወይም ራሳቸውን መግደል እንዳለባቸው ይመከሩ ነበር።

"የሜታፊዚክስ አባት" ይባል የነበረው ፕሌቶ ሳይቀር፥ "ነፍስ ሰውነትን ልትገዛና ልትመራ ይገባል... እውነተኛ ፈላስፋ ራሱን ለመግደል ወደ ኋላ አይልም። ምክንያቱም ከሞት በኋላ ነፍሱ ከሥጋዊ እስራቶች ነጻ እንደምትሆንና ወደ መጀመሪያ ጥንተ-ነገሯ እንደምትመለስ ስለሚያውቅ ነው"[35] ብሏል።

የዛሬዎቹ የእምነት አስተማሪዎች ደግሞ የሥጋን ወይም የሰውነትን እርባና-ቢስነት የሚያስፋፉት ለየት ላለ ዓላማ ነው። ይኸውም ሥጋ ምንም ስለማይጠቅምና ዋነኛውም ሰው መንፈስ ስለሆነ፥ የዚህ እምነት ተከታዮች በሥጋቸው ኃጢአትን ቢሠሩ ምንም አይደለም ባዮች ናቸው። ለዚህም ነው አንዳንድ የእምነት እንቅስቃሴ አባላት "ኢየሱስን የመሰለ አዳኝ ይዞ ለኃጢአት ማለቃቀስ ምን ያስፈልጋል?" የሚሉት። ኬነት ሐገን የሚከተለውን በመጽሐፋቸው ውስጥ አስፍረዋል።

*"ክርስቲያን ሆኜም ብዙ ጊዜ ኃጢአትን እሠራለሁ። ነገር ግን የውስጥ ሰውነቴ ኃጢአትን አያደርግም... ስለሆነም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው በመንፈሴ ውስጥ እንጂ በሥጋዬ ውስጥ አይደለም..."*[36]

መጽሐፍ ቅዱስ ግን፥ "ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?" ይለናል (1ኛ ቆሮ. 6፡19-20)።

ሌላው አደገኛ አዝማሚያው ደግሞ ሰው መንፈስ እንደመሆኑና ችግሩም መንፈሳዊ እንደመሆኑ፥ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ችግሮች ለማቃለል በመንፈሱ እንደሞተ ለማስተማር በር ይከፍትላቸዋል። እናም ክርስቶስ ሰውን ለማዳን መንፈሳዊ ሞት ማለት በሲኦል ዳግም ልደት አገኘ የሚባለው ለዚህ ነው። ስለሆነም፥ ሰውነትን የሰው አካል አድርጎ ያለመመልከቱ ዋንኛ አደጋ እነዚህንና ሌሎችንም ብዙ ችግሮች አስከትሎ የሚታይ ነው።

እዚህ ላይ የእምነት ዶክትሪን ወጥ-አልባነት መመልከቱ ቀላል ነው። በአንድ በኩል የሥጋን ከንቱነት ሲያስተምር፥ ዞር ብሎ ደግሞ "ብልጽግና" በተሰኘው ብልሃት ሥጋዊ ሀብት ለማግበስበስና ዓለማዊ ቅንጦትን ለመሻማት ይሽቀዳደማል።

እንደዚሁም፥ ሰው በኃጢአት በመውደቁ ሰይጣናዊ ባህርይ ወረሰ የሚለው በምንም መልኩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን አይችልም። የሰው ባህርይ "በእግዚአብሔር አምሳል" የተፈጠረ ቢሆንም፥ ሙሉ ሰብአዊነት ያለው ነው። ለመሆኑ ይህ የእግዚአብሔር አምሳል ምንን ያመለክታል?

በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርነው የፈጣሪያችንን ክብር እንድናንጸባርቅና በምድር ላይ እርሱን ወክለን እንድንሠራ እንጂ አማልክት እንድንሆን አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የማይታይ አምላክ ምሳሌ" (ቆላ. 1፡15)፥ "የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ" (ዕብ. 1፡3) እንደሆነ ተገልጾአል። ይህም ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን በትክክል የምንረዳበት ነው።

እኛ ግን ራሳችንን ወደዚህ ደረጃ እንድናሻቅብ የሚያደፋፍር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አናገኝም። በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መፈጠራችን የእርሱን ፍቅርና ቸርነት በማንጸባረቅ ተግባራዊ እንድምታን ሊያሳይ ይገባል። "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" (ኤፌ. 2፡10)።

ውድቀቱም ቢሆን፥ አምሳላችንን በማበላሸት እንደተሰበረ መስታወት አደረገን እንጂ ሰይጣናዊ ባህርይ አላለበሰንም – ሙሉ ለሙሉ አምሳሉን አላወደመብንም (ዘፍጥ. 9፡6፤ ያዕ. 3፡9)። እንደ ምክኮንል፥ "የእግዚአብሔር አምሳል ከሰው ልጅ ሙሉ ለሙሉ ተደምስሶ ወይም በሰይጣን ተይዞ ቢሆን ኖሮ፥ ሰው ከእንስሳት ባልተለየ ነበር። ሰው ሰው መሆኑ ይቀርና ከሥነ-ምግባር ኃላፊነት ወይም ከደኅንነት ምላሽ ይርቅ ነበር።"[37]

የተበላሸው አምሳልም ቢሆን በክርስቶስ ታድሶ ሰው ዳግም የእግዚአብሔር አምሳልና ክብር ለመሆን በቅቷል (1ኛ ቆሮ. 11፡7)። "የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል" (ቆላ. 3፡10)። ለመሆኑ የዚህ አዲስ ሰውነት አንድምታ ምንድን ነው?

*"ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፤ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፤ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" (ኤፌ. 4፡24)።*

ይህ ክርስቲያን በክርስቶስ በኩል ባገኘው ደኅንነት የተፈጠረበትን የእግዚአብሔርን አምሳል ተግባራዊ እንዲያደርግ ያደፋፍረዋል። ይህም እንደ እግዚአብሔር የጽድቅና ቅድስና ባህርያትን በማሳየት ተግባራዊ ይሆናል። በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራችንም እነዚህን የእግዚአብሔርን ባህርያት በምድር ላይ እንድናንጸባርቅ እንጂ፥ ስለ አምላክነትና ስለ ሰይጣንነት እያነሣን እንድንወዛገብ አልተሰጠንም።

## *ክርስቶስ ለሰይጣን ተሠውቷል?*

የክርስቶስ ሞት ለእግዚአብሔር የቀረበ መሥዋዕት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ "ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን

መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን እንደ ሰጠ . . ." ሲል ምስክርነቱን ይሰጣል (ኤፌ. 5፡2)።

እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 4፡4፥ ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ መሆኑን የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ስላሉ፥ የኪንየን ስሕተት የሰይጣንን አገዛዝ መግለጻቸው አይደለም - "በሕጋዊ መብት ገዛ" ማለታቸው እንጂ! ሰይጣን አገዛዙን የተቀበለው በማታለል እንጂ በሕጋዊነት አይደለም (ራእይ 12፡9-10፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡4)፤ እግዚአብሔርም ምንም የሰይጣን ዕዳ የለበትም - ቤዛ የሚከፍልበት!

እስኪ ረጋ ብለን ቅዱስ ቃሉ ላይ በመንተራስ እናስብ... እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ ሲያበቃ፥ በምታምር ዔድን ገነት ውስጥ አስቀመጣቸው። ይህ ከኦሪት ዘፍጥረት ውስጥ የምናገኘው ታሪክ ነው። በዚህም ጊዜ እርሱን በመታዘዝ እንዲኖሩ ነገራቸው። ካልታዘዙት ግን ሞት እንደሚጠብቃቸው አስጠነቀቃቸው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፥ እነ አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሰው በመገኘታቸው የተባለው ሞት በትረ መንግሥቱን ዘረጋባቸው፤ ይህም ሞት መንፈሳዊና ሥጋዊ ነበር። መንፈሳዊ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ኅብረት መቋረጡ ሲሆን፥ ሥጋዊው ሞት የነፍስና የሥጋ መለያየት ነበር።

ከኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ እንደምናስታውሰው፥ ሰውን ለዚህ ሞት የዳረገው ሰይጣን መሆኑ ግልጽ ነው። ይህንንም ያደረገው እነ ሐገን እንደሚሉት፥ በሕጋዊ መብቱ ተጠቅሞ ሳይሆን በማታለል ነበር - በአባቢቱ አማካኝነት። በዚህም ጊዜ፥ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደመሆኑ ሕጋዊ ባለቤትነት ቢኖረውም፥ የሰው ልጆች በሰይጣን አገዛዝ ሥር ነበሩ። እግዚአብሔር ግን የሰው ልጅ በሰይጣን ተታሎ የሞትን ጽዋ ሲጠጣ በማየቱ አዘነ። ስለሆነም፥ አንድ ነገር አደረገ።

ይህም አንድ ነገር የእግዚአብሔርን የፍቅርና የጽድቅ ባህርያት አጣምሮ የያዘ ነበር። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በፍቅሩ የሰውን ልጆች ከሰይጣን እስራት ለማላቀቅ ቢፈልግም፥ 'ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ' (ዘፍጥረት 2፡17) ሲል የተናገረው ቃል መፈጸም እንዳለበት ያውቅ ነበር - የራሱን ቃል ራሱ እንዲሽር የጽድቅ ባህርዩ አይፈቅድለትምና። እናም ሰው ዳግም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲያደርግና የኃጢአቱ ደመወዝ የሆነው ሞት እንዲነሣ ከተፈለገ፥ አንድ ሰው መሞት ነበረበት። በመሆኑም፥ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው እግዚአብሔር 'ሞትን ትሞታለህ' ሲል ለአዳም የተናገረውን ለመፈጸምና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለማሟላት እንጂ፥ የእምነት ሰዎች እንደሚሉት ለሰይጣን ለመክፈል አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱሳችን፥

*"በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ አያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው"*

ስለሚል፥ እግዚአብሔር የሰይጣንን ኃይል የሰበረው "ከኃጢአትና ከሞት ሕግ" እኛን ነጻ በማውጣት ነው (ሮሜ 8፡2፤ ቆላ. 2፡14–15ን አነጻጽር)። ዶ/ር ራይት በዚህ ጥቅስ ላይ ከሰጡት ማብራሪያ፥ "ክርስቶስ በመሚሕነቱ በእኛ ፋንታ በመሞት ይህንኑ የሚቃወመንን የዕዳ ጽሕፈት አሟልቷል" ብለዋል።

*እናም እግዚአብሔር የሰይጣንን አገዛዝ ያፈራረሰው ኢየሱስን በቤዛነት ለሰይጣን በመክፈል ሳይሆን፥ ሰይጣን ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ለመክሰስ የሚጠቀምበትን የእግዚአብሔርን ሕግ በማሟላት ነው።*

ሚላርድ ኤሪክሰን እንደተናገሩት፥

*"የእግዚአብሔርን ድልና የሰይጣንን ሽንፈት ያረጋገጠው ለሰይጣን የቀረበለት ቤዛ ሳይሆን፥ ይልቁንም ክርስቶስ ከሕግ ርግማን እኛን ነጻ ለማውጣት ስፍራችንን በመውሰዱ ነበር። [ቤዛነቱ ለሰይጣን መሰጠቱ ሳይሆን፥ የእኛን የምስኪንነት ስፍራ በመውሰድ ነጻ ሊያደርገን መቻሉ ነበር!] የኃጢአታችንን ቅጣት በመሸከምና በዚሁም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሕጉን ፍትሐዊ መመዘኛዎች በማሟላት፥ ክርስቶስ ሰይጣን በእኛ ላይ የነበረውን ቁጥጥር ምንም አድርጎታል – ከርግማንና ከሕግ ኩነኔ ሥር ያደረገን ኃይል ስለሆነም የክርስቶስ ሞት ቤዛዊ መሥዋዕት በመሆኑ፥ እግዚአብሔር በክፉ ኃይላት ላይ የተቀዳጀው ድል ነበር።"[38]*

የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች በዚህ የሥነ–መለኮት ውጥረት ውስጥ ራሳቸውን የከተቱት፥ ምናልባትም ዘመናዊውን የቤዛነት ፍች ተከትለው በመሄዳቸው ይሆናል። በዛሬው ዓለም ቤዛ የሚከፈለው ባብዛኛው በአጋቾች ቁጥጥር ሥር ለዋለ ሰው ነው። በምዕራቡ ዓለም ሰዎች ለፖለቲካዊና መዋዕለ–ንዋያዊ ጠቀሜታዎች ሲባል ይታገታሉ። አውሮፕላኖች ይጠለፋሉ። ጠላፊዎቹ ወይም አጋቾቹም ከመንግሥት ወይም ከተወሰነ ወገን የሚፈልጉትን እስካላገኙ ድረስ በቁጥጥር ሥር ያዋሏቸውን ሰዎች እንደሚፈጁ ያስፈራራሉ።

ይህንኑ ግንዛቤአቸውን ነው፡ እንግዲህ እነ ሐገን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስገብተው ለማብራራት የሞከሩት – ምንም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ባያገኙም። እንደነርሱ መረዳት ከሆነ፥ ሰይጣን የሰውን ልጆች ሁሉ ከቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ወደ ሲኦል ካልጨመርኋችሁ እያለ ሲፎክር፥ እግዚአብሔር ኢየሱስን በቤዛነት አስይዞ አስለቀቃቸው ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን የቤዛን አሰጣጥ የሚያስተምረው ከዚህ በተለየ መንገድ ነው። እስኪ ስለ ቤዛነት ወይም መቤዠት ከሚናገሩ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚከተሉትን እንመልከት።

"የቅርብ ዘመድ መሆኔ እውነት ነው፤ ነገር ግን ከእኔ የቀረበ ዘመድ አለ... እርሱ ዋርሳ መሆን ቢወድድ መልካም ነው፥ ዋርሳ ይሁን፤ ዋርሳ ሊሆን ባይወድድ ግን፥ ሕያው እግዚአብሔርን! እኔ ዋርሳ እሆንሻለሁ..." (ሩት 3፡12-13)።

"ከሰው ወይም ከእንስሳ ቢሆን፥ ለእግዚአብሔር ከሚያቀርቡት ሥጋ ሁሉ ማኅፀን የሚከፍት ሁሉ ለአንተ ይሆናል፤ ነገር ግን የሰውን በኩራት ፈጽሞ ትቤዠዋለህ፥ ያልነጻውንም እንስሳ በኩራት ትቤዠዋለህ። ከአንድ ወር ጀምሮ የምትቤዠውን እንደ ግምትህ ትቤዠዋለህ፤ ግምቱም እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን አምስት ሰቅል ይሆናል... ነገር ግን የላም በኩራት ወይም የበግ በኩራት ወይም የፍየል በኩራት አትቤዥም፤ የተቀደሱ ናቸው፤ ደማቸውን በመሠዊያው ላይ ትረጨዋለህ፥ ስባቸውንም ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን ለእሳት ቁርባን ታቃጥለዋለህ" (ዘኁልቁ 18፡ 15-20) ።

ከነዚህና ከሌሎችም በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች የምንረዳው እውነት ቢኖር፥ ቤዛነት ወይም መቤዠት ለሚከተሉት ተግባራት ማገልገሉን ነው።

- አንድ ሰው በሞት ሳቢያ ዘመድ-አዝማዱን አጥቶ መጠጊያ በሚያጣ ጊዜ የርዳታ እጅ መሰንዘርን። የሩት አማት ኑኃሚን ባሏንና ልጆቿን በባዕድ ምድር በሞት ተነጥቃ በተመለሰች ጊዜ፥ ቦኤዝ ሩትን በሚስትነት ደረጃ ተቀብሎ ማስተዳደርና መርዳት መጀመሩን ከሩት መጽሐፍ እንመለከታለን።
- አንድ ሰው መሥዋዕት ለማቅረብ በሚፈልግበት ጊዜ፥ ለመሥዋዕትነት ያዘጋጀው እንስሳ ብቁ ካልሆነ ይቤዠዋል - ማለትም የእንስሳውን ዋጋ በጥሬ ገንዘብ ይከፍላል።
- ሰውን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ከተሳለ፥ ሰው ለመሥዋዕትነት አገልግሎት ስለማይውል አሁንም ገንዘቡን ከፍሎ ይቤዠዋል ወይም ያስመልሰዋል።

ከዚህ ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ዳራ ስንነሣ አንግዲህ ድምዳሜአችን ምን ይሆናል?

ድምዳሜአችን የሚሆነው ኢየሱስ ለሰይጣን የማገቻ ዋጋ ሆኖ ተሰጠ የሚለው ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለሟሟላት በመስቀል ላይ ራሱን ለእግዚአብሔር አቀረበ የሚለው ነው። ስለሆነም፥ ክርስቶስ "ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ" መሆኑን ነው የምናምነው (ዕብራውያን 9፡14)።

## *ኢየሱስ ኃጢአት (ሰይጣን) ሆኖ ነበር?*

የእምነት አራማጆች ክርስቶስ ኃጢአት ወይም ሰይጣን ሆኖ ነበር ለሚለው ትምህርታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለድጋፍ የሚጠቅሱት በ2ኛ ቆሮንቶስ

5:21 "ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው" የሚለውን ክፍል ነው። እዚህ ላይ የእምነት አስተማሪዎች ያልተገነዘቡት ነገር እንዳለ ግልጽ ነው። ለመሆኑ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስን "ኃጢአት አደረገው" ሲል ምን ማለቱ ነው? ኮሊን ክሩዝ ሦስት የይሆናል መላ-ምቶች እንዳሉ በመግለጽ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

- የእምነት አስተማሪዎች እንደሚሉት ክርስቶስ ኃጢአት ሆኖ ነበር።
- ክርስቶስ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ነበር።
- ክርስቶስ የኃጢአታችንን ውጤቶች እንዲሸከም ተደርጎ ነበር።

እንደ ክሩዝ ማብራሪያ፥ የመጀመሪያው አማራጭ ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ስለሌለው ጊዜ ማጥፋት የሚያስፈልገው አይደለም። ሁለተኛው፥ ጳውሎስ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞት ከሚናገርበት አሳብ ጋር ሊዛመድ ይችላል (ለምሳሌ፥ ሮሜ 3:25፤ 1ኛቆሮ. 5:7)። እንዲሁም፥ በዘሌዋውያን 4:24 ይኸው ቃል "የኃጢአት መሥዋዕት" የሚል ፍች ይዞ ይገኛል። ይህም የብሉይ ኪዳንን የእንስሳት መሥዋዕትነት ተምሳሌት (Symbolism) እያመለከተ መሆኑ ነው (ሮሜ 8:3 ተመልከት።)

በብሉይ ኪዳን ኃጢአት የሠራ ሰው ነውር በሌለበት እንስሳ ላይ እጁን ይጭንና ኃጢአቱ ወደ እንስሳው ይተላለፋል። ይህ ማለት ግን እንስሳው በቀጥታ ኃጢአተኛ ሆነ ማለት አይደለም። እንዲያውም፥ መሥዋዕቱም ሆነ ከዚያ የበላ ሰው ሁሉ ቅዱስ ይሆን ነበር (ዘሌዋ 6:25-27፥ 29)።

ኃጢአቱ ወደ እንስሳው የሚተላለፈው በተምሳሌት መሆኑ ነው። የክርስቶስም ስለ እኛ ኃጢአት መሆን እንዲሁ ተምሳሌታዊ ነው። በመሆኑም ነው ክርስቶስ ራሱን ያለ ነውር ለእግዚአብሔር አቀረበ ለማለት የሚቻለው (ዕብ 9:14)። በርግጥም ኃጢአት ሆኖ ቢሆን ኖሮ ነውር እንደሌለው መሥዋዕት በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም ነበር።

በዚህ ማብራሪያ ያልረካ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚ ቢኖር ቀጥሎ የተመለከተውን አማራጭ ሊያገናዝብ ይችል እንደሆን እንጂ ከቶውንም አምላኩን ወደ ኃጢአትነት ወይም ወደ ሰይጣንነት ተቀየረ ሊል አይደፍርም። ስለሆነም፥ ወደ ሦስተኛው ማብራሪያ ስናልፍ ጳውሎስ በገላትያ 3:13 የክርስቶስን ሞት የኃጢአታችንን ውጤቶች ከመሸከሙ ጋር በማዛመድ ሲተረጉም እንመለከታለን። "በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን።"

ይኼኛው አተረጓጎም ይበልጥ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ደግሞ "ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው" የሚለው ዓረፍተ-ነገር በተቃርኖአዊ ትይዩነት (antithetical parallelism) ፥ "በእርሱ ሆነን

የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ" ከሚል አሳብ ጋር በመቀመጡ ነው። ስለሆነም፥ ሁለቱንም ተቃራኒ አሳቦች በመመልከት ተገቢውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍች ልናገኝ እንችላለን።

"የእግዚአብሔር ጽድቅ" መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት በምናደርገው ጥረት እንደ ሮሜ 3፡21–26፥ ፊልጵስዩስ 3፡7–9 የመሳሰሉ ሌሎች የጳውሎስ መልእክቶች እገዛ ያደርጉልናል። በነዚህ ምንባቦች መሠረት፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ ማለት ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በነርሱ ምትክ ከመሞቱ የተነሣ በፍርድ ብያኔው የኃጢአታቸውን ዕዳ ሳያስከፍላቸው እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ተገቢውን ግንኙነት እንዲመሠርቱ የሚያደርግበት መንገድ ነው።

ክሩዝ እንደሚሉት፥ "የእግዚአብሔር ጽድቅ መሆን ማለት እግዚአብሔር ለእኛ ፈርዶልን ከራሱ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ለማድረግ መታደል ከሆነ፥ ኃጢአት መሆን ማለት ደግሞ በተቃራኒ ገጽታው እግዚአብሔር በክርስቶስ ላይ ፈርዶበት (ኃጢአታችንን በመሸከሙ ምክንያት – ኢሳይያስ 53፡ 4–6፥ 12) ለጊዜውም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት የተቋረጠበት እንደሆነ እንመለከታለን። ይህም በመሆኑ ነው ጌታ በጌቴሰማኔ፥ "አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ" (ሉቃስ 22፡42)፤ "አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?"(ማቴዎስ 27፡46) ሲል በውጥረት የቃተተው።

እናም፥ ጌታ ኃጢአት ወይም ሰይጣን ሆነ ለማለት የሚያስችል ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍተት እንደሌለ ልብ ልንል ያሻል።

## *የወኅኒው ስብከት*

መፍሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ሞት የሚለው ከዚህ በላይ የተብራራ ቢሆንም፥ ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት እንደ ሰበከ በሚናገረው የ1ኛ ጴጥሮስ 3፡19–20 ምንባብ ግራ እንዳይጋቡ በማሰብ ቀጥለን እናቀርባለን።

*"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤ ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18–20)።*

በዚህ ምንባብ፥ በተለይም "በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው" በሚለው ክፍል አተረጓጎም ላይ ሰፊ የአሳብ ልዩነት በመከሰቱ፥ የሚከተሉት ዐበይት ጥያቄዎች ተነሥተዋል።

1 በወኅኒ የነበሩ ነፍሳት እነማን ናቸው?

- ♣ ከዚህ ቀደም ሳያምኑ የሞቱ?
- ♣ ከዚህ ቀደም የሞቱ የብሉይ ኪዳን አማኞች?
- ♣ የወደቁ መላእክት?

2 ክርስቶስ የሰበከው ምን ነበር?

- ♣ ለንስሓ ሁለተኛ ዕድል?
- ♣ የማዳን ሥራውን ፍጻሜ?
- ♣ የኩኔነያቸውን ፍጻሜ?

3 መች ሰበከ?

- ♣ በኖኅ ዘመን?
- ♣ በሞቱና በትንሣኤው መካከል በነበረው የጊዜ ክፍተት?
- ♣ ከትንሣኤው በኋላ?

ሰዎች ለነዚህ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች፥ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለዚህ ምንባብ አምስት ዓይነት ዐበይት አመለካከቶች እንዲወለዱ አድርገዋል።

<u>አመለካከት 1</u> – ኖኅ መርከቡን በሚሠራበት ጊዜ፥ ክርስቶስ በመንፈስ በኖኅ ውስጥ ሆኖ በዚያን ጊዜ በምድር ላይ ለነበሩትና አሁን ግን በወኅኒ ወይም በሲኦል በእስር ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ንስሓንና ጽድቅን በኖኅ በኩል ይሰብክ ነበር።

<u>አመለካከት 2</u> – ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚያ ለተኮነኑት ሰዎች ሁለተኛ የንስሓ ዕድል በመስጠት ሰበከላቸው።

<u>አመለካከት 3</u> – ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚያ ለነበሩት ተኮናኞች ድል እንደነሣቸውና ኩነኔያቸውም ከፍጻሜ ላይ እንደደረሰ ሰበከላቸው።

<u>አመለካከት 4</u> – ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ወደ ሲኦል ወርዶ በጥፋት ውኃው ከመሞታቸው ጥቂት ቀደም ብለው ንስሓ የገቡትን ሰዎች ነጻ መውጣት በመስበክ፥ ታስረው ከነበሩበት 'ፑርገተሪ' ወደ መንግሥተ ሰማይ አስገባቸው።

<u>አመለካከት 5</u> – ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ማለትም ከሞት ከተነሣና ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፥ ወደ ሲኦል በመውረድ ከጥፋት ውኃው በፊት የሰዎችን

ሴቶች ልጆች በማግባት ኃጢአት በፈጸሙት የወደቁ መላእክት ላይ ድል መንሣቱን አወጀ።

ዶክተር ግሩደም በዚህ ምንባብ ላይ በሰጡት ማብራሪያ፥ ጴጥሮስ ለማለት የፈለገው በአመለካከት አንድ የተቀመጠውን አሳብ እንደሆነ በመግለጽ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

*"ወደ አሳቤ ከመሻገሬ በፊት በአመለካከት 5 ላይ አጭር አስተያየት ልሰነዝር እፈልጋለሁ። ይህ አመለካከት አይሁዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆኑ የተወሰኑ ትውፊቶች እንደነበሯቸውና በተለይም ሄኖክ ወደ ሲኦል ወርዶ ለወደቁት መላእክት የኩነኔ ቃል ማወጁ በአይሁዶች ዘንድ የታወቀ እንደነበር ያስረዳል። ስለሆነም፥ አሁን ጴጥሮስ ክርስቶስ 'በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው' በሚልበት ጊዜ፥ አይሁዳውያን የሄኖክን መልእክት በማስታወስ ጴጥሮስ የክርስቶስን የላቀ ድል (በወደቁት መላእክት ላይ ያገኘውን) ይገነዘባሉ። በዚህ አመለካከት መሠረት፥ 'ቀድሞ አልታዘዙም' የሚለው ሐረግ በዘፍጥረት 6፡2፥4 የሰውን ልጆች በማግባት ኃጢአት የፈጸሙትን መላእክት እንደሚያመለክት ይታሰባል።"[39]*

ይሁንና፥ በወኅኒ የነበሩት ነፍሳት እነማን ናቸው?

*1. መላእክት ናቸው ወይስ የሰው መንፈሶች?*

ይህ መንፈሶች (በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን ነፍሳት) የሚለው ቃል እንደ ዓውደ-ንባቡ የሰውን ወይም የመላእክትን መንፈስ ሊያመለክት ይችላል። ይህም የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ቋንቋ ውስጥ ያገለገለው የግሪክ ቃል 'ኒውማ' የሰውን ወይም የመላእክትን ወይም የአጋንንትን መንፈስ ሊያመለክት የሚችል በመሆኑ ነው። መክብብ 12፡7፤ ማቴዎስ 27፡50፤ ሉቃስ 23፤46፤ ዮሐንስ 19፡30፤ የሐዋርያት ሥራ 7፡59፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡5፤ 7፡34፤ 14፡14፤ ዕብራውያን 12፡23፤ ያዕቆብ 2፡ 26 ቃሉ የሰውን መንፈስ ለማመልከት እንዳገለገለ ያሳያሉ። መላእክትን ወይም አጋንንትን እንደሚያመለክት የሚያሳዩ ጥቅሶች ደግሞ 'መናፍስትን በቃሉ አወጣ' የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ ምንባቦች ይገኛሉ። (ማቴዎስ 10፡1፤ 12፡43፥ 45፤ ማርቆስ 1፡23፤ ሉቃስ 10፡20፤ የሐዋርያት ሥራ 23፡8 ይመልከቱ።)

2. እነዚህ መናፍስት በወኅኒ የኖሩት አሁን ነው ወይስ ክርስቶስ በሰበከላቸው ጊዜ?

ምንም እንኳ ክፍሉን መጀመሪያ ስናነበው 'በወኅኒ ቤት የነበሩ ነፍሶች' ስብከቱ በተካሄደበት ወቅት በመንፈስ ደረጃ እንደነበሩ ሊመስል ቢችልም፥ እውነቱ ግን የግድ ይኸው ነው ለማለት አይቻልም። ቁጥር 19 'አሁን በወኅኒ ለሚገኙ መንፈሶች' ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፤ ይህም ማለት እነዚህ ሰዎች በጥፋት ውኃው ወቅት በሰብአዊ አካል የነበሩና ጴጥሮስ መልእክቱን

በሚጽፍበት ጊዜ ግን በሲኦል የሚኖሩ መንፈሶች ነበሩ ማለት ነው። ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ አሳብ ጋር በሚቀራረብ መልኩ አስቀምጦታል። "በኖኅ መርከብ ጊዜ እግዚአብሔር በትዕግሥት ሲጠብቃቸው ሳለ ላልታዘዙትና አሁን ግን በወኅኒ ለሚገኙ መንፈሶች ሰበከላቸው" ይላል። የ1980ው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ቁጥር 20፥ "እነዚህ በወኅኒ የነበሩ ነፍሶች <u>ቀድሞ</u> በኖኅ ጊዜ መርከብ ሲዘጋጅ እግዚአብሔር በትዕግሥት ሲጠብቃቸው ሳለ አንታዘዝም ያሉ ናቸው። በመርከብ ውስጥ ገብተው በውኃ አማካይነት የዳኑት ቁጥራቸው ስምንት የሆነ ጥቂት ሰዎች ናቸው" ይላል።

ከዚህ በመነሣት፥ ግሩደም "አንድ ሰው የቀድሞ ደረጃውን ይዞ ባይገኝም፥ የቀድሞውን ሁኔታ ለማብራራት ሲባል በዚያው ባለፈው ደረጃ አንጻር መነጋገሩ እንግዳ ነገር አይደለም" ይላሉ። ለዚህ ምሳሌ ሲሰጡ፥ ምንም እንኳ ንግሥት ኤልሳቤጥ ንግሥት ሆና ባትወለድም፥ ንግሥቲቱ የተወለደችው በ1926 ነው ሊባል ይችላል።

*"ስለሆነም፥ ክፍሉ የሚያመለክተው በኖኅ ዘመን ያልታዘዙትንና ጴጥሮስ መልእክቱን በሚጽፍበት ጊዜ ግን ሲኦል ወርደው የነበሩትን ሰዎች ነው። ይህንን አሳብ ግልጽ ለማድረግ ከተፈለገ፥ መርከቡ በሚሠራበት ወቅት ያልታዘዘው ማን ነው? እግዚአብሔር በትዕግሥት ሲጠብቅ የኖረው ማንን ነው? የሚሉ ዓይነት ጥያቄዎችን ማንሣቱ ተገቢ ነው። እንደ ኦሪት ዘፍጥረት 6፡5-7፥ 12-13፤ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡5፡ ማቴዎስ 24፡37-39፤ ሉቃስ 17፡26-27 የመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ዘገባ፥ ኖኅ መርከብ እየሠራ ሳለ በማስገጥና በኃጢአታቸው በመቀጠል ያልታዘዙት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ናቸው።"*[40]

*ክርስቶስ ምን ሰበከላቸው?*

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው፥ የተለያዩ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልሶች ሰጥተዋል። ከነዚህም መካከል፥ በሲኦል ለነበሩ ሰዎች የማጠቃለያ ኩኔን ሰበከ (አመለካከት 3)፤ በሲኦል ለነበሩ መላእክት የማጠቃለያ ኩነኔ ሰበከ (አመለካከት 5) የሚሉ ይገኙባቸዋል። ግሩደም ግን እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ጴጥሮስ ፍርድን አወጀ ወይም የኩነኔ ብያኔ ሰጠ በማለት አሳቡን ግልጽ ያደርግ ነበር፤ አሊያማ ማን በመላ-ምት ይረዳዋል? ሲሉ ይጠይቃሉ።

ከዚህም በላይ፥ ክርስቶስ በሲኦል የሚገኙትን ኃጢአተኞች ኩነኔ ለማወጅ ሲል ወደ ሲኦል ከወረደ የኖኅን ዘመን ኃጢአተኞች ብቻ የሚለየው ለምንድን ነው? በዘመናት ሁሉ ያልታዘዙ ኃጢአተኞች ምልተው የለ? በማለት አሳባቸውን ይገልጻሉ።

ዶክተር ግሩደም ለብሉይ ኪዳን አማኞች የደኅንነታቸውን ፍጻሜ ለማወጅ ነው የሚሉትንም የአመለካከት 4 ቡድኖች አይቀበሏቸውም። ክፍሉ የሚናገረው በሲኦል ስለታሰሩት ኃጢአተኞች ሆኖ ሳለ፥ ለአማኞች

የደኅንነት ፍጻሜ ለማወጅ ነው ማለቱ ለምንባብ ክፍሉ ታማኝ አለመሆን ሲሆን ክፍሉ የማይለውን እንዲል ማስገደድ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ይሁን ቢባል እንኳ፥ በዘመነ-ብሉይ ኪዳን የነበሩ አማኞች ስምንት ብቻ አይደሉም። እና ለምን ይሆን ኢየሱስ በኖኅ የመርከብ ዘመን ለታዘዙት ስምንት ሰዎች ብቻ የማዳኑን ፍጻሜ የሚያበስረው? "ስለሆነም፥ የሰበካው ዓውድ ኃጢአተኞች ንስሐ ገብተው በእግዚአብሔር ሊያምኑ እንደሚገባ ለማሳየት ነው፥" እንደ ግሩደም።

*"ይህ አተረጓጎም ከ1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 አጠቃላይ ሐሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ከ2፡11 ጀምሮ ጠቅላላው ክፍል የማያምኑ ሰዎች በሞሉበት ዓለም ውስጥ እንደ ክርስቲያን ሆኖ በመኖሩ ላይ የሚያተኩር ስለሆነ፥ ጴጥሮስ ለክርስቲያን አንባቢዎቹ ጠላቶቻቸው ለሆኑት ኢ-አማንያን መልካም ምስክር መሆን እንደሚገባቸው አበክሮ ሲያሳስብ ነበር (2፡12፥ 15፤ 3፡1-2፥ 15-16)። በተለይም 'ሁልጊዜ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ' የሚለው የምስክርነት ጥሪ ከዚህ ሐሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ከመሆኑም በላይ፥ ለቀጣዩ የ3፡19-20 ክፍል መሠረት ይጥላል።"*

*ክርስቶስ የሰበከው መቼ ነበር?*

እስካሁን በወኅኒ የነበሩት ነፍሳት የተባሉት በኖኅ ዘመን የኖሩት ኃጢአተኞች እንደሆኑና የቀረበላቸውም ስብከት የንስሓ ጥሪ እንደነበር ተመልክተናል። ይህም ክርስቶስ የስብከቱን ተግባር ያከናወነው በኖኅ በኩል ነበር የሚለውን የአመለካከት 1 ሐሳብ ሲያጠናክር አመለካከት 3፥ 4ንና 5ን ፉርሽ ያደርጋቸዋል።

በሌላ በኩል፥ ክርስቶስ ወደ ሲኦል ወርዶ የሰበከው በሞቱና በትንሣኤው መካከል በነበሩት የሦስት ቀናት ጊዜ ነው የሚሉ የአመለካከት 2 አራማጆች አሉ። ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች እንደ እምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ሁሉ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ወደ ሲኦል እንደ ወረደ ቢያምኑም፥ ከእምነት እንቅስቃሴ የሚለዩበት መሠረታዊ ሐሳብ እንዳለ ልብ ልንል ይገባል። ይኸውም፥ የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ክርስቶስ ወደ ሲኦል የወረደው የሰይጣንን ባህርይ ወርሶ ዳግም ለመወለድ እንደሆነ ሲያስተምሩ፥ እነዚህኞቹ ግን በኖኅ ዘመን ሳይታዘዙ ቀርተው ሲኦል ለወረዱት ሰዎች ዳግም የንስሐ ዕድል ለመስጠት ነው ባዮች ናቸው። እውን ከሞት በኋላ የንስሐ ዕድል አለ?

ክርስቶስ ለነፍሳቱ የሰበከው በሞቱና በትንሣኤው መካከል ባለው ጊዜ ወይም ከትንሣኤው በኋላ ነው ለሚለው እምነት መሠረቱ፥ ከዚህ ክፍል ቀደም ብሎ በሚገኘው በቁጥር 18 ላይ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በግልጽ መቀመጡ ነው። ጴጥሮስ ክርስቶስ በሥጋ ከሞተና በመንፈስ ግን ሕያው ከሆነ በኋላ ወዲያውኑ የስብከቱን ተግባር እንዳከናወነ የሚያስረዳ ነው የሚመስለው።

እንደ ግሩደም ምልከታ ግን፥ "ጴጥሮስ በዚህ መልእክቱ ውስጥ በሚገኙት ሌሎች ስፍራዎች ከአንድ ክፍል መጨረሻ ላይ ሆኖ ወደ ሌላው ለማለፍ ቃላትን ወይም አሳቦችን እንደ መንደርደሪያ የመጠቀሙን እውነታ ስንረዳ፥ ከሞቱ በኋላ ወዲያው ለነፍሳቱ ሰበከ የሚለው አሳብ ክብደት ያጣል።"[41]

ለዚህ አሳብ ማጠናከሪያ ግሩደም ቀጥሎ የተመለከቱትን ምሳሌዎች አቅርበዋል። ጴጥሮስ በ1ኛ መልእክቱ 1፡6 "በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል" ሲል፥ ስለ ደስታ የሚናገር ይመስልና በዚሁ መንደርደሪያነት ስለ መከራ ማብራራቱን ይቀጥላል። በ1፡8 "አሁንም ምንም ባታዩት" የሚለውን ከክርስቶስ ጋር ለሚደረግ ኅብረት መሸጋገርያ አድርጎ ይጠቀምበታል። በ1፡10 "ስለዚህ መዳን" የሚለውን ስለ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ለመነጋገር መሸጋገሪያ ያደርገዋል። በ2፡4 "እየቀረባችሁ" የሚለውን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር አዲስ ሕዝብ ስለመሆኗ ለማብራራት ይጠቀምበታል። በ2፡22 "ኃጢአት አላደረገም" የሚለውን ስለ ክርስቶስ መከራዎችና የማዳን ሥራው ለመናገር መሸጋገሪያ ያደርገዋል። በ3፡21 "ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል" የሚለውን ስለ ጥምቀት ለመናገር መሸጋገሪያ ያደርገዋል።

ደራሲው ግሩደም ከነዚህ ተጨባጭ ማስረጃዎች ዝርዝር ቀጥሎ፥ *"በ1ኛ ጴጥሮስ ውስጥ ሁሉ የሚገኘው ይኸው የይትብሃል ድግግሞሽ እንደሚያሳየው፥ ማንም ሰው በቁጥር 19 ጅማሬ ላይ 'በእርሱ' የተሰኘው ቃል ይህ ጥቅስ የቁጥር 18ን አሳብ ወይም ተመሳሳይ የአሳብ ተዋረድ ይዞ እንደሚሄድ ሊከራከር አይችልም – ጴጥሮስ በዚህ መልእክቱ ውስጥ ብዙ ጊዜ ከአንዱ አሳብ ወደ ሌላው ሲሄድ ይህንኑ ይትብሃል ይጠቀማልና" በማለት ያስረዳሉ።*

*"ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በወኅኒ ለሚገኙ ነፍሳት የመዳንን መልእክት ሰበከ የሚለው አሳብ ከዓውደ-ንባቡም ጋር የሚሄድ አይደለም። ጴጥሮስ በመከራችሁ እንኳ ለክርስቶስ ታማኝ ምስክሮች መሆን አለባችሁ እያለ ነበር የሚናገረው። እንግዲህ፥ በታሪክ ሁሉ እጅግ የከፉት የጥፋት ውኃ ሰለባዎች እንኳ ከሞቱ በኋላ ሌላ የደኅንነት ዕድል ያገኙ እያለ የሚጽፍ ከሆነ፥ በመከራ ውስጥ ለሚገኙ አንባቢዎቹ ምን ዓይነት ማበረታቻ ሊሆን ነው?*

*"በተጨማሪም፥ የዳግም ንስሓው ዕድል በኖኅ ዘመን ለነበሩት ኃጢአተኞች ብቻ ለምን ተሰጠ? የሚለውም ጥያቄ ምላሽ የሌለው ነው። ሌሎች የማስጠንቀቂያ ድምፅ ለመስማት ያልታደሉትስ ለምን ችላ ተባሉ? ከዚህም በላይ ሰው ከሞተ በኋላ የደኅንነት ዕድል ያገኛል የሚለው ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር የማይዛመድ አሳብ ነው (ሉቃስ 16፡26፤ ዕብራውያን 9፡27)።"[41]*

ይህም የምንባብ ክፍሉ አሳብ በአመለካከት 1 እንደተመለከተው መሆኑን ያሳየናል። ስለሆነም፥ ክርስቶስ ስብከቱን ያከናወነው በኖኅ በኩል፥ በመንፈሱ አማካኝነት ኖኅ መርከብ በሚሠራበትና የጥፋት ውኃን መምጣት በሚያውጅበት ጊዜ እንደነበር እንረዳለን። ክርስቶስ ወደ ሲኦል አልወረደም – አይወርድምም። በመስቀል ላይ ሆኖ ለአንደኛው ወንበዴ "ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" ሲል ቃል እንደ ገባው እንዲሁ ሆኗል እንጂ!!

የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች ክርስቶስ ወደ ሲኦል እንደወረደ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ሌላም ምንባብ አላቸው – መዝሙር 21። በዚህ ክፍል "ብዙ በሬዎች ከበቡኝ" የሚለው በሲኦል አጋንንት እንደ ከበቡት የሚናገር ነው ሲሉ ለማስረዳት ይሞክራሉ። ይሁንና፥ ክፍሉን ቀረብ ብለን ስንመለከት በሲኦል ውስጥ ስለ ተፈጸመው ነገር ሳይሆን በክርስቶስ መስቀል ዙሪያ የተከናወነው ጉዳይ መሆኑን እንመለከታለን።

ለምሳሌ፥ በዚሁ የመዝሙር ክፍል ቁጥር 18፥ "ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ" የሚል እናገኛለን። ዮሐንስ በወንጌል ዘገባው፥ የሮም ወታደሮች ጌታን ከሰቀሉት በኋላ ልብሱን ዕጣ በመጣጣል እንደ ተከፋፈሉ ገልጧል። ከዚያም በመቀጠል፥ "ይህም፥ ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ፤ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው ብሏል" (ዮሐንስ 19፡24)። መጽሐፍ ቅዱስ ከማንም ምሁር በላይ ስለ ራሱ ለማብራራት ይችላል። ስለሆነም፥ የዚህ ትንቢት ፍጻሜ ይኼ ነው የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ችላ ብለን የራሳችንን ትርጉም ብንከተል የሚበጀን አይሆንም።

## የኢየሱስ ሁለት ሞቶች

የእምነት አስተማሪዎች የክርስቶስን ሞት "ሰው መንፈስ ነው" ከሚለው ዶክትሪናቸው ጋር ለማስማማት ጥረት ማድረጋቸው አልቀረም። በመሆኑም፥ ሰው መንፈስ እንደመሆኑ የክርስቶስ ሥጋዊ ወይም የመስቀል ሞት ሊረዳው አይችልም። የግድ በመንፈሱ መሞት ነበረበት ይሉናል።

ለዚህም ትምህርታቸው መሠረት ይሆናቸው ዘንድ ኢሳይያስ 53፡9ን ይጠቅሳሉ – "ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ።"

ኬንየን በዚህ ክፍል ሞትን የሚገልጸው የዕብራይስጡ ቃል ብዛትን የሚያመለክት (ሞቶች) ነው ባይ ናቸው። ይሁንና፥ እንደ አማርኛችን ሁሉ የዕብራይስጥ ቋንቋም ለአንድ ነገር ግርማ–ሞገስ፥ የደረጃ ልቀት፥ ጥልቀት ወዘተ. . . ለመስጠት ብዛትን የሚያመለክቱ ስሞችን እንደሚጠቀም ሊጤን ይገባል። የኢሳይያስ 53፡9 "ሞቶች" የሚያሳየው ሞቱ ምን ያህል የጠለቀና ጭካኔን የተሞላ እንደነበረ ነው።

ኢየሱስ በሞተበት ወቅት፥ ከፍተኛ የጩኸት ድምፅ ካሰማ በኋላ ራሱን ዝቅ አድርጎ "መንፈሱን ለእግዚአብሔር ሰጥቷል" (ማቴ. 27፡50፤ ዮሐ. 19፡30)። መንፈሱን የሰጠውና በሥጋ የሞተው በአንድ ቅጽበት በመሆኑ፥ "በሥጋ ከመሞቱ በፊት በመንፈስ ሞተ" ለማለት የሚያስችል መሠረት የለም። ምክኮነል "ደግሞስ ኢየሱስ እንደ እምነት አስተማሪዎች ከሞተ በኋላ ወዲያው ወደ ሲኦል የሚሄድ ቢሆን ኖሮ፥ ለምን ከጎኑ ለተሰቀለው ወንበዴ 'ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ' ማለት አስፈለገው?" ሲሉ ይጠይቃሉ።

ክርስቶስ በመንፈስ የሞተውን ሰው ለማጽደቅ፥ በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም መሞት ነበረበት፤ ማለትም ሁለት ጊዜ መሞት ነበረበት ቢባል እንኳ፥ ክርስቶስ ወደ ሲኦል መውረድ አለበት ወደሚል ድምዳሜ ሊወስደን አይገባም። ክርስቶስ ነፍሱን አሳልፎ ሊሰጥ በተቃረበ ጊዜ፥ "አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለምን ተውኸኝ?" ሲል እንደተጣራ ትዝ ይለናል። ይህም ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንደነበር ያመለክታል፤ ሞት ማለት ደግሞ ከእግዚአብሔር መለየት በመሆኑ፥ በመንፈሱ ሞቶ ነበር ቢባል እንኳ ይኸው ክንውን በቂ እንደሆነ እንገነዘባለን። በሥጋ የሞተውና ከእግዚአብሔርም ለአጭር ጊዜ የተለየው እዚያው መስቀል ላይ እንጂ ሲኦል በመውረድ አይደለም።

የእምነት ዶክትሪን የክርስቶስ ሥጋዊ ሞት ብቻውን ሊያስተሰርይ እንደማይችል በመግለጽ፥ የወንጌሉ አስኳል የሆነውን የኢየሱስን ደም ዋጋ ያሳጣዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የእነርሱን ተገላቢጦሽ ነው የሚያስተምረው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንን ያሸነፈው በመስቀል ላይ በተፈጸመው ሥጋዊ ሞት አማካኝነት እንጂ በሲኦል ውስጥ በተከናወነው "መንፈሳዊ ሞት" አይደለም። ይህንኑ እውነታ ከቆላስያስ 2፡13–15 እናነባለን። "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም _በመስቀል_ ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል።"

ሰይጣንን ያሸነፈው የኢየሱስ "መንፈሳዊ ሞትና ትንሣኤ" ሳይሆን፥ በሥጋው የተቀበለው መከራ እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል። ጴጥሮስ ክርስቶስ በሥጋው መከራ እንደተቀበለ ገልጾአል (1ኛጴጥ 4፡1)። "ኃጢአታችንን በሥጋው በመስቀል ላይ ተሸከመ" (1ኛጴጥ. 2፡24)። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊም፥ "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስን ነው፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" ይላል (ዕብ. 2፡14)።

በዚህ ምንባብ መሠረት፥ ክርስቶስ በሥጋው መከራ በመቀበል ከመሞቱም በላይ ደሙን በመርጨትና በመሠቃየት፥ ሞትንና "በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን" አሸንፎአል።

የኃጢአትን ይቅርታ በማስገኘት ሰውን ከሞት የሚቤዠው የኢየሱስ ሥጋዊ ሞት እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ሁሉ የሚስማሙበት እውነት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የደምን አጠቃቀም ስንመለከት፥ በሞት የሥጋዊ ሕይወትን ህልፈት የሚያመለክት ተምሳሌት ሆኖ እናገኘዋለን። የክርስቶስ ስርየት በአካላዊ ስቅላት የደሙን መፍሰስ የሚያካትት ሥጋዊ ተግባር ነበር።

በዕብራውያኑ ጸሐፊ አገላለጽ፥ "ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም" (ዕብ. 9፡22) የሚለው ቃል የሌዋውያንን ጠቅላላ ሥርዓት እንደሚገልጽ ያስረዳል። ጴጥሮስም ይህንኑ የሌዋውያንን የመሥዋዕት ሥርዓት እያስታወሰ፥ "ነውርና እድፈት እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር

የክርስቶስ ደም እንደተዋጀችሁ ታውቃላችሁ" ብሏል (1ኛጴጥ. 1:19)። ጳውሎስም በበኩሉ፥ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን... " እያለ ይናገራል (የሐዋ. 20:28፤ ኤፌ. 1:7፤ ራእይ 1:5 ተመልከት)።

የዕብራውያን ጸሐፊ በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች ባስተላለፈው መልእክት፥ "የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ... እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?" ሲል ያስጠነቅቃል (ዕብ. 10:30)። ከዚህም በላይ ጌታ የመስቀል ላይ ሥራው ለደኅንነታችን በቂ እንደ ሆነ ከመስቀል ላይ ሆኖ የተናገረውን ቃል ማስታወሱ ጠቃሚ ነው – ተፈጸመ! ደኅንነታችን በመስቀሉ ላይ ከተፈጸመ ዘንዳ፥ የሲኦልና የሌላው ጣጣ ምን ይረባን ይሆን?

# 4

# እምነት በእምነት ላይ

## (Faith in Faith)

ሴፕተምበር 19፥ 1986 ፍሬድሪክ ፕራይስ የስብከት መልእክታቸውን እያቀረቡ ነበር። እኚህ ሰው በስብከታቸው መሀል፥ "ልክ ነኝ አይደል? ታምናላችሁ?" የሚሉትን ዓይነት የማረጋገጫ ጥያቄዎች የማቅረብ ልማድ ነበራቸው። ብዙዎቹ የእምነቱ ተከታዮች ከሙሉ ልባቸው በሚያቀርቡት የመልእክት አሳብ ላይ የሚስማሙ ቢሆንም፥ ቅጽበታዊ ፈውስን አስመልክቶ በሚናገሩበት ወቅት በአድማጮቻቸው መካከል ውጥረት ይስተዋል ጀመር።

ስለሆነም፥ ፕራይስ በስብከታቸው ወቅት፥ "የሚያድናችሁ እምነታችሁ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም! ይህን ታምናላችሁ?" ባሉ ጊዜ፥ አንድ ትምህርቱ ያበሳጫቸው የሰሚናሪ ፕሮፌሰር ዝም ለማለት ባለመቻላቸው ድምፃቸውን አጉልተው፥ "አላምንም!!" ሲሉ እንደመለሱ ተደምጧል።

ኬነት ሐገንም "በራስህ እምነት ማመን" ("Having Faith in Your Faith") በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ቀጥሎ የተመለከተውን አሳብ አስፍረዋል።

*"በራስህ እምነት ስለማመን አስበህ ታውቃለህ? እግዚአብሔር በራሱ እምነት ላይ እምነት ነበረው፤ የእምነትን ቃላት ተናግሮ ተፈጽመዋልና... በሌላ አገላለጽ፥ በራስህ ቃላት ማመን በራስህ እምነት ላይ እምነት መጣል ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ነገሮችን ለማግኘት መማር ያለብህ ይህንኑ ነው – በእምነትህ ላይ እምነት ይኑርህ።"*

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ለዚህ አሳብ እንዲህ ሲል ተቃውሞውን ገልጧል።

*"በእምነቱ ላይ እምነት ያለው' የትኛውም አምላክ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ሊሆን አይችልም። አምላክ ነው ለማለትም አይቻልም። ይህ የሜታፊዝካል ኑፋቄዎች አካል-አልባ (impersonal) ኃይል ነው። ምንም እንኳ እነዚህ ሕግጋት፥ ቀመሮችና መንፈሳዊ ሕግጋት በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ 'እምነት' ቢሰኙም፥ የአዲሱ እምነት ሜታፊዚክስ እጅ-አዙር ቅኝቶች እንደሆኑ ግልጽ ነው።"*

## የእምነት ቀመር (Faith in Formula)

«የአብርሃምን እምነት የተከተለ ለእናንተም ሊሠራላችሁ የሚችል ትንሽ የእምነት ቀመር ወይም ፎርሙላ ይኸውላችሁ» ይሉናል ኬነት ሐገን።

አሳቸው ብቻ ሳይሆኑ፥ ብዙዎች በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኘውን የእምነት ጽንሰ-አሳብ እንደ "ፎርሙላ" ይገልጻሉ። ይህም የሆነው በእምነት ሥነ-ጽሑፎች ውስጥ "ፎርሙላ፥ ሕግ፥ ደረጃዎችና መመሪያዎች" የሚሉ ቃላት አዘውትረው ስለሚታዩ ነው። ለምሳሌ፥ ሐገን ኢየሱስ በራእይ ተገልጾላቸው፥ "ማንም ሰው፥ በየትም ስፍራ እነዚህን አራት ደረጃዎች ከተወጣ ወይም እነዚህን አራት መመሪያዎች በተግባር ላይ ካዋለ፥ ከእኔ ወይም ከእግዚአብሔር አብ የሚፈልገውን ሁሉ ያገኛል" እንዳላቸው ገልጸዋል። ሐገን ኢየሱስ ሰጠኝ የሚሏቸው "ደረጃዎች" "1. ተናገር፥ 2. አድርግ፥ 3. ተቀበል፥ 4. አውጅ" የሚሉ ናቸው። (በእንግሊዝኛው 1. Say it, 2. Do it, 3. Receive it [claim it], and Tell it.)[1]

*"በመጀመሪያ፥ አብርሃም የተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ነበረው። ሁለተኛ፥ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል አመነ። ሦስተኛ፥ አብርሃም እግዚአብሔርን አመሰገነ (በቅድሚያ ማለት ነው)" እያሉ ፎርሙላዎቹን ካዋቀሩ በኋላ፥ ሚስተር ሐገን የሚከተለውን መደምደሚያ አበጁ፤ "እነዚህን አራት ደረጃዎች ከተከተላችሁ **ሁልጊዜ** እምነታችሁ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይደርሳል። ከተለያዩ ነገሮች ነጻ ለመውጣት፥ ለመፈወስም ሆነ **ለምትፈልጉዋቸው ነገሮች ሁሉ** እነዚህ አራት ደረጃዎች አስፈላጊዎች ናቸው።"[2] (ያሰመርሁትና ያጎላሁት እኔው ነኝ።)*

ሐገን በተጨማሪም፥

*"የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ሆነ ፈውስ፥ የጸሎት መልስ ወይም ገንዘብ፥ በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር የምትቀበሉትን ሁሉ በሚመለከት የእምነት መመሪያው አንድ ነው። [ይህንን] የእምነትን መመሪያ ብትማሩ ከእግዚአብሔር **ማንኛውንም ነገር መቀበል ቀላል** ነው" ሲሉ ያስተምራሉ። ('እምነት ማለት' ገጽ 7።)*

እኚህ ሰው በኢየሱስ ስም መጸለይ እንጂ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ እንደማያስፈልግ ጭምር 'የጻድቅ ሰው ጸሎት' በሚል ርእስ ወደ አማርኛ በተተረጎመላቸው መጽሐፋቸው ውስጥ ይገልጻሉ።

*"በዮሐንስ 4:13 ላይ... ኢየሱስ 'ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ' በማለት የምናነበው ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አብ ስለመጸለይ መናገሩ አይደለም። እዚህ ላይ የሚናገረው እርሱ እንደሚሠራው በስሙ የሚለምንም የእርሱን ሥራ እንዲሠራ ነው።" (ገጽ 91።)*

ሐገን እንደሚሉት፥ አንድ ሰው እግዚአብሔር አጽናፈ-ዓለሙን ለማንቀሳቀስ ያዋቀራቸውን "መንፈሳዊ ሕግጋት" ካገኘ በኋላ፥ በሕግጋቱ አማካኝነት የሚፈልገውን ሊያገኝ ይችላል።

*"በመንፈሳዊው ዓለም እግዚአብሔር የተወሰኑ ሕግጋትን አዘጋጅቷል። እነዚያ በተፈጥሯዊ ዓለም ውስጥ የሚገኙ ሕግጋት ይሠራሉ! አይደል? ከነዚያ ተፈጥሯዊ ሕግጋት ጋር በምትገናኝበት ጊዜ ይሠሩልሃል። በመንፈሳዊ ዓለምም እንዲሁ ነው። የእምነት ሕግ መንፈሳዊ ሕግ እንደሆነ፥ እግዚአብሔርም ይህንን ሕግ እንዳዘጋጀና ከዚህ ሕግ ጋር በምትገናኝበት ጊዜ እንደሚሠራልህ በማመን ደምድሚአለሁ።"*[3]

ስለሆነም፥ ማንም ሰው ክርስቲያንም ሆነ ኢ-ክርስቲያን ይህንኑ አጽናፍ-አቀፉዊ የእምነት ሕግ በመያዝ "ውጤት" ሊያስመዘግብ ይችላል። ሐገን ስለዚሁ ጉዳይ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

*"ነገሩ ያሳሰበኝ ነበር። ማለትም ያልዳኑት ሰዎች ለስኬት መብቃት። በኋላም ተገለጸልኝ – ለካስ እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሕግ-ከእምነት ሕግ ጋር እየተባበሩ ነበሩ።"*[4]

ፍሬድ ፕራይስ እንደሚሉት፥ ሮሜ 10፡10 የስኬት ፎርሙላ ስለሆነ ማንም ሰው "የሚፈልገውን ነገር ሁሉ – ፊውስ፥ ማንኛውንም ፍላጎት፥ አዲስ ቤት፥ መኪና፥ ወዘተ."[5] በፎርሙላው ውስጥ ሊያስቀምጥ ይችላል።

የእምነት ሥነ-መለኮት ስለ መንፈሳዊ ሕግጋትና ፎርሙላዎች የሚያቀርበው ትንታኔ ከሜታፊዝካል ኑፋቄዎች ዶክትሪን አንጻር የሚታይ መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ። ሜታፊዝካል ኑፋቄዎች የሚያምኑበት አምላክ አጽናፈ-ዓለምን በሉዓላዊነቱ የሚያስተዳድር አካላዊ ህልውና ያለው (personal) ሳይሆን፥ ይልቁንም አካላዊ ህልውና የሌለው ኃይል (impersonal force) ነው።

ኬንየን፥ "የማይታዩትን የሕይወት ኃይላት ስለሚያስተዳድሩት ታላላቅ መንፈሳዊ ሕግጋት" ሲናገሩ፥ የሚታፊዝክሱን የዴይዝም አስተሳሰብ ማራገባቸው እንደሆነ ግልጽ ነው – አጽናፈ-ዓለሙ በእግዚአብሔር ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕግጋት እንደሚተዳደር። ይህንኑ የዴይዝም አስተሳሰብ የሚከተሉ ፈላስፎች እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ዓለምን ከፈጠረ በኋላ፥ ራቅ ብሎ እንደሚታዘብና ከአጽናፈ-ዓለሙ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደማያደርግ ያስተምራሉ። ይህም የእምነት ሥነ-መለኮት በመርህ ደረጃ ስለ አካላዊው አምላክ ቢያስተምርም፥ በተግባር ግን የሚታፊዝክስ አቀንቃኞችን አስተሳሰብ እንደሚከተል ያሳያል።

ልብ ሊባል የሚገባው ግን፥ እግዚአብሔር አጽናፈ-ዓለሙን የሚያስተዳድረው በሰዎች ፎርሙላዎች፥ ሕግጋትና መመሪያዎች ሳይሆን፥ "በራሱ ፈቃድ" እንደሆነ ነው (ኤፌ. 1፡11)።

## *በኢየሱስ ስም የጠየቅነውን ሁሉ እናገኛለን*

ሌላው የእምነት ሥነ-መለኮት ችግር፥ በኢየሱስ ስም ለቀረበ ጥያቄ እግዚአብሔር ሁልጊዜም አዎንታዊ ምላሽ መስጠት እንዳለበት ያስረዳል። ኬነት ሐገን፥

*"ለ45 ዓመታት በሙሉ በኢየሱስ ስም ጠይቄ ያላገኘሁት ነገር የለም... . ለጥያቄውም የሚሰጠው ምላሽ ሁልጊዜም 'አዎን' የሚል ነው"*[6] ሲሉ ጽፈዋል።

"እምነት ማለት" በሚል ርእስ በ'ኤልሻዳይ ኮይኖንያ ቤተ ክርስቲያን' በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በቀረበው መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ የሚከተሉት የኬነት ሐገን አሳቦች ተካተዋል።

*"ስለ አንድ ነገር አንድ ጊዜ ጸልዩ ካላገኘሁ የጸሎቴን ስልት መቀየር እጀምራለሁ... ይህንን መመሪያ ለዓመታት ተከትዬዋለሁ፤ መቶ በመቶም የሚሠራ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።"*[7] (የጎላው ለአጽንኦት ነው።)

*"አንዳንዶች የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይሆን ይችላል ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ። እኔ ግን እግዚአብሔር ሰዎችን ለመፈወስ ፈቃዱ እንደሆነ አውቃለሁ... "*[8]

ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ የምንጠይቀውን ነገር እንደሚሰጠን ቃል ቢገባም፥ በሌሎች ስፍራዎች የተቀመጡትን ጠቃሚ አሳቦች መዘንጋቱ ተገቢ አይደለም። በዮሐንስ 14:14 ላይ "በስሜ የምትለምኑትን አደርግላችኋለሁ" ያለው ኢየሱስ፥ በ15:7 በእርሱ እንድንኖርና ቃሎቹም በእኛ እንዲኖሩ፥ በ1ኛ ዮሐንስ 3:22 እንደ ፈቃዱ እንድንጸልይ ይጠብቅብናል።

አንድ ያልታተመ ሰነድ እንደጠቀሰው ቤንሂንም «ፈቃድህ ቢሆን» የሚለውን ሐረግ በመቃወም የሚከተለውን ብለዋል።

*"አንዲት ጠንቋይ እንዲህ ብላ ነገረችኝ፥ 'በጥንቆላ እንዴት ወፎችን በቃል፥ ሰዎችን ደግሞ በአፋችን እንደምንገድል ተምረናል። የሚሸኑባቸውን የተወሰኑ ቃላት በመናገር በወፎችና በሰዎች በሽታን ማምጣት እንደምንችል ተምረናል' አለችኝ። እኔም እግዚአብሔር ሆይ፥ ሰይጣን ይህን የመሰለ ኃይል እንዳለው አላውቅም ነበር አልሁ። እግዚአብሔርም አለኝ፤ 'ሰይጣን በቃል ይገድላል፤ አንተ ደግሞ በቃል ሕይወትን ልትሰጥ ትችላለህ።' እኛ ክርስቲያኖች በአፋችን ያለውን ኃይል አናውቅም። ይህም በመሆኑ በፍጹም በፍጹም በፍጹም ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርባችሁ ጌታ ሆይ፥ 'ፈቃድህ ቢሆን' የሚል እምነትን የሚገድል ጸሎት ከአፋችሁ አይውጣ። ትህትና ይመስላችኋል እንጂ ደደብነት ነው። እግዚአብሔርን ሞኝ ነህ ማለታችሁ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ጸሎት እምነትን ከቦታው አጥፍቶ ፍርሃት እንዲያድግና ሰይጣን እንዲሠራ ያደርጋል።"*[9]

ምክኮንል እንዳስቀመጡት፥ አንድ ሰው የራስ– ወዳድነት (ወይም ምግባረ–ብልሹ) ዓላማዎች ኖረውት፥ "እምነቱ" የጸሎት መልስ የሚያገኝ ከሆነ፥ ጸሎቱን የሚመልሰው እግዚአብሔር ሳይሆን ሌላ ኃይል እንደሆነ ግልጽ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው እግዚአብሔር ከዚህ ዓይነቱ አመለካከት ጋር የሚዛመድ አይደለምና።

ብዙውን ጊዜ የእምነት አስተማሪዎች በማርቆስ 11:22 "በእግዚአብሔር እመኑ" የሚለውን አጣመው በመተርጎም፥ "እንደ እግዚአብሔር ዓይነት እምነት ይኑራችሁ" ሲሉ ያስተምራሉ። ይህም እምነትን አዎንታዊ አስተሳሰብ ካላችሁ ሁሉም ይሆንላችኋል ወደሚሉት ሰብአዊ ጽንሰ–አሳቦች ለመንዳት በር ይከፍትላቸዋል። እግዚአብሔር በቃሉ ላይ ባለው እምነት እንደፈጠረ ሁሉ እናንተም የእምላክነት ብቻ ሳይሆን የፈጣሪነትም ሚና ይኖራችኋል የሚሉንም ከዚሁ ከእግዚአብሔር በተፋታ የእምነት ግንዛቤአቸው ነው። መታወቅ ያለበት ግን የእምነት ምንጩም ግቡም እግዚአብሔር እንደሆነ ነው። ሰው በእግዚአብሔር ሲያምን እንጂ እግዚአብሔር አማኝ ሆኖ ሲቀርብ የሚታይበት ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀርቶ በተረት መጻሕፍትም ሲደገፍ አላየንም። እናም እምነት በእምነት ብሎ ራስን ከማታለል እምነትን በእግዚአብሔር ላይ መጣሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሥነ–መለኮት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸውና ለብዙ የሥነ–መለኮት ትምህርቶች የመማሪያ መጽሐፍ ሆኖ የሚያገለግለውን "ክርስቲያን ቲዎሎጂ" መጽሐፍ የጻፉት ሚላርድ ኤሪክሰን እንዳመለከቱት፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የእምነትን ጽንሰ–አሳብ የሚያስጨብጠን አንድ ቃል አለ። ይህም ቃል ሁለት መሠረታዊ ፍችዎች ሲኖሩት፥ "የመጀመሪያው አንድ ሰው የተናገረውን ማመን፥ በተለይም ሃይማኖታዊ ባህርይ ያለውን አሳብ እንደ እውነት መቀበል"[10] ማለት ነው።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፥ በ1ኛ ዮሐንስ 4:1፥ "ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ" የሚለው ነው። በማቴዎስ 8:13፥ ጌታ ይህንኑ ቃል በመገልገል ለመቶ አለቃው ምላሽ ሲሰጥ እንመለከታለን – "ሂድ፥ እንደ እምነትህ ይሁንልህ።" ኢየሱስ በጣም በመደነቁ፥ ባሪያው እንደሚፈወስ በማመን የመቶ አለቃው የተደገፈበትን እምነት ሸለመው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኢያኢሮስ ልጁ እንደምትፈወስ እንዲያምን የጠየቀው ሲሆን (ማርቆስ 5:36፤ ሉቃስ 8:50)፥ ወደ እርሱ የመጡትንም ዕውሮች፥ "ይህን ማድረግ [መፈወስ] እንድችል ታምናላችሁን?" (ማቴዎስ 9:28) ሲል ጠይቋቸዋል። እነዚህና ሌሎችም አያሌ ምሳሌዎች እምነት የአንድን ነገር እውነተኛነት ከማመን ጋር እንደሚዛመድ ያሳያሉ። የዕብራውያን ጸሐፊም፥ እምነት

የአንድን ነገር እውነትነት በመቀበል ገጽታው ከደኅንነት ተነጥሎ እንደማይታይ ገልጾአል፤ "ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም። ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" (ዕብራውያን 11፡6)።

ከዚህም በላይ ግላዊው እምነት የአንድን አሳብ እውነተኛነት ከማመን የሚልቅ መሆኑ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የተመለከተ እውነት ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ከታሰረ በኋላ፥ በማርቆስ 1፡15 ኢየሱስ፥ "ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ" ሲል ሰብኳል። በሐዋርያት ሥራ 10፡43ም፥ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል" የሚል ተጽፎአል። ይህንኑ የግላዊ እምነትን አስፈላጊነት ከሚያመለክቱት ሌሎች ጥቅሶች መካከል ማቴዎስ 18፡6፤ ዮሐንስ 2፡11፤ የሐዋርያት ሥራ 19፡4፤ ገላትያ 2፡16፤ ፊልጵስዩስ 1፡29 እና ሌሎችም ይገኙባቸዋል።

ከዚህም ጋር፥ ሐዋርያው ዮሐንስ በኢየሱስ ስም ስለማመን የሚናገረውን መመልከቱ ጠቃሚ ነው። "ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው" (ዮሐንስ 1፡12)። "የአዲስ ኪዳን ሥነ–መለኮት" የሚል መጽሐፍ እንደገለጸው፥ "የዚህ ዓይነቱ የቃላት አጠቃቀም የአንድን ሰው ባህርይ ለመግለጽ በስሙ ይገለገሉ ለነበሩት አይሁዶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው።" ስለሆነም፥ በኢየሱስ ስም ማመን ማለት በኢየሱስ ማመን ማለት ነው።

ከዚህ እንደምንመለከተው፥ ለደኅንነት የሚያስፈልገው እምነት እውነታውን መቀበልንና በእውነታው አካል መታመንን ያካትታል። በመሆኑም አንድ ሰው *ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በተገለጠው እውነትና በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ይጠበቅበታል።*

ሌላው ስለ እምነት ልንመለከት የሚገባን አንዳንድ ጊዜ እምነት ያለ መረጃ የምንቀበለው እንደሆነ የሚነሣው አሳብ ነው። የእግዚአብሔርን መኖር በመጠራጠሩ ምክንያት፥ "እስኪ ያንተን አምላክ አሳየኝና ልመን..." ላለው ከሃዲ፥ አንድ አባት "እስኪ አንተ ደግሞ ከዋክብትን አሳየኝ" ብለውታል ይባላል። ከሃዲው ከዋክብትን ለማየት ጨለማ እንደሚያስፈልግ ሲናገር፥ እርሳቸውም እግዚአብሔርን ለማየት እምነት እንደሚያስፈልግ መናገራቸው ተደምጧል። አንዳንዶች ከዚህ ዓይነቱ ግንዛቤ በመነሣት ሊሆን ይችላል እምነት በጭፍን የሚቀበሉት መሠረተ–ቢስ አሳቤ እንደሆነ የሚናገሩት።

ይሁንና፥ አንዴ በእምነት ከገቡበት በኋላ ያንኑ እምነት የሚደግፉትን የተለያዩ መረጃዎች ማግኘት እንደሚቻል ብዙዎች ይስማሙበታል። ትረቨር ምክልዌይን በዚህ ላይ የሚከተለውን ብለዋል።

*"እምነት የሆነ ምሥጢራዊ ስሜት አይደለም። ባዶ ተስፋ ወይም ዕውር ዕድልም አይደለም። እምነት ከአመክንዮ ጋር የሚቃረን፥ ምሁራዊ ክስረትም አይደለም።*

*የሚያድን እምነት ተጨባጭ በሆኑ ታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ላይ የሚመሠረት ነው። በመሆኑም፥ የሚያድን እምነት ጠንካራ መሠረት ያለው ነው። እውነተኛ እምነት በተረጋገጠው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ያርፋል። ስለሆነም፥ ወንጌሉ ለነፍስ መዳን የሚታመንበት ከሆነ ግንዛቤው የግድ ሊኖር ይገባል። ኃጢአተኛው እውነተኛ የሚያድን እምነት እንዲኖረው ከተፈለገ፥ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት እውነቱን ሊያስጨብጠው ይገባል።"*

እውቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ አገስቲንም ይህንኑ አሳብ ይደግፋሉ። እናም እምነት የአመክንዮ (reason) ጠላት እንዳይደለ እንረዳለን። ለዚህ በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችለው፥ ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ለላካቸው ሁለት ደቀ መዛሙርት የሰጠው ምላሽ ነው (ሉቃስ 2፡19)። ኢየሱስ ለነዚህ ሰዎች ዲዳዎች እንደሚሰሙና ደንቆሮዎች እንደሚፈወሱ በመግለጽ፥ ይኸው መረጃ መጥምቁ ዮሐንስን ከመጠራጠር እንዲጠብቀው ተናግሯል።

ኤሪክሰን እንደሚሉት፥ እምነት በመረጃ ላይ አይደገፍም ለሚለው አሳብ መስናክል ከሚሆኑት ነገሮች አንዱ የቶማስ ጉዳይ ነው። ቶማስ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር ስላልነበር፥ ጌታ ከትንሣኤው በኋላ ሲታያቸው ለመመልከት አልታደለም ነበር። በኋላም ከሄደበት ሲመለስ፥ ይህንኑ ትኩስ ዜና ቢያበስሩለት የማይዋጥለት ሆነ። ቶማስ የራሱን እጆች ምስማሮች በበሱት የኢየሱስ እጆችና ጎኖች ውስጥ አስገብቶ ካላየ በቀር ለማመን እንደማይችል ተናገረ (ዮሐንስ 20፡25)።

ኢየሱስ በሌላ ቀን ሲመጣ፥ ቶማስን ጠርቶ ከማመኑ በፊት ለማየት የፈለገውን ጎኑንና እጆቹን አሳየው። ቶማስም፥ "ጌታዬ፥ አምላኬ" ሲል በሰገደለት ጊዜ፥ "አንተስ ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩኝ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው" ብሎታል። እንግዲህ፥ ኢየሱስ ይህን ሲል ቶማስ ያለ ምንም የመረጃ መሠረት በዕውር እምነት እንዲከተለው ይጠብቅ ነበር ማለት ነው? ኤሪክሰን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፥ ቶማስ ከጌታ ጋር ለሦስት ዓመታት ተከል አብሮ ያሳለፈ በመሆኑ የጓደኞቹን ቃል ማመን እንደነበረበት ገልጸዋል። አብርሃም ልጁን እንዲሠዋ በተጠየቀበትም ጊዜ እንኳ ለአብርሃም ጥሩ መረጃ እንደነበረው ነው እኚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር የሚናገሩት።

*"እውነት ነው ለመሥዋዕት የሚሆን በግ በዚያ ስፍራ አልነበረም፤ ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ የሚታይ ነገር ባይኖርም፥ አብርሃም ያህዌን ለረዥም ዓመታት ያውቀው ነበር። ከዚህ በፊት እግዚአብሔር የተስፋ ቃል የገባለትን ምድርና ልጅ ሊሰጠው አይቷል። ስለሆነም፥ አብርሃም ልጁን ለመሠዋት በመፍቀድ ያሳየው እምነት ከዚህ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ባሳለፈው ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነበር።"[12]*

ከዚህ እንደምንመለከተው፥ እምነት የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል የሚያስችለን በመሆኑ፥ የወንጌሉ እምብርት ነው ማለቱ ተገቢ ነው። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱሳችን በእምነት ላይ ከፍተኛ አጽንኦት የሚያደርገው።

"በእግዚአብሔር እመኑ። እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ ተነቀለህ ወደ ባህር ተወርወር ቢል ይሆንለታል" ከሚለው የነ ሐገን መሪ ጥቅስ ሌላ፥ የሚከተሉትም በእምነት ላይ የሚያተኩሩ ሆነው እናገኛለን።

በማርቆስ 10:52 ጌታችን የበርጤሜዎስን ዓይኖች ከፈወሰ በኋላ፥ "ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል" ብሎታል። ለአሥራ ሁለት ዓመታት ደም ሲፈሳት ለኖረችውም ሴት፥ "ልጄ ሆይ፥ አይዞሽ እምነትሽ አድኖሻል" ብሏታል (ማቴዎስ 9:22)። በተጨማሪም፥ "ለሚያምን ሁሉም ይቻለዋል" (ማርቆስ 9:23፤ ማቴዎስ 17:20፤ ማርቆስ 11:23፤ ሉቃስ 17:6፤ ዮሐንስ 11:40)፤ "የማያምን ትውልድ" (ማርቆስ 9:19፤ ዮሐንስ 4:48)፤ . . . "ይህን ተራራ ወደ ባህር ተወርወር ቢል ይሆንለታል" (ማርቆስ 11:23) የሚሉ ጥቅሶች ሞልተዋል።

እነዚህና ሌሎችም በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚነግሩን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት እምነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ወደ መዳን የመጣንበትንም ሁኔታ ስናስታውስ፥ <u>"ጸጋው በእምነት</u> አድኖናል" (ኤፌሶን 2:8-9)።

ይህንኑ ሁኔታ በእግዚአብሔር የእይታ መነጽር ስንመለከት፥ "በእኛ እምነት" ላይ የእርሱ ማተኮር ተገቢ ነው እንላለን። ለምን? ትንሿ እምነታችን የተትረፈረፈ ጸጋውን በሕይወታችን ከሥራ ላይ እንዲያውል በር ትከፍታለችና። እኛ ለተቀበልነው መገለጥ የእምነት ምላሽ ካልሰጠን፥ እግዚአብሔር 'በጉልበት' በሕይወታችን ሊሠራ አይፈልግም - ሙሉ ለሙሉ ይህንን የማድረግ ዓቅምና ችሎታ ቢኖረውም! እርሱ ጨዋ አምላክ በመሆኑ፥ የእኛን የፍጡራኑን ነጻነት ያከብራል። ለዚህም ነው በአንዳንድ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ ከሰዎቹ ተቃውሞ የተነሣ ጌታ ብዙ የፈውስና የተአምራት ተግባራት እንዳላከናወነ ተጽፎ የምናነበው። ስለሆነም፥ አመንን ማለት እግዚአብሔር እንዲሠራ ፈቀድን፤ በር ከፈትን ማለት ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ የእርሱን ፈቃድ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ የግድ ነው። *<u>እግዚአብሔር እንድናምን ሲፈልግ የእኛን ፈቃድ እያከበረ መሆኑ ከገባን፥ እኛም በእምነት ፈቃዳችንን ለገለጽንበትና የእርሱን ሁሉን ቻይነት ለተቀበልንበት ጉዳይ ፈቃዱን የማክበር ኃላፊነት ይኖርብናል።</u>* እናም ስላመንሁ ብቻ 'ልቤ የፈለገውን ሁሉ አገኛለሁ' ብለን እንድንል የሚያደርገን ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ አይኖርም።

*እግዚአብሔር ከአምላካዊ የእይታ መነጽሩ በእኛ የሰናፍጭ ቅንጣት እምነት ላይ ካተኮረ፥ እኛስ ለምን ይሆን እጅግ በበዛልን ጸጋው ላይ የማንመለከተው!* የእኛዋን ቅንጣት ታህል እምነት ከእርሱ የላቀ ጸጋ ጋር ለማወዳደር እየጣርን ከሆነ፥ በእኔ ግንዛቤ ተሳስተናል። ለማመን መቻላችንም ራሱ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የሚሠራው ተግባር እንጂ በራሳችን የምንወጣው አይደለም። "ስለ

በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" (ፊልጵስዩስ 2፡13)።

ኢየሱስም፥ "የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለምና፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" (ዮሐንስ 6፡44)። "አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም... እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል" ብሏል (ዮሐንስ 6፡37፥ 45)።

አንድ አንበሳና አንዲት አይጥ አብረው ድልድይ በመሻገር ላይ ሳሉ ድልድዩ ተሰበረ አሉ። አይጢቱም ፈጠን ብላ፥ "ድልድዩን ሰበርነው አይደል!" ስትል አቅራራች ይባላል። በመሠረቱ ድልድዩን የሰበረው አንበሳው እንጂ አይጢቱ እንዳልሆነች ግልጽ ነው። ተራራውንም የናደው ጌታ እንጂ እኛ ወይም እምነታችን አይደለም።

ጌታ ግን ለእምነታችን ካለው ብርቱ ከበሬታ የተነሣ፥ "እምነትህ አድኖሃል!" "እምነትሽ አድኖሻል..." ይለናል። ያዳነን ግን እርሱ አዳኛችን ነው። የክብር በገና ሊደረደር የሚገባውም ለእኛ ወይም ለቅንጣቷ እምነታችን ሳይሆን ለእርሱና ለእርሱ ብቻ ነው። ስንቱን ጉድለታችንን ሳያይ እያለፈ ቅንጣቷን እምነታችንን እንደሚመዘግብ ልብ ልንል ያሻል።

♣

# 5

# ፈውስና ተአምራት

## (Healing & Miracles)

*"እርሱ መፈወሴን ስለነገረኝ እንደተፈወስሁ አውቃለሁ፤ በሰውነቴ ላይ የበሽታ ምልክቶች መኖራቸው ለውጥ አያመጣም። እኔ እስቅባቸዋለሁ፤ የበሽታ ደራሲ የሆነው [ሰይጣን] ሰውነቴን እንዲለቅ በኢየሱስ ስም አዘዋለሁ" (ኢ. ደብልዩ ኬንየን)።*

*"ለእምነት እንቅስቃሴ አባላት ፈውስ የሕይወት አቅጣጫ ነው። ሀልቁ መሰፍርት የሌላቸው ተከታዮቻቸው በእውነተኛ የስሜት ሕዋሳት እውቀት ሳይሆን በእምነት የመገለጥ እውቀት እንደሚፈወሱ ስለሚናገሩ መረጃ ማቅረቡ ቢያስቸግርም፥ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ከየትኛውም የቤተ ክርስቲያን ዘመን በላይ በእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች በርካታ ፈውስ-ተብዬ ተግባራት ተፈጽመዋል። እነዚህ ፈውሶች በእርግጥ ተፈጽመዋል ወይ የሚለው ጥያቄ በእንቅስቃሴው አራማጆች ዘንድ አይነሣም። የእነዚህን ፈውሶች ዜና የሚያራግቡ ግለሰቦች መፈወሳቸውን ይናገራሉ፤ የሕመም ሥቃይም ሆነ የበሽታ ምልክት አለመፈውሳቸውን በመግለጽ ሊያሳምናቸው አይችልም" (ምክኮነል)።*

እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ስላጋጠማት ሁኔታ አንዲት ወጣት የሰጠችውም አስተያየት ለዚህ አብነት ሊጠቀስ ይችላል።

*"ከወጣቷ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ እንተዋወቃለን። መንፈስ ነን ማለት ከመጀመራቸውም በፊት 'ቢቢሲ' አብረን እንካፈል ነበር። ስናውቃት ታዲያ አንድ እግሯ አጭር እንደሆነም ግልጽ ነበር። አንድ ቀን ከመድረክ ላይ ወጥታ ባንድ እግሯ ፈንጠር ፈንጠር እያለች 'ተፈውሻለሁ' ትል ገባች። ከመድረኩ ስትወርድ ለመሆኑ ምኑ ላይ ነው የተፈወስሽው ብንላት፥ 'ድሮ እንደዚህ አልነበረም!' ስትል ሞገተችን። ስናየው ግን ልጂቱ በፊትም አሁንም አንድ እግሯ አጭር ነው።"*

የአዲሱ እምነት እንቅስቃሴ ተከታዮች ነፍስ-ውጪ ነፍስ-ግቢ ላይ ሆነውም "ተፈውሻለሁ" ከማለት አይመለሱም።

ምክኮነል፥ የእምነት ልምምድ ካደረጉ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ሰዎች ሁሉ ይፈወሳሉ የሚለው የዚህ ግትር አቋም መሠረት ምን እንደሆነ በማራዎት ይጠይቃሉ። የእንቅስቃሴው አራማጆች የፈውስ እምነታቸው ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ይናገራሉ። ምንም እንኳ በዚህ እምነት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳቦች ቢኖሩም፥ ሙሉ ለሙሉ እምነቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳልተመሠረተ ግልጽ ነው። ሌላው አማራጭ ምንጭ "ሁለተኛው የዓለም

ጠርነት የፈውስ መነቃቃት" ነው፤ ይህም ኬኒት ሐገንንና ሌሎችንም የእንቅስቃሴውን መምህራን እንደተጸናወተ ይታወቃል። እንደ አንድ ምሁር፥ "የፔንተኮስታል የፈውስ መነቃቃት (Pentecostal Healing) ከፍተኛ የእምነት ፈውስ ዶክትሪን (Doctrine of Faith-Healing) በማስገኘቱ፥ ብዙዎች የሕክምና ሳይንስን እስከ ማናናቅ ደርሰው ነበር። ይሁንና፥ በፈውስ መነቃቃት ውስጥ የማይገኙ የእምነት ፈውስ ዶክትሪን አካላት አሉ። እነዚህ ተጨማሪ የእምነት ፈውስ ዶክትሪን አካላት ከሜታፊዚካል ኑፋቄዎች እንደተወሰዱ እሙን ነው።"

በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ወሳኝ ነጥቦችን እንመለከታለን። የመጀመሪያው ነጥብ ተአምራትና ፈውስ የአንድን ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም እውነተኛነት ሊያረጋግጡ እንደማይችሉ ነው። የአሜሪካውያኑ የ'ፕራግማቲክ ቫልዩ' ፍልስፍና ማንኛውም ስኬት የሚያስገኝ ነገር እውነት እንደሆነ ይናገራል። ይህ ግን እውነት እንዳልሆነ ሁላችንም እናውቃለን። ለምን? በስርቆትም ጥቅም ማግኘት ይቻላልና! የፈውስ ዶክትሪን የተመሠረተው በፈውስና ተአምራት መመዘኛ ላይ ከሆነ፥ የሜታፊዚካል ኑፋቄዎች ዶክትሪንና ልምምዶችም እውነት ናቸው ማለት ነው። በክርስቲያን ሳይንስ፥ አዲስ አሳብ፥ ዩኒቲ፥ ሃይማኖታዊ ሳይንስ፥ ወዘተ. . . ውስጥም አያሌ የፈውስ ተአምራት ይፈጸማሉ።

የፈውስ ስጦታ የአንድን ሰው አገልግሎት እውነተኛነት እንደማያረጋግጥ ለማመልከት ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ፥ አስደናቂ የፈውስ አገልግሎት ሲያበረክት ቆይቶ ወደ ሕይወቱ ማብቂያ አካባቢ የሥላሴን ትምህርት ያወገዘውንና ወደ "ኢየሱስ ብቻ" እምነት የተመለሰውን ዊሊያም ብራንሃምን መመልከት ይቻላል። የሚገርመው ይህ ሰው "ነቢዩ ኤልያስ ነኝ!" በማለት አገልግሎቱ እስከ ኢየሱስ መምጣት የሚቀጥል መሆኑን ተናግሮ እንደነበር መዛግብት ያስረዳሉ።

ሁለተኛው ነጥብ፥ ፈውስና ተአምራት ከብዙ ምንጮች እንደሚመጡ ምክኮንል ያመለክታሉ። "ፈውሶች ሁሉ መለኮታዊ ፈውሶች አይደሉም፤ ተአምራቱም ሁሉ ከእግዚአብሔር አልመጡም።" ለምሳሌ፥ የሜታፊዝካል ኑፋቄዎች በሽታን ለመፈወስ አዎንታዊ የአእምሮ አመለካከትንና አዎንታዊ ኑዛዜን በመሣሪያነት ይጠቀማሉ። ምትሐት አድራጊዎች ለፈውስ የሰይጣንን ኃይል ይጠቀማሉ። ጠንቋዮችም እንደዚሁ፥ በሰይጣን ኃይል ጊዜያዊ ፈውስ ያስገኛሉ። ሥነ-ልቦናዊ የፈውስ ጥበብም እንዳለ ይታወቃል። ስለሆነም፥ *__የእምነት አራማጆች የሚያከናውኗቸው ፈውሶች በመነሾነት ከኑፋቄ ጋር ከተያያዙ፥ ዛሬ የሚታየው መሳይ "ስኬታቸው" ከእግዚአብሔር ውጭ ከሆነ ምንጭ የማይቀዳበት ምን ምክንያት አለ?__*

በእምነት ሥነ-መለኮት፥ የስርየቱ ዓላማ *የኃጢአት ይቅርታ የማስገኘቱን ያህል የበሽታን ፈውስ ማምጣት ነው*[1]። የእምነት አስተማሪዎች የበሽታዎች

ፈውስ የተገኘው በመስቀል ላይ በተፈጸመው ሥጋዊ ሞት እንደሆነ ያምናሉ።

## በሽታ መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ አይደለም

ኪንየን "በሽታ በሥጋዊ አካል ላይ የሚታይ መንፈሳዊ ሁኔታ"[2] እንደሆነ ገልጸዋል። ስለሆነም፥ በሽታ ሁሉ የሚመጣው ከሰይጣን መንፈሳዊ ዓለም ነው[3]። ሐገንም መሪያቸውን በመከተል በሽታ ሁሉ ከመነሾው መንፈሳዊ ስለሆነ፥ የእግዚአብሔርም የፈውስ ብልሃት ሙሉ ለሙሉ መንፈሳዊ መሆን እንዳለበት አስተምረዋል[4]።

የሜታፊዚካል ኑፋቄ አራማጅና በኤመርሰን ኮሌጅ ከኪንየን ጋር የተማሩት ራልፍ ዋልዶ ትራይን፥ በሽታ ሥጋዊ መልክ ቢኖረውም መንፈሳዊ መነሾ እንዳለው ለማስረዳት ይጥራሉ።

*"በሚታየው ቁሳዊ ዓለም ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ምንጭ የማይታይ፥ መንፈሳዊ የአሳብ ዓለም ነው።"[6]*

*"ማንኛውም ነገር በሚታየው [ዓለም] ውስጥ ይኖራል፤ ከዚህ እንደምንረዳው፥ እውነተኛው የማይታየው ነገር ሲሆን፥ የሚታየው እውነተኛ አይደለም። የሚታየው ውጤት ሲሆን የማይታየው መነሾ ነው።"[6]*

ፕላቶም ይኸው ተመሳሳይ ፍልስፍና የነበረው መሆኑ፥ የፈውስ ዶክትሪን ከሜታፊዚክስ እንደመነጨ የሚያሳይ ነው።

## ለአማኝ መታመም ተገቢ አይደለም

"እግዚአብሔር እነዚያን በሽታዎች በኢየሱስ ላይ ካደረገ በኋላ በሰውነታችን ላይ በሽታን ማስተናገዱ ስሕተት ነው"[7] ከሚለው የኪንየን ትምህርት የተነሣ፥ የእምነቱ አባላት እውነተኛ አማኝ መታመም እንደሌለበት ይገልጻሉ።

"በሽታ ተገቢ ወይም ተፈጥሮአዊ አይደለም"[8] የሚለው የኪንየን አሳብ፥ "በሽታ የሚመጣው አማኙ መንፈሳዊ ሕግ በመተላለፉ ነው" ከሚለው ቀጣይ የሜታፊዚካል ኑፋቄ ጋር እንደተዋሃደ መመልከት ይቻላል።

*"ተፈጥሮአዊው የሕይወት ገጽታ ሙላት፥ ብልጽግናና ሙሉ ጤንነት ነው። ከዚህ ውጭ ያለው ጤናማ ያልሆነ ሁኔታ ሲሆን፥ ይህም ጤናማ ያልሆነ ሁኔታ የሚመጣው ከጥመት ነው። በሽታ፥ ሥቃይና ሕመም በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ሳይሆኑ ሰው የፈጠራቸው ናቸው፤ የሚመጡትም የሚኖርባቸውን ሕግጋት ከማበላሸቱ የተነሣ ነው።"[9]*

## *አሉታዊ ቃል በሽታን ያስከትላል*

አማኝ ለበሽታ ሊጋለጥ የሚችልበት አንዱ የተረጋገጠ መንገድ አሉታዊ ኑዛዜ መናገር ነው። ይህም አሉታዊ ኑዛዜ በሰውነት ውስጥ በሽታ መኖሩን በአእምሮ ማመን ወይም በቃላት መግለጽ ነው። የበሽታን መኖር በቃላት መግለጽ ለሰይጣን የማሠቃየትን መብት ይሰጠዋል[10]። ስለ በሽታ መነጋገር ዲያብሎስን የማምለክ ያህል በመሆኑ ኬንየን ይከለክላሉ[11]። በመሆኑም፥ እውነተኛ የእምነቱ ተከታዮች እንኳንስና ስለ በሽታ ሊነጋገሩ መታመማቸውንም አይቀበሉም። ይበልጥ ጠበቅ በሚሉ የእምነት አማኞች ዘንድ የጸሎት እገዛ ለመጠየቅ እንኳ በሽታን መጥቀስ አይፈቀድም። በሚታፈዝከል ኑፋቄዎችም ዘንድ ይኸው አመለካከት የተለመደ ነው። እንደ ትራንስ ማስጠንቀቂያ፥ አሉታዊ ኑዛዜዎች ሌሎችን በበሽታ የመበከል ኃይል አላቸው[12]።

ፓስተር ፀሐይ ታደሰ «እምነት እንዴት በሥራ ላይ እንደሚለቀቅ» በሚል ርእስ በአማርኛ ቋንቋ ተርጉመው ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ ኬነት ሐገን የሚከተለውን ብለዋል።

*"እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር አንድ ጊዜ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፤ ስለማመን ከምትሰብከው… የበለጠ ስለ ማለት ወይም ስለ መናገር የምታስተምረው በሦስት ጊዜ መብለጥ አለበት፤ ምክንያቱም ሰዎች የሚስቱት ስለ ማመን ሳይሆን ስለ መናገር ወይም ስለ ማለት ነው።"*[13]

ለኬነት ሐገን አዎንታዊ ቃል ከእምነት በላይ መሆኑን ልብ ማለቱ ጠቃሚ ነው። እኚህ ሰው፥ "ሁሉም ለምን አይፈወሱም?" ለሚለው ጥያቄ፥ "የእምነት ቃል" በተሰኘው መጽሔታቸው ፌብሩዋሪ 1996 እትም የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተዋል።

*"የለም፥ አስቀድመን እንዳየነው፥ አንዳንድ ሰዎች የማይፈወሱበት ምክንያት ሰይጣን መጥቶ ዘሩን ስለሚነጥቅባቸው ነው። ሌላው ምክንያት አንዳንዶቹ እንደ ጭንጫ መሬት በመሆናቸው ነው። የቃሉ ዘር ፍሬ የሚያፈራባቸው ቢመስልም፥ በራሳቸው ምንም ጥልቀት የላቸውም። በቃሉ ላይ ስለማይመሠረቱ ዘሩ በልባቸው ውስጥ እንዲተከል አይፈቅዱም።"*

በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 4፡3–8 ባለው የዘሪው ምሳሌ ላይ ተንተርሰው ባቀረቡት በዚሁ ማብራሪያቸው፥ ሐገን የሚከተለውን ጨምረው ገልጸዋል።

*"በዚህ ምሳሌ መሠረት፥ ቃሉን ከሚሰሙ ሰዎች ሦስት አራተኛው እጅ አይፈውሱም። ወይም ለጊዜው ይፈወሳሉ። ነገር ግን ከአራቱ እጅ ሦስቱ ፈውሳቸውን አይጠብቁም።*

*"አሁን አንዳንድ ሰዎችን ሊያስገርም የሚችል አንድ ነገር እነግራችኋለሁ። ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መገለጦች ወይም በሁሉም ሰው ላይ በሚወርድ የጋራ ቅባት ሊፈወሱ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ ሁሉም ሰው እግዚአብሔርን በሚያምንበት ስብሰባ ውስጥ መፈወስ ቀላል ነው። ነገር ግን ሰዎች እምነታቸውን ለማሳደግ*

*የሆነ ነገር ካላደረጉ እነዚያ ፈውሶች ዘላቂ አይሆኑም። ለምን? ምክንያቱም ሰይጣን የተዘራውን ቃል ለመሥረቅ ስለሚሞክር ነው! እነዚህ ሰዎች በቃሉ ጸንተው ፈውሳቸውን ለራሳቸው የሚያደርጉበትን መንገድ ሊማሩ ይገባል።*

*"በ1950 በተቀበልሁት የመጀመሪያው ራእይ ኢየሱስ ከተገለጠልኝ በኋላ፥ በጉባኤዎቼ ላይ ስለዚያ ራእይ ስናገር ካየቻሁት ሁሉ በላይ የሚያስደንቁ ፈውሶች ተከናወኑ። ይሁንና፥ በመጀመሪያው ሳምንት የተፈወሱት ሰዎች በሦስተኛው ሳምንት ታመው ሊመጡ አይ ጀመር።"*

ሐገን ለሰዎቹ ዳግም መታመም ታማሚዎቹን ቢወቅሱም፥ መጀመሪያውኑ መፈወሳቸውን ማረጋገጡ ይገባ ነበር ነው የምንለው። ለምሳሌ፥ ካሪዝማን ጨምሮ አያሌ መጽሔቶች የዘገቡት የሣራ የፈውስ ተአምር አጠራጣሪ እንደነበር ጀምስ ቢቬርሊ በመጽሐፋቸው ውስጥ ገልጸዋል። በተጨማሪም፥ ሰዎቹ በመጀመሪያው ሳምንት ተፈውሰው በሦስተኛው ሳምንት ዳግም የሚታመሙ ከሆነ፥ የፈውሱ ምንጭ እግዚአብሔር ላይሆን ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። እግዚአብሔር ከፈወሰ፥ ፈውሱ ሙሉና የማያዳግም መሆኑ ራሱ የፈውሱን ፍቱንነት የሚያረጋግጥ ነው።

ሌላው ሐገን ስለ ፈውስ ለማስተማር የተጠቀሙበት የዘሪው ምሳሌ ስለ ፈውስ የሚያስተላልፈው መልእክት እንደሌለ ስንረዳ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እንዳሻቸው የሚያጣምሙ መሆናቸውን ልንመለከት እንችላለን። ክፍሉ የሚያወራው ስለ እምነት እንጂ ስለ ፈውስ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። "ቃሉን ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል... ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ... " (ማር. 4:17)።

## *የበሽታ ምልክቶችን መካድ*

ኬነት ሐገን እንደሚሉት፥

*"የድካምን፥ የበሽታን፥ የሥቃይን ኑዛዜ/ንግግር እስከተናገራችሁ ድረስ እነዚህ ችግሮች ሁልጊዜ አብረዋችሁ ይኖራሉ። የእምነት ሰዎችን እየፈለጋችሁ የእምነትን ጸሎት እንዲጸልዩላችሁ ታደርጉ ይሆናል፤ ነገር ግን ያለ ምንም ውጤት፤ ምክንያቱም የእናንተ አለማመን የዚያን ሰው እምነት ውጤት-አልባ/ባዶ ያደርገዋል...*

*"ብዙዎች ሰዎች ምንም እምነት የላቸውም ምክንያቱም በሚጸልዩበት ጊዜ ራሳቸውን ከእምነት ያወጡታል። እንዴት? እያንዳንዱ ኃጢአትና ወደ አእምሮአቸው የሚመጣውን የሠሩትን ስሕተት ሁሉ በጸሎታቸው ውስጥ ያመጡታል፤ ጸሎታቸውን በሚጨርሱት ጊዜ ምንም እምነት አይኖራቸውም ምክንያቱም ጸሎታቸው ሁሉ በተሳሳተ ንግግር የተሞላ ስለሆነ ራሳቸውን በፍርድ/ኩነኔ ውስጥ ከተውታል።"[14]*

በመሆኑም የእምነት እንቅስቃሴ አማኞች የበሽታን ምልክቶች እያዩ "ተፈውሻለሁ" ብለው ድርቅ እንዲሉ ይመክራሉ።

ኬንየን እንደሚሉት፥

*"ሁልጊዜም ኑዛዜ ከፈውስ ቀድሞ ይሄዳል። ከቶውንም ምልክቶቹን አትመልከት - ቃሉን ተመልከት! ኑዛዜህም ድፍረትና ጥንካሬ የተሞላበት እንደሆነ ልብ በል። ሰዎችን አትስማቸው። በቃሉ ላይ ተራመድ። የሚናገረው እግዚአብሔር ነው። ተፈውሰሃል- ቃሉ ፈውሰሃል ይላል። ስሜቶችህን አታዳምጥ። ለቃሉ ሰፍራውን አትንፈግ። እግዚአብሔር አይዋሽም።"*[15]

ሐገንም በእግዚአብሔር ላይ ያለ እውነተኛ እምነት - የልብ እምነት ከሥጋዊ መረጃዎች ባሻገር የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚያምንና ፈውስን የሚፈልገውም ሰው የበሽታ ምልክቶቹን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል መመልከት"[16] እንዳለበት አስተምረዋል።

የእግዚአብሔር ቃል መፈወሳችንን እንደሚያረጋግጥ እነ ሐገን ከሚጠቅሱዋቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱ የሚከተለው ነው - እስኪ ዓውደ-ንባቡን አስተውለው ይመልከቱ።

*"ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ! በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል"(1ኛ ጴጥ. 2፡24)።*

በግልጽ እንደሚታየው፥ ክፍሉ የሚናገረው ስለ ጠቅላላው የደኅንነት መልእክት ነው። ቃሉ መጀመሪያ ወደ ተነገረበት ኢሳይያስ 53፡6 ሄደን ብናይ፥ እሳቡ የበለጠ ግልጽ ይሆንልናል። ሊተላለፍ የተፈለገውም መልእክት ጌታ በመስቀል ላይ በመቁሰሉ ምክንያት ደኅንነትን እንዳገኘን ነው። ጌታ የፈወሰን "ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር" ነው - ክፍሉ እንደሚናገረው።

ይህን ስል ጌታ ሕዝቡን አይፈውስም ማለቴ አይደለም! እንደ እርሱ ያለ ፈዋሽ እንደሌለ አምናለሁ። ነገር ግን ይህ ምንባብ የሚናገረው የእምነት አስተማሪዎች እንደሚሉት፥ ስለ ሥጋዊ ፈውስ አይደለም ለማለት ነው። ስለ ሥጋዊ ፈውስ የሚናገሩ ሌሎች በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ።

## *ሕመምን መታገሥ*

ኬንየን "ሕመም ሰውነትህን እያሠቃየ በእምነት ተፈውሰሃል"[17] ሲሉ ያውጃሉ። ሐገንም ሕመም በማይኖርበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚፈውስ በቀላሉ ማመን እንደሚቻልና እውነተኛው የእምነት ፈተና የሚመጣው አዎንታዊ ኑዛዜ ለመስጠት ሕመምን መካድ በሚያስፈልገበት ጊዜ እንደሆነ ገልጸዋል[18]። ከሐገን ደቀ መዛሙርት አንዱ የሆኑት ፍሬድ ፕራይስ የሕመምን ሥቃይ ታግሠው እምነታቸውን ተግባራዊ ስላደረጉበት ወቅት እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

*"ስለ እምነትና ፈውስ ባልሰማሁ ምናለ ብዬ እስከማማርር ድረስ ነበር ከፍተኛ የሕመም ሥቃይ የደረሰብኝ። አንዳንድ ጊዜም ወደ ሐኪሞች ሄጄ ከበሽታዬ ልገላገል ተመኝቻለሁ። ይሁንና፥ እኔ የሚሻለውን ስለማውቅ... ወደዚያ ለመሄድ አልፈለግሁም።"*[19]

ይህንን ስናይ፥ የእምነት አስተማሪዎች ለበሽታና ለፈውስ የሚሰጡት ፍች እኛ ከምናውቀው የተለየ መሆኑን እንረዳለን። እስከምናውቀው ድረስ፥ ፈውስ ማለት "ከበሽታ መፈወስና መዳን፥ የቀድሞውን ጤንነት ማግኘት፥ ደኅና መሆን ማለት ነው።"[20] የእምነት እንቅስቃሴ ፈውስ ግን በሽታን ታግሦ መቋቋም እንጂ ከበሽታ መገላገል አይደለም። የክርስቲያን ሳይንሷ ሜሪ ቤከር እንደሚሉትም፥ በሽታ እውነተኛ ነገር ሳይሆን የአእምሮ ፈጠራ ወይም ስሕተት ነው።

*"የበሽታ ወይም የኃጢአት አእምሮአዊ ፈጠራ ሲፈትንህ፥ ወደ እግዚአብሔርና ወደ አሳቡ ቅረብ... ምንም ነገር በአሳብህ ውስጥ ስፍራ አይኑረው። ፍርሃትም ሆነ ጥርጣሬ እምነትህን አያናጋው . . . "*[21]

እንደ ሜሪ፥ "በሽተኛውን የማዳኛው መንገድ በሽታው እውነት እንዳልሆነ ማሳመን ነው።"[22] በመቀጠልም፥ በሽታን ለመከላከልም ሆነ ለማዳን የመለኮታዊው መንፈስ የእውነት ኃይል የቁሳዊ ስሜቶችን ኃይል መስበር አለበት"[23] ብለዋል። በሽተኛው ዓይኖቹን ከስሜቶቹ መረጃ ወደ ክርስቲያን ሳይንስ እውነታዎች እንዲመልስ ሊነገረው ይገባል ነው የሚሉት[24]።

## *የሕክምና ሳይንስ*

ሐገን ሕመም ሲሰማቸው ምን እንደሚያደርጉ ተጠይቀው፥ "እኔ የምሰብከውን አደርጋለሁ። የምሰብከው ለእኔ የማይሠራ ከሆነ በዓለም ውስጥ ለሌሎች እንዴት እንደሚሠራ አላውቅም"[25] ሲሉ መልሰዋል። ይሁንና፥ ሐገን አራት ጊዜያት በከፍተኛ የልብ ሕመም እንደተሠቃዩ ታውቋል።

የሐኪሞችን ሙያ ሲያጥላሉ ኬነት ኮፕላንድ፥

*"ዓለም የራሷ የሆነ የፈውስ መንገድ ያላት ሲሆን፥ ይህም ለምንም የማይረባ (በእርሳቸው አገላለጽ 'miserable failure') ነው"*[26] *ብለዋል።*

ፍሬድ ፕራይስ ደግሞ፥

*"ዶክተሮቹም እኛ የምንዋጋውን ያንኑ በሽታ እየተዋጉ ናቸው! ልዩነቱ እኛ አቶማቲክ በምብ ስንጠቀም እነርሱ ግን በጥርስ መንቀያ መሣሪያ የሚገለገሉ መሆናቸው ነው"*[27] *ብለዋል።*

ኬንየንም በሕክምና መገልገል ከእምነት ጋር እንደሚቃረን ገልጸዋል። እንደ ፍሬድ ፕራይስ ዓይነቶቹ ግን የአማኙ እምነት እስኪጠነክር ድረስ

"ምርኩዝ" ብለው የሚጠሩትን ሕክምና መውሰድ እንደሚቻል ያትታሉ። "ምርኩዝም ሆነ ሌላ ድጋፍ ከፈለግህ እግዚአብሔርን አመስግን፤ እምነትህ ምርኩዝ ወደማትፈልግበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ተጠቀምበት።"[28]

## *አማኞች ከቶውንም ታመው መሞት የለባቸውም*

የእምነት ሥነ-መለኮት ብዙዎችን ለመሳብ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ይህንኑ ከበሽታ የጸዳ ሕይወት ተስፋ መስጠት ነው። ይሁንና፥ ምን ያህል እውነተኛ የሆነው አማኝ ነው የማይታመመው የሚለው አጠያያቂ ይሆናል። ኬንየን ለዚህ ጥያቄ፥ "ማንኛውም አማኝ እንዳይታመም የአባታችን ፈቃድ ነው፤ ሙሉ ዘመኑን ኑሮ ማንቀላፋት አለበት"[29] ሲሉ ይመልሳሉ። ሐገንም የኬንየንን ፈለግ በመከተል የሚከተለውን አክለዋል።

*"ማንኛውም አማኝ ለመቼውም እንዳይታመም የእግዚአብሔር አባታችን ዕቅድ እንደሆነ አምናለሁ። እያንዳንዱ አማኝ ሙሉ ሕይወቱን ኖሮ ሲያበቃ ማንቀላፋት አለበት... በካንሰርና በሌሎችም አሠቃቂ በሽታዎች እንድንሠቃይ የእግዚአብሔር አባቴ ፈቃድ እንዳልሆነ በድፍረት እናገራለሁ። የለም! እንፈወስ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።"[30]*

የእምነት ሥነ-መለኮት፥ አማኞች ሞትን እስካናካቴው ሊያሸንፉ ይችላሉ የሚለውን የ"Manifest Son of God" ዶክትሪን ባይከተሉም፥ የአማኙ አሟሟቱ የእምነቱን ጥንካሬ ይወስናል ብለው ያምናሉ። ኬንየንና ሐገን እንደሚሉት፥ አማኞች ታመው መሞት የለባቸውም።

## *አማኞች ከ70 ዓመታት በፊት መሞት የለባቸውም!*

*"አነስተኛው የአማኝ ዕድሜ 70 ዓመታት መሆን አለበት... እግዚአብሔር በራሱ አፍ በብሉይ ኪዳን ዘመንህ 120 ዓመታት ይሆናል ብሏል። ይኼ እኔ ያልሁት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ያለው ነው። አነስተኛው 70 ዓመታት መሆን አለበት። ከዚያ በኋላም በበሽታ መሞት የለብህም።"[31]*

እንደ እምነት ሥነ-መለኮት፥ 70ዎቹ ዓመታት ሲያልቁ አማኙ የሚሞትበትን ጊዜ "ይመርጣል።" ፕራይስ እንደሚሉት፥ "ሰዎች ከ70-120 ዓመታት በፊት የሚሞቱበት ብቸኛው ምክንያት ሞትን ለመከላከል በቃሉ መሠረት እምነታቸውን መለማመድ ስለማይገባቸው ወይም ከጊዜያቸው በፊት ለመሞት ስለሚመርጡ ነው።"[32]

ልጆች ለምን እንደሚሞቱ ወይም ሞተው እንደሚወለዱ ሚስተር ፕራይስ ሲያብራሩ፥ "ሞተው የሚወለዱ ልጆች በሕይወታቸው ላይ ለመቆጣጠር ባይችሉም፥ ወላጆቻቸው ግን ይህንኑ ለማድረግ ይችላሉ። ይሁንና፥ ወላጆች የእግዚአብሔርን ቃልና በክርስቶስ ያላቸውን መብት ለማስጠበቅ ካልቻሉ፥ ልጆቻቸው ይሞታሉ" ብለዋል።

ትራይን እንደሚሉት፥ ሰዎች ከ70–120 ያለውን ዕድሜያቸውን ሳይሞሉ የሚሞቱት በአጠገባቸው የሚገኙ ሌሎች ሲያረጁ አይተው እኔም አረጃለሁ ብለው ስለሚሰጉ ነው።

## *አካለ–ስንኩልነት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እንደሚያደናቅፍ*

*"ሰውነታችሁ በትክክል የማይሠራ ከሆነ እንዴት እግዚአብሔርን በሰውነታችሁ ልታከብሩት ትችላላችሁ? ማየትና መስማት የተሳናቸው ዓይኖችና ጆሮዎች ባሉት ሰውነት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለምን ለመኖር ይፈልጋል ብላችሁ ታስባላችሁ? እጅና እግር፥ እንዲሁም ሌሎች ብልቶችና ሕዋሳት በትክክል መሥራት በማይችሉበት አካል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለምን ሲል መኖር የሚፈልግ ይመስላችኋል?... በሰውየው ዓይን ሊያይበት፥ በእግሮቹ ሊጓዝበት፥ በእጆቹ ሊሠራበት ካልቻለ፥ መንፈስ ቅዱስ ምን በወጣው በዚያ መቅደስ ውስጥ ይኖራል?... "*[33]

የዚህ ዓይነቱ የእምነት አስተማሪዎች ትምህርት ሳናውቅ እንኳ ስሜታቸውን እንዳንነሳ ለምንጠነቀቅላቸው የአካል ጉዳተኛ ወገኖቻችን ምን ያህል ቅስም–ሰባሪ እንደሆነ ለመገመት አይከብድም። ለመሆኑ፥ እጅንና እግርን የፈጠረው መንፈስ ቅዱስ ለምን ሲል ነው በሰው እጅና እግር የሚገለገል? የዚህ ዓይነቱ አመለካከት አካል ጉዳተኛነት ወይም ማንኛውም በሽታ የኃጢአት ውጤት ነው ተብሎ የሚታመንበትን የአይሁዶች ግንዛቤ ከሚያስታውሰን በቀር፥ በማንኛውም መልኩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን አይችልም።

አንድ ታትሞ ያልወጣ የአማርኛ መጽሐፍ እንደዘገበው፥ ከፈረንጅ አገር መጥተው በዘዳግም 28ቱ በረከት ላይ የሰበኩት ኢትዮጵያዊ "ሰማያዊ በረከትን የምንወርሰው በእምነት ሲሆን፥ ምድራዊ በረከትን ደግሞ በመታዘዝ ነው" ሲሉ፥ ፈውስን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት ምድራዊ በረከት ማግኘት እንደሚቻል አስተምረዋል። ይህ ግን ከሕግ ቀንበር ተላቀው በአዲስ ኪዳን በጸጋ የሚመሩትን አማኞች ወደ ሕግ እስራት የኋሊት የሚያስጉዝና ለበረከት ብለው የሚሰብኩት ትምህርት ለእርግማን የሚዳርግ መሆኑን ይኸው መጽሐፍ ያስረዳል። ለዚህም ምክንያቱ "ሕግን በመፈጸም እንጸድቃለን የሚሉ የተረገሙ ናቸው" ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ በግልጽ ያስቀመጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ነው (ገላ. 3፡10–14 አንብብ)።

## *ኢዮብ*

ከዚህ የእምነት እንቅስቃሴ ትምህርት በንስሓ እንደተመለሱና የካሴት ሽያጩን ትርፍ ላለማጣት ወደዚያው እንደተመለሱ የሚነገርላቸው ቤንሂን ስለ ኢዮብ የሚከተለውን ብለው ነበር።

*"ይህን ታውቃላችሁ? ሚሊዮን ጊዜ ተናግራችሁታል፤ ከኢዮብ የተነሣ ነው እንጂ ፈጽሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፥ እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሣ*

*የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን (ኢዮብ 1፡21)። ዜና አለኝ ለእናንተ፥ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ አይደለም። እግዚአብሔር ይሰጣል፥ እግዚአብሔር በፍጹም አይነሣም። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ስላለ ብቻ ትክክል ነው ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ሲል ሃይማኖተኛ መምሰሉ ነው፤ ሃይማኖተኛ ብንመስል ደግሞ ትክክል ነን ማለት አይደለም።"*

እግዚአብሔርስ ስለ ኢዮብ ምን አለ?

*"ፍጹም ቅን እግዚአብሔርን የሚፈራ ከክፋትም የራቀ" (ኢዮብ 1፡1፥8)።*

*"በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፥ ለእግዚአብሔር ስንፍና አልሰጠም"(ኢዮብ 1፡22)።*

*"እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር አልተናገራችሁምና ቁጣዬ በእናንተ ላይ ነድዶአል . . . የሚቃጠልን መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ" (ኢዮብ 42፡7)።*

እግዚአብሔር እንዲህ የመሰከረለትንና ሐዋርያው ያዕቆብም የእምነትና የትዕግሥት ምሳሌ አድርጎ የሣለውን ኢዮብን የዘለፉት የእምነት እንቅስቃሴ አማኞች፥ በጊዜ "ስለ ራሳቸው መሥዋዕት ቢያሳርጉ" መልካም ነው እንላለን። ጌታ እጅግ የሚራራ የሚምርም ነውና የጥፋት ሩጫቸውን ላፍታ ገትተው፥ እንደ ጂም ቤከር የቆሙበትን የእምቡዋይ ካብ ቢያስተውሉ መልካም ነው።

ከእግዚአብሔር ቃል ምስክርነት ይልቅ እነርሱን እንድንሰማቸው መፈለጋቸው፥ "አምላክ ነን" ማለታቸውን ብቻ ሳይሆን "ከአማልክት አምላክ" በላይ ለመሰየም መሻታቸውን ያሳየናል። ይህ ደግሞ ለሳጥናኤልም አልበጀውም (ኢሳ. 14፡ 1–14)።

ቀድሞ ነገር "እግዚአብሔር ሰጠ – እግዚአብሔር ነሣ" የሚለው ቃል የመጣው መከራው ከደረሰበት በኋላ እንጂ ከመከራው በፊት አይደለም። ስለሆነም፥ በኢዮብ ላይ ያ ሁሉ መከራና በሽታ የደረሰው አሉታዊ ቃል በመናገሩ ነው ማለቱ ለራስ ሕሊና አለመታመን ነው።

ከላይ የገለጽሁት ያልታተመ መጽሐፍ፥ በፈውስ አገልግሎቷ ታዋቂ የነበረችውንና በሽተኛ ሁሉ መፈወስ አለበት ትል የነበረችውን የካትሪን ኩልማንን ገጠመኞች ይጠቃቅሳል።

*"በዚህ አገልግሎቴ አሁን ያለኝ የጠለቀ እውቀት ባልነበረኝ በወጣትነት ጊዜዬ ሰዎችን፥ ፈውስ ከእግዚአብሔር ለመቀበል እነዚህንና እነዚያን ፎርማሊቲዎች ማሟላት አለባችሁ፤ በተለይም ፈውስ ለመቀበል የሚፈልገው ሰው እምነት ሙሉ ለሙሉ አስፈላጊ ነው እል ነበር። ነገር ግን በአንድ የፈውስ አገልግሎቴ ላይ የነበረ አንድ መስማት የተሣነው ሰው ፈውስ ይህንን የከረረ አቋሜን እንድመረምር አደረገኝ። ሰውየው ፈጽሞ እምነት አልነበረውም፤ ነገር ግን ጆሮው ተከፍቶ፥ 'ይኼ ለማመን የሚያስቸግር ነገር ነው፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን*

*እንኳ ሄጄ አላውቅም' እያለ ይጮኽ ጀመር። በዚህ ጊዜ ነው እግዚአብሔርን በእኔ እውቀት የወሰንሁበትን ግንዛቤ በመስኮት የወረወርሁት።"*

ኩልማን እንደዚህ ዓይነት ገጠመኞችን ከተለማመደች በኋላ የሚከተለውን ብላለች።

*"ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት በነበረኝ እምነት ሰማይ ዝቅ ቢል ምድርም ከፍ ቢል ማንኛውም ሰው የሥጋ ፈውስ ማግኘቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብዬ አምን ነበር። ነገር ግን በአገልግሎቴ ዘመን ይህንን ጉዳይ በጥንቃቄ ተመለከትሁት። እግዚአብሔርን ይህንን ነገር ካላደረግህ በማለት ማስገደድ እንደማይቻል ተገነዘብሁ። ስለዚህ በአንዳንድ የተወሰኑ ነገሮች ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ወይም ያ ነው ለማለት አስቸጋሪ መሆኑን ተረዳሁ።*

*"እግዚአብሔር በእኛ የሥነ-መለኮት ግንዛቤ በመወሰን የሚሠራ አለመሆኑን በማወቅ ወሰኛለሁ . . . እኛ ግን በአምላክነቱ ዙሪያ አጥር ልናበጅለትና በእኛ ደረጃ ዝቅ ልናደርገው እንሞክራለን። ይህ አይሠራም! እግዚአብሔርን ልንወስነው እስከማንችል ድረስ ታላቅ ነው።*

*"በዚህ የፈውስ አገልግሎቴ እግዚአብሔር በዚህና በዚያ መንገድ እንደሚፈውስ የሚናገር መጽሐፍ እንድጽፍ ብዙ ጊዜ ብጠየቅም፥ እግዚአብሔር እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈውስ ማወቅ አለመቻሉን በመገንዘቤ እንዲህ ዓይነት መጽሐፍ አልጻፍሁም። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ፈውስ የሚገኘው በዚህና በዚያ መንገድ ነው የሚል መጽሐፍ ለመጻፍ ስንዘጋጅ፥ መንፈስ ቅዱስ እኛ ካሰብነው ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መንገድ ሲሠራ አየዋለሁ። እኔ ራሴ ገና እግዚአብሔር የሚሠራቸውን ምሥጢራዊ መንገዶች እየተማርሁ ነኝ።"*

ኩልማን ለሕሊናዋና ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆኗ እንጂ፥ "ሰባቱ አስደናቂ የፈውስ ማግኛ መንገዶች" በሚል ርእስ መጽሐፍ ብታሳትም ኖሮ፥ ከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ ማግበስበሷ አይቀርም ነበር። ለመሆኑ፥ የእምነት እንቅስቃሴው ፈዋሾች ከዚህ ምን ይማሩ ይሆን?

## *ፈውስና ተአምራት በመጽሐፍ ቅዱስ*

*". . . ከዚያ በፊትም ቢሆን እግዚአብሔርን ለማመን ጠንካራ መረጃ ስሻ ቆይቼ ነበር። እነሆም፥ አንድ ዕለት አገኘሁት – በቴሌቪዥን መስተዋት ላይ። አንዲት ሴት ታላቅ የፈውስ አገልግሎት እያካሄደች ነበር። በዚህ ዕለት የተለያዩ ሰዎችን ወደ ምስባኩ እያመጣች ቃለ-መጠይቅ ስታደርግ ለጥቂት ደቂቃዎች ተመለከትሁ። እነዚህም ሰዎች አስደናቂ የሆነ ልዕለ-ተፈጥሯዊ ፈውስ በሕይወታቸው እንደ ተፈጸመ ይመሰክሩ ነበር። ካንሰር፥ የልብ ድካም፥ ሽባነት፥ የተረፈ የበሽታ ዘር አልነበረም።*

*"የዚህችን ሴት የፈውስ ፕሮግራም ስመለከት ሳለሁ በፈጣሪ ህልውና ላይ የነበረኝ ጥርጣሬ በንኖ ጠፋ። በመጨረሻው አንድ እውነተኛና ተጨባጭ ነገር እንዳገኘሁ ሆኖ ተሰማኝ። የፈውስ አገልጋይዋ ዘማሪው፥ 'ዳስሶኛል' የሚለውንና እርሷ*

*የምትወደውን መዝሙር እንዲዘምር ጠየቀችው። እኔም የምፈልገው ይህንኑ እንደሆነ አሰብሁ – በእግዚአብሔር መዳሰስ። አገልጋይዋም ይህንኑ የተሰፋ ቃል በመስጠቷ ልቤን ከፈትሁላት።*

*"ከሦስት ሳምንታት በኋላ ያቺ በቴሌቭዥን ላይ የተመለከትኋት የፈውስ አገልጋይ እኔ ወደምኖርበት አካባቢ በመምጣቷ፥ የትምህርት ክፍለ-ጊዜዬን ዘግቼ አንድ ቀን ለግማሽ ሰዓት የፈውስ አገልግሎቷን ተከታተልሁ። የስብሰባው ዓውድ እጅግ የሚጥም ነበር – ለሆሳስ የኦርጋን ሙዚቃ ድምፅ በአዳራሹ ውስጥ ያስተጋባል፤ ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲጸልዩ የሚሰማ ማጉተምተም፥ የአንዳንዶች የልዩ ቋንቋ ድምፅ፥ በየደቂቃው ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ብድግ ብሎ 'ተፈውሻለሁ!' ሲል የሚደመጠው አስደሳች ስሜት . . . አዳራሹን ሞልቶት ነበር።*

*"ከሁሉም በላይ ያስደነቀኝ በቃሬዛ ተሸክመው ወደ አዳራሹ ያስገቡት አንድ ሰውዬ ነበር። በምስባኩ ላይ ተነሥቶ ሲንቀሳቀስ ሁላችንም ራሳችንን መቆጣጠር ተስኖን አዳራሹን በጩኸት አናወጥን። ንግግሩን ሲጀምር የሕክምና ዶክተር እንደሆነ ነገረን፤ ይህም የበለጠ አስገረመኝ። የሳንባ ካንሰር እንደነበረበትና ሐኪሞች የስድስት ወራት ዕድሜ ብቻ እንደቀረው መናገራቸውን ገለጸልን። ይሁንና፥ በዚሁ ምሽት እግዚአብሔር እንደፈወሰው ነገረን። በወራት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ቆሞ መሄዱ እንደሆነ በመግለጽ፥ ስለ ተሰማው ታላቅ ደስታ አወጋን።*

*"እኔም የዚህን ሰውዬ ስም ጻፍሁና ከስብሰባው ወጥቼ ሄድሁ። ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ የእምነት ዋስትና አግኝቼ አላውቅም ነበር። ከምስባኩ ላይ ቆመው ምስክርነት በሰጡት ሰዎች ውስጥ የሕያውን አምላክ ህልውና ስላየሁ ምርምሬ ከፍጻሜ ደረሰ። በነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ተጨባጭ ተአምር ሊፈጥር ከቻለ ለእኔም የሚሆን ነገር በመዝገቡ ውስጥ እንዳለ እርግጠኛ ሆንሁ።*

*"ከዚያ የእምነት ጀግና ጋር ለመገናኘት በጣም ስለጓጓሁ፥ ልክ በሳምንቱ ወደ መረጃ ቢሮ ደውዬ የስልክ ቁጥሩን አገኘሁ። አንዲት ሴት ስልኩን ስታነሣው፥ 'ከዶክተር እገሌ ጋር ለመነጋገር ነበር' አልኋት።*

*"ለረዥም ጊዜ ጸጥታ ነገሠ። በመጨረሻም፥ 'አንተ ማን ነህ?' ስትል ጠየቀችኝ። እኔም የስልክ ጥሪዎች ከበሽተኞች መሆናቸውን ወይም ሌላ ነገር ለማጣራት እየፈለገች እንደሆነ መሰለኝ። ስለሆነም፥ ስሜን ከነገርኋት በኋላ ዶክተሩን እንደማደንቃቸውና ከዚያን የፈውስ ስብሰባ ዕለት ጀምሮ ላነጋግራቸው ስፈልግ እንደቆየሁ ነገርኋት። በዶክተሩ ታሪክ በጣም መደነቄንም አልሸሸግሁባትም።*

*"አሁንም ሌላ ረዥም የፀጥታ ጊዜ ሆነ። ከዚያም በሚቆራረጥ ድምፅ እያንዳንዱን ቃል እየቆጠረች፥ 'ባለቤቴ . . . ሞቷል . . .' አለች።"*[34]

እንግዲህ፥ ይህ ማለት እግዚአብሔር የፈውስና የተአምራት ሥራውን አቁሟል ማለት ይሆን? በፍጹም አይደለም! አንድ ጸሐፊ ያስፈራቸው ቀጣይ አሳቦች በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሉት አላቸው።

*"እግዚአብሔር ሁልጊዜም ተአምራት ሠሪ አምላክ ነው፤ ወደፊትም በተአምራት ሠሪነቱ ይቀጥላል። ምንም እንኳ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ተአምራት መሥራቱን እንዳቆመ ቢናገሩም፥ ለዚህ ዓይነቱ አሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ዓይነት ድጋፍ አይሰጥም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታዩ የተለያዩ የፈውስና የተአምራት ክስተቶችም ለዚህ መረጃዎች ናቸው። ስለሆነም፥ ዛሬም እግዚአብሔር ፈውስ፥ ተአምራትና ከአጋንንት ነጻ ማውጣት የመሳሰሉትን ነገሮች ማድረጉን እንደሚቀጥል እናምናለን። ይሁንና . . . ማንም ሰው ተአምራትንና ፈውስን እንደ ፈለገ ሊሠራ አይችልም። ተአምራትን የማድረጉ ኃይል የሚያርፈው በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ላይ አይደለም። እንዲሁም ደግሞ ማንም ሰው እግዚአብሔር ተአምራት ይሠራ ዘንድ ሊያዘው አይችልም። ተአምር በመሥራቱ ላይ ሰው ሊያደርግ የሚችለው ነገር ቢኖር የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መከተል ብቻ ነው። ይህም ደረጃ በደረጃ ሊካሄድ የሚገባው ሆኖ ሳለ ሰዎች ግን በፈውስና ተአምራት ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸው ከጥንቶቹ ምልክት ፈላጊ አይሁዶች ጋር አዛምዷቸዋል። ስለሆነም፥ የዮናስን ምልክት ማለትም የጌታን ከሞት የመነሣት ምልክት ከምልክቶች ሁሉ እንደሚበልጥ የእምነት ዋስትና አድርገን እንመለከትም (ማቴዎስ 12፡39–41)።"*[35]

ይሁንና፥ እግዚአብሔር ተአምር ሠራ ወይም አንድን ሰው በልዕለ–ተፈጥሯዊ መንገድ ፈወሰ ስንል ምን ማለታችን ነው? ተአምር ተፈጸመ የምንለው እግዚአብሔር አጽናፈ–ዓለሙ ዕለታዊ ተግባሩን እንዲያንቀሳቅስ የፈጠራቸውን ተፈጥሯዊ ደንቦች ሲጥስ ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር በተፈጥሮ የማይዘለቁትን ነገሮች አከናውኖ ሲገኝ ማለት ነው። መለኮታዊ ፈውስ ተፈጸመ የምንለውም እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ውስጥ ተፈጥሯዊውን የሕመምና የማርጀት ሁኔታ ሲቋቋም ነው። እግዚአብሔር በሰው ልጅ ሰውነት ውስጥ በተፈጥሯዊ መንገድ ፈውስን እንዲያስገኝ የሰጠውን የሕክምና መድኃኒት በማይነካ መልኩ በሽታን አስወግዶ ጤንነትን ሲመልስ መለኮታዊ ፈውስ ተገኘ እንላለን።

አስደናቂ ነገሮች በሚያምኑትም ሆነ በማያምኑ ሰዎች ሕይወት ይፈጸማሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ ለሰው ልጆች ፈውስን የሚሰጠው በመለኮታዊ ጣልቃ–ገብነት ሳይሆን በሕክምናና በሌሎችም ለሰው ልጆች በሰጣቸው ጥበቦች ነው። ይሁንና፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኙ ፈውሶች በምንናገርበት ጊዜ፥ ለሰው የማይቻሉና እግዚአብሔር ራሱ በጣልቃ–ገብነቱ የፈጸማቸውን ነገሮች መናገራችን እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

## *ፈውስና ተአምራት በብሉይ ኪዳን*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ የተአምራት ዝርዝሮች ይገኛሉ (ዘጸአት14፡15–22፤ ኢያሱ 10፡11–14፤ 1ኛ ሳሙኤል 12፡18፤ 1ኛ ነገሥት 18፡30–38፤ 2ኛ ነገሥት 4፡32–35)። ከብሉይ ኪዳን የምንማረው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ታላቅና ኃያል፥ ብሎም ተአምራት አድራጊ እንደሆነ ነው፤ ይህንንም

የተአምራት ሥራ ለሕዝቡ ሲሠራ እንደኖረ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ካደረጋቸው ተአምራት መካከል ቀይ ባህርን ያህል ታላቅ ባህር መክፈል፥ የኢያሪኮን ግንብ ማፈራረስ፥ የታመሙትን መፈወስ፥ የሞቱትን ማስነሣትና ሌሎችም አስደናቂ ክስተቶች ይገኙባቸዋል።

ይህም ሆኖ፥ ብሉይ ኪዳንን በምንመለከትበት ጊዜ ሁልጊዜም መለኮታዊ ፈውስና ተአምራት ሲከሰቱ አንመለከትም። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ብዙ ተአምራት ሲሠራ፥ በሌላ ጊዜ ግን ዝምታን ይመርጣል። ፊሊፕ ያንሲ በነቢያት መጻሕፍት ላይ የሚከተለውን አስተያየት ሰንዝረዋል።

*"የነቢያትን መጻሕፍት ሁልጊዜም በተሳሳተ መንገድ ስረዳ ኖሬአለሁ። ነቢያት ሁሉ እንደ ነቢዩ ኤልያስ በአረማውያን ላይ ከሰማይ እሳት የሚያወርዱ ኃይለኛ ሰዎች እንደሆኑ ይመስለኝ ነበር። የሚገርመው ግን የጥንቶቹ የነቢያት መጻሕፍት ከማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በላይ 'ዘመናውያን' መሆናቸውን መገንዘቤ ነው። በዘመናችን ላይ እንደ ደመና ከሚያንዣብቡ ዓይነተኛ ጥብጠቦች ጋር ነበር ሲታገሉ የኖሩት! እነዚህም የእግዚአብሔር ዝምታ፥ የክፋት የይምሰል ሉአላዊነትና በዓለም ላይ የሚታየው የማይረግብ ሥቃይ ናቸው። የነቢያት ጥያቄዎች የዚህ መጽሐፍ [የዚህ ዘመን] ጥያቄዎች ናቸው ...*

*"በታሪክ ሁሉ፥ እንደ እስራኤል ነቢያት በእግዚአብሔር ማዘናቸውን የገለጹ ሰዎች አልታዩም። አምላክ የሌላቸው ሰዎች የሚለሙት ለምንድን ነው? ሲሉ ጠይቀዋል። በዓለም እንዲህ ያለ ረሃብና ችግር የሚበዛው ለምንድን ነው? ብዙ ተአምራት የማይከሰቱት ለምንድን ነው? ወዴት ነህ፥ እግዚአብሔር ሆይ? 'ለምን ሁልጊዜ ትረሳናለህ?' ራስህን ግለጥልን! ዝምታውን ግፈፍልን። እግዚአብሔር ሆይ፥ ስለ እግዚአብሔር ብለህ በቀጥታ ሥራህን ግለጥ!'*

በዚህ ዓይነት ድምፃቸውን ካሰሙት ነቢያት መካከል ኢሳይያስና ኤርምያስ ይገኙባቸዋል። በተለይም ሰቆቃወ ኤርምያስ በዋይታ የተሞላ እንደሆነ ግልጽ ነው። እስኪ ነቢዩ ኢሳይያስ በ64ኛ ምዕራፉ ከሚናገራቸው የምሬት ቃላት ጥቂቶቹን እንመልከት።

*"ሰማዮችን ቀድደህ ምነው ብትወርድ! ተራሮችም ምነው ቢናወጡ! እሳት ጭራሮውን እንደሚያቃጥል፥ እሳትም ውኃውን እንደሚያፈላ፥ ስምህ ለጠላቶችህ ይገለጥ ዘንድ፥ አሕዛብም በፊትህ ይንቀጠቀጡ ዘንድ"(ቁጥር 1-3)።*

ይህንን ስንመለከት፥ ምናልባትም አንዳንዶቻችን ብዙ የፈውስና የተአምራት ክስተት ያልታየባቸው ጊዜያት የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት የወደቀባቸው ጊዜያት ናቸው ወደሚል ድምዳሜ ልንሄድ እንችላለን። ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ የሞከረ አንድ ግለሰብ "ከፍተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ይታይ በነበረበት የዳዊት ንግሥና ዘመን ስንት ተአምራት ተከሰቱ?" ሲል ይጠይቅና፥ "ምንም!" የሚል ምላሽ ይሰጣል። በዚሁ ጸሐፊ ምልከታ መሠረት፥ በእስራኤል ታሪክ ተአምራት በርከተው የታዩባቸው ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው።[36]

* እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ በፈጠረባቸው የፍጥረት ጊዜያት

* እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባርነት ነጻ አውጥቶ በምድረ በዳ በመራበትና ወደ ተስፋዪቱ ምድር ባስገባበት ወቅት

* ኤልያስና ኤልሳዕ በነቢይነት ባገለገሉበት ወቅት

ይህም ሲባል፥ እግዚአብሔር ከነዚህ ጊዜያት ውጭ ተአምራት ሠርቶ አያውቅም ማለት አይደለም፤ ይልቁንም፥ እግዚአብሔር ለዓላማው ብዙ ተአምራት ለመሥራት የሚፈልግባቸውና ጥቂት ተአምራት ብቻ ለመሥራት የሚፈቅድባቸው ጊዜያት እንዳሉ ያሳየናል።

የሚገርመው ግን ተአምራት በበረከቱባቸው ዘመናት፥ ባብዛኛው የሰዎቹ እምነት እንደመነሳበት መመንመኑ ነው። ምንም እንኳ ተአምራት የእግዚአብሔርን ክብር የሚያሳዩ ታላላቅ ክስተቶች ቢሆኑም፥ ሰዎቹ ይኼን ያህል በእግዚአብሔር አይታመኑም ነበር። በምድረ በዳ፥ እግዚአብሔር በሙሴ እጅ ብዙ ተአምራት በሚያደርግበት ወቅት በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረማቸው ብዙዎቹ በሞት እንደተቀጡ ትዝ ይለናል። በኤልያስና በኤልሳዕ ዘመንም የሰዎቹ መንፈሳዊ ሕይወት እስከዚህም አልተለወጠም ነበር። ስለሆነም፥ ከብሉይ ኪዳን ስለ ተአምራት የሚከተሉትን ነገሮች ልንመለከት እንችላለን።

* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተአምር የሚሠራ አምላክ ነው።

* እግዚአብሔር ሁልጊዜም ተአምራትን የሚሠራው በተመሳሳይ ብዛትና ድግግሞሽ አይደለም።

* ተአምራት በራሳቸው የእግዚአብሔርን ኃይል ቢገልጹም፥ የግድ የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ወደ ብስለት የሚያደርሱ ነገሮች አይደሉም።

## *ተአምራትና ፈውስ በአዲስ ኪዳን*

አዲስ ኪዳን በኢየሱስ የፈውስና የተአምራት ሥራዎች የተሞላ ነው (ሉቃስ 4፡38–41፤ 5፡12–14፥ 17–26፤ 6፡6–11፤ 7፡1–17፤ 8፡26–58፤ 9፡10–17)። እነዚህም ተአምራትና ፈውሶች በዓይነታቸውም ሆነ በጥልቀታቸው የተለያዩ ናቸው። የእኛም የተአምራትና የፈውስ ትኩረት እየላቀ የሄደው በአዲስ ኪዳን ገጾች ላይ የሚገኙ አስደናቂ ተአምራት በዘመናችንስ ለምን አይፈጸሙም? ከሚል መንፈሳዊ ቅንዓት ሳቢያ እንደሆነ እገምታለሁ። ቅንዓታችን ክፉት ባይኖረውም፥ ጌታ ያንን ያህል ተአምራትና ፈውስ ለመሥራት ለምን እንደፈለገ መረዳቱ ለቤተ ክርስቲያን የፈውስ አሠራር ጠቃሚ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ለዚህም ምክንያት የሚሆነን የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፥ ለፈውስም ሆነ ለማንኛውም አገልግሎት መሪዋን መከተል ከስህተት የሚጠብቃት በመሆኑ ነው። አንድ የጥናት ጽሑፍ ኢየሱስ

ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ገጾች ውስጥ የተጠቀሱትን ፈውሶችና ተአምራት የሠራው ለሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆነ ይገልጻል።[37]

- ለሕዝበ–እስራኤል ኢየሱስ እርሱ በብሉይ ኪዳን የተተነበየለትና የተስፋ ቃል የተሰጠው መሢሕ እንደሆነ ለማሳየት።

- ብዙውን ጊዜ ፈውሶቹና ተአምራቶቹ ኢየሱስ በተፈጥሮ፥ በበሽታ፥ በሰይጣን፥ ወዘተ. . . ላይ ሥልጣን እንዳለው በማሳየት፥ አምላክነቱን ለማጉላት የሚሠሩ ነበሩ።

- ብዙዎቹ የኢየሱስ ተአምራት ለችግርተኞች፥ ለአካል ጉዳተኞችና የተለያዩ ችግሮች ላሉባቸው ሰዎች ካለው ኃዘኔታ የመነጩ ነበሩ። አምስት ሺህ ረሃብተኞችን መመገቡ ለዚህ በዋቢነት ሊጠቀስ ይችላል።

- አጋንንትን ማውጣቱ ለሚከታተሉት ፈሪሳውያን በሰይጣን ላይ ሥልጣን እንዳለው ያሳይ ነበር።

- የኢየሱስ ተአምራት ንጉሡ በመካከላቸው እንዳለና የእግዚአብሔርም መንግሥት እንደቀረበች ያመለክት ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራቱን የሠራው ለነዚህ ምክንያቶች ከሆነና ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስን አርአያነት መከተል ካለባት፥ ከነዚህ መካከል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፈውስና የተአምራት አገልግሎት ለማካሄድ ተገቢ ምክንያቶች ሊሆኑ የሚችሉት የትኞቹ ሊሆኑ ይገባል? የሚለው ጥያቄ ለቤተ ክርስቲያን በጣም አስፈላጊ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ባደረጋቸው ፈውሶችና ተአምራት ውስጥ የሚከተሉትን ነገሮች እንመለከታለን።[38]

- ኢየሱስ ሰዎችን ለማስደነቅ ሲል ተአምራትም ሆነ ፈውስ አድርጎ አያውቅም። ይህንንም የሚያሳየን ሰዎች ተአምራት እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ ነው (ማቴዎስ 12፡38–39)። በመሆኑም፥ ፈውስና ተአምራት ተመልካችን ለማዝናናት የሚቀርቡ ትእይንቶች እንዳልሆኑ ልንገነዘብ እንችላለን።

- ኢየሱስ ሰዎች በተሰባሰቡበት እየተገኘ የጅምላ ፈውስ አላካሄደም። የእርሱ የፈውስ ሥራ በተናጠል የሚካሄድ ነበር። ይህም፥ "ሽባ ይሁን፥ ደንቆሮ፥ ማንኛውም ዓይነት በሽተኛ በዚህ ጊዜ ተፈውሷል!" ከሚባልበት ከአሁኑ ዘመን የፈውስ አገልግሎት እጅግ የተለየ ነው።

- ኢየሱስ ከፈወሳቸው ሰዎች የገንዘብ ወይም ሌላ የጥቅማጥቅም ገጸ–በረከት የተቀበለበት ጊዜ የለም።

* የኢየሱስ ፈውሶችና ተአምራት ሙሉ ለሙሉ ስኬታሞች ነበሩ። ይህም ሲባል አንድን ሰው ለመፈወስ ሞክሮ ያልተሳካበት ወይም ከፊል ፈውስ ብቻ የተፈጸመበት ጊዜ አልነበረም ማለት ነው።

* ኢየሱስ ስለ በሽተኞቹ እምነት መጠንና ጥልቀት ምንም ሳይገልጽ የፈወሰባቸው ጊዜያትም ነበሩ። ይሁንና፥ ግልጽ ተቃውሞ ባለበት ስፍራ የፈውስን አገልግሎት ከመስጠት የተቆጠበባቸው ወቅቶችም አልታጡም። ይህ ማለት ግን እንደ እምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች ለመፈወስ ሞክሮ ሲሳነው በሰዎቹ የእምነት ማነስ አሳቧል ማለት አይደለም።

* ኢየሱስ በአገልግሎቱ ወቅት ያተኮረው የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማሩ ላይ ነበር። ፈውሶቹና ተአምራቱም ቢሆኑ የሚናገራቸውን የእውነት ቃላትና የእግዚአብሔር ልጅነቱን የሚያጠናክሩና የሰዎችን ችግሮች የሚፈቱ የፍቅር መግለጫዎች እንጂ ከቶውንም 'የፈዋሽነት' ወይም 'የተአምራት አድራጊነት' ጥማት ለማርካት ሲባል የሚከናወኑ አልነበሩም። እንዲያውም፥ ሰዎች በተአምራት አድራጊነቱ ላይ እያተኮሩ ሲመጡ፥ ጌታ ያለበትን ስፍራ ለቅቆ የሚሄድ ከመሆኑም በላይ ያደረጋቸውን የፈውስና ተአምራት ተግባራት እንዳይናገሩ ሕዝቡን ያስጠነቅቃቸው ነበር (ማርቆስ 1:32–38፤ 1:44)። ይህ በዛሬው ዘመን ምን ያህል ሰው "እንደፈወሱ" በማሳየት ሌሎችን ለማስደነቅ የቪድዮ ካሜራ ለሚያንጓጉ ግለሰቦች ትልቅ ትምህርት ሊሆናቸው ይገባል።

* የኢየሱስ ተአምራት መሢሕነቱን የሚያረጋግጡ ቢሆኑም፥ ብዙ ሰዎች በተአምራቶቹ አገዛ ወደ እምነት ሊመጡ አልቻሉም ነበር። እንዲያውም፥ ተአምራቱን ለሥጋዊ ጥቅም፥ ለእንጀራ መብያ ይጠቀሙት ነበር (ዮሐንስ 6:30–48)።

* ኢየሱስ በይበልጥ ያተኩር የነበረው በደኅንነት ተአምር ላይ ነበር። ሰዎች አንድ አስደናቂ ነገር አይተው ከሚደነቁ ይልቅ፥ የሕይወት መዳን ማግኘታቸው ከሁሉም እንደሚልቅም ተናግሯል (ሉቃስ 10:21)። ለዚህም ምክንያቱ ሥጋዊ ፈውስም ሆነ መሰል ምድራዊ ችግር ማቃለያ ተአምራት ጊዜያዊ መፍትሔዎች ሲሆኑ፥ የነፍስ መዳን ግን እንከን ከሌለው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የሚያዛምደን መሆኑ ነው። ፊሊፕ ያንሲ እንደሚሉት፥ በሥጋዊ ተአምር የተፈወሱ ሰዎች የኋላ ኋላ መሞታቸው የማይቀር ነው። የዘላለም ደኅንነት ያገኙት ግን በመንግሥተ ሰማያት ይኖራሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓይነት ሁኔታ አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ አብ ቀኝ ሲሻገር፥ ሐዋርያት እርሱ የጀመረውን ሥራ ቀጥለዋል። ጌታ በዮሐንስ 14:12፥ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ የበለጠ ሥራ እንደሚያከናውኑ በተናገረው መሠረት፥ ሐዋርያቱ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ፈውስና ተአምራት ጭምር በከፍተኛ ደረጃ ሲያካሂዱ ቆይተዋል። ለመሆኑ፥ ጌታ "ከእኔ በላይ" ትሠራላችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር፥ "መቼም ከሐዋርያቱ በሁለት ዓሣና በአምስት እንጀራ አምስት ሺህ ሕዝብ አብልቶ ያጠገበ አልነበረም፤ ከዓሣ ውስጥ የቀረጥ ገንዘብ ያወጣም አልተጻፈም" ብሏል። ይኸው ሰው አሳቡን በመቀጠል፥ ጌታ የተናገረው ሐዋርያቱ በመጠንና በጥልቀት ከእርሱ የላቁትን ተአምራት እንደሚሠሩ ሳይሆን፥ ይልቁንም እነርሱ ብዙዎች እንደመሆናቸው በርከት ያሉ ተአምራት እንደሚሠሩ ነው ሲል አጠቃሏል። ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ መድረስ፥ ማገልገልም ሆነ ተአምራት ማድረግ የቻለው ይመላለስ በነበረው የገሊላ አካባቢ ነበር። ሐዋርያቱ ግን በዓለም ዙሪያ ሁሉ ቃሉን ብቻ ሳይሆን፥ ፈውሱንና ተአምራቱን ጭምር ይዘው ይዞሩ ነበር። ለዚህም ነው ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ ተአምራት እንዳዩ የጻፈላቸው (ገላትያ 3፡5)።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከፍተኛ የፈውስና የተአምራት ታሪኮች ተመዝግበው እንመለከታለን። የጴጥሮስ ጥላ እንኳ ፈውስን ያስገኘበት ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 5፡12–16 ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። ይሁንና፥ የሐዋርያት ዋንኛ ትኩረት ፈውስና ተአምራት ማድረግ ሳይሆን፥ ወንጌልን ማሰራጨት ነበር። እነዚህ ተአምራዊ ክስተቶች በአግረ–መንገድ የሚከናወኑ አስደሳች ገጽታዎች ነበሩ።

በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረገ አንድ ጸሐፊ እንዳጤነው፥ ከሐዋርያት ሥራና ከመልእክቶች ስለ ፈውስና ስለ ተአምራት የሚከተሉትን እውነቶች እንመለከታለን።[39]

- ተአምራት በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ በተደጋጋሚ ይታዩ ነበር።
- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ያደረገውን ያህል ብዙ የተለያዩ ተአምራት አድርገዋል። እነዚህም ተአምራት ፈውስ፥ ከሙታን ማስነሣት፥ ከአጋንንት ነጻ ማውጣት የመሳሰሉ ነበሩ።
- ሐዋርያትም እንደ ኢየሱስ ትኩረታቸውን ያደረጉት ቃሉን በማስተማርና በወንጌል ስርጭት ላይ እንጂ፥ ሕዝብን ጉድ ያሰኝ ተአምር በመሥራቱ ላይ አልነበረም። ተአምራትን ይመለከቱ የነበሩት እንደ አገልግሎታቸው ክፍል እንጂ፥ እንደ ዛሬዎቹ አገልጋዮች ለራሳቸው ዝናና ክብር ለማግኘት አልነበረም።
- የሐዋርያት ተአምራት ጌታ ከእነርሱ ጋር ሆኖ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ለማሳየት ያገለግሉ ነበር። የሚሠሩትና የሚያደርጉትም ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለሰዎች ለማሳየት አገልግለዋል (ገላትያ 3፡5)።
- ሐዋርያቱ ለሚያከናውኗቸው የፈውስና የተአምራት ሥራዎች ከማንም ሰው ገንዘብ አልተቀበሉም። ስምዖን ለሚፈልገው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን በማደል ገንዘብ ለማግበስበስ ፈልጎ እነ ጴጥሮስን ባነጋገረ ጊዜ፥ ጴጥሮስ በከፍተኛ ደረጃ እንደተቆጣው ተገልጾአል (የሐዋርያት ሥራ 8፡9–24)።

- ሐዋርያትም እንደ ኢየሱስ አንድ ሰው እንደሚፈወስ ከተናገሩ፥ ሰውዬው ያለምንም ቅድመ–ሁኔታ ይፈወስ ነበር። ግማሽ ፈውስ ወይም ያልተሳካ ፈውስ የሚባል ነገር በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ አልነበረም።

- በአንድ ሰው የመፈወስ ችሎታና ፈውሱን በሚቀበለው ሰው እምነት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ስለመኖሩ በግልጽ የተጠቀሰ ነገር የለም። ሐዋርያት ተአምራት ለማድረግ አስበው ተአምራቱ የሚደረግለት ሰውዬ እምነት በማጣቱ ተአምራቱ የተስተጓጎለበትም ጊዜ አልተጠቀሰም።

- ሐዋርያት ተአምራትን ለራሳቸው ጥቅም ያዋሉበት ጊዜ የለም። እንደዚሁም፥ ሐዋርያት የታመሙትን ሁሉ እንዳልፈወሷቸው ልብ ማለቱ ተገቢ ነው። ለምሳሌ፥ ከጳውሎስ ጋር ለማገልገል ከመጡት ሰዎች መካከል አፍሮዲጡ በከፍተኛ ደረጃ ታሞ ጳውሎስ ሊፈውሰው ቢፈልግም እንኳ አልቻለም ነበር (ፊልጵስዩስ 2፡27)። ለራሱም እንኳ ፈውስ ሊያመጣ አልቻለም ነበር (2ኛ ቆሮንቶስ 12፡7–10)። ስለሆነም፥ ክርስቲያኖች ሁሉ በጤንነት መኖር እንዳለባቸው የሚያመለክት ምንም ፍንጭ እንደሌለ እንመለከታለን። ክርስቲያኖችም እንደማንኛውም ሰው ምድራዊ ችግሮችን ከመጋፈጥ እንደሚያመልጡ የሚያሳይ መረጃ የለም – ይህ የሰው ልጅ ከንቱ ምኞት ብቻ ነው – የፍጹም ዓለም ምኞት።

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚታየው፥ እግዚአብሔር ተአምራትን በስፋት የሚያከናውንባቸው ሁለት ወቅቶች እንዳሉ እንረዳለን። ከነዚህም የመጀመሪያው ወንጌል ወደ አንድ አዲስ ስፍራ በሚሄድበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የእርሱ ኃይል አምላክ ከተባለው ሁሉ በላይ መሆኑን ለማሳየት ተአምራትን በብዛት ያሳያል።

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየቱን የሰነዘረው ግለሰብ እንዳመለከተው፥ ላለፉት ሰባ ዓመታት ወንጌል ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲገዝ እግዚአብሔር ብዙ ተአምራት አድርጓል። ቤተ ክርስቲያን እየተጠናከረች ስትመጣ ግን የተአምራቱ መጠን ቀንሷል። እንደ አጥኚው ግለሰብ አስተያየት፥ ይህ የሆነው እግዚአብሔር ክርስቲያኖች እምነታቸውን በተአምራት ላይ ሳይሆን በቃሉ ላይ እንዲያደርጉ ስለሚፈልግ ነው።

ሁለተኛው፥ ወንጌሉ ለብዙ ጊዜ ሲሰበክ ቆይቶ አማኞቹ መነቃቃትን አጥተው የልማድ ሃይማኖት መከተል በሚጀምሩበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሱን በመላክ የተአምራት ሥራውን ያካሂዳል። ይህንንም የሚያደርገው የዛሉትን ክርስቲያኖች ለማጠናከርና ልዩ ተሐድሶ ለማምጣት ነው።

- በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የትኛውም አገልጋይ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ጉባኤ ላይ ተገኝቶ፥ "ሁላችሁም ተፈወሳችኋል!" ያለበት ጊዜ የለም። የፈውስ ስብሰባዎችም እንኳ በሐዋርያት ዘመን የተለመዱ አልነበሩም፤ እግዚአብሔር ሲፈልግ በራሱ ተአምራዊ መንገድ ፈውስን እስኪያመጣ

ድረስ፥ እነርሱ ቃሉን በማስተማርና በወንጌል ስርጭት ይተጉ ነበር። እርሱ ሲፈውስ ደግሞ በምስጋና ይቀበሉ ነበር።

ስለሆነም፥ ከአዲስ ኪዳን የፈውስና የተአምራት ዘገባ የምንማረው እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ፈውስና ተአምራት ለማድረግ እንደሚችል ነው። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር በፈለግነው ጊዜ ሁሉ ይፈውሳል ወይም ተአምራት ይሠራል ማለት አይደለም። እርሱ የሁሉ ጌታ ስለሆነ፥ የሚሠራውም በራሱ ፈቃድ ነው።

እግዚአብሔር በብሉይና በአዲስ ኪዳን ለመፈወስ ከቻለ፥ ዛሬም የሚያግደው ነገር እንደሌለ አምናለሁ። ፈውስና ተአምራት፥ ልሳናትና ሌሎችም የጸጋ አገልግሎቶች በሐዋርያት ዘመን አብቅተዋል የሚሉ ሰዎች፥ በእኔ እምነት ከቃሉ እውነታ አፈንግጠዋል። እናም አመለካከታቸውን ከቅዱስ ቃሉ ጋር ለማስታረቅ፥ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ሥር ሆነው ሊመረምሩ ይገባል።

ይህንን ከተረዳን ዘንዳ፥ ስንታመም ወይም ሌሎች ሲታመሙ ስናይ ምን ማድረግ ይገባናል? ያዕቆብ 5፡14-15 አንዳንድ ጠቃሚ ነገሮችን ያስተላልፍልናል። በዚህ አሳብ ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች መመልከት ይቻላል።

- አንድ ክርስቲያን ሲታመም፥ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ይፈውሰው ዘንድ መጸለዩ ተገቢ ነው። እማኙ እግዚአብሔር በሽታውን የላከብኝ በኃጢአቴ ሊቀጣኝ ፈልጎ ነው የሚል እምነት ካለው፥ ከመንፈስ ቅዱስ ሥር ሆኖ ራሱን ሊመረምር ይገባል። ይህ ማለት ግን በሽታ ሁልጊዜም የኃጢአት ቅጣት ነው ማለት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ልጆቹን ለማስተማር በሽታን በመሣሪያነት ስለሚጠቀም፥ ላንተ ሊያስተምር የሚፈልገው ምን እንደሆነ በርጋታ ጠይቀው።
- ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ መድኃኒትና የሕክምና ርዳታ ተቀበል። ለመድኃኒት ቀማሚዎች ጥበብን የሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ልብ ብትል፥ በመድኃኒት መጠቀሙ ምንም ክፋት እንደሌለው ልትረዳ ትችላለህ። በመድኃኒትም ተፈወስህ በመለኮታዊ ፈውስ፥ ፈዋሽህ የእስራኤል አምላክ እንጂ መድኃኒቱ እንዳልሆነ ተረዳ። ሊፈውስህ ካልፈለገ ደግሞ የትኛውም ዓይነት መድኃኒት ሊያሽርህ አይችልም።
- በዚህ ሁሉ ፈውስ ካላገኘህ፥ 'እንፈውስሃለን!' ወደሚሉት ሰዎች ከመሄድ የያዕቆብ 5ን መመሪያ ተከትለህ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ ቤትህ ጥራ። ከዚያም እግዚአብሔርን ያሳዘንኸው ነገር እንዳለ ንስሐ በመግባት ከነርሱ ጋር ጸልይ። [በእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች ዘንድ ንስሐ መግባት 'አሉታዊ ቃል' ስለሆነ አይፈቀድም፤ እንዲያውም፥ የነ ደረጀ ከበደ ዓይነት የንስሐ መዝሙሮች በነዚህ ሰዎች በተደጋጋሚ ሲተቹ ተደምጧል።]

ሽማግሌዎቹም ዘይት ቀብተው ሊጸልዩልህ ይገባል። አንድ ጸሐፊ ለምን ዘይት እንደሚያስፈልግ ሲገልጽ፥ በጥንት ጊዜ ዘይት ከሁሉም የተሻለው

መድኃኒት እንደነበረ በማስረዳት ክርስቲያኖችም በዘይት ውስጥ የተለየ ኃይል እንዳለ ከማመን ይልቅ ለበሽታው የሚረዳውን መድኃኒት እየወሰዱ መጸለይ እንደሚኖርባቸው ተናግሯል። "ራሴን በዘይት ቀባህ" (መዝሙር 22፡5)። ይህ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ አባሎቻቸውን ዘይት ቀብተው ሲያበቁ፥ "የነካችሁ ሁሉ ይፈወሳል!" ከሚሉት የእምነት እንቅስቃሴ መሪዎች አሳብ የተለየ መሆኑን ማጤኑ ተገቢ ነው።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡9-10 እንደ ተጠቀሰው፥ ጌታ የፈውስ ስጦታ የሚሰጣቸው ሰዎች አሉ። እነዚህም ሰዎች የበሽተኛውን መፈወስ ሊናገሩ ይችላሉ። በአማርኛችን ግልጽ ባይሆንም፥ በሌሎች ቋንቋዎች ጳውሎስ በዚህ ክፍል ፈውስንና ተአምራትን የጠቀሰው ከሌሎቹ ለየት ባለ አገላለጽ ማለትም በብዙ ቁጥር ነው። ለምን ይህን አደረገ? አንዳንዶች እንደሚሉት፥ ለዚህ ምክንያቱ እነዚህ ስጦታዎች በቋሚነት ከአንድ ሰው ጋር የሚኖሩ ሳይሆኑ የመምጣትና የመሄድ ዝንባሌ ስላላትው ነው። ይህም ማለት አንድ ጊዜ ፈውስ ያገለገለ ሰው የግድ ሁልጊዜም የፈውስ መልእክት ማስተላለፍ አይኖርበትም ማለት ነው። ጌታ መልእክቱን ሲያመጣለት ያስተላልፋል፤ ጌታ የፈውሱን መልእክት ሳያመጣ ሲቀር፥ እርሱም ዝም ብሎ ይቀመጣል። እንደዚሁም፥ ጌታ ዛሬ በአበበ በኩል ስለ ከበደ ፈውስ ተናግሮ ከሆነ፥ ነገ አበበን ዝም ይለውና በከበደ ወይም በከተማ በኩል ለሌላው ሰው የፈውስ መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል።

አንድ የፈውስ አገልጋይ እንዳጫወተኝ፥ ብዙ አገልጋዮች የሚፈተኑት እዚህ ላይ ነው። አንዴ የፈውስ መልእክት ከመጣላቸው ሁልጊዜም ይህንኑ ይፈልጋሉ። በሽተኛ ባዩ ቁጥር 'ጌታ ፈውሶሃል!' ማለት ያምራቸዋል፤ እያማራቸው ቢቀር ባልከፋ - አንዳንዶ ደፍረው ያልተላኩትን ይናገሩና በዚህ ክፍል መጀመሪያ ላይ የተመለከትናቸውን ዓይነት ችግሮች ይፈጥራሉ።

ልብ ማለት ያለብን ሰኞ ዕለት ስኳር እንዲገዛ የተላከ ልጅ ማክሰኞም ይህንኑ ሥራ ላይታዘዝ እንደሚችል ነው። ምናልባትም ማክሰኞ ዕለት ቡና እንዲገዛ ሊታዘዝ ይችላል። ረቡዕ ዕለት ደግሞ ጨው እንዲገዛ ሊላክ ይችላል። እናም አንድ ወይም ሁለት ጊዜ የፈውስ ድምፅ መጥቶልኛል ብሎ እዚያው ላይ ማተኮሩ ተገቢ አይደለም። ሲልከን መላክ - ሳይልከን አርፎ መቀመጡ ተገቢ ነው። [የስኳሩንና የቡናውን ምሳሌ የነገረኝ በዚህ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ የሰጠኝ የፈውስ አገልጋይ ነው።]

ሽማግሌዎች የጸለዩለት ሰው ቅጽበታዊም ሆነ ዘገምተኛ ፈውስ ካገኘ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን መንፈሳዊ ሕይወቱን ሊጎዳ የሚችል ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስድ፥ ጌታን በትዕግሥት ሊጠብቅ ያሻል። መፈወሳችን፥ በሕመም እየማቀቅን መቆየታችን፥ ሲሆንም ወደ እርሱ መሰብሰባችን የሚወስነው የሁሉ ጌታ በሆነው በአምላካችን እንጂ በእኛ ምርጫ አይደለም።

ስለሆነም፥ ዋናው ሥጋዊ ፈውስ ማግኘታችን ወይም አለማግኘታችን ሳይሆን፥ ለዋጀን ጌታ መኖራችንና መሞታችን ነው። "በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፥ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን" (ሮሜ 14፡8)።

ከእስካሁኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንደምንረዳው፥ ፈውስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በመሆን በቤተክርስቲያን ውስጥ ግልጋሎት መስጠቱ ተገቢ ነው (1ኛቆሮ. 12፡9)። ነገር ግን በፎርሙላዎች፥ በመመሪያዎችና ደረጃዎች ተካቶ ሁልጊዜም የሚፈጸም ፈውስ–ሜታፊዝካል፥ ማጂካል... ይሆን እንደሆን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን አይችልም።

ክርስቲያኖችም ሰዎች ናቸውና ይታመማሉ። በእምነት እንደታዘዝነው እንጸልያለን። እግዚአብሔር እንደፈቀደ የሚድን ይድናል–የሚሞት ይሞታል– እንደታመመ የሚቆይም እንዲሁ። የእምነት አስተማሪዎች ባይቀበሉትም የትዕግሥት ምሳሌ የሆነው ኢዮብ ለዚህ ጥሩ ትምህርት ይሰጠናል።

አማኞች ከማንኛውም ዓይነት ሥጋዊ ሥቃይ ይላቀቃሉ የሚለው ትምህርታቸውም ከጳውሎስ ትምህርቶች ጋር ፊት ለፊት ይላተማል። ጌታ እስኪመጣ ድረስ ፍጥረቱ ሁሉ አማኞችም ጭምር "በመቃተት" እንኖራለን።

አማኞች የማይታመሙ ቢሆኑና እነርሱ እንደሚሉት አሉታዊ ቃል ሰይጣንን ማምለክ ቢሆን ኖሮ፥ እንደ ሐገን ወደ ሲኦል በመመላለስ ፈንታ ወደ "ሦስተኛው ሰማይ" የተነጠቀውና የማይነገረውን ቃል የሰማው የጌታ ሐዋርያ፥ "ጥሮፊሞስን ግን _ታሞ_ በሚሊጢን ተውሁት" (2ኛጢ.ሞ. 4፡20)፤ "ስለ ሆድህና ስለ _በሽታህ_ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ" (1ኛጢ.ሞ. 5፡23) ባላለ ነበር።

ጳውሎስ ስለ ሥጋው መውጊያ የሚናገረውም ልብ ሊባል የሚገባው ነው።

*"ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ እርሱም የሚጎሰመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው። ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ለመንሁ። እርሱም ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ" (2ኛቆሮ. 12፡7–9)።*

ሐዋርያው ጳውሎስ ሦስት ጊዜያት የሥጋው መውጊያ እንዲነሣለት ጠይቆ 'ጸጋዬ ይበቃሃል" የሚል ምላሽ ሲያገኝ፥ ኬነት ሐገን ግን ለአርባ አምስት ዓመታት ላቀረቧቸው ጥያቄዎች ሁሉ አዎንታዊ ምላሽ አግኝተዋል። በበኩሌ፥ ሐገን የጸለዩት ለጳውሎስ አምላክ ነው ለማለት አልደፍርም!

# 6

# ብልጽግና

*(Prosperity)*

*«የተቆጣጠረውን ምስባክ የሚነጥቅበት ያለ ይመስል በጥርጣሬ በር–በሩን እጮልቆ የሚያየው የብልጽግና ሰባኪ፥ አዎንታዊ ቃል በመናገርና በኢየሱስ ስም በማዘዝ አድማጮቹ የሚፈልጉትን ሁሉ ሊያገኙ እንደሚችሉ ይናገራል። በኃይል ስለሚጮህ ምን እንደሚል መስማቱ ራሱ አስቸጋሪ ነበር። ባለፈው ሳምንት ሁሉም የሚፈልጉትን ነገር በኢየሱስ ስም ጠይቀው እንዳገኙና አንዳንድ የብልጽግና ሰባኪዎችም ባጭር ጊዜ ውስጥ የመርሴድስ ባለቤቶች ለመሆን እንደበቁ በመግለጽ የአድማጮቹን ምራል ቀሰቀሰ።*

*"ወዲያውም የተመኙትን መርሴድስ ከእኛቸው የሚያስገቡ የመሰላቸው ተሰብሳቢዎች የኢየሱስን ስም እየጠሩ፥ 'በኢየሱስ ስም መርሴድስ ለእኔ! በኢየሱስ ስም!' ይሉ ገባ። ከብዙ ሥርዓት–የለሽ ጫጫታ በኋላ ሰባኪው እንደገና መናገሩን ቀጠለ። መርሴድሱን በእምነት ስለተቀበላችሁ፥ በሉ አሁን እንንዳ። 'ፒ–ፒ . . . ሬጵ . . . ሬጵ . . .' ስፍራው ባንዴ ባቡር መንገድ ሆኖ አረፈ።"*

ይህ ለምዕራፉ መግቢያነት የመረጥሁት ታሪክ፥ በቅርቡ የእምነት አስተማሪዎች ብልጽግናን በተመለከተ የሚያቀርቧቸውን ነጥቦች አንሥቼ ለአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ንግግር ሳደርግ ብዙዎቹ ገጠመኞቻውን በማስታወስ ከተረኩልኝ የቀነጨብሁት ነው። የእምነት አስተማሪዎች የምድር ላይ ብልጽግና ሁሉ የእኛው ነው የሚሉት፥ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ አሳባቸውን በማንተራስ ነው።

## *በምድር ላይ ባለሥልጣኑ እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ነው*

ፍሬድርክ ፕራይስ እንደሚሉት፥

*"እኛ የክርስቶስ አካል የሆንን እንዲሠራ ከምንፈቅድለት ውጭ እግዚአብሔር በዚህች ምድር ውስጥ ምንም ማድረግ አይችልም። ይህ አባባል፥ በጣም እንግዳና ከተለመደው የክርስትና ባህል የሚቃረን ነው፤ እንዳልሁት፥ ለብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ይህ አባባል ኑፋቄ ስለሚመስላቸው ሊይዙኝ ቢችሉ፥ ሰውነቴን አቃጥለውና በጣጥሰው ለአዞ ይሰጡኝ ነበር።"*

ሰው በምድር ላይ ባለሥልጣን የሆነበትንም ምክንያት ሲያስረዱ፥ አዳም በመውደቁ ምድርን ሰይጣን ተቆጣጥሯታል ይላሉ።

*"እንዳልሁት፥ አዳም ምድርን ለአባብና ለሰይጣን ሰጠ። በዚህም ምክንያት ከገነት ተባረረ . . . አሁን እግዚአብሔር ምንም መብት አልነበረውም። እግዚአብሔር ከምድር አጽናፍ ውጭ ነበር። በምድር ላይ ምንም ማድረግ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር ወደዚህች ምድር መግባት የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ጥሪ ሲደረግለት ብቻ ነው፥ ሃ–ሃ! ጥሪ ያስፈልገዋል። ስለዚህ፥ እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ተመለከተ – የተለያዩ ሰዎችን አየ – ኖኅንና ሌሎች ሰዎችን ተመለከተ፤ አንዳንድ መመሪያዎችን ሰጣቸው። እነርሱም ያላቸውን አደረጉ፤ በመጨረሻም ዕቅዱ ሥራ ላይ የሚውልበት ቦታ ላይ ደረሰ። አብርሃም የተባለ ሰው አየ።"*

ቻርልስ ካፕስ በበኩላቸው የእምነት ባልደረባቸውን አሳብ በማጠናከር የሚከተለውን ብለዋል።

*"በዚህ በአብርሃም ቃል ኪዳን፥ እግዚአብሔር ወደ ምድር የሚመለስበትን ሕጋዊ መብት በማዘጋጀት፥ አብርሃም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንዲችል መብት ተሰጠው . . . እስከዚያች ቀን ድረስ በተወሰነ መልኩ እግዚአብሔር በውጭ ሆኖ በር እየፈለገ ነበር። በምድር ላይ ዓመፅን በማስፋፋት ላይ ያለውን የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ እግዚአብሔር ወደ ምድር የሚገባበትን ሕጋዊ መንገድ በሰው በኩል ማግኘት ነበረበት። አብርሃም እግዚአብሔር ወደ ምድር የሚገባበት መንገድ ነበር።"*

ኬኔት ሐገን ደግሞ፥ "እኛ እዚህ በምድር ላይ አንድ ነገር እስካላደረግን ድረስ በሰማይ ምንም ዓይነት ነገር አይደረግም"[1] ብለዋል "ዎርድ ኦፍ ፌይዝ" ለተባለው መጽሔታቸው የኤፕሪል 1997 እትም ባቀረበቡት ጽሑፋቸው።

መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን አሳባቸውን እንደሚከተለው ይፈታተነዋል።

*"ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር ናት ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ (መዝ. (24):1)።* ሉዐላዊው እግዚአብሔር ምን አጥቶ ይሆን የሰውን እገዛ የሚፈልገው? የእርሱ አመጣጥ ለእኛ ለሰው ልጆች የማዳንን መንገድ ለማዘጋጀት እንጂ የምድርን በረከት ለመቋደስ እንዳልሆነ ግልጽ ነው . . .

## *ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ባለጠጎች ነበሩ*

ጆን ኢቫንዚኒ የተባሉት የእምነት አስተማሪ የኢየሱስን ሀብታምነት ለማሳየት እንደሚከተለው ይገልጻሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፥ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት፥ "ረቢ ወዴት ትኖራለህ?" ሲሉ በጠየቁት ጊዜ፥ "መጥታችሁ እዩ" ያለው ትልቅ ቤቱን ነው።

*"ኢየሱስ ድንቅ ቤት ነበረው – ከእንግዶች ጋር አብሮ ሊያድር የሚችልበት ትልቅ ቤቱን ላሳያችሁ? ወደ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ሂዱና አንብቡ፤ ቤቱን ታያላችሁ። እንግዲህ፥ የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ፥ ያ ቤት ትልቅ ነበር።*

*"ኢየሱስ ብዙ ገንዘብ ስለነበረው ነው ሌባ የሆነ ገንዘብ ያዥ የኖረው። ያ አገልግሎት በጥቂት ገንዘብ ሊካሄድ ይችላል ልትሉኝ አትችሉም። ይሁዳ ከዚያ ገንዘብ ይሰርቅ ስለነበር ያንን አገልግሎት ለማካሄድ ብዙ ገንዘብ ያስፈልግ ነበር።*

*"ዮሐንስ 19 ኢየሱስ የሚለብሳቸው ልብሶች በሞዴል አውጪ እንደተሠሩ ይነግረናል። ታዲያ ምን ትላላችሁ?....ነገሥታትና ባለጸጎች የሚለብሱት ዓይነት ልብስ ነበር... "*

ይህንኑ የፈጠራ አሳባቸውን ለማስደገፍ ሲሉ በግልጽ ቋንቋ የተቀመጠውን የወንጌል ቃል ለውጠው ያቀርቡታል።

*"ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ጉዞ ቀጥለው በመንገድ ላይ ሳሉ አንድ ሰው ኢየሱስን እኔ ወደምትሄድበት ሁሉ ልከተልህ እፈልጋለሁ አለ። ኢየሱስም ቀበሮዎች ጉድጓድ አላቸው፤ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሳርፍበት ስፍራ የለውም ሲል መለሰለት።"*

በእነ ጆን ኢቫንዚኒ ማብራሪያ መሠረት፥ ኢየሱስ ለማለት የፈለገው "ቀበሮዎች በሰማርያ ጉድጓድ አላቸው፥ ወፎችም በሰማርያ ጎጆ አላቸው፤ እኔ ዛሬ በሰማርያ የማሳልፍበት ስፍራ የለኝም" ነው። ይህም ማለት ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ማለፊያ ቤት ኖሮት በሰማርያ ማረፊያ እንዳልነበረው ለመግለጽ ነው ሲሉ ይሟገታሉ።

እከተልሃለሁ ያለው ሰውዬ መቼ "ዛሬ አብሬህ ልደር" አለ? "ልከተልህ! በቀሪው ዘመኔ ሁሉ አብሬህ ልኑር" አልነበር ያለው? ደግሞስ ለሀብታም ምን ስፍራ ይገደዋል? የትም ቢሄድ በገንዘቡ ያዛል። "ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ" እንዲሉ!

ወንጌላዊ ሽፈራው ፈይሳ በአንድ የመድረክ ውይይት ላይ ባቀረቡት መልእክት ስለዚሁ የነ ጆን ትምህርት የሚከተለውን ብለው ነበር።

*"ኑና እዩ' ሲል ትልቅ ቤቱን ሊያሳያቸው ፈልጎ ነው? የለም! ኢየሱስ ሊያሳያቸው የፈለገው ሕይወቱን፥ ኑሮውን እንጂ ቤቱን አልነበረም። ይሁዳም ቢሆን ይይዝ የነበረው ለዕለት ጉርስ የምትሆነውን ትንሽ ገንዘብ እንጂ ብዙ ሀብት አልነበረም - ልክ እንደ ቡሄ ማንቲምና ዳቦ። እለዚያ ለምን ይሆን ለአገልግሎት ስትወጡ ገንዘብ አትያዙ ብሎ የሚያስተምረው?"*

የሐዋርያትንም ባለጸጋነት ለማሳመን ጆን እንደሚከተለው ጥረት ያደርጋሉ።

*"እነዚህ ሐዋርያት ከቦታ ቦታ ይዘዋወሩ የነበረው ያለ ገንዘብ ነው ብላችሁ ልታስቡ ይገባልን? እኔና ቤተሰቤ ተቸግረን ከመኖራችን በፊት ይህን በማየቴና የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ከያዙት መስመር ተላቅቄ ወደ እግዚአብሔር አሳብ በመግባቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ወደ ሐዋርያት ሥራ 24 ተመልከቱ። ማለቴ ጳውሎስ ብዙ ገንዘብ አልነበረውም ብላችሁ ልታስቡ*

*ትችላላችሁን? ጳውሎስ ብዙ ገንዘብ ስለነበረው የመንግሥት ባለሥልጣናት ከሸማግሌው ጳውሎስ ጉቦ ለመቀበል ሲሉ ፍትህ ያዛቡበት ነበር . . ."*

ጳውሎስ ግን ስለ ራሱ፥

*"እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤ እንጠማለን፤ እንራቆታለን፤ እንሰደባለን፤ መጠለያ በማጣት እንከራተታለን። በገዛ እጃችን እየሠራን እንደከማለን፥ ሲረግሙን እንመርቃለን፥ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፥ ሲሰድቡንና ስማችንን ሲያጠፉ በጥሩ ቃል እንመልስላቸዋለን፤ እስከ አሁን ድረስ የዚህ ዓለም ውዳቂና የምድር ጥራጊ ጉድፍ ሆነናል"* ብሏል (1ኛቆሮ. 4፡11–13)።

የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ስለ ጳውሎስም ሆነ ኢየሱስ ከእነርሱ በላይ ሊናገሩ መሞከራቸው፥ ከግብዝነት የራቀ ሊሆን አይችልም። እንግዲህ፥ "ማንን እንመን? ማን ያርዳ? የቀበረ! ማን ይናገር? የነበረ!" እንዲሉ የእግዚአብሔር ቃል ያስቀመጠልንን እውነት ልናምን ይገባል – ስተን እንዳናሳስት... "ሆዳቸው አምላካቸው . . . አሳባቸው ምድራዊ . . ." (ፊልጵ. 3፡18–19) ከተባሉትም ጎራ እንዳንገባ።

## *የብልጽግና ወንጌል ኑፋቄያዊ ባህርይ*

"ሁሉም ነገር ይቻላል" በሚለው መጽሐፋቸው፥ ዴቪድ ሐረስ "የብልጽግና ዶክትሪን የካሪዝማቲክ ሪቫይቫል እጅግ ከፍተኛው አዲስ አሳብ ሆኗል፤ ይህም በመሆኑ ከዚህ ቀደም በፈውስ ላይ ይደረግ የነበረውን አጽንኦት ወደ መተካቱ ተቃርቦአል" ብለዋል። የእምነት እንቅስቃሴ በትክክል የዴቪድን አባባል ትክክለኛነት አረጋግጧል። በሕፃንነቱ በፈውስ ላይ በነበረው ከፍተኛ ትኩረት ይታወቅ የነበረው የእምነት እንቅስቃሴ፥ ዛሬ በዘመናዊ ካሪዝማቲክስ ውስጥ ከሚገኙ ዐበይት የብልጽግና ትምህርት ምንጮች አንዱ ለመሆን በቅቷል።

ምንም እንኳ የብልጽግና ዶክትሪን ጀማሪዎችና ብቸኛ የትምህርቱ አራጋቢዎች ባይሆኑም፥ የእምነት አስተማሪዎች ለብልጽግና ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። ብዙዎቹ የዚህ እንቅስቃሴ ሰለባዎች ለመሆን የበቁት የቁሳዊ ብልጽግናና የሀብት ክምችትን በተመለከተ የሚያቀርቡአቸውን ማራኪ አሳቦች በመስማታቸው ነው።

የእምነት–ፈውስ ወንጌላውያን ሁልጊዜም በብልጽግና ትምህርቶች ተለይተው ይታወቃሉ። ምክኮነል እንደሚሉት፥ እነዚህ ትምህርቶች ከሚከተሉት ሁለት ጎራዎች በአንደኛው ውስጥ ይመደባሉ። መጀመሪያ፥ በብልጽግና ላይ የራስ–ወዳድነት ትምህርት ያቀርባሉ። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት ለወንጌላውያኑ አገልግሎት ገንዘብ ለሚሰጡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስኬትና ብልጽግና እንደሚመጣ ተስፋ ይሰጣል። ራስ–ወዳድነቱ የሚታየው ለወንጌላዊው በማሰብ የሚከናወን ከመሆኑ ላይ ነው።

ይህም ማለት ሰዎች ገንዘብ ይሰጧቸው ዘንድ ከማስፈራራት እስከ ማስጠንቀቅ ይደርሳሉ። "የዘር ገንዘብ" በሚለው ትምህርታቸውም ሰዎች

ለነርሱ ገንዘብ እስካልሰጡ ድሆች ሆነው እንደሚቀሩ በመግለጽ ብዙዎችን ይዘርፋሉ። ለምሳሌ፥ ኤጽስ ቆጶስ ዴቪድ ኦዬዶፖ "የአሸናፊዎች መና" በተባለው በራሪ ወረቀት ላይ "እነዚህን ያሰላስሉ..." ከሚል ርእስ ሥር ያስቀመጧቸውን መመልከቱ ለዚህ ጥሩ መረጃ ይሆናል።[2]

- *ብዙ ነገሮች እንዳያስሩህ (እንዳያስቸግሩህ) አስራትህን ክፈል።*
- *መሪህ ሲያዝንብህ አንተን እንድታዝን ያደርግሃል።*
- *አንድ ነገር ከአንተ እስኪወጣ ድረስ ምንም ነገር አታገኝም።[3]*

አንድ ዕለት *የእምነት ሠራዊት(Faith Army)* በተባለው በዚሁ የነ ኬንት የብልጽግና ወንጌል ሥራ ላይ ከተሰማራው ወጣት ጋር ተገናኝተን እየተነጋገርን ሳለ፥ በአንደኛው የአምልኮ ዕለት ሰዎችን በማስፈራራት እንዴት ብዙ ገንዘብ ሊሰበስብ እንደቻለ ገለጸልኝ። ከአጠገቤ ቆጭ ብሎ ሲናገር የሰማሁት ጆሮ የሚያሳክክ ነገር!

*"ክርስቶስ 'ሌባው ሊሠርቅና ሊያርድ ይመጣል' እያለ የሚናገርበትን የወንጌል ክፍል ከትንቢተ ሚልክያስ ጋር አጋጭቼ ሰበክሁና... መቼም እኛ ጋ እንደናንተው ዓውደ-ንባብ ብሎ ነገር የለ... ብዙ ገንዘብ ተሰበሰበ... እናንተም ለእግእዚአብሔር አሥራት ካልከፈላችሁ ልክ ክርስቶስ እንደሚናገረው ሌባ ናችሁ ስል አስፈራራኋቸው።"*

የእንቃስቃሴው ተከታዮችም ገንዘብ ማግኘትን እንደ ትልቅ ድል ይቆጥራሉ። እነዚህ ወገኖች በደስታ የሚምነሸነሹት አንድ ሰው መቶ ወይም ሁለት መቶ ብር የሰጣቸው እንደሆነ እንጂ፥ ላልዳኑት የወንጌል ብርሃን ስለበራላቸው አይመስልም። የሚያሳዝነው ደግሞ ገንዘቡ የሚመጣው ከሌላው ሰው እንጂ ተሠርቶበት አለመሆኑ ነው። ይህም "እኛ አንለምንም!" እያሉ አዬዶፖ የሚደጋግሙት ከንቱ የቃላት ብክነት እንደሆነ ያሳየናል። "ስለ ማርያም" ባንልም ሕይወታችንን የመሠረትነው ከሰው በምንቀበለው ገንዘብ ላይ ከሆነ ለማኞች ነን። እስኪ የሚከተለውን በጋዜጣ ላይ የወጣ ምስክርነት ያጢኑ።

*"ከ4 ወር በፊት የራሴን ንግድ ፈለግኩና ለፓስተር ሚሊዮን ነገርሁት። ፓስተርም እንድከናወን ተናገረኝ። አሁን ንግዴ በጣም እየተከናወነ ነው። ትላንትና አንቴ ሉቅ መጥቶ ነበር። 200 ብር ሰጥቶኝ ሄደ (እህት ገነት)።"[4]*

ሁለተኛ፥ በብልጽግና ላይ ዓለማዊ ትምህርት ይሰጣል። የዚህ ዓይነቱ ትምህርት የመዋዕለ-ንዋይ ብልጽግናን የሚያስተዳድሩትን አጽናፈ-አቀፋዊ መንፈሳዊ ሕግጋት ለሚያውቁ ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስኬትና ብልጽግና እንደሚመጣ ቃል ይገባል። ዓለማዊ የተሰኘውም እግዚአብሔር በዓለም ላይ ባዋቀራቸው አጽናፈ-አቀፋዊ የብልጽግና መመሪያዎች ላይ ስለሚመሠረት ነው። ግልጽ ለማድረግ፥ ወደ ላይ የምንወረውረው ዕቃ በመሬት ስበት ተመልሶ ከመሬት እንደሚወድቅ ሁሉ፥ በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ ሕግጋት ይሠራሉ ማለት ነው።

ለዚህ ዓይነቱ ሂደት የኬነት ኮፕላንድ ገለጻ ሁነኛ መረጃ ሊሆን ይችላል።

*"በመኖር ሂደት ላይ ያለውን ማንኛውንም ነገር የሚያስተዳድሩ ሕግጋት እንዳሉ ልብ ልንል ይገባል። ባጋጣሚ የሚሆን ነገር የለም። የተፈጥሮ ዓለምና የመንፈሳዊ ዓለም ሕግጋት አሉ . . . መንፈሳዊ ዓለምና ሕግጋቱ ከቁሳዊ ዓለምና ከሕግጋቱ የበለጠ ኃይል እንዳላቸው መገንዘብ አለብን። ዓለምና ዓለምን የሚያስተዳድሩ ቁሳዊ ኃይላት የተፈጠሩት በእምነት ኃይል ነበር – በመንፈሳዊ ኃይል . . . የመናፍስት ዓለም ሕግጋት እንዲሠሩ የሚያደርገው ይኸው የእምነት ኃይል ነው . . . በብልጽግናም ረገድ ይኸው ደንብ እውነት ነው። በእግዚአብሔር ቃል ብልጽግናን የሚያስተዳድሩ የተወሰኑ ሕግጋት አሉ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚገኙ የስኬት ፎርሙላዎች በታዘዘው መሠረት ከግልጋሎት ላይ ሲውሉ ውጤቶችን ያስገኛሉ።"[5]*

ከእነዚህ "የስኬት ፎርሙላዎች" አንዱ በማርቆስ 10:30 ላይ የተመሠረተውና "የመቶ እጥፍ ትርፍ" በመባል የሚታወቀው የኮፕላንድ የመስጠት መመሪያ ነው። የኬነት ኮፕላንድ ሚስት የሆኑት ግሎሪያ ኮፕላንድ ይህንኑ ሕግ እንደሚከተለው ያፍታቱታል።

*"ለወንጌሉ ብለህ 1 ዶላር ብትሰጥ 100 ዶላሮች ታገኛለህ፤ 10 ስጥና 1000 ታገኛለህ፤ 1000 ብትሰጥ ደግሞ 100,000. . . አንድ ቤት ስጥና አንድ መቶ ቤቶች አግኝ። አንድ መኪና ስጥና ለዕድሜ ልክ የሚበቁ መኪኖች አግኝ። ባጭሩ፥ ማርቆስ 10:30 ቀላል ትርፍ አይደለም።"[6]*

እውነትም ቀላል ትርፍ አይደለም! በዚሁ የትርፍ መመሪያ ሰዎችን ሁሉ ለማበልጸግ መሰማራታቸውን ነው የምንመለከተው። የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች ሰዎችን ከድህነት አላቅቆ በብልጽግና ለማኖር እግዚአብሔር ልኮናል ሲሉ ራሳቸውን ይሾማሉ። በአገራችንም ሳይቀር ይህን የኑፋቄ ትምህርት የሚዘሩት ናይጄሪያዊው አዱዲፖ፥

*". . . ገንዘብ ብዙዎችን ምርኮኛ አድርጎ ጥፋት በሚመጣበት ጊዜ ሕይወትን ለማዳን እግዚአብሔር ዮሴፍን እንደላከው እኔንም ልኮኛል። ማንም በዚህ አገልግሎት ውስጥ ድሀ እንዲሆን ወይም ለሥቃይ እንዲዳረግ አልተፈቀደለትም። ሂድና የሰዎችን ዕንባ አቁም በማለት እግዚአብሔር ተናግሮኛል። በጣም በግልጽ ሰምቼዋለሁ። ከገንዘብ እጦት እንድትድኑ እግዚአብሔር ልኮኛል።"*

እርሳቸው የሰዎችን ዕንባ ለማቆም መጥቻለሁ ይበሉ እንጂ፥ ብዙዎችን እያስለቀሱ እንዳሉ የሚገልጹ ሕያዋን ምስክሮች አሉ። እዚሁ አገራችን ባለው የእምነት እንቅስቃሴ "ቤተ ክርስቲያን" የሚካፈል አንድ ወጣት ገጠመኙን እንዲህ ሲል አውግቷል።

*"ሰባኪዎቻችን ገንዘብ ይዘን እንድንመጣ ይገፋፉናል። ገንዘብ ከሰጣችሁ ባለጸጋ ትሆናላችሁ ሲሉ ይሰብኩናል። እኔም አንድ ቀን (ሥራ-አጥ ወጣት እንደመሆኑ፥) የምተኛባትን ታጣፊ አልጋ ሸጬ ለመስጠት ወሰንሁ። እናቴ ግን*

*'አብደሃል?' ስትል ተቃወመችኝ። የእግዚአብሔርን በረከት እፈልጋለሁ በሚል አሻፈረኝ ብዬ በሃያ ብር ሸጥሁና ገዝንዘቡን ወስጄ ሰጠሁ። የሚገርመው እስከ ዛሬ ጠብ ያለልኝ ነገር የለም። መሬት ላይ አንጥፌ እየተኛሁ ነኝ።"*

ማርቆስ 10፡30ን ያነበበ ሰው ግን ለአገልጋዮች የምትሰጠውን መቶ እጥፍ ታገኛለህ የሚል ተስፋ አያገኝም። እንዲያውም የአሳቡ መነሻ፥ አንድ ሀብታም ሰውዬ ጌታን ስለ መንግሥተ ሰማይ ሲጠይቅና ጌታም "ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መስቀሉንም ተሸክመህ ና፥ ተከተለኝ" ባለው ጊዜ እያዘነ ወደ ቤቱ መመለሱ ነበር።

በዚህ ጊዜ ጌታ ለብልጽግናው የአድናቆት ቃላት አላዥጎደጎደም። ይልቁንም፥ "ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል" ሲል በምድራዊው ሀብት እየተንበሸበሹ ሰማያዊውን መንግሥት መውረስ አዳጋች እንደሆነ አስጠንቅቋል።

ይህንን የሰሙት ደቀ መዛሙርት ተገርመው፥ "እንግዲያ ማን ሊድን ይችላል?" ተባባሉ። ኢየሱስም ይህ በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር እንደሚቻል ገለጸላቸው።

ቀጣዩ ተናጋሪ የሆነው ጴጥሮስ፥ "እነሆ፥ እኛ *ሁሉን ትተን* ተከተልንህ" ይለው ጀመር።

እንግዲህ ጌታ የእምነት አስተማሪዎች "የብልጽግና ፎርሙላ" የሚሉትን ቃል የተናገረው፥ ለነዚህ ሁሉን *ትተው ለተከተሉት* ነበር፥ እንጂ *በፎርሙላው ለማትረፍ* ለሚፈልጉት አልነበረም።

*"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ፥ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችንም ወንድሞችንም እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣው ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም" (ማርቆስ 10፡29–30)።*

*ክፍሉ የመቶ እጥፍ ቃል የሚገባው ትርፍ ፍለጋ ለሚሰጥ ሰው ነው? ከቶውንም አይደለም! ይህ የምንባብ ክፍል ብልጽግናን ስለ ማግኘት የሚናገር ቢሆን፥ ከጥቂት መስመሮች ከፍ ብሎ ኢየሱስ ለምን ሀብታም ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ጭንቅ እንደሚሆንበት ተናገረ? ጌታ ስለ እኔ ያለውን ነገር በስደት ምክንያት ያጣ ይካሳል ነው የሚለው።*

*የምንባብ ክፍሉ እንደ ግሎሪያ ትንታኔ ስለ መኪኖችና ስለ ዶላሮች አያወራም – ይልቁንም ስለ ቤተሰባዊ ዝምድናዎች ይናገራል። ይህም ብዙ ጊዜ እንደሚሆነው፥ ክርስቶስንና ወንጌሉን በመቀበላችን ስለሚደርስብን ስደትና በዚያ ውስጥ ግን ጌታ በራሱ መንገድ እንደሚክሰን ነው።*

ለመሆኑ፥ የምንሰጠው የበለጠ ለመቀበል ነው? አቶ ጥላሁን ኃይሌ ለሕይወት መጽሔት ቁጥር 32 ባቀረቡት ጽሑፍ መስጠት እግዚአብሔርን የበለጠ ይሰጠን ዘንድ ለመሸንገል ሳይሆን፥ ፍቅራችንን ለመግለጽ የምናበረክተው ጉዳይ እንደሆነ ገልጸዋል።

*"ስጦታችን ለጌታ ያለንን ፍቅርና አክብሮት ያመለክታል። መስጠት አምልኮም ነው። ሰው እውነተኛ የልብ መነካት ሲኖረው ገንዘቡን፥ ጊዜውን፥ እውቀቱን፥ ንብረቱን፥ ከዚህም በላይ ራሱን ለእግዚአብሔር ይሰጣል።"*

በዚሁ የመጽሔት እትም ላይ አቶ ወርቅአገኘሁ ገረመውም በመሠረታዊነት ከአቶ ጥላሁን አሳብ ጋር የሚመሳሰል ጽሑፍ አቅርበዋል።

*"2ኛ ቆሮንቶስ 8፡1-2 የውጭ ጫማ ካላረጋችሁ ጌታን አላመለካችሁም ለሚሉን፥ የሕይወታችንን ችግር ከአላፊው ልብስ ጋር ሊያያይዙት ለሚሞክሩ ለዘመነኞቹ ብልጥ የብልጽግና አስተማሪዎች ትልቅ መልእክት አለው። ክርስትና በጉድለትና በመከራ እግዚአብሔርን የመምረጥ ሰማያዊ ስጦታ እንጂ፥ እነርሱ እንደሚሉት ክርስትናችን የሚለካው በሞላን [ቁሳዊ] ነገር አይደለም።*

*"ይህ የተሳሳተ ትምህርት ድሎት ለበዛላቸው ለውጭዎቹ ምዕራባውያን ... ክርስቲያኖች ቢባል ግን ላይደንቅ ይችላል። ምናልባት በነርሱ ዘንድ ከአገሪቱ ዕድገት የተነሣ ሁሉን ማግኘት ቀላል ሊሆን ይችላል። አፍሪካ ውስጥ መጥቶ ይህንን መስበክ ግን እግዚአብሔርን የሀብታሞችና የገንዘብ ወዳዶች አጋዥ፥ የድሆችም ጠላት ማድረግ ነው። እንደነዚህ ዓይነት አስቸጋሪዎች ሲሰብኩ በቤተ ክርስቲያን ያሉትን የዋሃን ሰዎች የተለያዩ ቃላት እየተጠቀሙ ከወጣቶች ሳይቀር ለታክሲ የያዙትን ገንዘብ ይሰብስባሉ። ወጣቶቹ ያላቸውን መስጠታቸው አግባብነት ያለው ቢሆንም አስተማሪዎቹ ሲመቻቸው እንጂ፥ የእግዚአብሔር ሥራ ሲሠራበት አናይም።"*

የእምነት አራማጆች ግን ይህ ሕግ ለሚያውቁት ሁሉ በአጽናፈ-አቀፋዊ መልኩ እንደሚሠራ ከመናገር አይመለሱም። የብልጽግናን ሕግ ስለሚጠቀም አማኝ ያልሆነ ሰው ሐገን የሚከተለውን ጽፈዋል።

*"እግዚአብሔር የባረከው ኃጢአተኛ ስለሆነ አይደለም። የእግዚአብሔርን በረከት የተቀበለው እግዚአብሔርን ስላከበረ ነው። እግዚአብሔር የተወሰነ የብልጽግና ሕግ አለው! አንተም ከዚያ ሕግና ከእነዚያ ደንቦች ጋር ስትገናኝ፥ ማንም ሁን ማን እንዲሁ ይሠራልሃል። ከእግዚአብሔር ሕጎች ጋር ስትገናኝ ይሠራሉ።"*[7]

እንግዲህ፥ በኃጢአት የሚመላለሰው ሰው በብልጽግና ሕግጋት አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝ ከሆነ፥ በድህነት የሚኖረው አማኝ ክርስቶስን ቢያውቅም እግዚአብሔርን ያሳዝናል ማለት ነው።

ሜታፊዚካል ኑፋቄዎችም ስለ ብልጽግና የሚያቀርቡት ትንታኔ ከኮፕላንድ አሳብ የተለየ አይደለም። የዩኒቲ መሥራች የሆኑት ቻርልስ ፍልሞር "ብልጽግና" (Prosperity) በሚለው መጽሐፋቸው፥ "የዩኒቲ የብልጽግና ሕግ

ከጊዜ ወደ ጊዜ በእውነትነቱ እየተረጋገጠ መጥቷል። የበለጸጉት ሰዎች ሁሉ ይህንኑ ሕግ ተጠቅመዋል – ሌላ አማራጭ የለምና" ሲሉ ገልጸዋል።

ገና ኮፕላንድ የብልጽግና ሕግጋት አግኝቻለሁ ብለው ከማወጃቸው ከብዙ ዓመታት በፊት፥ ፍልሞርር ሁሉም ነገር በሕግ እንደሚተዳደርና የሀብትን መገለጽ የሚያስተዳድር ሕግ እንዳለ ጽፈው ነበር። እንደ ኮፕላንድ ሁሉ፥ ፍልሞርርም የብልጽግና ሕግ እንዲሠራ ከተፈለገ ከአንድ ሰው የሚጠበቀው መጀመሪያ መረዳት፥ ሁለተኛ ማመን፥ ሦስተኛ ለራሱ ጉድለት ከሥራ ላይ ማዋል እንደሆነ ይናገራሉ። ስለሆነም፥ የሚታፊዝካል ኑፋቄዎችም ሆኑ የእምነት ሥነ–መለኮት ብልጽግና የተመሠረተው መንፈሳዊ ሕግጋትን ለራስ ጥቅም በማዋሉ ላይ እንጂ፥ በእግዚአብሔር ሉአላዊ ልግስና ላይ በሚጣል ግላዊ እምነት ላይ እንዳልሆነ ልንመለከት እንችላለን።

የኪንየን የአዲሱ አሳብ ትምህርት ቤት ጓደኛ የነበሩት ራልፍ ዋልዶ ትራይንም ከኮፕላንድ ዓለማዊ አሳብ ጋር የሚመሳሰል መልእክት አላቸው።

*"አንድ ሰው ስለ ድህነት የሚያስብ ከሆነ፥ በድህነቱ ይኖራል። ይሁንና፥ አሁን ያለበት ሁኔታ ምንም ቢመስልም ባለማቋረጥ ስለ ብልጽግና የሚያስብ ከሆነ፥ በፍጥነትም ይሁን ዘግይተው ወደ ብልጽግና የሚያደርሱትን ኃይሎች እየተጠቀመ ነው።"*[8]

እንደ እምነት አስተማሪዎች ሁሉ ትራይንም በአጽናፈ–ዓለሙ ውስጥ ብልጽግናን የሚያስተዳድሩ "ሕግጋት" እንዳሉና እነዚህም ሕግጋት በእምነት አማካኝነት ተግባራቸውን እንደሚያከናውኑ ያስተምራሉ።

በተጨማሪም፥ ትራይንም ሆነ ኮፕላንድ እነዚህ ሕግጋት ከሥራ ላይ የሚውሉት በአዎንታዊ የአእምሮ አመለካከትና አዎንታዊ ኑዛዜ እንደሆነ ያስተምራሉ። በተለይም ኮፕላንድ ብልጽግናን ከአንድ ሰው አመለካከትና ኑዛዜ ጋር ያዛምዱታል።

*"የምትናገረውን ነገር ልታገኝ ትችላለህ! እንዲያውም፥ የምትናገረው ነገር አሁኑኑ እያገኘህ ያለኸው ነው። በድህነትና በጉስቁልና የምትኖር ከሆነ፥ የምትናገረውን ቀይር። ይህም የሚኖርህን ነገር ይቀይራል . . . ቃላትህን ተቆጣጠር። የምታደርገውን፥ የምትናገረውንና የምታስበውን ሁሉ እግዚአብሔር ከሚያደርገው፥ ከሚናገረውና ከሚያስበው ጋር አስተካክል። ይህም ሲሆን ከቃሉ የተነሣ እግዚአብሔር መሻትህን ለመሙላት <u>ይገደዳል</u> . . . በዚህ ላይ ጸንተህ ብትቆም፥ መሻትህ ይሟላል።"*[9]

ኮፕላንድ መገለጥ መጣልኝ ከማለታቸው ከብዙ ዓመታት በፊት፥ የአዲሱ አሳብ መሪ ትራይንም ብልጽግና ከአዎንታዊ አስተሳሰብ ጋር ያለውን ቁርኝት እንደሚከተለው ገልጸው ነበር።

*"ይህ የብልጽግና ሕግ ነው፦ ጉስቁልና መሳይ ነገር ሲያጋጥምህ፥ ተስፋ አትቁረጥ፤ ነገሮችን ወደፊት ተመልከት። በዚህ የአእምሮ ዝንባሌ መመራቱ ዛሬ አሳብ ብቻ ሆኖ የሚታየውን ሁኔታ አሁንም ሆነ ወደ በኋላ በቁሳዊ መልክ*

*ተግባራዊ የሚያደርጉትን ድብቅ፥ ዝምተኛና ተቋቋሚ የሌላቸውን ኃይሎች ያሠራቸዋል። አሳቦች ምትሐታዊ ኃይል ስላላቸው፥ በትክክል ከተተከሉ፥ ቁሳዊ ሁኔታዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ዘሮች ናቸው።"*[10]

በትራይን አገላለጽ፥ የብልጽግና ኑዛዜ "ምትሐታዊ ኃይል" አለው። ስለሆነም፥ "አሳብ ኃይል" እንደሆነና በተገቢው መንገድ ከተጠቀሙበትና በጥበብ ከመሩት የማይገመት የምትሐት ኃይል" እንዳለው ያምናሉ።

ይህ የምትሐታዊ ኃይል አጠቃቀም የእምነት አስተማሪዎች አንቀበልም የሚሉት ቢሆንም፥ አዎንታዊ የአእምሮ ዝንባሌ አዎንታዊ ኑዛዜ በማድረጉ የተከተሉት ሰዎች ሀብት የማግኘት ችሎታቸው ከሳይኪክና ምትሐታዊ ኃይል እንደመጣ ማመናቸውን ልብ ማለቱ ተገቢ ነው። ለምሳሌ፥ ትራይን ባለጸጋ ለመሆን ምትሐታዊ የዓይነ-ሕሊና ልምምድ (Visualization) ማድረግ እንደሚገባ አስተምረዋል። ለዚህም የዓይነ-ሕሊና ጥበብ በአእምሯቸው እንዲያስቡና በቃላቸው እንዲናገሩ ለተከታዮቻቸው ገልጸዋል።

*"ለራስህ የብልጽግናን አሳብ አቅርብ። ራስህን በበለጸገ ሁኔታ ውስጥ ተመልከት። በዝምታና በዝግታ ጸና ግን በብርታትና በድፍረት አጠናክረህ እመነው – በፍጹም እመነው። ተጠባበቀው – የመጠባበቅን ውኃ እየጠጣህ ባለማቋረጥ ጠብቀው። የምትፈልጋቸውን ነገሮች ለመሳብ ራስህን ማግኔት ማድረግ አለብህ።"*[11]

*"እምነት እንዴት በሥራ ላይ እንደሚለቀቅ" በሚል ርእስ በተተረጎመላቸው መጽሐፋቸው ውስጥ ኬነት ሐገንም ተመሳሳይ አሳብ አቅርበዋል።*

*"ጌታ አንድ ጊዜ እንዲህ አለኝ፤ 'ከአሁን በኋላ ስለ ገንዘብ አትጸልይ። በሰማ ሥልጣን አለህ። እኔ ብሩንም ወርቁንም እንስሳውንም በሺህ ተራሮች ላይ አስቀምጫለሁ። እኔ እንዳደርግልህ ከመጸለይ ይልቅ በቀላሉ እንዲህ ማለት ትችላለህ፤ ሰይጣን፥ ከገንዘቤ ላይ እጅህን አንሣ ካልህ በኋላ የሚያስፈልግህን ወደ አንተ እንዲመጣ እዘዝ።'*

*"እኔም ጌታ ሆይ፥ እንዴት ነው ይህንን የማደርገው?' ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም እንዲህ አለኝ፤ 'በዚህ ሳምንት ሁለት መቶ ዶላር ቢያስፈልግህ ሁለት መቶ ዶላር የእኔ ነህና ወደ እኔ ና ብለህ ታዘዋለህ።'*

*"በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ሞከርሁት። (አንድ ነገር በእርግጠኛነት የማታውቁት ከሆነ እግዚአብሔር ትንሽ ጥርጣሬን ይፈቅድላችኋል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በብዙ ይጠብቅባችኋል።)*

*"ከዚያም በመቀጠል፥ እንድሰብክ ወደተጋበዝሁበት ቤተ ክርስቲያን ስደርስ ለጌታ እንዲህ አልሁት፤ 'ጌታ ሆይ፥ የሚያስፈልገኝን ነገር ካገኘሁ ይህ የሰጠኸኝ መመሪያ ይሠራል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ባለፈው ጊዜ እዚህ ስሰብክ በሳምንት የሰጡኝ ስድሳ ዶላር ብቻ ነበር። እነርሱ ሊሆን ይችላል*

*ብለው ከሚገምቱት በላይ ወደ እኔ እንዲመጣ አዛለሁ።' (ራሳችሁን ሊሆን በሚችለው ነገር ብቻ አትወሰኑ፤ ለማይቻለው ነገር እመኑ።)*

*"ስለዚህ ሰይጣን ከገንዘቤ ላይ እጅህን አንሣ አልሁ። በዚህ ሳምንት አንድ መቶ ሃምሳ ዶላር እንዲመጣ እጠብቃለሁ ብዬ አወጅሁ።*

*"... መጋቢው መባ መሰብሰቢያው እንዲዞር ባደረገበት ጊዜ ሁለት መቶ አርባ ዶላር ተቀበልሁ። ከዚያን ጊዜ በኋላ ፊት ባገለገልኋቸው አብያተ ክርስቲያናት ስጋበዝ ስለ ብልጽግና ማስተማር ጀመርሁ..."*[12]

ተራ ዓይነ-ሕሊናዊ አስተሳሰብ ምንም ጉዳት ላያደርስብን ይችላል፤ እንዲያውም መልካም ማሰብና ማድረግ ለተቃና ሕይወት የሚመረጥ መሆኑ ይታሰባል። ይሁንና፥ የሚላስ የሚቀመስ ሳይኖር ራስን እንደ ከበርቴ መቁጠር፥ በህመም ደዌ እየተንገላቱ "ተፈውሻለሁ" ማለት አዎንታዊነት ወይም የዓይነ-ሕሊና ጥበብ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም - ከእውነታ ራስን ማራቅ እንጂ። በመሆኑም፥ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ለብልጽግና ፍቱን መድኃኒት አድርገው የሚያቀርቡት ዓይነት ዓይነ-ሕሊናዊ ጥበብ ከምሥራቃውያን ሃይማኖት የተወሰደ ኑፋቄ መሆኑን ብዙዎች ያምናሉ። መሠረቱ ጥንቆላ-መሳይ ዘዴ እንጂ የእግዚአብሔር እውነት አይደለም። በመሆኑም፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት ለመተካት የተደረገ ጥረት ነው ሲሉ የሚመክሩት ብዙዎች ናቸው።

ሚካኤል ቡርናም "ክርስቲያኒቲ ኢን ፓወር" ሲሉ ባሳተሙት መጽሐፋቸው፥ ይህንኑ የዓይነ-ሕሊናን ጥበብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት ጌዴዎን ፍልስጥኤማውያንን እንዳሸነፈ፥ ኢያሱ ፀሐይን እንዳቆመ፥ ኤልያስ ዝናብን እንዳስቆመና እንዳዘነበ ሁሉ ይዘረዝራሉ። እስኪ ስለ ኤልያስ ከሚናገሩት አሳብ የሚከተለውን እንመልከት።

*"በ[1ኛ ነገሥት 18] ቁጥር 41 ኤልያስ የድፍረት ኑዛዜ ቃል ተናግሯል። 'የዝናብ ውሽንፍር እጅግ ነውና' ብሏል። በዚህ ጊዜ የኃይለኛ ዝናብ ድምፅ አልነበረም። ለሦስት ዓመታት ተከል አልዘነበም ነበር! ይህ የዓይነ-ሕሊና ጥበብ የመጀመሪያው ነገር ነው። ከዚያም በድፍረት መንፈስ ቅዱስ ከሰጠው ተስፋ ጋር እምነትን ቀላቀለ።"*[13]

እንደዚህ የእምነት መሪ እምነት፥ ዝናቡ እንዲዘንብ ያደረገው የኤልያስ ዓይነ-ሕሊናዊ ጥበብ ከእምነት ጋር መቀላቀሉ ነው። እርሳቸው የጠቀሱት ክፍል ግን ይህንን አያመለክትም። ኤልያስ ያመነው እንደ ነቢይነቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውን ቃል እንጂ፥ ቡርናም እንደሚሉት የራሱን የዓይነ-ሕሊና ጥበብ አይደለም። እግዚአብሔር ሳይናገር፥ እኔ ብያለሁና (በእምነት ሰዎች ቋንቋ ከሌይም አድርጌአለሁና) ይሆናል ማለቱ ግን ራስን በሁሉን ቻይ አምላክ ስፍራ የማስቀመጥን ያህል ዕቡይነት ነው።

እንደ በሽታው ሁሉ፥ ድህም የሆነ ሰው ካለ ጥፋተኛው ራሱ ነው ይሉናል- የእምነት አስተማሪዎች።

*"እያችሁ ወዳጆቼ፥ ብዙዎቻችን የደኸየነው እግዚአብሔርን ስላስከበርነው ሳይሆን ስላላስከበርነው ነው። ነገሩ ትክክል ስለሆነ አሜን ልትሉ ትችላላችሁ።"[14] – ሐገን።*

እስኪ "ተፈጥሯዊ ሕግጋት" ስለተባለው ነገር አብረን እናስብ... በተፈጥሮ ሕግ ፀሐይ ትወጣለች፤ ማንም ሰው አማኝ ይሁን ከሃዲ በሙቀቷ ሐሜት ያደርጋል። በተፈጥሮ ሕግ ዝናብ ይዘንባል፤ የሚያምንም የማያምንም እህል ዘርቶ ያበቅላል። ቀንና ሌሊት፥ ክረምትና በጋ፥ ሞቃትና ነፋሻ አየር፥ ከዋክብትና የሰማይ ጭፍሮች ሁሉ፥ የአማኞችም የማያምኑ ሰዎችም ጥረት ሳይታከል ለፍጥረት ሁሉ ግልጋሎታቸውን ያበረክታሉ። የሚያምኑም ሆነ የማያምኑ ሰዎች ይጋባሉ፤ ይወልዳሉ... እግዚአብሔር 'ተባዙ' ስላለ! የብልጽግናም ጉዳይ እንዲሁ በተፈጥሮ ሕግጋት የሚሠራ ይሆን?

ይህ ከሆነ ታዲያ ብዙ ሰዎች ለምን በገንዘብ እጦት ይሠቃያሉ? እነርሱ ገንዘብ እንፈልግም ብለው ነው? በተፈጥሮአዊ ሕግ ገንዘብ ይገኛል ከተባለ የሚሠራውም የማይሠራውም፥ አማኙም ከሀዲውም በገንዘብ መበልጸግ ነበረበት። ለተጋቡት ሰዎች መውለድ የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑ የሚያሳድጉበት ገንዘብ ስለሌላቸው ለመውለድ የማይፈልጉ ሰዎች ሳይቀር ይወልዳሉ – የወሊድ ቁጥጥር ካላደረጉ። ብልጽግናም በተፈጥሮ ሕግ የሚገኝ ከሆነ፥ እነ ኬነት ሐገን ብቻ ሳይሆን የሬማ ተከታዮች በሙሉ መበልጸግ ነበረባቸው! ይህ ግን እውን ሆኖ አላየንም... እንግዲያው ለምን ራሳችንን እናታልላለን?

የእምነት እንቅስቃሴ መሥራች ኬነየን ብልጽግናን ከአማኙ መሠረታዊ ፍላጎት መሟላት ጋር አያይዘው የተነተኑ ሲሆን፥ የአሁኖቹ ተከታዮቻቸው ግን ብዙ ርቀው ሄደዋል። እግዚአብሔር የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ሊሰጠን ይሻል ይላሉ።

ሐገን፥ "እግዚአብሔር የሚፈልገው አማኞችን ከድህነት ለማላቀቅ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ልጆቹ ከማንም የተሻለ እንዲመገቡ፥ ከማንም የተሻለ እንዲለብሱ፥ ከማንም የተሻለ መኪና እንዲኖራቸውና በሁሉም የበላይ እንዲሆኑ ነው"[15] ሲሉ ጽፈዋል። የንጉሡ ልጆች (King's Kids) በክርስቶስ ካላቸው የክብር ስፍራ ጋር የሚመጣጠን ኑሮ ይገባቸዋል። ፍሬድ ፕራይስ እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚፈልገው የአማኙን የትራንስፖርት ችግር ማቃለል ብቻ ሳይሆን፥ ማንኛውንም ዓይነት ምቹ ኦቶሞቢል ለመስጠት ነው።

"ቀድሞ ነገር ማፊያዎች በእነዚህ ዓይነት ምርጥ መኪኖች የሚዘንጡ ከሆነ፥ የንጉሥ ልጆችማ እንዴታ? "[16] ሲሉ ይጠይቃሉ ፍሬድ። ፍሬድ ምናልባትም ደካማ አማኝ እግዚአብሔር ምርጥ መኪና ይሰጠኛል ብሎ ለማመን ስለሚቸገር፥ በቮልስዋገን ሊጀምር እንደሚችል ይናገራሉ። ከዚያ በኋላ፥ እየገዛና እየሸጠ በመሄድ፥ እግዚአብሔር ሮልስ ሮይስ እንደሚሰጠው ሊያምን ይችላል።

## *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብልጽግና*

*"እግዚአብሔር የገንዘብ ባንኬ ነው፤ ጥሩ የገንዘብ ምንጭ አለኝ።*

*ሁልጊዜም በማይጠፋ መትረፍረፍ ውስጥ ያሳርፈኛል።*

*የሚጥኑን ቀልፍ ይሰጠኛል።*

*እምነቴን በሀብት ውስጥ ያከማቻል።*

*ስለ ስሙ በብልጽግና መንገድ መራኝ።*

*በብድር ሸለቆ መካከል ብሄድ እንኳ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ከፋን አልፈራም።*

*ወርቅህና ብርህ ያድኑኛል።*

*በገንዘብ ሰብሳቢው ፊት መንገድን አዘጋጀህልኝ።*

*ቦርሳዬን በገንዘብ ሞላህልኝ፤ መጠኑ በዝቶ የተረፈ ነው።*

*መልካምነትና ሀብት በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል። ለዘላለም በእግዚአብሔር ስም ቢዝነስ እሠራለሁ።"*

የእምነት እንቅስቃሴ ምንጮች እንደሆኑ ከሚገለጹት ሜታፊዚካል ፍልስፍናዎች አንዱ ዩኒት የሚባለው ሲሆን፥ ይህ የገንዘብ ፍቅርን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማድረግ የተሞከረበት የመዝሙር 23 ክፍል የተዘጋጀው ቻርልስ ፊልሞር በተባሉት የዩኒት መሪ ነው። እግዚአብሔር በብዙ ስፍራዎች የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን ይናገራል፤ አስቀድመን የእርሱን መንግሥት ከፈለግን፥ ሁሉም እንደሚሟላልንም ይገልጻል (ማቴ. 6:33)።

"የሚያስፈልገን ምን ያህል ነው?" ጌታ በተራራው ስብከት ላይ "የሚያስፈልጋችሁ" (ማቴ. 6:8) ይላል። በኢየሱስ አገላለጽ፥ የሚያስፈልገን ጥቂት ነው። በተራራው ስብከት ውስጥ የተጠቀሱት ምግብ፥ መጠጥና ልብስ ሲሆኑ፥ ጳውሎስ ወደ ሁለት ይቀንሳቸዋል – ምግብና ልብስ (1ኛጢሞ. 6:8)። በሌላ ስፍራ፥ ኢየሱስ "የሚያስፈልገን ነገር አንድ" እንደሆነ ይናገራል (ሉቃ. 10:42)። ይህም ከኢየሱስና ከቃሉ ጋር መሆን ነው።

ምክኮንል እንዳጤኑት፥ የሚያስፈልገን ነገር ያለእርሱ ልንኖር የማንችለው መሠረታዊ ነገር ነው። የምንፈልገውና የምንመኘው ደግሞ ሌላ ነው። እግዚአብሔር በብዙ ስፍራዎች የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን ይናገራል። የእምነት አስተማሪዎች እንደሚሉት ግን በየትኛውም ስፍራ ለፍላጎታችንና ለምኞታችን ቃል አይገባልንም። እንዲያውም፥ ምኞታችንን እንድንሰቅል ያዛል (ሮሜ. 6:1–14፤ 8:12፤ ገላ. 5:16–24)።

ጳውሎስ፥ የመጀመሪያው ምእተ ዓመት "ካሪዝማቲካዊ" እንቅስቃሴ ተዋናዮች ለነበሩቱና እንደ አዲሱ የእምነት እንቅስቃሴ አባላት በብልጽግና ላይ ለሚያተኩሩት ቆሮንቶሶች የሚከተለውን ጽፎላቸዋል።

*"ለዓለም ለመላእክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና። እኛ ስለ ክርስቶስ ሞኞች ነን፤ እናንተ በክርስቶስ ልባሞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን እናንተ ግን ኃይለኞች ናችሁ፤ እናንተ የከበራችሁ ናችሁ እኛ ግን የተዋረድን ነን። እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፥ እንጠማለን፥ እንራቆታለን፥ እንጎሰማለን፥ እንከራተታለን፥ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፥ ሲሰድቡን እንመርቃለን፥ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፥ ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፥ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል" (1ኛቆሮ 4:9-13)።*

ለገላትያ ሰዎችም ሲጽፍ፥ የክርስቶስ የሆኑቱ ሥጋን ከምኞቱ ጋር እንደሰቀሉት ገልጧል (ገላ. 5:24)። ሐዋርያው ዮሐንስም በበኩሉ፥ ዓለምንና ምኞቶቿን እንዳንወድ ያስጠነቀቀን ሲሆን (1ኛዮሐ 2:15-17)፥ ጌታችንም ራሱ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ልንገዛ እንደማንችል አስተምሯል (ማቴ. 6:24)።

ይሁንና፥ የብልጽግና ሰባኪዎች ለአብርሃም በተገባለት የቃል ኪዳን በረከት ላይ በመንተራስ አግኝ ሁሉ መበልጸግ እንዳለበት ያስተምራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ ምዕራፍ 3፥ በክርስቶስ አምነው ከዳኑ በኋላ ሕግን ወደ መጠበቁ እስራት ለተመለሱት የገላትያ ሰዎች፥

*"ይህም 'አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት' ተብሎ እንደተጻፈው ነው። እንግዲህ የሚያምኑ ሁሉ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ እወቁ። እግዚአብሔር አረማውያንን በእምነት እንደሚያጸድቅ መጽሐፍ አስቀድሞ አይቶ 'ሕዝቦች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ' በማለት አስቀድሞ ከአብርሃም የምሥራቹን ቃል አብሥሮአል። ስለዚህ ያመኑ ሁሉ ከአመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ" ብሏል (ገላትያ 3:6-9)።*

ለመሆኑ፥ የተባለው በረከት የምንድን ነው? የዶላር ወይስ... ሌላ? ጳውሎስ ስለ የትኛው ዓይነት በረከት እንደሚናገር ለማወቅ የመነሻ ጥያቄውን መመልከቱ ተገቢ ነው። በቁጥር 5፥ "እግዚአብሔር *መንፈሱን የሚሰጣችሁና* በእናንተ ዘንድ ተአምራትን የሚያደርገው ሕግን በመፈጸማችሁ ነው፥ ወይስ *የምሥራቹን ቃል ሰምታችሁ* <u>*በማመናችሁ*</u> ነው?"

የአብርሃም የእምነት ምሳሌነት የተፈለገው እንግዲህ ይህንኑ ነጥብ ለማብራራት መሆኑ ግልጽ ነው። እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር የሚያምኑ የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው፥ ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ። ይህም በረከት የወርቅና የብር ሳይሆን፥ ሰማያዊ የሕይወት በረከት ነው። ጳውሎስም እግዚአብሔርን ስለዚህ በረከት ሲያመሰግን፥ "በሰማይ *መንፈሳዊ በረከትን* በመስጠት በክርስቶስ የባረከን፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶች አባት የሆነው አምላክ ይመስገን" ብሏል (ኤፌሶን 1:3)። ስለሆነም፥ ከበረከት ሁሉ የሚልቀው በረከት በክርስቶስ በኩል ያገኘነው የዘላለም ሕይወት እንጂ ከአድማስ ማዶ የማይታይ ብርና ወርቅ አይደለም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዳንዶቻችንን የሚያደናግረን በዘዳግም 28 መጽሐፍ ቅዱስ ሥጋዊ በረከት የመታዘዝ ፍሬ ሆኖ መጠቀሱ ነው። እዚህ ላይ እግዚአብሔር የተናገረው ለአይሁዶች እንጂ ለእኛ ለክርስቲያኖች እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ክርስቲያን ደግሞ የአይሁዶችን ሕይወት ሊደግም አልተጠራም። የምንኖረው ከአይሁዶች በላቀ ቃል ኪዳን በመሆኑ፥ ከጌታ ልንጠብቅ የሚገባንም ከዚሁ አኳያ ነው። እስኪ ቆም ብላችሁ አስቡ... በአይሁዶቹ ብሉይ ኪዳንና በክርስቲያኖቹ አዲስ ኪዳን መካከል የሚከተሉትን እውነታዎች መመልከት ይቻላል።

- የብሉይ ኪዳኖቹ አይሁዶች እግዚአብሔርን በታዘዙ ጊዜ ቁሳዊ በረከቶችን ይቀበሉ እንደነበር ተገልጾአል። ክርስቲያኖች ግን ኢየሱስ ክርስቶስን በመታዘዛቸው ከአካላዊ ሥቃይ እስከ ሞት ድረስ መከራን ተቀብለዋል። እስከ አሁኗ ደቂቃም ድረስ የዚህ ዓይነት ሥቃይ የሚደርስባቸው በርካታ ናቸው።

- የብሉይ ኪዳኖቹ አይሁዶች በኃጢአት ሲወድቁ የበግና የፍየል መሥዋዕት ማቅረብ ይጠበቅባቸው ነበር። ለክርስቲያኖች ግን ከእንስሳት የሚልቀው የክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ ስለፈሰሰ ወደ አይሁዶቹ ወግ አንመለስም።

- የአይሁዶች ውጊያ ሥጋዊ በመሆኑ እንደ ጎልያድ ያለ ግዙፍ ጦረኛ የነበረበትን የፍልስጥኤም ጠላት ሲዋጉ ኖረዋል። ክርስቲያኖች የሚዋጉት ግን መንፈሳዊ ውጊያ ነው። "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ" (ኤፌ. 6፡12)።

- በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ የተወሰነ ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔር አማኑኤልነቱን ገልጾአል (ዮሐ. 4፡20–24)። ይህም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ሁሉ ጋር መሆኑን የሚያስገነዝበን ነው።

- ተስፋችንም እንዲሁ የተለያየ ነው። የብሉይ ኪዳኖቹ አይሁዶች ከነዓንን የመውረስ ተስፋ የተሰጣቸው ሲሆን፥ የክርስቲያኖቹ ተስፋ ግን ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የምትወርደው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ነች (ራእይ 21)።

የብልጽግና ሰባኪዎች ከብሉይ ኪዳን ራስ አልወርድም የሚሉት እንግዲህ አዲስ ኪዳን ዓላማቸውን ለማሳካት ብዙም ስለማይረዳቸው ነው። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ መታዘዝ የበረከት ሳይሆን የመከራና የሥቃይ ምልክት ሆኖ እናገኘዋለን። ጌታችንና ሐዋርያቱ ለእግዚአብሔር በፍጹም ልባቸው ተገዝተው ቢኖሩም፥ በሀብት ሲምነሸነሹ አይታዩም – በተቃራኒው ግን የመከራ እሳት ወርዶባቸዋል! ለጌታ ሕይወታቸውን ሠውተው ተስፋቸውን በምትመጣ መንግሥት ላይ ማሳረፋቸውን ነው ቅዱሱ ቃል የሚነግረን። ለእኛም ውርሳችን ይኸው ነው – መስቀሉ – የስደት፥ የትግል፥ የመዘበት፥

የመገረፍ፥ የመሞት... ተምሳሌት! በዚያ ውስጥ ግን የመንፈስ ቅዱስ ማጽናናትና የእግዚአብሔር ቸርነት ያለበት ሕይወት! መንፈሳዊነት በብልጽግና የሚለካ ከሆነማ፥ ሙስሊም ቱጃሮችም ቁጥር አንድ መንፈሳውያን ናቸው ማለት ነው።

የሕይወታችን ዋናው ቁም-ነገር ገንዘብ ማግኘት ከሆነ፥ በአጭር ጊዜ ውስጥም ይህንኑ ማድረግ ይቻላል። ይህም "ከትልቅ ሀብት በስተጀርባ አንድ ትልቅ ኃጢአት አለ" እንደሚባለው፥ በማታለል፥ ጉቦ በመቀበል፥ በመሥረቅና ማናቸውንም ወደ ብልጽግና የሚያደርሱ ጎዳዎች ሁሉ በመጠቀም የሚፈጸም ይሆናል። እውነተኛ ክርስቲያኖች ግን ንጹሕ ኑሮ እየኖሩ፥ በማጣታቸውም ሆነ በማግኘታቸው ውስጥ አምላካቸውን ያስከብራሉ። ዘማሪው ጂም ሪብስ ይህንን በመገንዘቡ ሳይሆን አይቀርም፥ "ዓለም ከሚሰጠኝ ነገር ሁሉ ይልቅ ኢየሱስ ቢኖረኝ እመርጣለሁ... ንጉሥ ከምሆን ይልቅ እውነተኛ ብሆን እሻለሁ... " እያለ ያዜመው።

ከዚህም በተጨማሪ፥ የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን ሐዋርያው ዮሐንስ ለወዳጁ ለጋይዮስ፥ "ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ" (3ኛ ዮሐንስ 2) ሲል የጻፈውን በመጥቀስ፥ አማኝ ሙሉ ጤነኛና ሀብታም መሆን እንዳለበት ይናገራሉ። በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከፍተኛ አክብሮት የሚሰጣቸውና የበርካታ መጻሕፍት ደራሲ የሆኑት ዶክተር ጆን ስቶት ይህንን ክፍል እንደሚከተለው ያብራራሉ።

*"በላቲን ቋንቋ በሚጻፉ ደብዳቤዎች የዚህ ዓይነቱ የሰላምታ ልውውጥ የተለመደ በመሆኑ፥ የዚያን ጊዜ ሰዎች ባብዛኛው 'አንተ ደህና ከሆንህ መልካም ነው፤ እኔ ደህና ነኝ' በማለት ይጀምሩ ነበር። ምንም እንኳ ዮሐንስ የሰላምታ ልውውጡን የጀመረው በዘመኑ የደብዳቤ አጻጻፍ ብሂል ቢሆንም፥ የምኞት መግለጫው ከልቡ የመነጨ ነበር... ለክርስቲያን ወዳጆቻችን ሥጋዊና መንፈሳዊ ደኅንነት መመኘቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያለው ነው።"*

ዶክተር ጆን የብልጽግና ወንጌል አስተማሪዎች ለትምህርታቸው ከዚህ ምንባብ ብዙ ድጋፍ ሊያገኙ እንደማይችሉ ሲያስረዱም የሚከተለውን ብለዋል።

*"በቅርቡ የብልጽግና ወንጌል ማለትም የእግዚአብሔር ልጆች በተትረፈረፈ ሀብትና ጤንነት ሊንበሸበሹ ይገባል የሚል ትምህርት የጀመሩት ሰዎች ከዚህ ክፍል ብዙ ድጋፍ ሊያገኙ አይችሉም። እስኪ የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ በል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ እነዚህ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ ትምህርታቸውን የሚያሳርፉት በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእስራኤላውያን በተሰጡትና በአዲስ ኪዳን ዘመን ለማለሰብ ክርስቲያኖችም ሆነ ለክርስቲያን ማኅበረሰብ በድጋሚ ባልታዩ የብልጽግና የተስፋ ቃሎች ላይ ነው። ሁለተኛ፥ የብልጽግናው ወንጌል ላልደረሳቸው የሦስተኛው ዓለም ነዋሪዎች አይገዳቸውም። ሦስተኛ፥ አዲስ*

*ኪዳን መከራ የተቀበለው አገልጋይ ተከታዮች ዋንኛ ምልክት አድርጎ የሚያቀርበውን ሸካራ ሕይወት ወደ ጎን ትተው በብልጽግና ላይ ያተኩራሉ።"*[17]

## የብልጽግና ችግሮች

ቢያንስ በሦስት መንገዶች መስቀሉን ይቃረነዋል። አንደኛ፥ መስቀሉ የሚጠይቀውን ራስ-መካድ ይጋፋዋል። አማኙ የልቡን አሳብና ምኞት ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚያገኝ ቃል ይገባለታል። ሁለተኛ፥ የብልጽግና ዶክትሪን እግዚአብሔርን መሣሪያ ያደርገዋል። ብዙዎች በእግዚአብሔር መሣሪያነት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንጂ በእግዚአብሔር በራሱ ለመርካት አያስቡም። እግዚአብሔር ብልጽግና ያለበት ስፍራ የሚያደርስ መሣሪያ ሆኗል። ይህም ሰባኪው አልዓዛር እንደሚለው፥ ኢየሱስን ተቦጫጭቆ እንደሚጣል የስጦታ ዕቃ መጠቅለያ ማድረግ መሆኑ ነው። ሦስተኛ፥ የብልጽግና ዶክትሪን የዚህን ዓለም ሀብት የበረከት ምልክት አድርጎ ይወስዳል። በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ምልክት ነው። ዓለምን ወደ ኋላ እየዞርን እንዳንመለከት የሚያዘን የኢየሱስ ቃል ተዘንግቷል። ስለሆነም፥ በብልጽግናው ወንጌል የሚገነው ኢየሱስ መከራን የተቀበለው መሢሕ አይደለም።

እንግዲህ፥ በብልጽግና ላይ የሚኖረን አመለካከት ምን ሊሆን ይገባል? **ሚዛናዊ!** በብልጽግና ዶክትሪን ላይ ብዙ ጽሑፎችን ያቀረቡት የፔንቴኮስታል ምሁር ጎርደን ፊ ሁለት አክራሪ ጫፎችን ማስወገድ እንዳለብን ይመክራሉ። ብልጽግናን ማግለልና-ብልጽግናን ማሳደድ! እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት፥ በብልጽግና ላይ ሚዛናዊ አመለካከት ሊኖረን ይገባል።

ወንጌላዊው ቨፈራውም በዚህ አሳብ መስማማታቸውን በአንድ ስብሰባ ላይ ያቀረቡት መልእክት ያስረዳል።

*"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ብልጽግና ብዙ ተናግሯል። በሉቃስ 12፡15፥ የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት እንዳይደለ በመግለጽ፥ ከመጎምጀትና ከመስገብገብ እንድንጠበቅ አስጠንቅቆናል። ጌታ በዚህ ስፍራ ያስጠነቀቀው በገንዘብ መገልገሉን ሳይሆን መጎምጀቱን ነው። ባለጸጋ ለመሆን መመኘት፥ መጎምጀት - አደጋው ያለው እዚህ ላይ ነው። ጌታ እንደሚለው ግን መቅደም ያለበት የእግዚአብሔር መንግሥትና የእግዚአብሔር ጽድቅ ስለሆነ፥ በብልጽግና ላይ የሚያተኩሩ ሰዎች ኑሮዬ ይበቃኛል ለማለት ይቸገራሉ።"*

የሚበልጠው ሥጋዊ ብልጽግና ሳይሆን መንፈሳዊ ብልጽግና እንደሆነም በአስረጅነት ሲያስረዱ፥ የያዕቆብን ምሳሌነት ጠቅሰዋል። ምንም እንኳ ብዙ ሀብት ቢኖረውም፥ ያዕቆብ "ካልባረክኸኝ አልለቅህም!" ሲል ተማጽኗል።

ጳውሎስም በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ሰዎች ገንዘብ ወዳዶች እንደሚሆኑ ገልጾአል። በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 6 የሐሰተኛ አስተማሪዎችን ባህርይ እየተነተነ ሳለ በቁጥር 5 ላይ፥ "... እንዲህ ዓይነት ሰዎች ሃይማኖት የገንዘብ

ማግኛ ዘዴ መስሎ ይታያቸዋል" ሲል ገልጾአል (የ1980 እትም መጽሐፍ ቅዱስ)። ስለሆነም፥ "ባለጸጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ" ሲል ያስጠነቅቃል (1ኛ ጢሞቴዎስ 6:9)።

ሐዋርያው ጴጥሮስም ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ባቀረበው ሰፊ ዘገባ ውስጥ የገንዘብ ፍላጎትና ጊዜያዊ ደስታ ዓይነተኛ ባሕርያቸው እንደሆነ በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 2 ገልጾአል።

3– እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን ለገንዘብ ከመስገብገባቸው የተነሣ ራሳቸው የፈጠሩትን ታሪክ እያወሩ ይበዘብዙአችኋል... 13– የእነርሱ ደስታ ቀኑን ሙሉ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ማርካት ነው... (ከ1980 ዓ.ም እትም።)

ወደ አማርኛ ሲመለስ «ሰዎች በገጠር ልማት ውስጥ» የሚል ትርጉም በሚሰጠው መጽሐፋቸው ፒተር ባችለር አንዳንድ የብልጽግና አደጋዎችን ዘርዝረዋል።

«በልማት ውስጥ አንዱ ዓላማ ሰዎች ከጉስቁልናና ከጭንቀት በላይ እንዲኖሩ መርዳት ነው። በመሆኑም፥ ሰዎች ተስፋና ድፍረት ብሎም የአሠራር ዘዴዎችን ሲያዳብሩ የአኗኗር ደረጃቸው ወደ ላይ ማሻቀብ ይጀምራል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔርን የመተው ፈተና ያይላል።

*«ይኼ መቼም አዲስ ነገር አይደለም። ዘዳግም 8:11–18 የሚያስጠነቅቀው ሰዎች በዚህ ችግር እንዳይወድቁ ነው። 'ከበላህና ከጠገብህ በኋላ፥ መልካምም ቤት ሠርተህ ከተቀመጥህ... በኋላ ልብህ እንዳይኳደድ . . . አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ።' ቁጥር 17፥ 'በልብህ፥ ጉልበቴ የእጄም ብርታት ይህን አመጣልኝ እንዳትል' ሲል ያስጠነቅቃል።*

*"እስራኤላውያን በምድረ በዳ የሚቅበዘበዙ ድሀ ዘላኖች በነበሩበት ጊዜ፥ አንዳንድ ጊዜ ካልሆነ በቀር ለእግዚአብሔር ታማኞችና በእርሱም ላይ የሚደገፉ ሰዎች ነበሩ። በመጨረሻው ግን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ደርሰው የምድሪቱን ብልጽግና በቀመሱ ጊዜ፥ ታማኝነትን ማጉደላቸው ቅጥ አጣ።*

*"ኢየሱስ የሞኙን ሀብታም ሰው ታሪክ ከመናገሩ በፊት፥ የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት እንዳልሆነ አስረድቷል። 'አንድ ሰው ከሚያስፈልገው በላይ ቢኖረውም፥ ሀብቱ ሕይወት አይሰጠውም።'*

*"እንግዲህ፥ በሕይወታችን ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ ሊይዙ የሚገቡ ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ወደሚለው ጥያቄ መመለስ የግድ ይሆንብናል። ዘላለማዊነት ያላቸው መንፈሳዊ ነገሮች የማይታዩና በእምነት የምንቀበላቸው ናቸው፤ ቁሳዊ ሀብቶችና የነዚህም ሀብቶች አሳቦች ግን በአካባቢያችን በብዛት የምናገኛቸው ስለሆኑ፥ የምናየውን ለማግኘት እንድንሞክር ከፍተኛ ውጥረት ይታገለናል። ይህ የሕይወታችን መሪ እንዲሆን ከፈቀድን የሞኙን ሀብታም መንገድ መከተላችን ነው።"[18]*

# መጽሐፍ ቅዱስና ድህነት

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለድሆች እንደሚራራና ለሀብታሞች ግን ማስጠንቀቂያ እንደሚሰጥ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ያዘጋጀውን ሠንጠረዥ እንደሚከተለው አቅርቤአለሁ።

| ለድሆች | ለሀብታሞች |
|---|---|
| <u>የእግዚአብሔር ርኅራኄ</u> | <u>የእግዚአብሔርማስጠንቀቂያ</u> |
| . እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ነውና (ሉቃ. 6:20) | . ነገር ግን እናንተ ባለጠጎች ወዮላችሁ፥ መጽናናታችሁን ተቀብላችኋልና (ሉቃ. 6:24) |
| . የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና (ሉቃ.) 4:18 | . ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል (ማር. 10:25) |
| . አንድ ነገር ጎደለህ፤ ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መስቀሉንም ተሸከምና፥ ተከተለኝ (ማር 10:21) | . ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ (ማቴ. 6:19–21) |
| . አንዳች የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን ምን ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመስግናችሁ? አላመሰግናችሁም። (1ኛቆሮ. 11:22) | .. [ባለጠጎች] እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ፥ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፥ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለጠጎች እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው (1ኛጢ.ሞ. 6:18–19) |
| . የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ አርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን? እናንተ ግን ድሆችን | . አሁንም እናንተ ባለጠጎች፥ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ። ሀብታችሁ ተበላሽቶአል፥ ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል። ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል፥ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል፤ |

| | |
|---|---|
| *አዋረዳችሁ (ያዕ. 2፡5)* | *ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል (ያዕ. 5፡1–3)* |

ባጠቃላይ፥ የብልጽግና ዶክትሪን "ዓለም አልተገባቸውም" (ዕብ. 11፡37–38) ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያፈነገጠ፥ የራስ–ወዳድነት መንገድ መሆኑ ግልጽ ነው። የጌታችንና የሐዋርያትም ትምህርት ከዚህ ጋር የሚዛመድ አይደለም። ሠርቶ መከበሩ ያለና የሚኖር እውነት ቢሆንም፥ *በማሰብ መከበር* ግን የኬንየንና የሌሎችም ሜታፊዝካል መናፍቃን ፈጠራ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል።

ምንጊዜም ቢሆን ለገንዘብ ፍቅር የወደቀ ሰው መንፈሳዊ ሕይወቱ ጤነኛ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡6 ላይ እንደገለጸው፥ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆነው ከሁኔታዎች በላይ ልቆ ሲገኝ ነው። "ኑሮዬ ይበቃኛል" ብለን የእርካታን ቡሉኮ ካልደራረብን ምንጊዜም ሊበቃን አይችልም።

የሚያሳዝነው ደግሞ ገንዘብ ደስታ ሊሰጥ የማይችል ደካማ ሥር መሆኑ ነው። አሥር ሚሊዮን ብር ያለው ሰው 9 ሚሊዮን ብር ካለው የበለጠ ደስተኛ አይደለም። ሀብት ጊዜያዊ አሻንጉሊት ነው። ለጊዜው ያጫውተናል። የኋላ ኋላ ግን ባዶ እጃችንን እንደመጣን ባዶ እጃችንን ተመልሰን እንሄዳለን። ስለሆነም ደስ ልንሰኝ የሚገባን ከሞት ጥቁር ጥላ በስቲያ ብሩኅ የሕይወት መንግሥት እንዳለ በመረዳታችንና በክርስቶስ አማካኝነት የዚያ መንግሥት ነዋሪዎች በመሆናችን እንጂ አላፊ በሆነው ቁሳዊ ሀብት ሊሆን አይገባም። ብዙ ምሁራን ሀብታቸውን፥ ዝናቸውን፥ ትዳራቸውን... ጥለው በመድኃኒት ራሳቸውን ይገላግላሉ – ሞትን ስለፈሩት ዛሬ ነገ መጣ እያሉ ከመስጋት ራሳቸውን ገድለው ያርፋሉ። እናም ደስታ ከሀብት በላቀ መሠረት ላይ መደገፍ አለበት።

ከገንዘብ ይልቅ ልንከታተላቸው የሚገቡንን ዘላለማዊ በረከቶች ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡11–16 ገልጾአል። እነዚህም ጽድቅ–እግዚአብሔርን መምሰል–እምነት–ፍቅር–መጽናናት–ደስታ–የዋህነት ናቸው። እነዚህ ከዐለቱ ላይ ስንመሠረት የሚፈልቁ ውብ ፍሬዎች ናቸው! በመንፈስ ቅዱስ አምራችነት እየተሸለቀቁ የክርስቶስን የሕይወት ንጉሥነት የሚያውጁ ማለፊያ በረከቶች! እናም ክርስቲያን ሊያተኩር የሚገባው እዚህ ላይ ነው።

*"የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ... " (ሉቃስ 12፡15)።*

# 7

# የእምነት እንቅስቃሴ የሐገን ወይስ የኬንየን?

ምንም እንኳ ኬነት ኮፕላንድ በኦራል ሮበርትስ ዩኒቨርስቲ ውስጥ አጭር ቆይታ ቢያደርጉም፥ ሐገን መንፈሳዊ አባታቸው እንደሆኑ ይናገራሉ። የኬነት ሐገን ልጅ ኮፕላንድ ከአባታቸው ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ሲናገሩ፥

*"አንድ ጉስቁልና የተጫወተበት ተማሪ ከኦራል ሮበርትስ ዩኒቨርስቲ መጥቶ በ60ዎቹ አጋማሽ አካባቢ የአባቴን ሰሚናሮች በመከታተሉ ወደ እግዚአብሔር ቃል ተመለሰ። ተማሪው ብዙ የገንዘብ ዕዳ ቢኖርበትም፥ የአባቴን የካሴት መልእክቶች በከፍተኛ ደረጃ ፈለገ። እናም መኪናውን አስይዞ ካሴቶቹን ለመውሰድ ፈለገ። በዚያን ጊዜ አገልግሎቱን የሚያካሂደው አጎቴ ቡዲ ሐርሰን ስለነበር፥ ወጣ ብሎ አርጊ መኪናውን ተመለከተ፤ ከዚያም፥ 'ካሴቶቹን ወስደህ ተጠቀም። ገንዘቡን ስታገኝ ታመጣለህ' አለው። በመሆኑም፥ ወጣቱ ኬነት ኮፕላንድ እነዚያን ካሴቶች በአንዴ ሸምድዶ ሲያበቃ፥ ሌላ ትልቅ አገልግሎት አቆጠቆጠ"*[1] ብለዋል።

የቅርብ ጊዜ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ኮፕላንድ አሁን የሐገንን ዙፋን ወርሰው የእምነት እንቅስቃሴ መሪ ሆነዋል። ሌላው የእምነት እንቅስቃሴ ሰባኪ፥ ፍሬድርክ ፕራይስ፥ "ሐገን ከማንኛውም ሰው በላይ በሕይወቴ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል"[2] ሲሉ ተናግረዋል። እንደ ጆን ኦስቲን ዓይነት ታዋቂ የካሪዝማቲክ ተሐድሶ ሰባኪም ሳይቀር፥

*"እኔ እንደሚመስለኝ ወንድም ሐገን በእግዚአብሔር የተመረጠ በመሆኑ፥ በእምነት መልእክት ግንባር ላይ ይታያል"*[3] ብለዋል።

በሌላ በኩል፥ ዋሽንግተን የሚገኘው የኬንየን የወንጌል ኅትመት ማኅበር ፕሬዝዴንት የሆኑት ሩት ኬንየን፥ በ1948 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) የሞቱት አባታቸው ኢ.ደብልዩ. ኬንየን "የእምነት እንቅስቃሴ አባት" እንደሆኑ ይናገራሉ። አባታቸው የጻፉአቸውና የእርሳቸው የኅትመት ማኅበር ያሳተማቸው 18 መጻሕፍት በቃላትም ሆነ በአሳብ ደረጃ የዛሬዎቹ የእንቅስቃሴው ሰባኪዎች የሚጠቀሙባቸው ምንጮች ናቸው።

*"የመጀመሪያው መጽሐፉ የታተመው በ1916 ቢሆንም፥ መገለጦቹን ያገኘው ከዚያ ቀደም ብሎ ነው። የዛሬዎቹ አገልጋዮች ግን አሁን ተነሥተው እምነቱንም አሁን እንደጀመሩት ነው የሚናገሩት፤ ነገሩ ትንሽ ያስቃል። ለአንዳንድ ሰዎች ለሌሎች ክብር ሰጥቶ መክበሩ በጣም አስቸጋሪ ነው"*[4] ይላሉ።

ኬንየንን በቅርብ የሚያውቁትና አንዳንዴም አብረዋቸው ያገለገሉት ጆን ኪንግተንም የበኩላቸውን ምስክርነት ሰጥተዋል።

*"እያንዳንዱ የሐገን አሳብ የመጣበትን መጽሐፍ፥ ምዕራፍና ገጽ ልነግራችሁ ስለምችል ነገሩ ንጹሕ ስርቆት እንደሆነ ግልጽ ነው። በመሆኑም የእምነት እንቅስቃሴ አባትነት የሚገባው ለኬንየን ነው።"*[5]

ኪንግተን በመቀጠል፥

*"እንዲያውም አንድ ፔንተኮስታል አገልጋይ ጸሐፊዎችን ቀጥሮ የኬንየንን መጻሕፍት ገለብጠው በእርሱ ስም እንዲያሳትሙ አድርጓል"*[6] ብለዋል።

ሐገን በ20 ዓመታቸው "የአሴምብሊስ ኦፍ ጎድ" ሰባኪ ሆነው በተቀጠሩበት ወቅት፥ ኬንየን የ70 ዓመት አዛውንት ነበሩ። ጊዜው 1937 መሆኑ ነው። ይሁንና፥ ሐገን የኬንየንን መልእክት ከመስማቴ በፊት እንኳ የእምነት ፈውስ ትምህርት በማስተማር ላይ ነበርሁ ነው የሚሉት።

*"ሚስተር ኬንየን ወደ ጌታ የሄደው በ1948 ነው። እኔ ግን ስለ መጽሐፉ የሰማሁት በ1950 ዓ.ም. ነው። አንድ በጌታ ወንድሜ የሆነ ሰውዬ፥ የዶክተር ኬንየንን መጽሐፍ አንብበህ ታውቃለህ? ሲል ጠየቀኝ። ሰምቼውም እንደማላውቅ ገለጽሁለት። ስለ እምነት ፈውስ የምትሰብከው ልክ እንደ እርሱ ነው አለኝ። ከዚያም አንዳንድ የኬንየንን መጻሕፍት ሰጠኝ። የእምነትና ፈውስ ስብከቱ ልክ እንደ እኔው ነበር። በመሠረቱ፥ ሁለቱም ሰዎች ስለ አዲስ ልደት የሚሰብኩ ከሆነ መልእክታቸው መመሳሰል አለበት። እንደዚሁም፥ ስለ እምነትና ፈውስ – ማለቴ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እምነትና ፈውስ – የሚሰብኩ ሰዎች መልእክትም መመሳሰል አለበት። የምንገልጽባቸው ቃላት ሊለያዩ ቢችሉም፥ ነገሩ ከእግዚአብሔር ቃል ከሆነ መመሳሰሉ አይቀርም . . ."*[7]

ይህ ተገቢ ማብራሪያ ይመስላል። ሁለታችንም ከአንድ ምንጭ ስለቀዳን፥ "የምንገልጽባቸው ቃላት ሊለያዩ ቢችሉም፥ መልእክቱ አንድ ነው ብለዋል" – ሐገን። ቀጥለን እንደምንመለከተው፥ ቃላቱም ሳይቀር በቀጥታ ከኬንየን እንደተቀዳ የሚያሳየው የጽሑፍ መረጃ የሐገንን ቃል ይፈታተነዋል–ከፉኛ።

## *ሐገን የኬንየንን አሳቦች እንደሠረቁ (Plagiarism)*

ሐገን እስከ 1950 ድረስ ከኬንየን ጽሑፎች ጋር አልተዋወቅሁም ቢሉም፥ በ1949፥ "እግዚአብሔር በጸሎት ሕይወታችን የተወሰነ ይመስላል፤ ማለትም አንድ ሰው ካልጠየቀው ለሰው ልጅ ምንም እንደማያደርግ። ይህ ለምን እንደሆነ አላውቅም" የሚል ጥቅስ ያለበትን መጽሐፍ እንዳነበቡ ትዝ ይላቸዋል። ይህ ጥቅስ የተወሰደው ደግሞ "ሁለት ዓይነት እምነት" (The two kinds of faith) ከሚለው የኢ. ደብልዩ ኬንየን መጽሐፍ መሆኑን ምኮንል ያስረዳሉ። በጣእረ–ሞት ላይ ሳሉ እንደተሰጣቸው የሚናገሩት "መገለጥ" ሳይቀር ከዚህ መጽሐፍ የተወሰደ ነው።

ለምሳሌ፥ ሐገን በየካቲት 1978 ዓ.ም. ጌታ "የኢየሱስ ስም" በሚል ርእስ ሴሚናር እንዲያዘጋጁ እንደጠየቃቸው ይናገራሉ። ከዚያ በፊት ግን ኬንየን "የኢየሱስ ድንቅ ስም" በሚል ርእስ መጽሐፍ አሳትመዋል። ይህንን በተመለከተ ሐገን፥

*"በዚያን ጊዜ (1978)፥ በዚህ ድንቅ ርእሰ-ጉዳይ ላይ አንድ ስብከት አቅርቤአለሁ.... በዚህ ጉዳይ ላይ የተጻፈው አንድ ጥሩ መጽሐፍ 'የኢየሱስ ድንቅ ስም' የሚለው ነው... ይህ የመገለጥ እውቀት ነው... የእግዚአብሔር ቃል ነው'*[8] ብለዋል።

በዚህ ስፍራ ብቻ የመጽሐፉን ምንጭ እንደጠቀሱ በምክኮነል ጥናት ውስጥ ተመልክቷል። ይህንን ከማለታቸው ከሁለት ዓመታት ቀደም ብሎ በመጽሔቱ ውስጥ ይህንኑ ትምህርት አሳትመው ሲያሰራጩ ግን ትምህርቱ ከኬንየን እንደመጣ ትንፍሽ አላሉም ነበር።

በሌሎቹ በርካታ መጽሐፎቻቸውና የመጽሔት ላይ ጽሑፎቻቸውም ውስጥ፥ ሐገን የኬንየንን አሳቦችና ቃላት ምንጭ ሳይጠቅሱ እንደራሳቸው አድርገው ሲጠቀሙ ኖረዋል። ምክኮነል እንደታዘቡት፥ "ለኬኔት ሐገንና ለእምነት እንቅስቃሴ በካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ኃይል ያስገኙት ዶክትሪኖች ሁሉ የመጡት ከኢ. ደብልዩ ኬንየን ነው ማለት ማጋነን አይሆንም።" ምክኮነል፥ ኬኔት ሐገን የኬንየንን አሳቦችና ቃላት እንዴት በቀጥታ ምንጭ ሳይጠቅሱ "የራሴ ናቸው" ብለው እንደተጠቀሙባቸው ለአብነት አቅርበዋል።

| <u>ኬኔት ሐገን</u> | <u>ኢ. ደብልዩ ኬንየን</u> |
| --- | --- |
| *መዝሙር 22 ስለ ኢየሱስ ስቅለት ሥዕላዊ መግለጫ ይሰጣል - ይህንኑ ከመሰከሩት ዮሐንስ፥ ማቴዎስ ወይም ማርቆስ በበለጠ ግልጸት።* *(Christ our substitute, pp. 1, 4, 5,7)* | *መዝሙር 22 ስለ ኢየሱስ ስቅለት ሥዕላዊ መግለጫ ይሰጣል። ይህም ከዮሐንስ፥ ከማቴዎስ ወይም ከማርቆስ የበለጠ ግልጽ ነው። (What happened from the cross to the throne, pp. 44-45)* |
| *መተባበር ምንድርነው? የእኛ ከክርስቶስ ጋር ሙሉ ለሙሉ መተባበር ማለት ነው። ይህም የመተባበርን ታላቅ የአንድነት ትምህርት ይገልጥልናል። (The Resurection! What it gives us ... p.5)* | *"መተባበር ማለት ምን ማለት ነው? " ብለህ ልትጠይቅ ትችላለህ። መተባበር ማለት የእኛ በእርሱ የምትክ መሥዋዕትነት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መተባበር ማለት ነው። ይህም የመተባበርን ታላቅ የአንድነት ትምህርት ይገልጥልናል።* |

| | |
|---|---|
| | *"(Identification: Romance in redemption, p. 6, 7).* |
| *ሰው በአካል ውስጥ የሚኖር መንፈስ ነው . . . እርሱም ከእግዚአብሔር ጋር በአንድ ዓይነት ምድብ ውስጥ ነው . . . (Man of three dimension)* | *ሰው መንፈስ የሆነ ኑባሬ ነው፤ ነፍስ ኖሮት በአካል ውስጥ ይኖራል . . . ከእግዚአብሔር ጋር በአንድ ምድብ ይኖራል "(The Hidden man, p. 40).* |

(የተቀሩትን ማነጻጸሪያዎች ከመጽሐፉ መጨረሻ ላይ በእንግሊዝኛ ያገኙአቸዋል።)

ከዚህ እንደምንረዳው፥ አብዛኛው የኬነት ሐገን ትምህርት የመጣው ቀጥታ ከኬንየን ተቀድቶ ነው። ይህም በበኩሉ፥ በቀጥታ በመገለጥ መጣልኝ የተባለው ትምህርት ከሰው የተገለበጠ መሆኑን ያሳየናል።

ነቢዩ ሞሐመድ ገብርኤል በመገለጥ ያመጣልኝ "ናዚል" ነው ሲል ያወጀው፥ ቅዱስ ቁርዓን ውሎ ሲያድር ከብሉይ ኪዳንና ከአይሁድ ጽሑፎች የተገለበጠ መሆኑ እንደታወቀ ሁሉ(ለምሳሌ ሱረቱ 5፡31ን ከዘፍጥረት 4፡1–6 ጋር ያመሳክሩ)፥ የኬነትም ጉድ ገሃድ ወጥቷል። ሰዎች ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው ሲያፋጥጧቸው፥ "በስሕተት" ምንጭ ሳይጠቅሱ እንደቀረ ተናግረዋል። ይህ ግን የሚታመን አይሆንም። አንድና ሁለት ስሕተት እውነትም ስሕተት ሊባል ይችላል፤ የመጽሐፍ መሠረት የተጣለበት ጉዳይ ግን በዚህ የሚታለፍ አይሆንም።

በመሆኑም፥ የእምነት እንቅስቃሴን የጠነሰሱት የሌላውን መጽሐፍ ገልብጠው ያሳተሙት ኬነት ሐገን ሳይሆኑ፥ በኋላ እንደምንመለከተው፥ ከክርስቲያን ሳይንስና ከሜታፊዚካል ኑፋቄዎች አዛምደው ለሕዝብ ያቀረቡት ኬንየን ናቸው።

(በነገራችን ላይ የአገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 676 እንደሚደነግገው፥ የሰውን መጽሐፍ፥ ዘፈን፥ መዝሙር፥ ሥዕል፥ ባጠቃላይም የጥበብ ወይም አርት ውጤት በከፊልም ሆነ ሙሉ ለሙሉ ገልብጦ ያሳተመ ሰው ለገንዘብ ወይም ለእስራት ቅጣት እንደሚዳረግ ይታወቃል።) ይህንን ስንመለከት፥ የእምነት እንቅስቃሴ ገና ከአጀማመሩ በሌብነት ላይ እንደ ተመሠረተ እንገነዘባለን። መሠረቱ ከተበላሸ ደግሞ፥ ያው...

በቀጣዩ ምዕራፍ ይህንኑ ጠለቅ ብለን እንመለከታለን።

♣

# 8

# የእምነት እንቅስቃሴ ኑፋቄያዊ መሠረቶች

ከዚህ በላይ የተመለከትነው መረጃ፥ የእምነት እንቅስቃሴ የተጠነሰሰው በኬንየን እንጂ፥ ከእርሳቸው በገለበጡት ሐገን እንዳልሆነ አሳይቶናል። የኬንየንስ ምንጭ ምን ይመስላል? የኬንየንን፥ በዚያውም የእምነት እንቅስቃሴን ኑፋቄያዊነት አስረግጦ ለማስረዳት የፈለገው አንድ ደራሲ በሚከተሉት ጥቅሶች ነበር ምዕራፉን አሀዱ ያለው። እስኪ አስተውለው ይመልከቷቸው።

*"ለአእምሮ በምናገርበት ጊዜ፥ አንዳንድ ሰዎች ይፈራሉ። ወዲያውም ስለ ክርስቲያን ሳይንስ ያስታውሳሉ" (ኬነት ሐገን)።*

*"የሚመራመሩ ወንዶችና ሴቶች አዲስ ዓይነት ክርስትና ለማግኘት ሲሞክሩ ቆይተዋል። የሚፈልጉትም አዲስ ፍልስፍና ወይም አዲስ ሜታፊዝካል ጽንሰ-አሳብ ሳይሆን፥ በኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት የታየውን የእውነታ መገለጥ ነው።" (ኬንየን)*

*«በአንድ ወቅት የኢ.ደብሊዩ. ኬንየን ዕውር ተከታይ ነበርሁ... አሁን ግን ጥቂት ጊዜና ግንዛቤ ካገኘሁ በኋላ ኬንየን ከክርስቲያን ሳይንስ ብዙ አሳቦችን 'እንዳጠመቀ' ልረዳ ችያለሁ። ይህንንም በማድረጉ 'ፔንተኮስታል ክርስቲያን ሳይንስ' የሚመስል ነገር ምንጭ ለመሆን በቅቷል - ሰውዬው ራሱ ፔንተኮስታል ባይሆንም!» (ጆን ከኒንግሃም)*

የዚሁ ደራሲ ጥናታዊ ጽሑፍ፥ "ከዚህ በላይ የተመለከቱት ጥቅሶች የኬንየን ትምህርት ከኑፋቄያዊ ምንጭ እንዳቆጠቆጠ ይጠቁማል" ሲል ማብራራቱን ይቀጥላል። ይህም ኑፋቄ በተለይም ክርስቲያን ሳይንስ የተሰኘው ነው። ሐገንም ራሳቸው የሚሰብኩባቸው ጉባኤዎች ትምህርቱ ከክርስቲያን ሳይንስ እንደመነጨ በመጠራጠር ከስጋት ላይ እንደወደቁ ገልጸዋል። የፍርሃታቸውን እውነተኛነት ከጥቂት ገጾች በኋላ እናብራራለን። ከዚያ በፊት ግን የእምነት ሥነ-መለኮትን በተመለከተ ጥቂት ነጥቦች እናነሣለን።

### *የእምነት ሥነ-መለኮት አዲስ መገለጥ ወይስ ኑፋቄ?*

'ኑፋቄ' የሚለውን አሳብ በተመለከተ፥ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ፍችዎች ሰጥተዋል። በመሆኑም፥ አንዳንዶች "ከመሠረታዊ የክርስትና እምነት

ያፈነገጠ ሃይማኖታዊ ተቋም ነው" ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ "አስመሳይ ክርስትና" በሚል አጠር ያለ ስያሜ ይገልጹታል። በበኩሌ ግን ስለ "ብልጽግና" በተነጋገርንበት ምዕራፍ ማጠቃለያ አካባቢ ከሁለተኛ ጴጥሮስ ውስጥ የተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የኑፋቄን ምንነት በግልጽ የሚያስረዳ ይመስለኛል።

*"ነገር ግን በቀድሞ ዘመን በሕዝቡ መካከል ሐሰተኛ ነቢያት እንደነበሩ፥ እንዲሁም በእናንተ መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይኖራሉ፤ እነርሱ ጥፋት የሚያስከትል ሐሰተኛ ትምህርት በስውር ያስገባሉ፤ የዋጃቸውንም ጌታ እስከመካድ ደርሰው በፍጥነት ጥፋት ይመጣባቸዋል፤ በዚህ ዓይነት ብዙዎች የእነርሱን አሳፋሪ መንገድ ይከተላሉ፤ ከእነርሱም አድራጎት የተነሣ የእውነት መንገድ ይሰደባል። እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን ለገንዘብ ከመስገብገባቸው የተነሣ ራሳቸው የፈጠሩትን ታሪክ እያወሩ ይበዘብዙአችኋል። ከብዙ ጊዜ በፊት ፲ምሮ ፍርድ ተዘጋጅቶላቸዋል፤ ጥፋትም ነቅቶ ይጠብቃቸዋል።*

*"... እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን ደፋሮችና ትዕቢተኞች ስለሆኑ፥ የሰማይ ሥልጣናትን እንኳ ሲሳደቡ አይፈሩም... እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን... ለማስተዋል ያቃታቸውን ነገር ይሳደባሉ፤ እነርሱ ለመያዝና ለመጥፋት እንደተወለዱ፥ በተፈጥሮ ስሜት [በደመነፍስ] እንደሚኖሩ፥ አእምሮ እንደሌላቸው እንስሳት ናቸው፤ እንስሳት እንደሚጠፉ እነርሱም ይጠፋሉ። የዓመፀኝነታቸው ዋጋ የሆነውን ቅጣት ይቀበላሉ፤ የእነርሱ ደስታ ቀኑን ሙሉ ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ማርካት ነው፤ አታላይ በሆነ ሥጋዊ ፍላጎታቸው ዘወትር የሚደሰቱ ሆነው ሳሉ፥ ከእናንተ ጋር በፍቅር ግብዣ ላይ በመገኘታቸው አስነዋሪዎችና አሳፋሪዎች ናቸው። እነርሱ የቀናውን መንገድ ትተዋል። ለክፉ ሥራው ዋጋ የሆነውን ገንዘብ የወደደውን የቢዖርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከትለው ተሳስተዋል...*

*"እነዚህ ሰዎች ውኃ እንደሌለባቸው ምንጮች ናቸው፤ በዓውሎ ነፋስ እንደሚወሰዱ ደመናዎች ናቸው፤ ድቅድቅ ጨለማም ይጠብቃቸዋል... "*

ቃለ እግዚአብሔር ሐሰተኛ አስተማሪዎችን የሚመለከተው እንዲህ ባለ ሰቅጣጭ መልኩ ነው። በየጊዜው የሰሙዋቸውን "የይምሰል–መገለጦች" እያመጡ ለምእመኖቻቸው "አዲስ እውነት" ያስጨበጡ ለሚመስላቸው ሰባኪያንና አስተማሪዎች ሁሉ ይህ ታላቅ ማስጠንቀቂያ ነው። መሳት የሚጀምረው ከዚህ ነውና!

ከላይ የቀረበው የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት እንደሚያስገነዝበን፥ በምድር ላይ እውነተኛ አማኞች እስካሉ ድረስ የሐሰት አስተማሪዎች ይኖራሉ። ይህም ብርሃን–ከጨለማ፥ ቀን–ከሌት፥ ክፋት–ከበጎነት... ጋር እየተቃረነ እንደሚኖርበት የሕይወት ዘይቤ ዓይነት ነው። በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የመጣውን እውነተኛ ቃል ሲናገር፥ በውሸት ቃላት ሕዝቡን የሚያጽናኑ ነቢያት ነበሩ። በአዲስ ኪዳንም "መጻን በመድኃኒተ ዓለም ላይ

በሚጣል እምነት ነው" ተብሎ ሲሰበክ፥ "የሙሴን ሕግ ካልጠበቃችሁ አትድኑም!" ሲሉ ውዝግብ የፈጠሩ ሐሰተኞች ነበሩ።

ከዚያ ወዲህም እነ አርዮስ (የይሆዋ ምስክሮች አባት)፥ ጆሴፍ ስሚዝ (የሞርሞን መሥራች) እና ሌሎችም እየተነሡ ቤተ ክርስቲያንን ማወካቸው አልቀረም። ወደፊትም ምጽአት እስኪዘከር ድረስ የሐሰተኞች መራኮት እንደሚቀጥል ተረድቶ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራስን ማዘጋጀቱ ወሳኝ ነው።

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው የኑፋቄ አስተማሪዎች <u>ለገንዘብ ሲሉ</u> የዋጃቸውን ጌታ መካዳቸው ነው። "ለገንዘብ ከመስገብገባቸው የተነሣ ራሳቸው <u>የፈጠሩትን ታሪክ እያወሩ</u> ይበዘብዙአችኋል።" ይህ በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ አሳዛኝ ክስተት ነው። ራሳቸው የፈጠሩትን ታሪክ እንደ ድንቅ መገለጥ እያጋነኑ በማውራት የምእመኖቻቸውን ቀልብ ይገዛሉ። ቀጣዩ እርምጃ እንግዲህ የስግብግብነት ዓላማቸውን ከዳር ማድረስ ይሆናል።

ወደ በኋላ እንደምንመለከተው፥ ኬነት ሐገን ኢየሱስ ወደ መኝታ ክፍላቸው ገብቶ እንዳነጋገራቸው፥ እርሳቸውም 5 ጫማ ቁመትና 180 ፓወንድ ክብደት እንዳለው መመልከታቸውን ሲተርኩ ዓላማቸው ምን ነበር? እሳቸው ብቻ አይደሉም። አዱዴፖም ጌታ በራእይ እንደተናገራቸው የሚተርክ ወሬ ፈጥረው እስከ አገራችን ድረስ በመስፋፋት ላይ መሆናቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል። እውነት እግዚአብሔር ተናግሮአቸዋል ወይስ ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደሚለው የፈጠራ ታሪክ እያወሩ ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ናቸው?

ሐዋርያው ጴጥሮስ እነዚህ ሐሰተኞች "ደፋሮችና ትዕቢተኞች ስለሆኑ፥ የሰማይን ሥልጣናት እንኳ ሲሳደቡ አይፈሩም" ይለናል። ይህ ከሌሎች ኑፋቄዎች ሁሉ በላይ በእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ላይ የሚታይ እውነት ነው። ከእነርሱ ጋር የመነጋገር ወይም ከሌላ ሰው ጋር ሲነጋገሩ የማየት ዕድል የገጠመው ሰው ካለ ምን ያህል ትዕቢተኞች እንደሆኑ ሊረዳ ይችላል። ከናይጀሪያውያኑ የሰሙአቸውን አንዳንድ የእንግሊዝኛ ስብርባሪዎች እየቀላቀሉና ማስቲካቸውን እያንጣጡ ሲንጠራሩ፥ ከሰብአዊነት መንደር ርቀው በመላእክት ደሴት የሚዝናኑ አማልክት ይመስላሉ። ለነዚህ ወገኖች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም ሆኑ ምእመናን ከትንኝ ያንሱባቸዋል።

እንደ እንስሳት በደመ−ነፍስ መነዳታቸውና ለጊዜያዊ ደስታ ሲሉ ዘላቂውን እውነት መጣላቸውም በትክክል የሚታይ እውነት ነው። በእነርሱ ግንዛቤ፥ ሕይወት ዛሬና ዛሬ ብቻ ናት። በዘላለማዊ መርሆዎች እየተራመዱ ሥቃይን ከመታገሥ ይልቅ የዛሬን 'ደስታ' ለመቀዳጀት ይጥራሉ። ይህም ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ "ውኃ እንደሌለባቸው ምንጮች... በዓውሎ ነፋስ እንደሚወሰዱ ደመናዎች... ድቅድቅ ጨለማ እንደሚጠብቃቸው ተከናኞች... " እያለ ከጠቃቀሳቸው ሐሰተኞች ጋር አነጻኝቶአቸዋል።

ብዙ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮች የሐገንን ትምህርት ሲጠቀሙ መቆየታቸው ይታወቃል። በየቤተ ክርስቲያኑ 'የንጉሥ ልጅ ነኝ፤ ተፈውሻለሁ....' ዓይነት አባባሎች ይደመጣሉ። ሰዎች ለበሽተኞች ከጸለዩ በኋላ፥ ጌታ ያንን ወንድም ወደ ራሱ ይወስድ እንደሆነ ሳይጠረጥሩ፥ 'ተፈውሰሃል፤ መድኃኒትህን ጣል' ይሉታል። ጌታ በቀጣዩ ዕለት እንደ ፈቃዱ ሲወስደው "እምነት ጎድሎት ነው" ሲሉ ያሙታል።

አንዳንዶች ለዚህ አጓጉል ሕይወት የሚዳረጉት በከንቱ 'የዩቶፒያ' ምኞት ነው – እንደ ኮሚኒስቶች ምድርን ገነት ካላደረግን በሚል ምኞት! የኬንየንም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አልነበረም።

የእምነት እንቅስቃሴ መሥራች የሆኑት ኬንየን፥ ወደዚሁ ኑፋቄ የገቡት "ሆን ብለው" ነው ማለት ያስቸግራል። በመጽሐፋቸው ውስጥ እንዳመለከቱት፥ በዘመናቸው የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን አሠራር ባለመውደዳቸው፥ "አዲስ ዓይነት ክርስትና" አመጣለሁ ብለው ነበር የተነሡት። ይህ አንጓዲህ፥ እኛም የቤተ ክርስቲያንን ድካምና ማሽቆልቆል አያየን እንደምናዝንና ለእድገቷ የሚበጀውን ሁሉ ለማድረግ እንደምንጥር ማለት ነው። አሳባቸው ግሩም ሆኖ ሳለ መፍትሔ ፍለጋ የሄዱት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ሳይሆን ወደሚያውቁት ሜታፊዚክስ ዘንድ ሆነ። ይህም የገዛ ወዳጃቸው ጆን ኬንግተን "ፔንተኮስታል ክርስቲያን ሳይንስ" ሲሉ የሰየሙትን ኑፋቄ እንዲፈጥሩ አድርጓቸዋል።

ለመሆኑ፥ "ኬንየን የሰበኩት አዲስ መገለጥ ይሆን?" ለሚለው ጥያቄ፥ ዶክተር ምክኮኔል የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

*"በመጀመሪያ ደረጃ፥ የኬንየን ፍልስፍና አዲስ ዓይነት ሜታፊዝክስም ሊባል አይችልም። ኬንየን ያስተማረው አዲስ አሳብና ክርስቲያን ሳይንስ ለአያሌ አሥርተ-ዓመታት ሲያስተምሩ የኖሩትን የፈውስ፥ የአዎንታዊ ኑዛዜና የብልጽግና ዶክትሪኖች ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ሰላለቀ ገና አዲስ መገለጥ ይመጣል ብዬ አልጠብቅም" (A Different Gospel, p.20)።*

የኬንየንና የሐገንን መገለጥ አዲስ አለመሆኑን ስንመለከት፥ በአገራችንም "ተገለጠልን" እያሉ ከየቤተ ክርስቲያናቸው አንድ እፍኝ ሰው ይዘው የሚዋከቡትን ሰዎች ጉዳይ የምንመለከተው በአንክሮ ይሆናል። በዘመናችን "ተገለጠልን" እያሉ የተነሡ ብዙ ሰዎች ለጥፋት ይጣደፋሉ! እንደ እኔ እንደ እኔ ዝግ ብለው የመገለጣቸውን ምንጭ ቢመረምሩና ለመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ቢገዙ መልካም ነው፤ ቃሉ እንደሚል–"ጥፋታቸው አያንቀላፋምና!"

የሚገርመው ደግሞ የእነ ሐገንን መጽሐፍ አንብበው ሲያበቁ መገለጥ እንደመጣላቸው የሚናገሩ ሰዎች መበራከታቸው ነው። እግዚአብሔር አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንዲከፍቱ እውነተኛ ምሪት ከሰጣቸው፥ ቀደም ሲል

ያመልኩ ከነበሩባት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን ጋር ተባብረው ራእያቸውን ከዳር እንዳያደርሱ ምን አቀባቸው? ዓላማቸው የክርስቶስን የማዳን ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ ማዳረስ ከሆነ፥ ይህ ሁሉ የመገለጥና የልዕለ–ተፈጥሮአዊ ገጠመኞች ጋጋታ በፈጠራ ታሪክ እየታጀበ መቅረቡ ለምን ይሆን?

## የኬንየን ወንጌል

ኬንየን "መገለጥ" ሲሉ ይጠሩ በነበረው ወንጌላቸው አማካኝነት በዓለም ላይ ለሚታዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ሁሉ መፍትሔ እንደሚያመጡ ተናግረው ነበር። ከዚህም በላይ "የመገለጥ እውቀት" ትምህርታቸው በአጋንንትም ሆነ በስሜት እውቀት ያልታሰሩ ምጡቅ ሰዎች (supermen) እንደሚያስገኝም ገልጸዋል።

*"እነዚህ እውነቶች ሕይወታችንን ሲቆጣጠሩ፥ መንፈሳዊ ምጡቅ ሰዎች፥ የአጋንንትና የበሽታ ጌቶች ያደርጉናል። ይህም የዝለትና የውድቀት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ሁሉም ነገር የእኛ ስለሆነ፥ ለእምነት የሚደረግ ትግል አይኖርም። እርሱም በውስጣችን ስለሚሆን፥ ለኃይል የሚቀርብ ጸሎት አይኖርም... በእነዚህ ድንቅ እውነታዎች ብድግ ብለን ሰፍራችንን እንይዛለን። ስንወጣም በእግዚአብሔር እንደተሞሉ ምጡቅ ሰዎች እንኖራለን።"[1]*

ወደ በኋላ እንደምንመለከተው፥ ይህ የምጡቅ ሰብነት ዶክትሪን የኒው ኤጅም ቁልፍ ግንዛቤ ነው።

## ኬንየንና ፔንተኮስታል እንቅስቃሴ

ላይ ላዩን ስንመለከት፥ የእማኞች "ምጡቅ ሰብነት" እና በሁሉም ላይ የበላይነትን መጎናጸፍ የሚያስረዳው የኬንየን ዶክትሪን ደንበኛው ፔንተኮስታሊዝም እንደሆነ ልናስብ እንችላለን። በተለይም ኬንየን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በፔንተኮስታል የፈውስ አገልጋዮች ላይ ያስከተሉትን ተጽዕኖ በማስመልከት የጻፉአቸውን አሳቦች ያገናዘብን እንደሆን ኬንየን ፔንተኮስታል ናቸው ማለቱ የሚቀል ይሆናል። ይሁንና፥ ኬንየን የፔንተኮስታል ሰባኪ እንደሆኑ የእምነት እንቅስቃሴዎች በስፋት ከሚናገሩት በተቃራኒ፥ የገዛ ልጃቸው ኬንየን በልሳን ተናግረው እንደማያውቁና ፔንተኮስታል እንቅስቃሴ ላይ የጥላቻ አመለካከት እንደነበራቸው መስክረዋል።

*"የፔንተኮስታል እንቅስቃሴ የሚባለው ነገር... ለብዙዎች በረከት ሆኗል! ይሁንና፥ ለሦስት ዓመታት በጥንቃቄ ካጠናሁ በኋላ፥ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ተረድቻለሁ።"[2]*

ኬንየን ወደ በኋላ የጻፉአቸው የፈውስ ጽሑፎች በፔንተኮስታሎቹ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኙም፥ መቼም ቢሆን የፔንተኮስታል የታሪክ ዘጋቢዎች

አጨብጭበው አልተቀበሉአቸውም። ኬንየን ከሕይወታቸው ማብቂያ አካባቢም ሁለት የፔንተኮስታል ዓይነተኛ ዶክትሪኖችን ማለትም የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ሁለተኛ የጸጋ ተግባር (Subsequence) እና የልሳንን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መረጃነት (Initial evidence) ተቃውመዋል።

*"መጽሐፍ ቅዱስ ልሳናት በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችንን እንደሚያረጋግጡ አለመግለጹ ብቻ ሳይሆን ልሳናትን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መረጃ ማድረግ እግዚአብሔር ከአዲስ ፍጥረት ጋር የሚያከናውነውን ተግባር ሕግ የሚቃረን ነው"*[3] *ብለዋል።*

ኬነት ሐገንም ተመሳሳይ አመለካከት አላቸው። "How You Can Be Led By The Spirit of God" ሲሉ በጻፉትና አይሸሹም መኮንን «የመንፈስ ቅዱስ ምሪት» በሚል ርእስ በአማርኛ ተርጉመው ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለው አሳብ ሰፍሮአል።

*"አንዳንዶች ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን የማይናገሩ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ እንደሌለባቸው አድርገው ይናገራሉ። ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም። ግማሽ ብርጭቆ ውኃ ብጠጣ ጥሜን ላረካ ይችላል። ይሁን እንጂ ጥቂት ውኃ በውስጤ እንዳለ ግልጽ ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ ከተወለደ በእርሱ ውስጥ የሚኖር የእግዚአብሔር መንፈስ አለ ማለት ነው። ስለዚህ ምሪት ሲያስፈልጋቸው እርሱን ሊጠይቁት ይገባል።"*[?] (ገጽ 22)

ሴት ልጃቸው እንደሚሉት፥ ኬንየን በስብሰባዎቻቸው ላይ የጸጋ ስጦታዎችን እስከዚህም አያደፋፍሩም ነበር። እንደ ኬነት ሐገንም ትንቢት እንደመጣላቸው ወይም ኢየሱስን እንዳዩ አልተናገሩም። ስለ መለኮታዊ ፈውስ የተናገሩትና ያደረጉትም ሁሉ ፔንተኮስታል ያልሆነ ሰው በሚያከናውንበት መልኩ ነበር። በአሜሪካ ከፔንተኮስታሎቹ ቀደም ብሎ ስለ መለኮታዊ ፈውስ ማስተማርና መተግበር የጀመሩት ኬንየን፥ የፔንተኮስታሎቹ የፈውስ ትምህርት ይበልጥ "በስሜት እውቀት" ላይ ያተኮረ እንደሆነ በመግለጽ ተቃውመው ነበር።

## ኬንየንና ሜታፊዝካል ኑፋቄዎች

የኬንየን የፈውስ ሥነ-መለኮት ከፔንተኮስታሎቹ ጋር ካለመስማማቱም በላይ፥ ሐገን እንደሚሉት በቀጥታ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ አልነበረም። ይልቁንም፥ ኬንየን የሚፈረጁት "ሜታፊዚክስ" ተብሎ በሚጠራውና እንደ ክርስቲያን ሳይንስ፥ አዲስ አሳብ፥ አንድነት የክርስትና ትምህርት ቤት (Unity school of christianity)፥ የአእምሮ ሳይንስ ያሉትን ባጠቃለለው መለኮታዊ ፈውስ ውስጥ ነው። (ስለነዚህ ጽንሰ-አሳቦች የዚህን መጽሐፍ የመጨረሻ ገጾች ይመልከቱ።) ኬንየን የእምነት እንቅስቃሴ ትምህርታቸውን

*"በዚያን ጊዜ ግራ ያጋቡኝ ከነበሩት ነገሮች መካከል አንዱ በእርሱ [በኬንየን] እና በክርስቲያን ሳይንስ ትምህርቶች መካከል የነበረው መመሳሰል ነበር። እናም ስለዚሁ መመሳሰል እንነጋገር ነበር። እርሱም ይህንኑ እውነታ ተቀበለው። በክርስቲያን ሳይንስ ውስጥ የሚጎድለው ነገር የኢየሱስ ደም ብቻ ነው ሲል እንደመለሰልኝም ትዝ ይለኛል። ኬንየን የክርስቲያን ሳይንስ ጽንሰ-አሳቦችን ብቻ ሳይሆን የአመሠራረቱንም ዝርዝር ጉዳዮች ያውቅ ነበር። ስለ ክርስቲያን ሳይንስና የሄግሊያን አስተሳሰብ ፍልስፍናዊ ሥሮች ወይም በውቅያኖስ ላይ ስትጓዝ የሜሪ ቤከር ኤዲን ሕይወት ስለለወጠው የሕግ ባለሙያ ሲናገር እሰማው ነበር። እናም የፍልስፍናውን ውኃ ከዚሁ የውኃ ጉድጓድ እንደጨለፈ ገልጾልኛል።"[4]*

ሌላውና ከኬንየን ጋር በርካታ ጊዜያቸውን ያሳለፉት ኤርን ቦክስተር፥ "ያለ ጥርጥር ሜሪ ቤከር ኤዲ በኬንየን ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደሩ" ይናገራሉ።

*"ይህን ያልሁበት ዋንኛው ምክንያት በክርስትና ስም ከተናገራቸው ነገሮች ውስጥ ሜታፊዚካል አሳቦችን ለይቼ ለማውጣት በመቻሌ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ከዚህ በፊትም ለጥቂት ጊዜያት እንዳደረገው፥ አንድ ከሰዓት በኋላ በቤቱ ውስጥ ዘና ብለን ተቀምጠን ነበር። በመደርደሪያዩ ውስጥ ከተቀመጡት አያሌ መጻሕፍት የሜሪ ቤከር ኤዲን የቅዱሳት መጻሕፍት ቁልፍ ተመለከተ፤ የዚህችን ሴትዮ አጠቃላይ አቋም ስለምቃወም እንዲሁ ለማጣቀሻ ያህል ነበር ያስቀመጥሁት። እርሱ ግን ብድግ አድርጎ ያነበው ጀመር፤ እኔም ልረብሸው ስላልፈለግሁ ዝም ብዬው ወደ ሌላ ክፍል ሄድሁ። ከ30 ወይም 40 ደቂቃዎች በኋላ ስመለስ አሁንም እያነበበው ነበር። በዚህ ጊዜ አስተያየቴን ስሰነዝር፥ ከሜሪ ቤከር ብዙ ጠቃሚ ነገሮች እንደሚገኙ ገለጸልኝ። ይህም የእምነት አቋሞቹን ያውጣጣው ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን፥ ከሜታፊዚክስም ጭምር እንደሆነ እንዳውቅ አደረገኝ።"[5]*

ኬንየንም ራሳቸው በእነ ክርስቲያን ሳይንስ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እንደነበራቸው የሚከተለው ጽሑፋቸው ዋቢ ይቆማል።

*"የክርስቲያን ሳይንስ፥ የአንድ አምላክን፥ የአዲስ አሳብንና መናፍስትን አስደናቂ እድገት ልናገንቅ ዋቢ ይቆማል።*

*«የክርስቲያን ሳይንስ፥ የአንድ አምላክን፥ የአዲስ አሳብንና መናፍስትን አስደናቂ እድገት ልናገንቅ አንችልም... ይህ በዘመናዊቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚሰነዘር የስም ግድፈት ነው - ግድፈትም ብቻ ሳይሆን ተግዳሮት ነው።»*

*ኬንየን እንግዲህ የእነ ክርስቲያን ሳይንስና አዲስ አሳብ ልምምድ ስለማረካቸው ነበር። ወደ ቤተ ክርስቲያን ጨልፈው ያስገቡት።*

*«እዚህ ላይ አንድ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነጥብ አለ፤ በአዎንታዊ አስተሳሰብ የታጀቡና (እንደ ኖስቲክ ሁለትዮሽ እውነታን ክዶ) በሽታን ምልክት ብሎ የመጥራት ዶክትሪኖች፥ አዲሱ አሳብና ውላጆቹ ከመከሰታቸው በፊት በክርስቲኖች ማጻሕፍት ውስጥ አልተጠቀሱም ነበር። ስለሆነም፥ ዶክትሪኑ ከእነዚህ ኑፋቄዎች መንጭቶና ተደራጅቶ ሲያበቃ፥ የፈውስ አገልግሎት ለማካሄድ በሚጓጉ ክርስቲያኖች ተጨልፎ እንደተወሰደ መመልከቱ ቀላል ነው።»*

*በክርስቲኖች ማጻሕፍት ውስጥ አልተጠቀሱም ነበር። ስለሆነም፥ ዶክትሪኑ ከእነዚህ ኑፋቄዎች መንጭቶና ተደራጅቶ ሲያበቃ፥ የፈውስ አገልግሎት ለማካሄድ በሚጓጉ ክርስቲያኖች ተጨልፎ እንደተወሰደ መመልከቱ ቀላል ነው።» (ተረስ ኒውማን) (ስለ አዲሱ አሳብ የኒው ኤጅና የእምነት እንቅስቃሴ ዝምድና ከሚቀርብበት ምዕራፍ ይመልከቱ።)*

*ስለሆነም፥ «ኪንየን ለኑፋቄዎቹ ተግዳሮት ምላሽ በመስጠት፥ የፈውስን አገልግሎት በቤተክርስቲያን ውስጥ ለማካሄድ ሲሉ የሚታፈዚክስ አሳቦችን* አሰባሰበዋል" (A Different Gospel, p. 29)።

♣

# 9

# ኬኔት ሐገንና
# የእምነት እንቅስቃሴ

*"አንዳንዶቻችን እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ከአንድ የበረከቱ የጸጋ ስጦታዎች አሉን... ይመስገነው የመሰበክና የማስተማር ስጦታዎች አሉኝ። ምንም እንኳ በልሳንና በትንቢት ብናገርም፥ እስከ 1952 ድረስ ሥልጣኑ አልነበረኝም። ወደ ነቢይነት አገልግሎት የገባሁበትን ጊዜ በትክክል አውቃለሁ" (ኬኔት ሐገን)።*

*"ምንም እንኳ ኬንየን የእምነት እንቅስቃሴ የተመሠረተባቸውን ትምህርቶች ቢደርሱም፥ በካሪዝማቲክ ክርስቲያኖች ዘንድ ትምህርቶቹ በፍጥነት እንዲያድጉ ያደረጉት ኬኔት ሐገን ናቸው" (A different gospel)።*

የልጅነት ሕይወታቸውን በልብ ድካም በሽታና በትካዜ ተሸብበው የኖሩት ሐገን ወደ "ሲኦል ወርደው" እንደነበር ጽፈዋል።

*"የምድር ብርሃናት እስኪደበዝዙ ድረስ፥ ታች፥ ታች፥ ታች፥ ወረድሁ... ወደ ታች በወረድሁ ቁጥር የጽልመቱ መጠን እያየለ ሄደ! በመጨረሻው ጭልም አለ። እጄ አንድ ኢንች ያህል ወደ ዓይኖቼ ቢቀርብ እንኳ ላየው አልችልም ነበር። ወደ ታች በወረድሁ ቁጥር ሙቀቱም እያየለ ሄደ። በመጨረሻም፥ በጥልቁ ዋሻ ግድግዳዎች ብርሃናት ደምቀው ሲያበሩ አየሁ። እነዚህም ከሲኦሉ እሳት የመጡ ናቸው። ልክ ማግኔት ብረትን እንደሚስብ፥ ግዙፉ የእሳት ነበልባል ወደ ራሱ ሳበኝ። እኔ ወደዚያ ለመሄድ አልፈለግሁም ነበር። እናም በእግሮቼ ሳልራመድ፥ ልክ ብረት ወደ ማግኔት እንደሚሳብ መንፈሴ ወደዚያው ተሳበ። ዓይኖቼን ከነገሩ ላይ ለማንሣት አልቻልም ነበር። ሙቀቱ ፊቴን ጠበሰው። ይህ ከሆነ ብዙ ዓመታት ቢያልፉም፥ ልክ ያኔ ካየሁት ባላነሰ ደረጃ አስታውሰዋለሁ። ትናንት ምሽት የተፈጸመ ያህል በአእምሮዬ ውስጥ ትኩስ ትውስታ አለው።"[1]*

ይኸው ገጠመኝ ለተጨማሪ ሁለት ጊዜያት የደረሰባቸው ሲሆን፥ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ሲኦል ከወረዱ በኋላ፥ ሐገን ሕይወታቸውን ለክርስቶስ በመስጠት በሰላም ለመሞት እንደተዘጋጁ ይናገራሉ።

ሌላው የሐገን "አቅጣጫ-ለዋጭ" ገጠመኝ የአገልግሎታቸው መልሕቅ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (ማርቆስ 11:23-24) "መገለጥ" ነበር። ሐገን ይህንን "መገለጥ" ያገኙት ታመው ለመሞት በሚያጣጥሩበት ወቅት ነበር።

ሌላው የሐገን "አቅጣጫ-ለዋጭ" ገጠመኝ የአገልግሎታቸው መልሕቅ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (ማርቆስ 11፡23-24) "መገለጥ" ነበር። ሐገን ይህንን "መገለጥ" ያገኙት ታመው ለመሞት በሚያጣጥሩበት ወቅት ነበር።

"እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ፦ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።"

ሐገን ከዚህ ጥቅስ በመነሣት፥ "የእምነት መመሪያ ይህ ነው - በልብህ እመን፥ በአፍህ ተናገር፥ የምትፈልገው ሁሉ ይሆንልሃል"[2] የሚል ደንብ አውጥተው፥ በየዕለቱ በበሽታቸው ላይ መለማመድ ያዙ። ይሁንና፥ ፈውሱ ፈጥኖ አልመጣም።

"በመጨረሻም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ነሐሴ በገባ ሁለተኛው ማክሰኞ በ1934 ዓ.ም. ለ16 ወራት በአልጋ ላይ በበሽታ ከቆየሁ በኋላ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል እንዲህ ብዬ መጸለይ ጀመርሁ። 'አሁን ውዱ ጌታ ኢየሱስ፥ በምድር ላይ በነበርህበት ጊዜ በማርቆስ ወንጌል 11፡24 ላይ እንዲህ አልህ፤ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም እንዳገኛችሁት እመኑ፤ ይሆንላችሁማል። ውዱ ጌታ ኢየሱስ፥ እንድፈወስ እፈልጋለሁ።

"ስትጸልዩ ብለሃል። ጸልያለሁ። እመኑ ብለሃል አምናለሁ። ውድ ጌታ ኢየሱስ፥ ልክ እናቴ በአልጋዬ አጠገብ እንደምትቆም አንተም በሥጋ አጠገቤ ብትቆም፥ በዚህ በዓይኔ ልክ እናቴን እንደማይ አንተን ባይህ፥ እጆቼን ዘርግቼ እናቴን እንደምይዛት አንተንም ብይዝህ፥ 'ልጄ የአንተ ችግር ያለማመን ነው' ብትለኝ መልሼ፥ ውዱ ጌታ ኢየሱስ፥ እየዋሸህ ነው... እኔ አምናለሁ' እልሃለሁ... " ( 'እምነት ማለት' በሚል ርእስ 'በኤልሻዳይ ኮይኖንያ ቤተ ክርስቲያን ወደ አማርኛ ከተመለሰው የኬነት ሐገን መጽሐፍ የተወሰደ፥ ገጽ 23)

በዚህ ጊዜ ነበር የማርቆስ 11፡23-24 ቀጣይ "መገለጥ" የመጣላቸው።

"በዚህ ጊዜ በማርቆስ 11፡24 ውስጥ ያለው ጥቅስ ምን እንደሚል በትክክል ተረዳሁ። እስከዚያን ጊዜ ግን እስክፈወስ ድረስ ልጠብቅ ነበር። ይሁንና፥ ጥቅሱ ስትጸልይ ማመን አለብህ እንደሚል ተመለከትሁ። ፈውሱ የሚመጣው ከእምነት በኋላ ነው። እኔ ግን ቅደም-ተከተሉን እያቀያየርሁ ነበር። ገብቶኛል ገብቶኛል አልሁ በደስታ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ ገብቶኛል። ጌታ ሆይ፥ እዚህ ከአልጋዬ ላይ ተለጥፌ ሳለሁና ልቤም በትክክል ሳይሠራ፥ ሽባነቴ እንደተወገደ ማመን አለብኝ።"[3]

ይህንኑ ኑዛዜ ካሰሙ ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ፥ መንፈስ ቅዱስ፥ "እንደተፈወስህ ታምናለህ። እናም ከተፈወስህ እንግዲህ ከአልጋው መነሣት አለበህ" እንዳላቸው ሐገን ይናገራሉ። በዚህ ጊዜ ሐገን ብድግ ብለው

በአካባቢው በነበረችው የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ከዶክትሪኗ ጋር የማይዛመድ አገልግሎት ማቅረብ የጀመሩት ሐገን፥ በ1937 ወደ ፔንተኮስታሎቹ ማዘውተር ያዙ። ይህንንም ያደረጉት በልሳን የመናገር ፍላጎት ስላደረባቸው አልነበረም። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ሐገን ይህንን ልምምድ ያወግዙ ነበር። ወደዚያ የሄዱት በወቅቱ እርሳቸው በጣም የሚያምኑበትን የፈውስ አገልግሎት የሚለማመዱት የሙሉ ወንጌል አብያተ ክርስቲያናት ስለነበሩ ነው። በዚያን ዓመት ሐገን "የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት" አግኝተው በልሳን እንደተናገሩ ይገልጻሉ።

በ1937 ሐገን በአሴምብሊስ ኦፍ ጎድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማገልገል ዕድል ስላገኙ፥ በቴክሳስ ውስጥ በተለያዩ ትናንሽ አብያተ ክርስቲያናት የመጋቢነትን አገልግሎት አበርክተዋል። "ክክብር ደመና" በተጨማሪ፥ ሐገን አንዲት ሴት እርሳቸው በሚመሩት አገልግሎት ውስጥ እየደነሰች ሳለ በአየር ላይ እንደተንሳፈፈችና ሌላዋ ደግሞ ለ8 ሰዓታትና 40 ደቂቃዎች እእምሮዋን ስታ እንደቆየች ገልጸዋል[5]። በሐገን የመጋቢነት አገልግሎት ውስጥ ተደጋጋሚ የፈውስ ክስተቶችና "የሙታንም ትንሣኤ" እንደታዩ ሐገን "plead your case" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ዘግበዋል[6]።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ አንድ የሐገን ቤተ ክርስቲያን ንቁ አባል ይሞትና ወደ መንግሥተ ሰማይ ይሄዳል። ሰውዬው የሰንበት ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪና ከገቢው ሃያ እጅ አሥራት የሚከፍል በመሆኑ፥ ይህንኑ ግለሰብ ላለማጣት ሲሉ ሐገን ተግተው ይጸልያሉ። በዚህ መሀል ሰውዬው መንግሥተ ሰማይ ደርሶ ከኢየሱስ ጋር ሲገናኝ፥ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ይነገረዋል። ሰውዬው ግን ለመመለስ እንደማይፈልግ ሲናገር፥ "ወንድም ሐገን ያንተን መምጣት አይደግፍም!" የሚል ምላሽ ከኢየሱስ እንደተሰጠው ይነገራል። ከዚያም ይህንኑ ታሪክ እየተረኩ፥ ኬነት ሐገን የምልጃ ሥልጣን አለኝ ሲሉ ያውጁ ጀመር።

ይሁንና፥ ሐገን ለመጋቢነቱ አገልግሎት የሚበቃ "ቅባት" የለኝም የሚል እምነት ስላላቸው፥ የመጋቢነት አገልግሎታቸውን በተመለከተ "መለኮታዊ ንስሐ" መግባት እንዳለባቸው ገልጸዋል[7]። በባፕቲስት ወንጌላዊነት ለሦስት ዓመታት (1934–1937)፥ በአሴምብሊስ ኦፍ ጎድ መጋቢነት ለ12 ዓመታት (1937–1949) ያገለገሉት ሐገን፥ የመጨረሻ ስብከታቸውን በቴክሰስ በ1949 ነበር ያቀረቡት።

ከዚያ በኋላ ወደ ፈውስ ሪቫይቫል ፊታቸውን አዞሩ (1947–1958)። በዚህ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ሳይሆን፥ እንደ ጎርደን ሊንዶሲ ከመሳሰሉት ግለሰቦች ጋር በመሆን "ተጠራሁበት" ያሉትን የነቢይነትና የመምህርነት አገልግሎት "የመጀመሪያ ክፍል" ጀመሩ። ሐገን ከፈውስ አገልጋዮች ጎን ቢሰለፉም፥ እንደ ብራንሃም፥ ሮበርትስና ኤለን አዎስከምስህ ስላሉበት፥ የፈዋሽነት ሚና ሊጫወቱ አልቻሉም። እናም የነቢይነትና የአስተማሪነት አገልግሎት አበርክተዋል።

ቢሰለፉም፥ እንደ ብራንሃም፥ ሮበርትስና ኤለን አዮስከምስህ ሰላሉበት፥ የፈዋሽነት ሚና ሊጫወቱ አልቻሉም። እናም የነቢይነትና የአስተማሪነት አገልግሎት አበርክተዋል።

## *ሐገን እንደ አስተማሪና ነቢይ*

ሐገን የማስተማር ስጦታ እንዴት እንደመጣላቸው ሲገልጹ፥

*"ስተኛ ቆይቼ ነበር። የምጠጣውን ውኃ ለማግኘት ስል በሳሎኑ በኩል ወደ ኩሽና (ማዕድ ቤት) አመራሁ። ከዚያ ተመልሼ ሳሎኑ ቤት ስደርስ በላዩ ላይና በውስጤ አንድ ነገር ወደቀብኝ። ልክ የሕዝብ ስልክ ለመደወል የምታስቀምጡት ሣንቲም ወደ ታች ሲወርድ እንደሚሰማው ያህል ነበር። ፈዝዤ ቆምሁ። ወዲያውም ነገሩ ምን እንደሆነ አወቅሁ። የማስተማር ስጦታ ነበር። የማስተማር ቅባት ነበር ወደ ውስጤ የወረደው። እኔም እንግዲህ፥ ማስተማር እችላለሁ አልሁ።"*[8]

በመደበኛ ትምህርት ወይም በሥነ-መለኮታዊ ሥልጠና ብዙ ያልገፉት ሐገን፥ ትምህርታቸው "ከከፍተኛ ምንጭ" እንደሚመነጭ ይናገራሉ። ይህም በእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች "የመገለጥ እውቀት" የሚባለው ስውር "ቅባት" ነው።

የነቢይነት ስጦታ ተቀብያለሁ ያሉት ደግሞ ከ9 ዓመታት በኋላ በ1952 ነበር። ሐገን ለነቢይነት የሚሰጡት ፍች "ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ራእዮችና መገለጦች ያሉት"[9] የሚል ነው።

*"ጌታ ኢየሱስ በ1959 ዓ.ም. በራእይ በተገለጸልኝ ጊዜ 'ትንቢቱ ቀደም ሲል በውስጥህ ያለውን ካረጋገጠልህ ተቀበለው። እንደዚያ ካልሆነ ግን አትቀበለው' ብሎኛል" ሲሉ ጽፈዋል። (የመንፈስ ቅዱስ ምሪት፥ ገጽ 69።)*

መጽሐፍ ቅዱሳዊው መመሪያ ትንቢትን በእግዚአብሔር ቃል መመርመር ሆኖ ሳለ፥ ኢየሱስ ለእርሳቸው በአቋራጭ ቀደም ሲል "በውስጣቸው ባለው" ወይም "በውስጥ መረዳት" እንዲመረምሩ መናገሩ አስገራሚ ነው።

እኚህ ሰው ስምንት ጊዜ ኢየሱስን እንዳዩና በመጽሐፍ ተጠርዘው ሊወጡ የሚችሉ ራእያዊ ገጠመኞችን እንዳሳለፉ ይተርካሉ። በመጀመሪያ ሐገን ኢየሱስን ያዩት ከሥጋቸው ተለይተው ወደ ሰማይ በመጓዝ እንደነበር ይናገራሉ። በ1950 ዓ.ም. በወንጌል ስርጭት ስብሰባ ላይ ሳሉ አንድ ድምፅ ከሰማይ ወደ ላይ "ና!" ሲል ይጠራቸዋል። ልክ ሐዋርያው ዮሐንስ ከፍጥሞ ደሴት ተነጥቆ በመሄድ የራእይን መጽሐፍ መልእክት እንደተቀበለ ሁሉ፥ ሐገንም ወደ "መናፍስት ዓለም" እንደዘለቁ ይናገራሉ። በዚህም ዓይነት ከመንግሥተ ሰማይ ደጅ ባለው ተራራ ላይ ደረሱ።

ስም" እንዲያነቡ ስለታዘዙ፥ የመጽሐፍ ጥቅሉን ከመልአኩ እጅ ወስደው በአሜሪካ ከተሞች ላይ ስለሚደርሰው ጥፋትና በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆነው ታላቅ መነቃቃት እንዳነበቡ ይናገራሉ። ሐገን እንደሚሉት፥ በዚያ የወንጌል ስብሰባ ላይ የነበሩት ሰዎች የመጽሐፉን ጥቅልል ሲያነቡ ሰምተዋል። አንብበው እንደጨረሱትም ወደ ስብሰባው መመለሳቸውን ይናገራሉ።

አሁንም ራእዩ ገና አላለቀም። ኢየሱስ ስለ አገልግሎቱ ሊያነጋግራቸው ፈልጎ ጓግም ወደ ሰማይ እንደወሰዳቸው ያስረዳሉ። በዚህም ጊዜ በወንጌላዊነትና በመጋቢነት ያሳለፉአቸው የመጀመሪያዎቹ 15 ዓመታት በራሳቸው ፈቃድ ያቃጠሏቸው እንደሆኑ ተነገራቸው። ይህንን አገልግሎት ትተው ወደ ፊውስ እንቅስቃሴ በመዛወራቸው ወደ አገልግሎቱ "የመጀመሪያ ክፍል" እንደገቡ ተገለጸላቸው። በዚህ በመጀመሪያው ክፍልም ቢሆን፥ ኢየሱስ "እኔ ያልሁህን አልፈጸምህም። ይህም የሆነው ላንተ የተናገረው መንፈሴ እንደሆነ ስለተጠራጠርህ ነው" እንዳላቸው ይገልጻሉ። ስለሆነም፥ ሐገን ላለማመናቸው ንስሓ ገብተው ለስምንት ወራት (ከጥር – እስከ ነሐሴ 1950) ወደቆየው "ሁለተኛው ክፍል" አመሩ። ሐገን በአገልግሎታቸው ኢየሱስን ሙሉ ለሙሉ ያስደሰቱት በዚህ ጊዜ እንደሆነ ይናገራሉ። (የሚገርመው ሐገን የኬንየንን መጻሕፍት ለመጀመሪያ ጊዜ አነበብሁ የሚሉትም በዚሁ በ1950 መሆኑ ነው! ይጠርጠር።)

በዚሁ በመስከረም 1950ው ራእይ፥ ኢየሱስ ወደ "ሦስተኛው ክፍል" አገልግሎታቸው እንደሚገቡ እንደገለጸላቸው ይናገራሉ። በዚህ ጊዜ ታማኝ ሆነው ከተገኙም፥ ኢየሱስ እንደገና መጥቶ ወደ "አራተኛውና የአገልግሎቱ ማጠቃለያ ወደሚሆነው ክፍል 4" እንደሚመራቸው የተገለጠላቸው መሆኑን ጽፈዋል[10]።

ከ1950 እስከ 1959 የነበረው ጊዜ የሐገን አገልግሎት ያዘቀዘቀበት ጊዜ ነበር። ምንም እንኳ ኢየሱስ ሰባት ጊዜ እንደታያቸው ቢናገሩም፥ አገልግሎታቸው ተዳክምዋ ነበር። ሐገንም ቢሆን ይህ ወቅት የዕዳ ብርካቴና የሕዝብ ብዛት መመንመን የተከሰተበት መሆኑን አምነዋል[11]።

በየካቲት 1959 ከኢየሱስ በተሰጠው ስድስተኛው ራእይ፥ ሐገን ለዚህ ችግር ከፊሉ መንስዔ ምን እንደሆነ ለማወቅ መቻላቸውን ይናገራሉ። በዚህ ጊዜ ሐገን በቴክሳስ ከተማ በመውደቃቸው እጃቸው ስለተጎዳ ሆስፒታል ውስጥ ተኝተው ይሠቃዩ ነበር። አሁንም ኢየሱስ ወደ ሆስፒታሉ ድረስ መጥቶ "በእግዚአብሔር ፈቃድ" ብቻ እየተራመዱ እንዳሉ ነገራቸው። በመሆኑም፥ ከነቢይነት አገልግሎታቸው በላይ ለማስተማር አገልግሎታቸው ትኩረት የሚሰጡበትን "ቀልብ ለማሰር" ሲል ሰይጣን የሐገንን እጅ እንዲጎዳው እንዳደረገ ኢየሱስ ይገልጽላቸዋል። ለሐገን ኢየሱስ የትንቢት አገልግሎቱ ከማስተማር እንደሚበልጥና የሐገንም ጥሪ ይኸው የሚበልጠው ትንቢት

"በእግዚአብሔር ፈቃድ" ብቻ እየተራመዱ እንዳሉ ነገሩቸው። በመሆኑም፥ ከነቢይነት አገልግሎታቸው በላይ ለማስተማር አገልግሎታቸው ትኩረት የሚሰጡበትን "ቀልብ ለማሰር" ሲል ሰይጣን የሐገንን እጅ እንዲጎዳው እንዳደረገ ኢየሱስ ይገልጽላቸዋል። ለሐገን ኢየሱስ የትንቢት አገልግሎቱ ከማስተማር እንደሚበልጥና የሐገንም ጥሪ ይኸው የሚበልጠው ትንቢት እንደሆነ ይነግራቸዋል። ይህንንም ለማድረግ እግዚአብሔር ለ25 ዓመታት ያገኙትን መለኮታዊ ፈውስ እንደነጠቃቸው ይናገራሉ[12]።

ሐገን በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ የተጫወቱትን ሚና ለመረዳት የነቢይነትና የአስተማሪነት ሚናቸውን መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ራሳቸው እንደተናገሩት፥ "ከአንዱ ወደ ሌላው ሲዋዥቁ" ነበርና የኖሩት። እንደ ነቢይ በመለኮታዊ ድምፅ፥ በራእይ ወይም ከኢየሱስ ጋር በመገናኘት የተቀበሉትን መገለጥ ያስተላልፋሉ። እንደ አስተማሪ ደግሞ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ግልጽና ቀልድን በተላበሰ መንገድ ይገልጻሉ። ሁለቱም በአንድነት ሲጣመሩ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊነቱን ያልለቀቀ "ልዕለ–ተፈጥሯዊ" አገልግሎት ተበረከተ ይባላል።

በመሆኑም፥ ተከታዮቻቸው ሐገንን "ታላቅ ተንባይና የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ" አድርገው ይቆጥሩአቸዋል። የሐገንን የነቢይነት አገልግሎት የሚጠራጠሩ ሰዎች "የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቃወሙ" ተደርገው ሲገለጹ፥ በአመክኒአአዊ መሠረት (rational basis) የሚሞግቷቸው ደግሞ "ጌታ የቀባውን አትንካው!" በሚል ማስፈራሪያ እንዲርቁ ይደረጋል። ስለሆነም፥ በእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች ዘንድ የሐገን ትምህርት ከሂስ የራቀ ነው – ልክ እንደ ሙስሊሞቹ ቁርአንና ሞሐመድ።

## መለኮታዊ ጉብኝት

ኬነት ሐገን መልእክታቸውን የተቀበሉት በቀጥታ ከኢየሱስ ዘንድ እንደሆነ ይናገራሉ። ቢያንስ ቢያንስ ከሐገን መጻሕፍት ሦስቱ ማለትም "የነቢዩ አገልግሎት" (The Minstry of the prophet)፥ "በራእይ አምናለሁ" (I Believe in Visions) እና "እንዴት በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት እንደሚቻል" (How to be Led by the Spirit of God - ይኼኛው በአማርኛ ተተርጉሞ ታትሞአል) በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ በመለኮታዊ ጉብኝቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። በዚህም ሐገን ከኢየሱስ ጋር ፊት ለፊት በመነጋገር፥ ከራሱ ከክርስቶስ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስን አተረጓጎም እንዳካሄዱ ይናገራሉ። ሐገን እንደሚሉት ከሆነ ከነዚህ ገጠመኞች አንዱ የሚከተለው ነበር።

*"እስከ በየካቲት 1959 ኢየሱስ ወደ ነገረኝ ነገር ልመለስ... ከአልጋዬ ላይ ቁጭ ብዬ ሳጠና ነበር። ዓይኖቼ በግልጽ ተከፍተው ሳሉ... የሰው ኮቴ ተሰማኝ። ማን ይሆን ብዬ ለማየት ስሞክር ኢየሱስን አየሁት... ነጭ ልብስ ለብሷል። የሮማውያን ዓይነት ነጠላ ጫማ አድርጓል። (ኢየሱስ ስምንት ጊዜያት ሲገለጽልኝ፥ ከዚህ ጊዜ በቀር ጫማ አያደርግም ነበር። በዚህ ጊዜ ጫማ*

*ጀመረ..."[13] ('የመንፈስ ቅዱስ ምሪት' ተብሎ ከተተረጎመው መጽሐፍ የጀርባ ሽፋን ላይ ከሰፈረው ጋር ያነጻጽሩ።)*

ከዚያም እንደዚህ "ግልጽ ራእዮች" ባሉት "ውስጣዊ ምስክርነቶች"[14] መመራት እንዳለባቸው የተገለጸላቸው መሆኑን ያትታሉ – "በመንፈስ መመራት" መሆኑ ነው!

ሐገን እርሳቸው በውስጥ መረዳታቸው ሳያውቁ በቅርብ ቤተሰቦቻቸው ላይ የደረሰ የሞት አደጋ እንደሌለ ገልጸዋል። (የመንፈስ ቅዱስ ምሪት፥ ገጽ 39።) በተጨማሪም፥ ከትናንሽና ትላልቅ መላእክት ጋር ያደረጉትን ውይይት በዚሁ "የመንፈስ ቅዱስ ምሪት" ተብሎ በተተረጎመው መጽሐፍ ውስጥ አስፍረዋል (ገጽ /78-79)።

*"ከዚያም ጌታ እንዲህ አለኝ፤ ይህም ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለእናንተው ጥቅም ነው፤ ያንን ውስጣዊ ምስክርነት ከተከተልህ አበለጽግሃለሁ... የልጆቼን መበልጸግ አልቃወምም። የምቃወመው መመኘታቸውን ነው። እኔ ሐገን ያንን ውስጣዊ ምስክርነት በመከተሌ፥ እርሱም የተናገረውን ፈጽሞልኛል። አበልጽጎኛል።"[15]*

ሐገን ይህንኑ የብልጽግና አሳብና የእምነት ፍልፍስና ለማስተማር መለኮታዊ ሥልጣን እንደተሰጣቸው ይናገራሉ።

*"ከዓመታት በፊት ጌታ፥ 'ሂድና ሕዝቤን እምነት እንድታስተምር እፈልጋለሁ፤ በቃሌ አማካኝነት እምነትን አስተምሬሃለሁ፤ በተወሰኑ ልምምዶችም ውስጥ እንድታልፍ አድርጌሃለሁ። በመሆኑም፥ እምነትን ከቃሌና ከልምድ ተምረሃል። አሁን ሂድና ሕዝቤን እምነት አስተምር። እኔ ያስተማርሁህን አስተምራቸው።' አንድ ድምፅ ከሰማይ ሆኖ እነዚህን ቃላት ሲናገር ሰማሁ።"[16]*

ሐገን "መገለጡን" ከኢየሱስ መቀበላቸው ብቻ ሳይሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎምም ላይ ከኢየሱስ ጋር እንደተከራከሩ ጽፈዋል። በዚህ ዓይነት አንድ ጊዜ ከኢየሱስ የሰሙት ነገር "ሌሎች ሲሰብኩ ከሰሙት ወይም ራሳቸው ከሰበኩት እንደሚለይ" በመግለጽ ማጉረምረማቸውንና እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት "ሥነ-መለኮቴን ይገለብጠዋል" ሲሉ መስጋታቸውን ይተርካሉ። ኢየሱስም "አንዳንድ ጊዜ ሥነ-መለኮትህ የግድ መገልበጥ አለበት"[17] እንዳላቸው ጽፈዋል።

ጽሑፎቻቸው እንደሚያሳዩት፥ ሐገን የኢየሱስን ሥነ-መለኮት ለመገልበጥ የሚከጅሉ ይመስላል። ለዚህ አብነት ከሚሆኑት መካከል አንዱ የሚከተለው የሐገን ጽሑፍ ነው። ሐገን ኢየሱስ ከአንድ በበለጡ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች እስካላረጋገጠላቸው ድረስ አሳቡን ንከች እንደማያደርጉለት በመግለጽ መሞገታቸውን ያስነብቡናል።

*"ምንም ያህል ጊዜ በራእይ ባየውም፥ ከአዲስ ኪዳን ቢያንስ በሦስት ጥቅሶች ሊያረጋግጥልኝ የግድ ነበር...ኢየሱስም ፈገግ ብሎ አራት ጥቅሶች እንደሚሰጠኝ*

እስካላረጋገጠላቸው ድረስ አሳቡን ንክች እንደማያደርጉለት በመግለጽ መሞገታቸውን ያስነብቡናል።

*"ምንም ያህል ጊዜ በራእይ ባየውም፥ ከአዲስ ኪዳን ቢያንስ በሦስት ጥቅሶች ሊያረጋግጥልኝ የግድ ነበር...ኢየሱስም ፈገግ ብሎ አራት ጥቅሶች እንደሚሰጠኝ ተናገረ። እኔም አዲስ ኪዳንን ለ150 ጊዜያት ሳነብ፥ ብዙ ክፍሎችን ግን ከዚያ በላይ አንብቤአለሁ። አንተ የምትለው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለመኖሩ ግን የማውቀው የለኝም አልሁት።"*[18]

## መለኮታዊ ፍርዶች

ሐገን የትምህርታቸውን መንፈሳዊ ምንጭነት በመግለጽ ብቻ አልታቀቡም፤ ይልቁንም፥ የእርሳቸውን ትምህርትና ነቢይነት የማይቀበል ማንም ቢሆን ለቅስፈት እንደሚዳረግ ዝተዋል። የዚህ ዓይነቱም ፍርድ በአገልግሎታቸው መጀመሪያ አካባቢ እንደተከሰተ በመግለጽ አባባሉን እንደሚከተለው በመረጃ ለማስደገፍ ይሞክራሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፥ ከአገልግሎቶቻቸው በአንደኛው ወቅት በአየር ላይ የመንሳፈፍ ልዕለ–ተፈጥሯዊ ክስተት ከታየ በኋላ፥ የሐገን ሚስት ብሎም ሐገን የሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሚስትና ወንድሟ በአየር ላይ የመንሳፈፉ ትርዒቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ተጠራጠሩ። በቀጣዩ ዕለት፥ ሐገን ሲጸልዩ ሳለ "የእግዚአብሔር ቃል" ወደ እርሳቸው እንደመጣና የሦስቱንም ሰዎች ግንባሮች እንዲነኩ እንዳደረጋቸው ያስረዳሉ።

የሚስታቸውንም ግንባር በነኩ ጊዜ፥ "ልክ አንድ ሰው በዱላ እንደመታትና ወደ ኋላዋ እንደገፈተራት"[19] መውደቋን ይናገራሉ። ሌሎች ሁለቱም "በመንፈስ ታርደው" ነበር። ለሽባነት የተዳረጉት ሦስቱ ሰዎች "ከወለሉ ጋር ተጣበቁ።" ጉዳዩ ያሳሰበው መጋቢ ሚስቱን ለማስነሣት ሲሞክር፥ "እንኳንስ ሰውነቷን እጇንም ከወለሉ ሊያነሣው" እንደተሳነው ይተርካሉ።

ከዚያም አንድ ድምፅ ወደ እርሳቸው መጥቶ፥ "ከእያንዳንዳቸው አጠገብ በመንበርከክ ለመነሣት እንዲሞክሩ እንዲናገሩ" እና "በእነርሱ ላይ እየደረሰ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ መቀበላቸውን እንዲጠይቁ" ይነግራቸዋል። ሰዎቹም ለመነሣት ሞክረው ሲሳናቸው፥ የሐገን አገልግሎትና ኃይል ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆናቸውን ለመናገር ተገደዱ። (አንዳንድ 'ጉልቤ' ፖሊስ በቆመጥ ማሳመኑን ልብ ይሏል!) ከዚያም፥ ሐገን በጣቶቻቸው በመንካት እንዲያስነሡአቸው ያ የቅድሙ ድምፅ እንደነገራቸው ጽፈዋል።

ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ ምክኮንል አስተያየታቸውን ሲሰነዝሩ፥ "ሐገን 'የውስጥ ድምፁን' በመስማት በጣቶቻቸው ብቻ ይህንን ማድረግ ከቻሉ፥ አገልግሎቱ እየሰፋ ሲሄድ እንዲህ ዓይነት ትንቢታዊ ፍርዶች መጨመራቸው የማይቀር ነው" ብለዋል። የተባለው አልቀረም በ1959 ሐገን "ካልሰማችሁኝ

*"ለግለሰብ፥ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለመጋቢ መልእክት ሰጥተህ ባይቀበሉ፥ ኃላፊነቱ ያንተ አይደለም – የእነርሱ እንጂ። መልእክትህን ባለመቀበላቸው ከምስባኩ ላይ የሚደፉ አገልጋዮች ይኖራሉ"*[21] ሲሉ ጽፈዋል።

ለመሆኑ፥ አንድን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዓውደ–ንባብ የማይጠብቁትን ግለሰብ መልእክት አለመቀበል እውን "ከምስባክ ላይ ይደፉ" ይሆን? ሐገን የሚመኩበት ትንቢትም ሆነ ማንኛውም የጸጋ ስጦታ ቤተ ክርስቲያንን "ለማነጽ" የተሰጠ እንጂ "እደፉሃለሁ!" እያሉ የሚያስፈራሩበት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ሐገን ከላይ የተናገሩት ቃል ባዶ ግነት እንደሆነ ለሚያስቡ ሰዎች ጠበቅ አድርገው ሲናገሩ የሚከተለውን አክለዋል።

*"ይህን የምናገረው ወድጄ ባይሆንም፥ አንድ ጊዜ በሰብክሁበት ስፍራ ተፈጽሞ አይቻለሁ። ስብሰባውን ከዘጋሁበት ከሁለት ሳምንታት በኋላ፥ መጋቢው ከመድረኩ ላይ ተደፍቶ ሞቷል። እኔም እያለቀስሁ ወደ ቤቴ ተመለስሁ። ስብሰባ ላካሂድ በሄድሁበት ቤተ ክርስቲያን ለነበረው መጋቢ፥ 'ያ ሰው በምስባኩ ላይ እንደሚሞት ነገርሁት።' ይህንን ካልሁ ብዙም ሳይቆይ ሞቶ ተገኘ። ለምን? ምክንያቱም እግዚአብሔር እንድነግረው በመንፈስ ቅዱስ የሰጠኝን መልእክት ስላልተቀበለ ነው።"*[22]

ኬነት ሐገን ያስፈራሩት አገልጋዮችን ብቻ አልነበረም። አገልጋዮቹ መድረኩ ላይ ሲሞቱ፥ "ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚሞቱ"[23] የገዛ ጽሑፋቸው ያስረዳል።

እውን ይህ ለሚሰቅሉት እንኳ "አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ሲል የይቅርታን ጸሎት ካደረሰውና በኃጢአታቸው የሲኦልን ደጅ ለሚጠባበቁ የሰው ልጆች ከተሰጠው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የመጣ ትምህርት ይሆን? ጌታ አልሰማኸኝም ብሎ የሰውን ልጆች ከመድረክ ላይ የሚደፋ ቢሆን፥ ሐገንም ዛሬ በሕይወት ባልኖሩና "እደፉሃለሁ!" እያሉ ባላስፈራሩ ነበር!

## *የሐገን ትምህርት ከሰዎች እንደተቀዳ*

ምንም እንኳ ኬነት ሐገን መልእክታቸውን የተቀበሉት በቀጥታ ከኢየሱስ እንደሆነና ይህንንም የማያምን ሰው በሞት እንደሚቀጣ በመግለጽ ቢዝቱም፥ ምክኮንል ትምህርታቸው ከሰዎች እንደተቀዳ አመልክተዋል። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ የሐገን ትምህርት የተመሠረተው በኬንየን መጻሕፍት ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ፥ ሐገን የኤፍ.ኤፍ. ቦስዎርዝን፥ የጆን ኤ. ማክሚላንንና የሌሎችንም ሰዎች አሳቦች በቀጥታ ወስደው እንደተጠቀሙ ታውቋል።

ለምሳሌ፥ በ1967 አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ ይሸጥ የነበረው የሐገን መጽሐፍ "የአማኝ ሥልጣን" በ1932 በዚሁ ርእስ በጆን ኤ. ማክሚላን ታትሞ

ማክሚላንንና የሌሎችንም ሰዎች አሳቦች በቀጥታ ወስደው እንደተጠቀሙ ታውቋል።

ለምሳሌ፥ በ1967 አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ ይሸጥ የነበረው የሐገን መጽሐፍ "የአማኙ ሥልጣን" በ1932 በዚሁ ርእስ በጆን ኤ. ማክሚላን ታትሞ እንደነበርና በኋላ ሐገን ቃል በቃል እንደገለበጡት ዴይል ሳይመንስ አጋልጠዋል።

ሳይመንስ ሐገን የማክሚላንን መጽሐፍ እንደሠረቁ ሲረዱ፥ መጽሐፉን ያሳተመው የሲኤምኤ(CMA) ክርስቲያን አሳታሚ ምክትል ፕሬዚዴንት ወደነበሩት ሮበርት ካውልስ ደብዳቤ ጻፉ። ሚስተር ካውልስም በበኩላቸው ለኬኔት ሐገን ሁኔታውን በደብዳቤ ገልጸው አጋፈጧቸው። ሐገን በፌብሯሪ 28፥ 1984 ለአሳታሚ ድርጅቱ በጻፉት ምላሽ፥ "የአማኙ ሥልጣን" በዚሁ ርእሰ-ጉዳይ ላይ ካቀረበው ስብከት ላይ የተወሰደ መሆኑን ገልጸው ሲያበቁ የሚከተለውን ብለዋል።

*"ይሁን እንጂ ስብከቴ በከፊል ጆ ኤ. ማክሚላን በጻፈው መጽሐፍ ላይ እንደ ተመሠረተ ጠቅሼ ነበር። ይህንኑ የገለጽሁበት ዓረፍተ-ነገር በአርማት ላይ በስህተት ተፍቋል።"*

በመቀጠልም፥

*"በዓመታት ውስጥ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ግለሰቦች በአንድ ርእሰ-ጉዳይ ላይ በሚናገሩበት ጊዜ፥ በመሠረታዊነት አንድ ዓይነት ነገር ይናገራሉ። ይህም የሚሆነው የሚመራቸው አንድ መንፈስ ስለሆነ ነው። ከሌላው ሰውዬ ጋር ተገናኝተህ ባታውቅና መጽሐፉንም አንብበህ ባታውቅም እንኳ፥ መንፈሱ ነገሮችን በተመሳሳይ መንገዶች ስለሚያሳይህ ተመሳሳይ አሳቦች ይኖሩሃል"*[24]

ሐገን ትምህርታቸው ከኬንዮን ጋር አንድ ስለመሆኑም የሰጡት ምክንያት ይህንኑ እንደነበር ይታወሳል። ደግነቱ ሐገን ከማክሚላን መጽሐፍ "በከፊል" ገልብጫለሁ ስለሚሉ፥ ይኼኛው ማስተባበያ ትምህርቱ ከመለኮታዊ ምንጭ ያለመሆኑን ሐቅ ከማመልከት አይበዝንም። በመሆኑም፥ ቀጣዩ የሳይመንስ ምልከታ አስተውሎታዊ ነው እንላለን።

*". . . የሐገን ማመኻኛ እጅግ ደካማ ይመስላል። መንፈስ ቅዱስ የአንድን ሰው መጽሐፍ ሳያነብ ወይም ከሰውዬው ጋር ሳይገናኝ የዚያን ሰውዬ አሳብ የሚያስጨብጠው ከሆነ፥ የሌላውን ሰው መጽሐፍ [በከፊልም ቢሆን] ማንበቡ ለምን አስፈለገው? ወጣም ወረደ አንድ ሐቅ በግልጽ ይታየኛል፤ ሐገን 'የአማኙ ሥልጣን' የሚለውን መጽሐፍ ለመጻፍ በመንፈስ በተነሣሣበት ወቅት ለልቡ የተናገረው ድምፅ የጆን ኤ. ማክሚለን ነበር።"*[25]

## የሐገን ነቢይነት ሲገመገም

በሌላ በኩል፥ ከኢየሱስ ጋር መገናኘታቸው እውነትነት እንዲኖረው ከተፈለገ ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎችን ሊያልፍ የግድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም እንኳ፥ "እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን" ብሏልና (ገላትያ 1፡8)። እርሳቸው ግን ቃሉን ሳይሆን የፈጠሩትን ተረት በማውጋት የሚደሰቱ ይመስላል። ለምሳሌ "የመንፈስ ቅዱስ ምሪት" በሚል ርእስ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በቀረበልን መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ፥ "እግዚአብሔር ልጆቹን የሚመራበት የመጀመሪያው መንገድ የውስጥ ድምፅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። እንዲሁም በዚሁ መጽሐፍ በገጽ 15 ውስጥ የሚከተለውን አስፍረዋል።

*"ከዚያም በውስጤ ትንሽ ድምፅ ሰማሁ። እዚህ ላይ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ድምፅ ለመናገር አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ሲናገር በታላቅ ሥልጣን ነው፤ ትንሹ ድምፅ ግን የውስጥ ሰውነታችን የሚናገረው ድምፅ ነው። ይሁን እንጂ የውስጥ ሰውነታችን የሚናገረውን የሚያገኘው በእኛ ውስጥ ከሚኖረው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። የውስጥ ድምፅ ንግግር ሥልጣን ያለው አይደለም። በመሆኑም በውስጤ ሆኖ በለሰለሰ ድምፅ 'ያን ሕንጻ እሰጥሃለሁ' አለኝ።"*

ይህ "የውስጥ ድምፅ"፥ "የውስጥ መረዳት" እያሉ የሚተነትኑት ስሜት እንዳልሆነ ለማስረዳት ቢሞክሩም፥ ሥጋዊ ፍላጎትን ለማሟላት የተፈለሰፈ ስልት መሆኑ ግልጽ ነው። አሊያማ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቁልጭ ብሎ ከሚታየው የቃሉና የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ማለፍ አያስፈልጋቸውም ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ፥ "በውስጣቸው" ተመርተው እርምጃ የወሰዱበት ሁኔታ አልተስተዋለም። የሐገን የውስጥ ድምፅ አስተምህሮ የሰውን አምላክነት ለማስረዳት፥ "... በውስጥህ ያለውን አምላክ ለማግኘት ወደ ውጥህ ልትቆፍርና ድምፁን ማለትም ያንተኑ ድምፅ ልትሰማ ይገባል" ከሚሉት የቲዎሶፊ ፈላስፎች የተለየ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

ከዚህ አኳያ፥ "እኔ ያልሁትን ያልሰማ" አገልጋይም ሆነ ተገልጋይ "ይደፋል!" የሚለው ማስፈራሪያ ትምህርታቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊያደርገው አይችልም። አገልግሎቱን ያልተቀበሉ ሰዎች ከወለሉ ጋር እየተጣበቁ "አምኛለሁ" እስኪሉ ድረስ የሚንገላቱበት ሁኔታ ደግሞ በክርስትና እምነት ውስጥ እንግዳ አሳብ ነው። ክርስቶስ ብዙዎችን ተከታዮች ያፈራው በመስቀል ላይ ዕዳቸውን ከፍሎ በፍቅሩ ስለማረካቸው እንጂ፥ ከወለሉ ስላጣበቃቸው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።

እንዲሁም ደግሞ፥ የሌሎችን ሰዎች መጻሕፍት ገልብጦ ማጣቀሻ ሳይጠቅሱ "የእኔ ነው!" እያሉ የሚያስራጩ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ሰው የሚናገሩትን ለማመን ድፍረት የሚኖራቸው በደመ ነፍስ የሚነዱ አክራሪዎች ብቻ ናቸው!

እንዲሁም ደግሞ፥ የሌሎችን ሰዎች መጻሕፍት ገልብጠ ማጣቀሻ ሳይጠቅሱ "የእኔ ነው!" እያሉ የሚያስራጩ ክርስቲያናዊ ሥነ–ምግባር የጎደላቸው ሰው የሚናገሩትን ለማመን ድፍረት የሚኖራቸው በደመ ነፍስ የሚነዱ አከራሪዎች ብቻ ናቸው!

♣

# 10

# የመገለጥ እውቀት

*"ወደ ጸሎት ስብሰባ እየሄድን ሳለ፥ አሁን ወደ ታላላቅ ነገሮች እየተንቀሳቀስን ነው፤ ወደ መንፈሳዊ ውብ ዛፎች እየመጣን ነው ስል በለሆሳስ ተናገርሁ... መንፈሳዊ ጀግኖችን፥ የላቁ ሰዎች ልንመለከት ነው። በውስጣቸው እግዚአብሔር ስለሚኖር እንደ ተፈጥሯዊው ሰው አይመላለሱም። እነርሱ የፍቅር ቡድን፥ የተአምራት ቡድን፥ የኢየሱስ ቡድን አባላት ናቸው። ከዝቅተኛው [የሰው] ቡድን ተመርቀው ወጥተዋል" – ኬንየን።*

*"በእምነት ፎርሙላ ትምህርትና በኖስቲሲዝም መካከል ሌላም ተመሳሳይነት አለ... ምንም እንኳ ትምህርቱ ከቁሳዊ ጥቅም ጋር በቅርብ የተቆራኘ ቢሆንም፥ ቁሳዊ ዓለም ቁሳዊ ካልሆነው ዓለም ዝቅ ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ ይታያል . . . መንፈሳዊው ዓለም የቁሳዊው ዓለም ጠላት ሆኖ ቀርቧል" – ጆን ፊከት።*

መጀመሪያ "የመገለጥ እውቀት" የሚለውን ሐረግ በእምነት እንቅስቃሴው መዝገበ–ቃላት ውስጥ ያከሉት ኬንየን ናቸው። ኬንየን "ሁለት ዓይነት እውቀት" (The Two Kinds of Knowledge) በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ፥ በስሜት እውቀትና በመገለጥ እውቀት መካከል ያለውን ልዩነት አጉልተው አሳይተዋል። እንደ ሐገን ማብራሪያ፥ የስሜት እውቀት በአምስት የስሜት ሕዋሳቶች እገዛ የሚታወቅ ሲሆን፥ የሳይንሳዊና የማስተዋል ሁሉ ምንጭ ነው። የስሜት እውቀት ለቴክኖሎጂ ዕድገትና ለማንኛውም ዓይነት የሰው ልጅ ሕይወት መሻሻል ከፍተኛ ድርሻ አለው።

ይህም ሆኖ፥ የስሜት እውቀት የሰውን ልጆች የጠለቁ ፍላጎቶች፥ በተለይም ለአምላክ ያለውን ፍላጎት ሊያረኩ እንደማይችሉ ኬንየን ያምናሉ[1]። ይህንኑ የሰው ልጅ ለአምላክ ያለውን ጥማት ሊያረካ የሚችለው የመገለጥ እውቀት ነው[2]። በኬንየን ግንዛቤ፥ የመገለጥ እውቀት የሚከተለው ፍች ይኖረዋል። *የመገለጥ እውቀት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ የተገለጸ ሲሆን፥ የሰው ልጅ የስሜትን እውቀት ግርዶሽ አሽንፎ*

2. ሁለቱም አንደኛውን ዓይነት እውቀት ለማግኘት ሌላኛውን መካድ እንደሚያስፈልግ ያምናሉ።

3. ሁለቱም በዚህ ምድር የእግዚአብሔርን ፍጹም እውቀት ማግኘት እንደሚቻል ያስተምራሉ።

4. ሁለቱም ሥጋዊ ውስንነቶችን ለማለፍ የሚያስችል ትምህርት እንደሚሰጡ ይናገራሉ።

5. ሁለቱም የክርስቲያኖችን ምድብ የማወቂያ መንገድ ያስተምራሉ።

## *ሁለትዮሽ (Dualism)*

ኬንየን እንደሚሉት፥ እውቀት ሁሉ የሚገኘው ከሁለት እርስ በርሳቸው ከማይገናኙ ምንጮች ነው። በመሆኑም፥ የስሜት እውቀት ከታችኛው ቁሳዊ ስፍራ ሲገኝ፥ የመገለጥ እውቀት ደግሞ ከላይ መንፈሳዊ ስፍራ ይገኛል። ከአንደኛው ስፍራ የሚገኘው እውቀት ለሌላኛው የሚሰጠው ፋይዳ አይኖረውም። የሜታፊዚካል ኑፋቄዎች መሥራች የሆኑት ፊኒያስ ቁምቢም በመንፈሳዊና ሥጋዊ እውቀቶች መካከል ፍጹም የሁለትዮሽ አሳብ እንደነበራቸው "Dresser" በሚል ርእስ ከጻፉት መጽሐፍ የሚከተለውን መመልከት ይቻላል።

*"ሁለት አሳቦች አሉ – አንዱ መንፈሳዊና ሌላው ቁሳዊ። ስለ ሰው ስትናገር ስለ ቁስ አካል መናገርህ ነው። ስለ መንፈስ ስትናገር ቁስ አካሉ ከጠፋ ወይም ከሞተ በኋላ ስለሚኖር እውቀት መናገርህ ነው። ይህ መንፈሳዊ እውቀት የክርስቲያኖች ጥበብ ነው።"[3]*

እኚህ ሰው «ከአእምሮ እገዛ ውጭ» ከመንፈሳዊ ስሜቶች የሚመጣው እውቀት ከቁሳዊ ስሜቶች ከሚመጣው እንደሚልቅ አስተምረዋል[4]።

የቁምቢ ደቀ–መዝሙርና የክርስቲያን ሳይንስ መሥራች የነበሩት ሚሪ ቤከር ኤዲም የመንፈስንና የቁስ አካልን ሁለትዮሽ በከረረ መልኩ አስተምረዋል። በእኚህ ወይዘሮ እምነት በስሜት ሕዋሳት አማካኝነት የሚገኘው እውቀት «ስህተት» እና የአእምሮ «የውሸት እምነት» ነው[5]። በተለይም የሚከተለው የኤዲ የእውቀት ትንታኔ ከኬንየን ጋር ያላቸውን የአሳብ ቁርኝት በጥብቅ ያሳያል። እርሳቸው እንደሚሉት፥ እውቀት «ከአምስቱ ሕዋሳት የሚመጣ» ሲሆን፥ መለኮታዊ ያልሆነና የኃጢአት፥ የበሽታና የሞት ምንጭ ነው። ይህም የመንፈሳዊ እውነትና ግንዛቤ ተቃራኒ ነው[6]።

## ስሜታዊውን እውነታ መካድ

ኬንየን አንድ አማኝ በመገለጥ እውቀት ለመመላለስ ከፈለገ የስሜትን እውቀት መካድ እንዳለበት አስረምረዋል። እንደኛህ ሰው መረዳት ሁልጊዜም በስሜቶቻችንና በዓለም መካከል ግጭት ይኖራል[7]። በመሆኑም፥ «ስሜቶች ተገቢ ስፍራቸውን በመውሰድ፥ ለመንፈስ የኑባሬህ ጌታ የመሆኑን ተግባር

ሲሆን፥ መለኮታዊ ያልሆነና የኃጢአት፥ የበሽታና የሞት ምንጭ ነው። ይህም የመንፈሳዊ እውነትና ግንዛቤ ተቃራኒ ነው[6]።

## ስሜታዊውን እውነታ መካድ

ኬንየን አንድ አማኝ በመገለጥ እውቀት ለመመላለስ ከፈለገ የስሜትን እውቀት መካድ እንዳለበት አስረምረዋል። እንደኘህ ሰው መረዳት ሁልጊዜም በስሜቶቻችንና በዓለም መካከል ግጭት ይኖራል[7]። በመሆኑም፥ «ስሜቶች ተገቢ ስፍራቸውን በመውሰድ፥ ለመንፈስ የኑባሬህ ጌታ የመሆኑን ተግባር የሚሰጡት መንፈስ አስተሳሰብህን ለመግዛት ሲችል ነው።"[8] የእግዚአብሔርን ነገሮች ለማወቅ ከአእምሮ ዘልቆ በማለፍ በውስጣዊው ሰው (ማለትም ልብ ወይም መንፈስ) መገልገል እንደሚያስፈልግ የሚናገሩት ሐገንም የኬንየንን ፀረ–ምሁራዊ አመለካከት እንደያዙ ግልጽ ነው[9]።

በተለይም የስሜትን ጉዳይ በጉልህ የምንመለከተው በፈውስ ዶክትሪናቸው ውስጥ ነው። ኬንየን እንደሚሉት፥ "የእምነት ኑዛዜ ሁልጊዜም ከፈውስ ይቀድማል። ስሜትህን፥ የበሽታን ምልክት ሳትመለከት ቃሉን እመን።[10] የወይዘሮ ሜሪም አሳብ ከዚህ የራቀ አይደለም። "ሳይንስና ጤንነት" በሚል ርእስ ባሳተሙት የክርስቲያን ሳይንስ መጽሐፍ ውስጥ፥ "የስሜት ሕዋሳት የክፋት ወይም የስህተት ምንጮች ብቻ ናቸው። ክርስቲያን ሳይንስ ውሸተኞች እንደሆኑ ያረጋግጣል" የሚሉ ቃላት አስፍረዋል።

## ፍጹም እውቀት

እንደ ኑፋቄዎቹ ሁሉ ኬንየንም በዚህ ሕይወት ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን እውቀት መለማመድ እንደሚቻል ያምናሉ።

ኬንየንና ትራይን እንደሚሉት፥ አማኝ ይህንን ፍጹም እውቀት ሲያገኝና የስሜትን እውቀት ሲያስወግድ፥ ሥጋዊ ውስንነቶችን አልፎ በቀጣይ መገለጦች ይረማመዳል። ኬንየን "ወሰን ከሌለው አካል ጋር ስለተባበረ በውስንነቶች እንደማይታቀብ"[11] ይናገራሉ። ትራይንም በበኩላቸው፥ "ከማንኛውም ሥጋዊ ወኪል አገዛዝ ሥር ልንኖር አይገባም!"[12] ካሉ በኋላ፥ በመቀጠል "የተወለድነው በአካባቢያችን ላይ ተቀናቃኝ የሌለው ቁጥጥር እንዲኖረን ነው"[13] ብለዋል።

ከዚህም በላይ እነ ኬንየን ይህንን የመገለጥ እውቀት ባገኙትና ባላገኙት አማኞች መካከል ልዩነት እንዳለ ያመለክታሉ። እንደ እነርሱ ትምህርት፥ ሁሉም አማኝ እኩል አይደለም።

*"እኛ ተራ ሰዎች አይደለንም። ይህ የመገለጥ እውቀት ከተራ ስፍራ ወደ ላቀ ደረጃ ይወስደናል። እናንተ እውነተኛ የላቃችሁ ሴቶችና ወንዶች ናችሁ።*

*የብልጽግናችን ምንጭ ለሆነው የውስጥ ሀሳቄ ሀልውና በመታዘዝ አማካኝነት ማስተማር ነው።"*[16]

## *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ*

"ዘ ኦክስፎርድ ዲክሽኔሪ ኦፍ ዘ ክርስቲያን ቸርች" እንደገለጸው፥ ኖስቲሲዝም ማለትም እውቀት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ልጆች ጅማሬና ፍጻሜ እንደተገለጸ ተደርጎ የሚወሰድ እውቀት ሲሆን፥ በሰው ውስጥ የሚገኘው መንፈስ ደኅንነትን ሊያገኝ የሚችልበት መንገድ ተደርጎ ይታመናል።" እነ ሩዶልፍ ቡልትማን እንደሚሉት ደግሞ የዚህ ዓይነቱ እውቀት አንድን ሰው ከተራ የሰው ደረጃ ወደ አምላክነት ያሸጋግራል ተብሎ ይታመናል[17]።

በእምነት አራማጆች ዘንድ ሰው ማለት መንፈስ ስለሆነ፥ *ሥጋዊው* ሰውነት ይህንኑ መለኮታዊ እውቀት ለመቀበልም ሆነ ለመገልገል አይችልም። እናም በስሜት ሕዋሳት አማካኝነት የሚገኘው እውቀት ተቀባይነት አይኖረውም።

የእነርሱ አሳብ እውነት ከሆነ፥ ሐዋርያት "አየን– ሰማን" እያሉ የስሜት ሕዋሳትን ጠቀሜታ በሚያጎላብት መልኩ የጻፉት ሁሉ ፋይዳ–ቢስ መሆኑ ነው። "ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን" (1ኛ ዮሐንስ 1፡1)። "ቃልም ሥጋ ሆነ"(ዮሐንስ 1፡14) የተባለለትና "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ እንደሚኖር" (ቆላስይስ 1፡9) የተጻፈለት ክርስቶስም ራሱ ከስሜት ሕዋሳቶች ለሚገኝ እውቀት ርባና እንደሚሰጥ በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ፥ የእምነት አስተማሪዎችም ሆኑ የኖስቲሲዝም ሰባኪዎች የሚቃወሙት የአእምሮ እውቀት የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የሚሰጠው አይደለም። የእግዚአብሔርን ነገሮች ለማግኘት ከአእምሮ እውቀት ማለፍ እንደሚገባ ሐገን ይናገራሉ።

ምንም እንኳ በራሳችን የአእምሮ እውቀት እግዚአብሔርን መርምረን ልናገኝ ባንችልም፥ በቃሉና በመንፈሱ አማካኝነት የሚገለጥልንን ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጠን አእምሮ ልናመዛዝን እንችላለን። ስለሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ አእምሯችንን እንዳንጠቀም አላዘዘንም። ይልቁንም፥

"በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ [ይህ የአእምሮና የልብ ሥራ እንደሆነ ልብ ይሏል!] በፍጹምም ኃይልህ፥ ጌታ አምላክህን ውደድ" (ማርቆስ 12፡30)። "በላይ ያለውን አስቡ" (ቆላስይስ 3፡1) ተብለን ተመክረናል።

ዘንድ በተሰጠን አእምሮ ልናመዛዝን እንችላለን። ስለሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ አእምሯችንን እንዳንጠቀም አላዘዘንም። ይልቁንም፥

"በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ [ይህ የአእምሮና የልብ ሥራ እንደሆነ ልብ ይሏል!] በፍጹምም ኃይልህ፥ ጌታ አምላክህን ውደድ" (ማርቆስ 12፡30)። "በላይ ያለውን <u>አስቡ</u>" (ቆላስይስ 3፡1) ተብለን ተመክረናል።

በሌላ በኩል፥ ከኖስቲሲዝም የተወረሰው የእምነት አስተማሪዎች የእውቀት ጽንሰ–አሳብ በዚህ ምድር ፍጹም እውቀት ማግኘት እንደሚቻል የሚናገር መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጾአል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ መልስ አለው።

*"ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ... እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን። ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ" (1ኛ ቆሮንቶስ 13፡9–12)።*

ይህንን እውቀት ነው እንግዲህ የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች አንዱን አማኝ ከሌላው ለመለየት የሚጠቀሙት። ብዙ የመገለጥ እውቀት ካለው ሰውዬው ወደ መለኮትነት እንዳደገ ይነገራል። መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን ለዚህ ስፍራ የለውም።

*"ጸጋው በእምነት አድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌሶን 2፡8–9)።*

ሁላችንም በጸጋ የዳንን ኃጢአተኞች ስለሆንን፥ የምንመካበት እውቀትም ሆነ ምንም ነገር የለንም። የጸጋ ስጦታዎችንም የወሰድን እንደሆነ፥ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ "ለጋራ ጥቅም" የሚውሉ እንጂ (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7 – ከ1980 የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይመልከቱ)፥ "ተገለጠልኝ፤ አወቅሁ" ብለው የሚኩራሩበት አይደለም።

*"እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል። ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም፤ ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው» (1ኛ ቆሮንቶስ 8፡1–3)።*

እጅግ በታወቀው የፍቅር ምዕራፍ ውስጥም ጳውሎስ ፍቅር በክርስቲያን ሕይወት ከምንም በላይ እንደሆነ ገልጧል።

*"ትንቢትም ቢኖረኝ፥ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትንም ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስከፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ" (1ኛ ቆሮንቶስ 13፡3)።*

ጌታችንም ያለው ሰዎች በፍቅራችን እንደሚያውቁን እንጂ በእውቀታችን እንደሚያደንቁን አይደለም።

# 11

# የእምነት እንቅስቃሴ ከኒው ኤጅ ጋር ሲነጻጸር

*«አንድ ጊዜ ሁላችንም አምላክ መሆናችንን ከተገነዘብንና አምላካዊ ባህርይ እንዳለን ከተረዳን በኋላ፥ የሰብአዊ ሕይወት ሙሉ ግላማ በውስጣችን ያለውን አምላካዊነት መልሶ ለመጨበጥ መትጋት ይመስለኛል። በዚህም ፍጹም ፍቅር፥ ፍጹም ጥበብ፥ ፍጹም መረዳት፥ ፍጹም ጉብዝና እንቀዳጃለን። ይህም ሲሆን፥ የኋለኛውን አርጊ ነገር መልሰን እንፈጥራለን። የምንፈጥረውም ያንኑ አስፈላጊ ነገር አንድነት ማለትም ንቃት (consciousness) ነው" (ሺርሊ ገልያን - የኒው ኤጅ አራማጅ)።*

*"እነዚህ እውነቶች ሕይወታችንን ሲቆጣጠሩ፥ መንፈሳዊ ምጡቅ ሰዎች፥ የአጋንንትና የበሽታ ጌቶች ያደርጉናል። ይህም የዝለትና የውድቀት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ሁሉም ነገር የእኛ ስለሆነ፥ ለእምነት የሚደረግ ትግል አይኖርም። እርሱም በውስጣችን ስለሚሆን፥ ለኃይል የሚቀርብ ጸሎት አይኖርም... በእነዚህ ድንቅ እውነታዎች ብድግ ብለን ሰፍራችንን እንይዛለን። ስንወጣም በእግዚአብሔር እንደተሞሉ ምጡቅ ሰዎች እንኖራለን"* (የእምነት እንቅስቃሴ አራማጁ ኬንየን)።

ብዙ ሰዎች "ሰው አምላክ ነው" የሚለውን አሳብ ሲሰሙ ወዲያውኑ አሳቡን ከኒው ኤጅ ጋር ያዛምዱታል። እኔም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን ምዕራፍ ያካተትሁት ቀደም ብለን የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች የሰውን አምላክነት በተመለከተ የሚያነሡአቸውን ነጥቦች የዳሰስን በመሆኑ ነው። አስቀድመን በአንድነት (Identification) ምዕራፍ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች እኛ "ክርስቶስ ነን!" ሲሉ ይናገራሉ።

ትናንሽ አማልክት ነን የሚሉትን ወገኖች ከኒው ኤጅ ጋር በፈረጀበት ንዑስ የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ አንድ ጸሐፊ የሚከተሉትን ነጥቦች ነካክቶ ነበር። ሚካኤል የተባለው ይኸው ጸሐፊ ኒው ኤጅ ሁለት ዓይነተኛ ዓላማዎች እንዳሉት ከጠቀሰ በኋላ፥ የትናንሽ አማልክትንም አስተምህሮ ከዚያው አኳያ ይዘግባል።

አምላክነት በተመለከተ የሚያነሡአቸውን ነጥቦች የዳሰስን በመሆኑ ነው። አስቀድመን በአንድነት (Identification) ምዕራፍ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች እኛ "ክርስቶስ ነን!" ሲሉ ይናገራሉ።

ትናንሽ አማልክት ነን የሚሉትን ወገኖች ከኒው ኤጅ ጋር በፈረጀበት ንዑስ የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ አንድ ጸሐፊ የሚከተሉትን ነጥቦች ነካክቶ ነበር። ሚካኤል የተባለው ይኸው ጸሐፊ ኒው ኤጅ ሁለት ዓይነተኛ ዓላማዎች እንዳሉት ከጠቀሰ በኋላ፥ የትናንሽ አማልክትንም አስተምህሮ ከዚያው አኳያ ይዘግባል።

"ፖልክም ሁለት ዓይነተኛ ዓላማዎች ያሉት ይመስላል – ግላዊ መለወጥ ማለትም ትናንሽ አማልክት እንደሆንን በመረዳት ወደ ብስለት ማደግና 'ፕላኔትሪ' መለወጥ ማለትም የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ መመሥረት። ፖልክ እንደሚለው፥ ክርስቲያኖች ከቶውንም እንደ ትናንሽ አማልክት ያላቸውን ስፍራ ያልተገነዘቡ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያንም ራሷ ዋንኛ የኃይል ምንጭ እንደሆነች አልተረዳችም፤ ስለሆነም፥ መንግሥቱ ሊገለጥ አይችልም።

"ፖልክ ሲጽፍ፥ 'እግዚአብሔር ሰውን በምሳሌያችን እንፍጠር ሲል፥ እንደ ትናንሽ አማልክት የፈጠረን ቢሆንም፥ ይህንኑ መረዳት ይሳነናል' ብሏል። እኛ ራሳችንን የምንመለከተው በጣም ትንሽ ኃይል እንዳለን ትናንሽ ሰዎች ነው። እንደዚህ ሰው ትናንሽ አማልክት መሆናችንን እስካልተገነዘብንና በዚያውም አኳያ ተግባራችንን ማከናወን እስካልጀመርን ድረስ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ልንገልጥ አንችልም።"

ሚካኤል እንዳጤነው፥ በዚሁ የትናንሽ አማልክት አስተማሪና በኒው ኤጅ መካከል አምስት ተመሳሳይነቶች ተስተውለዋል።

| <u>ኒው ኤጅ</u> | <u>ኤርል ፖልክ</u> |
|---|---|
| 1. *አምላክ ከውስጥህ እንዳለ ተገንዘብ* | 1. *ትናንሽ አማልክት መሆናችንን ተገንዘብ (ሐገንም በውስጥ ምስክርነቶች እንደተናገሩ ያስታውሱ።)* |
| 2. *ግንዛቤን በመለወጥ ወደ እውቀት መምጣት* | 2. *አዳዲስ መገለጦችን በማግኘት ወደ እውቀት መምጣት* |
| 3. *የአእምሮን አንድነትና ዓላማን ማግኘት* | 3. *የእምነትን አንድነትና ዓላማን ማግኘት* |
| 4. *ወደ ግላዊ መለወጥ በሚያድግ መልኩ* | 4. *ወደ ሕያውነት በሚያድግ* |

ለማንኛውም የእምነት እንቅስቃሴ ከዚሁ የኒው ኤጅ ትምህርት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ለመመልከት የኬንየን ትምህርት ምንጭ እንደሆነ ቀደም ብለን ከተመለከትንበት *አዲስ አሳብ (New Thouhgt)* ብንነሣ የሚሻል ይመስለኛል። ስለሆነም፥ የአዲስ አሳብ ፍልስፍና በሚያተኩርባቸው ነጥቦች መጀመሩ ጠቃሚ ይሆናል።

- *ቀደምት መነሾዎቹ በሙሉ ውስጣዊ ኃይላት ናቸው። (ውጫዊው እግዚአብሔር በዚህ ላይ አምብዛም ስፍራ የለውም ማለት ነው።)*
- *የጉድለቶችና የሥርዓት– አልበኝነቶች ሁሉ መፍትሔ የሚመጣው ከሜታፊዚክስ ነው።*
- *እግዚአብሔር እጅግ የቀረበ፥ በመንፈሱ በእኛ ውስጥ የሚያድር፥ ሁሉን አዋቂ፥ በሁለንተናው መልካም፥ አጽናፈ–ዓለሙን ሁሉ የሞላ ነው። ስለሆነም፥ ከፋት በዘለቄታዊ መልኩ በዓለም ውስጥ ስፍራ የለውም – የመልካምነትን አለመኖር ስለሚያሳይ።*
- *አዲሱ አሳብ በሽታ፥ ድህነትና ማንኛውም ክፉ ነገር የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል እንዳልሆነ ያምናል።*
- የእግዚአብሔር ህልውና ልምምድ ወደ ሳይንሳዊ ዘዴ ዝቅ እንዳለ፥ በእምነት አንድነት አማካኝነት ከራስ ወዳድነት የራቀ ሕይወት ስለመኖርም ያትታል።

አንድ ምሁር አዲሱን አሳብ እንዲህ ገልጾታል።

*"ይኸ ዓላማና እነዚህ መመሪያዎች የእግዚአብሔርን ቅርበት፥ የሰውን መለኮታዊነት፥ የእግዚአብሔርን ለሰው በተፈለገ ስፍራ መገኘት፥ የአጽናፈ–ዓለሙን መንፈሳዊ ባሕርይ፥ የኃጢአትን፥ የሰብአዊ ጉድለትንና የበሽታን የተሳሳተ አሳብ ውጤትነት ያጎላል። በርካታ የአዲሱ አሳብ ቡድኖች የኢየሱስን አስተማሪነትና ፈዋሽነት በማጉላት፥ መንግሥቱ በሰው ውስጥ እንደሚገኝ ያውጃሉ . . . የአዲሱ አሳብ መሪዎች የሀብት ብልጽግና የአዲሱ አሳብ አንዱ ውጤት እንደሆነ በአጽንኦት ያስተምራሉ። አዲሱ እምነት የዓለምን አንድ መሆን (ሞኒዝም) ቢያመለክትም፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍተኛ የሁለትዮሽ (Gnostic Dualism) ባሕርይ ይታይበታል! ይህም ማለት ምንም እንኳ አዲሱ አሳብ ለሁሉም ከፍት ቢሆንም፥ መንፈሳዊ ፈውስና የአእምሮ ብሎም የአካል ብርታት የሚመጣው ግንዛቤው ላላቸውና በአንድ ወቅት ወደ እንቅስቃሴው ለገቡት እንደሆነ ማስተማሩ ነው"["New Thought," Encyclopedia Britanica (15th Ed., 1983), Vol. 13, P. 15).*

በሌላ በኩል፥ 'ሁሉም አንድ ነው' የሚለው ዓረፍተ–ነገር አዲሱን አሳብ ከአዲሱ ዘመን (New Age) ጋር እንደሚያዛምደው መመልከቱ ተገቢ ነው። ጉዳዩን ከተከታተሉ በኋላ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ለኅትመት ያበቁት ግለሰብ የሚከተለውን ብለዋል።

*መሆን (ሞኒዝም) ቢያመለክትም፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍተኛ የሁለትዮሽ (Gnostic Dualism) ባሕርይ ይታይበታል፤ ይህም ማለት ምንም እንኳ አዲሱ አሳብ ለሁሉም ክፍት ቢሆንም፥ መንፈሳዊ ፈውስና የአእምሮ ብሎም የአካል ብርታት የሚመጣው ግንዛቤው ላላቸውና በአንድ ወቅት ወደ እንቅስቃሴው ለገቡት እንደሆነ ማስተማሩ ነው"["New Thought," Encyclopedia Britanica (15th Ed., 1983), Vol. 13, P. 15).*

በሌላ በኩል፥ 'ሁሉም አንድ ነው' የሚለው ዓረፍተ-ነገር አዲሱን አሳብ ከአዲሱ ዘመን (New Age) ጋር እንደሚያዛምደው መመልከቱ ተገቢ ነው። ጉዳዩን ከተከታተሉ በኋላ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን ለኅትመት ያበቁት ግለሰብ የሚከተለውን ብለዋል።

*"ይህ ሁሉም አንድ ነው የሚለው አሳብ ለአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መሠረት ነው። በመሆኑም፥ በተለያዩ የመገለጫ መንገዶቹ እንዲንቀሳቀስ ይረዳዋል – ከሙሉ ጤንነት ወደ አዲሱ ፊዚክስ፥ ከፖለቲካ ወደ ሳይኮሎጂ፥ ከምሥራቃውያን ሃይማኖት ወደ ምትሐት። ለዚህ አሳብ የተሰጠው ሌላው ስም 'ሞኒዝም' የተሰኘ ነው። 'ሞኖ' ማለት አንድ ማለት ስለሆነ፥ ሞኒዝም ሁሉም ነገር አንድ ነው ተብሎ ይተረጎማል። ሁሉም የተያያዘ፥ እርስ በርሱ የሚደጋገፍና እርስ በርሱ ጣልቃ የሚገባ ነው። በአጠቃላይ አነጋገር፥ በእግዚአብሔር፥ በሰው፥ በካሮትና በድንጋይ መካከል ምንም ልዩነት የለም።*

*"የአዲሱ ዘመን መለኮታዊ ትምህርት የሆነው ሞኒዝም፥ ከክርስትና እምነት ሙሉ ለሙሉ ይቃረናል። የክርስትናው ዓለም፥ የእግዚአብሔር ፍጥረት ያልተከፋፈለ አንድነት ሳይሆን ይልቁንም የተለያዩ ነገሮች፥ ክስተቶችና ሰዎችን ያካተተ መሆኑን ያረጋግጣል። በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ፥ እግዚአብሔር የተለያዩ ነገሮችን እንደፈጠረ እናነባለን። እግዚአብሔር ብርሃንን ከጨለማ፥ ቀንን ከሌሊት፥ ምድርን ከሰማይ እንዲሁም የብስን ከባሕር ለይቷል። ከዚያም እንስሳትንና ዕፅዋትን እንደየወገናቸው ፈጥሯል። በመሆኑም፥ ፍጥረት ልዩነት የሌለባቸው ነገሮች የሚገኙበት አንድነት ሳይሆን፥ በርካታ የተለያዩ ነገሮች የሚስተዋሉበት ነው... " (Unmasking New Age)*

ከላይ እንደተመለከትነው፥ ኬንየን የእምነት እንቅስቃሴን ለማዋቀር የተጠቀሙባቸው የአንድ አሳብ፥ የክርስቲያን ሳይንስና ሌሎች ሜታፊዚካል ኑፋቄዎች እርስ በርሳቸው እየተሳሳቡ የኒው ኤጅን ጠርዝ እንደሚነኩ ግልጽ ነው። ይህንን ስንመለከት፥ ሚስተር ቤንሂን ከእምነት እንቅስቃሴ ትምህርት ንስሐ ገብቼ ተመልሻለሁ ባሉበት ወቅት፥ "የእምነት እንቅስቃሴ ኒው ኤጅ ነው!" ሲሉ የሰነዘሩት አሳብ መሠረት እንዳለው እንረዳለን።

*"እምነት፥ እምነት፥ እምነት ብቻ። ኢየሱስ የትም ቦታ አይታይም። እምነታችን ሊያርፍ የሚገባው የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። ስለዚህ የእምነት አቋሜ ምን ይሆናል? እምነትን መፈለግ ትቼ ጌታን መሻት እጀምራለሁ። የእምነት ቃል ትምህርት*

*"የኒውኤጅ ተከታዮች (New Agers) አማልክት እንደሆኑ ይናገራሉ፤ ሞርሞኖችም አማልክት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይሰብካሉ፤ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሳይቀር ብዙ ካሪዝማቲኮች ትናንሽ አማልክት እንደሆኑ በድፍረት በማወጅ ላይ ናቸው። አንዳንዶቹም አማልክት አይደለንም ማለቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን እንደማይችል ይናገራሉ"* ኔ ለዋል።

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን የቀድሞው ፕሬዝዶንትና ነቢይ የነበሩት ሎረንዞ ስኖው፥ "ድሮም እግዚአብሔር እንደ ዛሬው ሰው ነበር፤ ወደፊት ሰው እንደ እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል" ሲሉ ባስተማሩት መሠረት፥ ሞርሞኖች አማልክት ለመሆን ይጣጣራሉ።

መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን፥ "እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው" ይላል (ዘዳ. 6:4)። በአዲስ ኪዳንም፥ "ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን" ተብሎ ተጽፎአል(1ኛቆሮ. 8:4፤ 1ኛተሰ. 1:9) )።

የአዲሱ ዘመን (New Age) እንቅስቃሴ አራማጆች "ሁሉም አምላክ ነው" (pantheism) የሚል አመለካከት አላቸው። እነዚህ ሰዎች ስለ እውነታ ሁለት ነገሮችን ያረጋግጣሉ – የእውነት ሁሉ አንድነትና የዚያ አንድነት መለኮትነት! ሁላችንም በውስጣዊ ባህርያችን አንድ ስለሆንንና የሁሉም አካል ስለሆንን፥ አንድ ቀን ወደ እግዚአብሔር ኑባሬ በመመለስ ከሁሉው ጋር እንቀየጣለን።

ለአዲሱ እንቅስቃሴ አራማጆች፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልካም ፈቃድና የፍቅር ግንኙነት ያለው ኑባሬያዊ አምላክ ሳይሆን፥ "የኑባሬ ቀጥተኛ አንድነት" (a literal oneness of being) ነው። ማይክል እንዳስተዋሉት፥ በዚህ ምክንያት ነበር የኒው ኤጅ ሺርሊ ማክላይን ከባሕር ዳርቻ ላይ ተጀንነው በመቆም "እኔ እግዚአብሔር ነኝ! " ሲሉ ያለ ፍርሃትና ኃፍረት ያስተጋቡት። እንደ እርሳቸው አባባል፥ የሰው ዘር ትልቁ አሳዛኝ ነገር እያንዳንዳችን መለኮትነታችንን መዘንጋታችን ነው።

ወደ እምነት ሥነ–መለኮት ስንመጣ ደግሞ፥ በኃጢአት መውደቅ የሰይጣንን ባህርይ መውረስ፥ ደኅንነት ደግሞ አምላክነት እንደሆነ ይነገረናል። እውነታው ግን፥ ደኅንነት ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ለአዳም ወደታቀደለት ደረጃ ሁሉ የሚታደስበት ሂደት ነው። ደኅንነት ሕይወታችንን የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ወደ መሆን የሚለውጥ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ቢሆንም፥ በየትኛውም ስፍራ የክርስቶስን ያህል ሥጋ– ለባሽ አማልክት እንደምንሆን አልተነገረንም። ይህ ቀድሞውንም የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አዳምና ሔዋንን የጣለ አምላክ የመሆን ምኞት እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ባለመሆኑ ልንጠነቀቅበት የሚገባን ነው።

ያስተጋቡት። እንደ እርሳቸው አባባል፥ የሰው ዘር ትልቁ አሳዛኝ ነገር እያንዳንዳችን መለኮትነታችንን መዘንጋታችን ነው።

ወደ እምነት ሥነ-መለኮት ስንመጣ ደግሞ፥ በኃጢአት መውደቅ የሰይጣንን ባህርይ መውረስ፥ ደኅንነት ደግሞ አምላክነት እንደሆነ ይነገረናል። እውነታው ግን፥ ደኅንነት ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ለአዳም ወደታቀደለት ደረጃ ሁሉ የሚታደስበት ሂደት ነው። ደኅንነት ሕይወታችንን የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ወደ መሆን የሚለውጥ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ቢሆንም፥ በየትኛውም ስፍራ የክርስቶስን ያህል ሥጋ- ለባሽ አማልክት እንደምንሆን አልተነገረንም። ይህ ቀድሞውንም የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አዳምና ሔዋንን የጣለ አምላክ የመሆን ምኞት እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ባለመሆኑ ልንጠነቀቅበት የሚገባን ነው።

## 'አማልክት ናችሁ'...

ይሁንና፥ መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል 10፡ 34-35 ከመዝሙር (82):6 በመጥቀስ፥ እንዲህ ይላል፡

*"ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። 'እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ' ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥ የእግዚአብሔር ልጅ ስላልሁ አናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን 'ትሳደባለህ' ትሉታላችሁን?"*

በዚህ ክፍል፥ አይሁዶች ራሱ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ለመቀበል ተቸግረው እንደነበር እንመለከታለን። ስለሆነም፥ ሰው ሆኖ ሳለ አምላክ ነኝ እንደሚል ሐሰተኛ ቆጥረው ሊወግሩት ድንጋይ አነሡበት። ኢየሱስም ሁልጊዜም እንደሚያደርገው ወደ ብሉይ ኪዳን በማጣቀስ፥ እንኳንስና ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ የመጣው ቀርቶ "እነዚያ የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውም[ሰዎች] "አማልክት" ተብለው እንደተጠሩ ያስረዳል። እነዚህ "አማልክት" የሚል ማዕረግ የተሰጣቸው ሰዎች እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም የሚጠቀምባቸው ፈራጆች፥ ነቢያትና እንደ ሙሴ ያሉ ሕግ ሰጪዎች ነበሩ።

ለምሳሌ፥ በዘጸአት 21፡6፥ 22፡ ከቁጥር 8 ጀምሮ፥ ወዘተ. . . ይህንኑ እውነት እንመለከታለን። በነዚህ ስፍራዎች "ፈራጆች" ተብለው የተጠቀሱት በአንዳንድ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ "አማልክት" ተብለዋል።

ሙሴም በዘጸአት 18፡ ከቁጥር 15 ጀምሮ፥ "ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ እኔ ይመጣሉ፤ ነገርም ቢኖራቸው ወደ እኔ ይመጣሉ፥ በዚህና

ማከናወናቸው እንጂ የዘመኑ ፈላስፎች እንደሚሉት የአምላካዊነት ኑባሬ(being) የመጋራታቸው አይደለም።

## የመለኮት ባህርይ ተካፋይነት

ሌላው አንዳንድ ካሪዝማቲኮችና የእምነት መምህራን የሚጠቅሱት በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡4፥ "ስለ ክፉ ምኞች በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ *ከመለኮት ባህርይ ተካፋዮች* በተስፋ እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን" የሚለው ነው።

ክፍሉ የሚያሳየው የእግዚአብሔር *ባህርይ* ተካፋዮች እንደምንሆን እንጂ፥ *የኑባሬው (being)* ተካፋዮች እንደምንሆን አይደለም። ዶክተር ዌርዝቢ "ንቃ" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንደጠቀሱት፥ ጴጥሮስ *ባህርይ* የሚለውን ቃል የመረጠው ዕድገትን፥ ጠባይን፥ ወዘተ. . . ስለሚያመለክት ነው። ማይክል ሞሪያሪቲ እንደሚሉት፥ ዓለማውያን ኃጢአትን የሚለማመዱት ከተበላሸው ባህርያቸው የተነሣ ነው። ክርስቲያኖች ግን በውስጣቸው የእግዚአብሔር ባህርይ ስላላቸው፥ ኃጢአትን አያደርጉም (1ኛ ዮሐንስ 3፡9)።

ማይክል እንደሚሉት፥ ባህርይ የአበላልና የአሠራር ልማድን ይወስናል። ውሻ የራሱንም ትውከት ሳይቀር ይመገባል፤ በግ ግን ለምለም ሣር ይፈልጋል። በተመሣሣይ ሁኔታ፥ የማያምኑ ሰዎች ባህርይ እንደ ሥጋቸው ምኞት ለመኖር ሲፈልግ፥ የክርስቲያኖች ባህርይ ግን እግዚአብሔርን ለማስደሰት ይፈልጋል።

በመሆኑም፥ የክፍሉ መልእክት ክርስቲያኖች በውስጣቸው ከሚኖረው መንፈስ ቅዱስ የተነሣ ያገኙትን መለኮታዊ ባህርይ በማሳደግ እግዚአብሔርን ከማያስደስት መንገድ ርቀው እንዲኖሩ እንጂ፥ በምንም መልኩ ክርስቲያኖች አምላክ ናቸው የሚል አይደለም። ሰው በፈጣሪው ላይ ተደግፎ የሚኖር ፍጡር እንጂ፥ ከቶውንም የዘላለማዊውን አምላክ ስፍራ የሚሻማ ሊሆን አይችልም። *"ልብህን እንደ እግዚአብሔር ልብ ብታደርግም <u>አንተ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም</u>" (ሕዝቅኤል 18፡1)።*

በመሆኑም፥ ከዚህ በላይ ስለ ሰው አምላክነት ከሚቀርበው ዘገባ፥ ከአዲሱ አሳብ ግንዛቤና ከሌሎችም አሳቦች ሳቢያ፥ የእምነት እንቅስቃሴ አደገኛ ስፍራ ላይ እንደሚገኝ ልንመለከት እንችላለን። ይሁንና፥ ኒው ኤጅ በርካታ ምንጮች ያሉትና የተደበላለቀ ፍልስፍና በመሆኑ፥ ከአንድ የእምነት ዘርፍ ጋር ለመፈረጅ አዳጋች እንደሚሆን እሙን ነው። ስለሆነም ራሱ ኒው ኤጅ ነው ማለቱ ማጋነን ከሆነ፥ ወደ ኒው ኤጅ የሚያሻግር ድልድይ ነው ማለት ይቻላል።

የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎችም እንደኛው የኒው ኤጅን ትምህርት እንደሚቃወሙ ከጽሑፎቻቸው ለመመልከት ይቻላል። ይህም ሆኖ፥

ከማያስደስት መንገድ ርቀው እንዲኖሩ እንጂ፥ በምንም መልኩ ክርስቲያኖች አምላክ ናቸው የሚል አይደለም። ሰው በፈጣሪው ላይ ተደግፎ የሚኖር ፍጡር እንጂ፥ ከቶውንም የዘላለማዊውን አምላክ ስፍራ የሚሻማ ሊሆን አይችልም። *"ልብህን እንደ እግዚአብሔር ልብ ብታደርግም <u>አንተ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም</u>" (ሕዝቅኤል 18:1)።*

በመሆኑም፥ ከዚህ በላይ ስለ ሰው አምላክነት ከሚቀርበው ዘገባ፥ ከአዲሱ አሳብ ግንዛቤና ከሌሎችም አሳቦች ሳቢያ፥ የእምነት እንቅስቃሴ አደገኛ ስፍራ ላይ እንደሚገኝ ልንመለከት እንችላለን። ይሁንና፥ ኒው ኤጅ በርካታ ምንጮች ያሉትና የተደበላለቀ ፍልስፍና በመሆኑ፥ ከአንድ የእምነት ዘርፍ ጋር ለመፈረጅ አዳጋች እንደሚሆን እሙን ነው። ስለሆነም ራሱ ኒው ኤጅ ነው ማለቱ ማጋነን ከሆነ፥ ወደ ኒው ኤጅ የሚያሻግር ድልድይ ነው ማለት ይቻላል።

የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎችም እንደኛው የኒው ኤጅን ትምህርት እንደሚቃወሙ ከጽሑፎቻቸው ለመመልከት ይቻላል። ይህም ሆኖ፥ ሳያውቁም ይሁን አውቀው ከሚነቅፉት ኒው ኤጅ ጋር ትከሻ ለትከሻ ሲጋፉ ይታያል። ስለሆነም፥ በዚህ አካሄዳቸው በሁሉም መልኩ ዓለምን ለመቆጣጠር ለሚጣደፈው ኒው ኤጅ በር መክፈታቸው እሙን ነው። እናም የእምነት እንቅስቃሴ አስተማሪዎች የመሰናከያ ዓለት ላለመሆን እንዲጠነቀቁና ሕዝበ ክርስቲያንም የሚሰማውን አዲስ ትምህርት ከመቀበሉ በፊት ከጌታ ቃል ጋር በጥብቅ እንዲያመሳክር ለማሳሰብ እሻለሁ። አዲስ ስለ መስለን ብቻ መከተሉ ተገቢ አይሆንምና።

*"አሮጌው ሁሉ ወርቅ ላይሆን ይችላል፤ አዲስ ስለሆነም እውነት ሊሆን አይችልም።"*

♣

# 12

# የእምነት እንቅስቃሴና የሳቅ ሪቫይቫል

*"...በዚያን ምሽት በአዳራሹ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሳቅ አስተጋባ፤ እኔና ጎልዴ (ባለቤታቸው) ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ሐሴት አደረግን። ሳቁ ከውስጣችን ዝም ብሎ ፈለቀና በአዲስ ጥንካሬ ሞላን። ሸክሞቻችን ሁሉ ከላያችን ላይ የተነሣ ይመስል በደመና ላይ እንደሚራመድ ሰው ሆነን ከአዳራሹ ወጣን።" (ዶናልድ ፒርሰን ለዎርድ ኦፍ ፌይዝ መጽሔት ፌብሯሪ 1996 እትም ከሰጡት ምስክርነት የተቀነጨበ።)*

ጋዜጠኛው ሮበርት ሑፍም ለቶሮንቶ ላይፍ መጽሔት ባቀረበው ዘገባ የሚከተለውን አትቷል።

*"ከአጠገቤ የተቀመጠው ሰውዬ ልክ እንደ ቆሰለ አንበሳ ያጓራ ጀመር። ከእርሱ አጠገብ የተቀመጠችው ሴት እጆቿ በመንቀጥቀጧ እጆቿ ፊቷን ይጠፈጥፉ ገባ። ሰዎች ወንበሮችን እያመነቃቀሩ ከወለሉ ላይ ይዘረገፉሉ። እንደ ተኩላም እንደ አህያም እያደረጋቸው መጮሃቸውን ቀጠሉ፤ ከሙዚቃ መሣሪያዎቹ አጠገብ የቆመው አንድ ወጣት ደግሞ እንደ ዶሮ አስካካ። የለቀለው ነገር አይነሣ! ሰዎች እንዲህ አምርረው ሲያለቅሱ አይቼ አላውቅም። በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ያጋጠማቸው አሳዛኝ ነገር ሁሉ የታወሳቸው ይመስል ከፉኛ አለቀሱ..."*

እንደሚታወቀው፥ ይህ ቅዱስ ሳቅ "ቶሮንቶ ብለስንግ" ከተባለው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ የእንቅስቃሴው ዋንኛ አራማጆችም ጆን ዊምበርና በ1987 ከደቡብ አፍሪካ ወደ አሜሪካ የተጓዘው ሮድኒ ሆዋርድ ብሮውን ናቸው። ምናልባትም አንባቢዎቼ፥ "ታዲያ ይህንን ከእምነት እንቅስቃሴ ጋር ምን አዛመደው?" የሚል ጥያቄ ሊፈጠርባቸው ይችላል። እኔም ለዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በከፊል ምላሽ ለመስጠት በማሰብ ነበር የእምነት እንቅስቃሴ መጽሔት "ዎርድ ኦፍ ፌይዝ" ስለ ቅዱስ ሳቅ የዘገበውን በመጥቀስ ምዕራፉን የጀመርሁት። የእምነት እንቅስቃሴ አባላትና ካሪዝማቲኮች ከሚለማመዱቸው ነገሮች አንዱ ስለሆነ፥ አጠር አድርገን እንመለከታለን።

## በክርስትና የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ

"ካሪዝማ" የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን፥ እንደ ፖለቲካዊ ክድሬ ወይም ሹም ሰዎችን መማረክ የሚችል ስብእና ያለውን ግለሰብ ያመለክታል። በግሪክ

እንደሚታወቀው፥ ይህ ቅዱስ ሳቅ "ቶሮንቶ ብለስንግ" ከተባለው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሲሆን፥ የእንቅስቃሴው ዋንኛ አራማጆችም ጆን ዊምበርና በ1987 ከደቡብ አፍሪካ ወደ አሜሪካ የተጓዘው ሮድኒ ሆዋርድ ብሮውን ናቸው። ምናልባትም አንባቢዎቼ፥ "ታዲያ ይህንን ከእምነት እንቅስቃሴ ጋር ምን አዛመደው?" የሚል ጥያቄ ሊፈጠርባቸው ይችላል። እኔም ለዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በከፊል ምላሽ ለመስጠት በማሰብ ነበር የእምነት እንቅስቃሴ መጽሔት "ዎርድ ኦፍ ፌይዝ" ስለ ቅዱስ ሳቅ የዘገበውን በመጥቀስ ምዕራፉን የጀመርሁት። የእምነት እንቅስቃሴ አባላትና ካሪዝማቲኮች ከሚለማመዱቸው ነገሮች አንዱ ስለሆነ፥ አጠር አድርገን እንመለከታለን።

## በክርስትና የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ

"ካሪዝማ" የእንግሊዝኛ ቃል ሲሆን፥ እንደ ፖለቲካዊ ካድሬ ወይም ሹም ሰዎችን መማረክ የሚችል ስብእና ያለውን ግለሰብ ያመለክታል። በግሪክ ቋንቋም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ተጽፎ የሚገኝ ሲሆን፥ ዶ/ር ፒተር ኮትሬል እንደሚሉት ካሪዝማቲኮች እውቀታቸውን ሳይሆን ልምምዳቸውን ለማጉላት ሲሉ አዘውትረው ይጠቀሙበታል። ከዘመናዊ የካሪዝማቲክ ቡድኖች የመጀመሪያው ፔንተኮስታል እንቅስቃሴ ሲሆን፥ የተጀመረውም በ1901 በቶፒካም ካንሳስ ነበር። የእንቅስቃሴው መሪ ሲኤፍ ፒርሃም የተባለ የሜተዲስት አገልጋይ ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት አግኝቶ በልሳን መናገር እንደጀመረ ገልጾአል። በአሱሳ ጎዳና ይካሄድ የነበረው የመነቃቃት ልምምድ ለእንቅስቃሴው ዝና በማትረፉ፥ የፔንተኮስታል ቤተ ክርስቲያን ልትስፋፋ ችላለች።

በ1960 ዓ.ም. እንቅስቃሴው አዲስ አቅጣጫ ይይዝ ጀመር። በዚህ ጊዜ በአሜሪካ አገር ኤጲስ ቆጶሳዊ አገልጋይ የሆኑት ዲ. ቤነት ይህንኑ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን የመናገር ልምምድ እንዳገኙ ተናገሩ። ልምምዱ ወደ ሌሎች ወንጌል አማኝ አብያተ ክርስቲያናት በመስፋፋቱ ኒዎ-ፔንተኮስታሎች ወይም ካሪዝማቲኮች ተብለው ይጠሩ ጀመር። በቀጣዩ ዓመት የተጀመረው የሙሉ ወንጌል የነጋዴዎች ኅብረት ካሪዝማቲክ ንድፈ-አሳቦችንና ልምምዶችን በዓለም ሁሉ ለማዳረስ ዐቀደ።

ይሁንና፥ በ1979 ዓ.ም. በደቡብ አፍሪካ የተጀመረው የቶሮንቶ ብለሲንግ እነዚህን እንቅስቃሴዎች ጋርዶአል። ከላይ እንደተገለጸው የእንቅስቃሴው መሥራች ሆዋርድ-ሮድኒ የተባለ የአሥራ ሰባት ዓመት ወጣት ነበር። በ1980 ዓ.ም. የመጀመሪያው በመንፈስ መታረድ ተከሰተ! ከአሥር ዓመታት በኋላ ወጣቱ ወደ አሜሪካ ተጓዘ። በዚህ ወጣት አገልግሎት ውስጥ ሰዎች በልሳን መናገር፥ በመንፈስ መታረድ፥ ከመሬት ጋር መጣበቅ፥ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሳቅ መሳቅና መንቀጥቀጥ የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ያሳዩ ነበር።

በ1990 ሮድኒ የቤንሂን ቤተ ክርስቲያን ወደምትገኝበት ወደ ኦርላንዶ፥ ፍሎሪዳ ተጋበዘ። እዚያም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ይካሄዱ ጀመር። ከዚያ በኋላ በብልጽግና ሰባኪነታቸው የታወቁት ኬነት ኮፕላንድና ኦራል ሮበርትስ

ነኝ፥" ወይም "አይደለሁም!" ብሎ መመለስ ሲቻል፥ ራሴን የአንድ ካምፕ ወይም ፈርጅ አካል አድርጌ አልመለከትም ማለቱ ከእውነት ጋር ለመፋጠጥ መሸሹን ያሳየናል።

ሆነም ቀረ የቶሮንቶውን ብለሲንግ የሚተቹ ጸሐፊዎች ሮድኒ ከእምነት እንቅስቃሴ ጋር ዝምድና እንዳለው ይናገራሉ። ከዚህም ከፍ ብሎ ከእነ ኬነት ሐገን ጋር የነበረው ጠንካራ ግንኙነት መገለጹ የቶሮንቶውን ብለሲንግ ከእምነት እንቅስቃሴ ጋር የሚያወዳጅ ነው። ለምሳሌ፥ አላን ሞሪሰን በደቡብ አፍሪካ ከሚገኘው የሬማ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ የኬነት ሐገንንና የኬንየንን አሳቦች እንደያዘ ገልጧል። ሞሪሰን ሲጽፍ፥ "ተገኘበት ከሚባለው ጥቅም ባሻገር፥ የቶሮንቶው ብለሲንግ ከነዚያ ጽልመታም መንፈሳዊ ምንጮች እንደ ተቀዳ ይታወቃል" ብሏል።

## *የቶሮንቶ ብለሲንግ ስብሰባዎች ምን ይመስላሉ?*

በዚህ በካናዳ አገር ቶሮንቶ ከተማ በተጀመረው 'የሳቅ ሪቫይቫል' ውስጥ እንደ ስብሰባው መሪና እንደ ተሳታፊዎቹ የተለያዩ ትእይንቶች እንደሚስተዋሉ ቢታመንም፥ አዚያው ቶሮንቶ የኦንታሪዮ ቲዎሎጂካል ሰሚናሪ ፕሮፌሰር የሆኑት ጄምስ በቬርሊ አራት ዋና ዋና ድርጊቶች እንደሚፈጸሙ በመጽሐፋቸው ውስጥ ጠቅሰዋል።

1. ስብሰባው የሚጀመረው ለአንድ ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ በሚቆይ የጉባኤ መዝሙር ነው። ይኸው የምስጋናና የአምልኮ ጊዜ የሚመራው ጀርሚ ሲኖት በተባለ ግለሰብ ኃላፊነት ሥር በሚሠራ የመዘምራን ቡድን ነው። በዚህ ጊዜ ተጋባዥ ዘማሪም እንደ ሁኔታው ሊቀርብ ይችላል። በዚህ ወቅት የተለያዩ ክስተቶች ወይም የሳቅና የስሚታዊነት ሁኔታዎች ሊስተዋሉ ይችላሉ። በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ለምስጋና ሲዘረጉ፥ ሌሎች ደግሞ ዳንሳቸውን ያስነካሉ። ቅዱስ ሳቅ ወይም ከዚህ በላይ እንግዳ የሆኑ ክስተቶች ማለትም እንደ መንቀጥቀጥ፥ እንደ አንበሳ ማጓራት ወይም ከፍተኛ ጩኸት የመሳሰሉ ነገሮች ሊታዩ ይችላሉ።

2. ቀጣዩ የምስክርነት ጊዜ ይሆናል። ጆን ኤርነት ወይም ሌሎች የቪንየርድ መሪዎች ሰዎች ወደ ምስባኩ መጥተው እግዚአብሔር በሕይወታቸው ስላደረገው ነገር እንዲናገሩ ይጋብዛሉ። እነዚህ ተጋባዦች አስደናቂ የተሐድሶ፥ የፈውስ ወይም የመለወጥ ታሪክ ስለሚናገሩ፥ ይህ የምስክርነት ጊዜ ባብዛኛው በጣም አስገራሚ ሆኖ ይታያል። ሰዎቹ ምስክርነታቸውን በሚሰጡበት ጊዜ አንዳንድ ምልክቶችን የሚያሳዩ ሲሆኑ፥ ብዙውን ጊዜ በምስክርነታቸው ፍጻሜ ላይ ተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ ይፈልጉ እንደሆነ ይጠየቃሉ። በዚህም ጊዜ የእንቅስቃሴው መሪዎች ለግለሰቡ ይጸልዩለትና "በመንፈስ ይታረዳል።" (ይህ በመንፈስ መታረድ የሚባለው ቀደም ሲል ሐገን ሚስታቸውና የሌላ መጋቢ ሚስት

ቅዱስ ሳቅ ወይም ከዚህ በላይ እንግዳ የሆኑ ክስተቶች ማለትም እንደ መንቀጥቀጥ፥ እንደ አንበሳ ማጓራት ወይም ከፍተኛ ጩኸት የመሳሰሉ ነገሮች ሊታዩ ይችላሉ።

2. ቀጣዩ የምስክርነት ጊዜ ይሆናል። ጆን ኤርነት ወይም ሌሎች የቪንየርድ መሪዎች ሰዎች ወደ ምስባኩ መጥተው እግዚአብሔር በሕይወታቸው ስላደረገው ነገር እንዲናገሩ ይጋብዛሉ። እነዚህ ተጋባዦች አስደናቂ የተሐድሶ፥ የፈውስ ወይም የመለወጥ ታሪክ ስለሚናገሩ፥ ይህ የምስክርነት ጊዜ ባብዛኛው በጣም አስገራሚ ሆኖ ይታያል። ሰዎቹ ምስክርነታቸውን በሚሰጡበት ጊዜ አንዳንድ ምልክቶችን የሚያሳዩ ሲሆኑ፥ ብዙውን ጊዜ በምስክርነታቸው ፍጻሜ ላይ ተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ ይፈልጉ እንደሆነ ይጠየቃሉ። በዚህም ጊዜ የእንቅስቃሴው መሪዎች ለማለሰቡ ይጸልዩለትና "በመንፈስ ይታረዳል።" (ይህ በመንፈስ መታረድ የሚባለው ቀደም ሲል ሐገን ሚስታቸውና የሌላ መጋቢ ሚስት አገልግሎታቸው ከእግዚአብሔር እንደሆነ እስኪያምኑ ድረስ ከወለሉ ላይ ራሳቸውን ስተው እንዲቆዩ አድርጌአለሁ ያሉት ዓይነት ነው።)

3. ሦስተኛው ክፍለ-ጊዜ የሚሰጠው ለስብከት ሲሆን፥ ይህም ከሃያ ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት የሚወስድ ይሆናል። በእንቅስቃሴው የመጀመሪያው ዓመት አምስት ጊዜያት ስብከቱ ከመቅጽበት የተገታ ሲሆን፥ ሌሎች ሁለት ጊዜያት ምንም ስብከት አልነበረም። ሁልጊዜም ባይሆን፥ ስብከቱ በቅዱስ ሳቅ የሚታጀብባቸው ጊዜያት አሉ። ምንም እንኳ የመልእክቱ ጥራት እንደ ሰባኪው የሚለያይ ቢሆንም፥ ብዙውን ጊዜ የሚያተኩሩት በእንቅስቃሴያቸውና ከዚያ ጋር በተያያዙ ታሪኮች፥ ብሎም እንቅስቃሴው በሌሎች የዓለም ክፍሎች እንደ ምን እየተዛመተ እንዳለ በሚቀርቡ ዘገባዎች ላይ ነው።

4. ከዚህ በላይ የተገለጹት የአምልኮው ክፍሎች ባብዛኛው ለሁለት ሰዓታት ያህል የሚከናወኑ ናቸው። ከስብሰባው ፍጻሜ ላይ የደኅንነት ጥሪ የሚቀርብ ሲሆን፥ እዚያ የተገኙትም ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ተሐድሶ እንዲለማመዱ ይጋበዛሉ። በዚህ ጊዜ ሰዎች የአገልግሎት ጊዜ ለመቀበል ወደ ምስባኩ እንዲመጡ ይጋበዛሉ። አንዳንዶም ከአገልጋዮች ቅባትና ጸሎት ለማግኘት ወደ ሌላ ክፍል እንዲሄዱ ይጠየቃሉ። ብዙውን ጊዜ ይኼኛው የምሽት ስብሰባ ክፍል ከሁሉም የበለጠ ጊዜ ይወስዳል። ባመዛኙ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ይጀምርና እስከ ስምንት ወይም አሥር ሰዓት ድረስ ይዘልቃል፤ ባብዛኛው ግን ከ6:30 እስከ 7:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ያልቃል።

በዚሁ ስብሰባ ላይ የአገልጋይነት ባጅ ወይም ምልክት ያላደረጉ ሰዎች ለሌሎች እንዲጸልዩ አይፈቀድላቸውም። ይህም የሆነው የእንቅስቃሴው መሪዎች አንዳንድ ጸሎቶች ትክክል እንዳልሆኑና የውሸት ትንቢቶችም እንደሚነገሩ በመግለጻቸው ነው። ጠንቋዮች እነዚሁኑ የምሽት ስብሰባዎች እየተጸናወቱ እንዳሉ የሚገልጹ ሰዎችም ነበሩ።

*"በሌላ ጊዜ በዚያው ረዥም ሰልፍ ውስጥ ለመቆምና ከጆን ኤርነት የጸሎት ድጋፍ ለማግኘት ፈለግሁ... መንፈስ ቅዱስ በሕይወቴ ውስጥ የፈቀደውን ሁሉ እንዲያደርግ ጠየቅሁ። ጆን እጆቹን በእኔ ላይ በጫነ ጊዜ የተሰማኝ ልዩ ስሜትም ሆነ የተከሰተ ነገር አልነበረም። ከአጠገቤ የነበረች አንዲት ሴት በመንፈስ የታረደች ስትሆን፥ እጄን ዘርግታ ከንዴን ያዘች። እኔ ምናልባት የወንድ ጓደኞቼ የያዙኝ ሲመስለኝ፥ የሴትዮዋ እንደዚህ መሆን አስደመመኝ።"*

ከወለል ላይ የተኛች ሴት የወንድን ክንድ ይዛ ሲታይ፥ ለሌላው የሚያስተላልፈው መልእክት ነበር ግለሰቡን ያሰጋቸው።

ዶክተር ጄምስ እንደገለጹት፥ አንድ የጋዜጠኞች ቡድን ለአውሮፓውያን ቴሌቪዥን ዘገባ እያዘጋጀ ነበር። ጋዜጠኞቹ ቃለ–ምልልስ ካደረጉላቸው ሰዎች መካከል አንዱ፥ የቶሮንቶውን ብለሲንግ የሚደግፍ አንድ የሥነ–ልቦና ምሁር ይገኝ ነበር። ይህ ሰው ከዚህ ስብሰባ ተካፋዮች አሉታዊ ስሜታዊም ሆነ ሥነ–ልቦናዊ አመለካከት ይዞ የሚመጣ ሰው እንደሌለ ገልጧል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በዚህ ስብሰባ አሉታዊ ገጽታዎች ያዘኑና የቆሰሉ ሰዎች በርካታ ናቸው። አንድ የስብሰባው ተካፋይ እንደተናገሩት፥ ልክ እንደ ውሻ የሚልከሰከስም ሰው አጋጥሟቸዋል። ይህም ብቻ አይደለም ሰውዬው አንድ እግሩን ብድግ አድርጎና እጆቹን ወደ መሽኒያው ልኮ፥ ሽንቱን ለማፍሰስ የተዘጋጀ ይመስል ነበር።

የሳቅ ሪቫይባል መሥራች ከሆኑት አንዱ ይህንኑ እንደ ውሻና አንበሳ ስለ መጮህ አስመልክቶ ሲናገር፥ "በመጀመሪያ ደረጃ በስብሰባዎቻችን ምንም ዓይነት የውሻ ወይም የአንበሳ ጩኸት አናሰማም። ልክ እንደ ውሻ የምትጮህ ከሆነ፥ የውሻ ምግብ እንሰጥሃልን። እንደ አንበሳ የምታገሳ ከሆነ፥ አንበሶች ወደሚጠበቁበት ዙ እንልክሃለን። እንደ ዶሮ ብታስካካ ደግሞ፥ ጥራጥሬ እንበትንልሃለን። ይህን ያልሁት ሰዎች ስብሰባ የራሱ ሥርዓት እንዳለው እንዲገነዘቡ ነው" ብሏል።

"እንደ አንበሳ መጮህ ትንቢታዊ ምልክት ነው የምትሉትስ ጉዳይ?" ተብሎ ሲጠየቅ እንዲህ ነበር ያለው።

*"አንድ ጊዜ ጓደኛዬ እያገለገለ ሳለ አንድ ሰው እንደ አንበሳ እያገሳ መጥቶ፥ 'እኔ የይሁዳ አንበሳ ነኝ' አለ። ጓደኛዬም ቀና ብሎ ከተመለከተው በኋላ፥ 'መልካም፥ እኔ ደግሞ አንበሳን አየገራሁ አስለምዳለሁ። አርፈህ ቁጭ በል! ብሎታል። ይሁንና፥ በቶሮንቶ እየተደረገ ስላለው ነገር ደስተኛ ስለሆንሁ፥ በዚህ ጉዳይ ከቶሮንቶዎች ጋር ለመጨቃጨቅ አልፈልግም።"*

ሮድኒ ያላስተዋለው ግን እውነተኛውን ነገር መፈለግና ከሁሉም ሰው ጋር ተስማምቶ መኖር እንደማይቻል ነው። እውነትን የምንወድ ከሆነ፥ የእውነት ጠላቶች የሚያደርሱብንን ጥቃት መፍራቱ እርባና የለውም!

ስብከቱ ለምን በቅዱስ ሳቅ እንዲታፈን እንደሚፈቅድ በተጠየቀበት ወቅት፥ ሮድኒ ጴጥሮስ ቃሉን ሲናገር መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደ የሚያስረዳውን

"እንደ አንበሳ መፎጎህ ትንቢታዊ ምልክት ነው የምትሉትስ ጉዳይ?" ተብሎ ሲጠየቅ እንዲህ ነበር ያለው።

*"አንድ ጊዜ ጓደኛዬ እያገለገለ ሳለ አንድ ሰው እንደ አንበሳ እያገሳ መጥቶ፥ 'እኔ የይሁዳ አንበሳ ነኝ' አለ። ጓደኛዬም ቀና ብሎ ከተመለከተው በኋላ፥ 'መልካም፥ እኔ ደግሞ አንበሳን እየገራሁ አስለምዳለሁ። አርፈህ ቁጭ በል! ብሎታል። ይሁንና፥ በቶሮንቶ እየተደረገ ስላለው ነገር ደስተኛ ስለሆንሁ፥ በዚህ ጉዳይ ከቶሮንቶዎች ጋር ለመጨቃጨቅ አልፈልግም።"*

ሮድኒ ያላስተዋለው ግን እውነተኛውን ነገር መፈለግና ከሁሉም ሰው ጋር ተስማምቶ መኖር እንደማይቻል ነው። እውነትን የምንወድ ከሆነ፥ የእውነት ጠላቶች የሚያደርሱብንን ጥቃት መፍራቱ አርባና የለውም!

ስብከቱ ለምን በቅዱስ ሳቅ እንዲታፈን እንደሚፈቅድ በተጠየቀበት ወቅት፥ ሮድኒ ጴጥሮስ ቃሉን ሲናገር መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደ የሚያስረዳውን የሐዋርያት ሥራ 10፡44ን ክፍል በመጥቀስ፥ የርሱም ጉዳይ ከዚያ አንጻር መታየት እንዳለበት ይገልጻል።

በአዲስ አበባችንም ይህንኑ ልምምድ የሚከተሉ ሰዎች የሚያሰሟቸው ሁከቶች እንኳንስና በአዳራሹ ውስጥ ያለውን፥ ከቤቱ የተቀመጠውን የአካባቢውን ሰው የሚያስጭንቁ እንደሆነ ነዋሪዎቹን በመጠየቅ ልረዳ ችያለሁ። የእምነቱ ተከታዮች የሚያሰሙትን ያልተለመደ ድምፅ ለመለየት የተቸገሩት አንዲት የአካባቢው የቤት እመቤት፥ "ይኼ ሰው ነው ወይስ ጅብ?" ሲሉ መደመጣቸውን ከአንዲት ወጣት ምስክርነት ልረዳ ችያለሁ።

እንደ ሐና የልባችንን ለአምላካችን በዝግታ መናገርስንችል፥ በጩኸታችን ብዛት የአምላክን ክንድ የምንቀሰቅስ ይመስል የአካባቢውን ጸጥታ ማደፍረሱ ተገቢ አይመስለኝም። የምንጸልየው የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ለሆነው እግዚአብሔር ከሆነ፥ ገና ሳንናገር የልባችንን እንደሚያውቅ ልብ ልንል ያሻል። አሰፋ ደስታና ፍስሐ በየነም እንደሚከተለው ተመሳሳይ ገጠመኝ አውግተዋል።

*"የተለያዩ ዓይነት ሰዎች ተገኝተዋል። ሥርዓትና ሕግ መንፈሳዊነት አይደለም ማለታቸውን ገና ከአለባበሳቸው ለማወቅ ጊዜ አልወሰደብኝም። የፀጉር አቆራረጣቸው በፈለጉት መንገድ የተዘበራረቀ ነበር። ከዚህ በፊት ስለነዚህ ሰዎች የሰማሁትንና ያነበብሁትን አስታወስሁ። ማየት ማመን ነውና ከዓይኔ ሌላ እማኝ አላስፈለገኝም። ጉባኤው በከፍተኛ ትርምስ ተሞልቷል። ስፖርታዊ የአካል እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ይመስል ከአንዱ ወንበር ወደ ሌላው የሚዘሉት ብዙዎች ናቸው። መድረኩ ላይ የሚታየውም የዘፈን ትርዒት ነው የሚመስለው። አዳራሹ የሙዚቃ ትርዒት የሚታይበት ቢመስልም አልፎ አልፎ መጽሐፍ ቅዱስ የያዙና ከዚህ በፊት የማውቃቸው ሰዎችም ነበሩ። የጆሮ ታምቡር በሚበጥስ አስፈሪና አሰደንጋጭ ድምፅ ጉባኤው 'ኡ...ኡ...ኡ...ዋ...ይ...ይ' ብሎ ሲጮኽ መሪው በማጨብጨብ አስቆመና መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍቶ፥ 'እግዚአብሔር ከተማዪቱን ሰጥቷችኋልና ጩኹ' (ኢያሱ 6፡16) የሚለውን አነበበ። ቶጩቱና ጩኸቱ ቀጠለ።*

ልብንና ኩላሊትን የሚያውቅ አምላክ ብቻ ነው። ጥያቄዬ ለእግዚአብሔር ክብር የግድ በዘመናዊው የሬጌ ስልት መደነስ አለብን ወይ ነው? ባህላዊው ሽብሸባችንን እግዚአብሔር አይወደውም ይሆን?

የወንጌል ስርጭት የተጠበቀውን ያህል እንዳይሮጥ ከተከላከሉት ነገሮች መካከል አንዱና ዋናልባትም ዋናው የወንጌል ስርጭት መዝሙሮቻችን ምዕራባዊውን ስልት የሚከተሉና ዘፈን የሚመስሉ መሆናቸው ነው። ይህም ከበገናና ከከበሮ በቀር ሌላው የሙዚቃ መሣሪያ ሁሉ ኃጢአት ለሚመስላቸው ወገኖች የወንጌሉን ተቀባይነት በእጅጉ ይጎዳዋል። ከብዙዎች አስተያየት እንደምሰማው፥ የዘማሪ ደረጀ ከበደን ተቀባይነት ከፍ ካደረጉት ነገሮች መካከል በዘመናዊ መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆን እንደ ማሲንቆና ጸናጽል በመሳሰሉ ባህላዊ መሣሪያዎች መገልገሉ ነው።

ለእኛም እንደ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች የሚያስፈልገን ሽብሸባ እንደሆነ እንጂ 'ዳንስ' ሊሆን አይገባም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ) በዓለም ከምትታወቅባቸው ትውፊቶች አንዱ የራሷ የሆነ አገራዊ ዝማሬ ያላት መሆኑ ነው። ይህም ብዙዎቻችን የምንወደው ያሬዳዊ ዝማሬ ነው። ያሬዳዊ ዝማሬ ለብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጆሮ የሚሰጠው ምልክት ቀውስ፥ ዳንስ፥ ወይም ጭፈራ ሳይሆን አምልኮ ነው። ብዙዎቻችን የበገናን ስንትርትር ዜማ ስንሰማ ልባችን ይቀልጣል። እንግዲያው፥ እግዚአብሔር በባህላችን ውስጥ ባስቀመጠው በዚህ መልካም ነገር ተጠቅመን ለማገልገልና ለማነጽ ብንሞክር መልካም ይመስለኛል – ቀናነት ካለን!

## *የሳቅ ሪቫይቫል አወዛጋቢ ገጽታዎች*

ይህንኑ እንቅስቃሴ አስመልክተው አንድ ግለሰብ ሲጽፉ፥ "ወንዶችና ሴቶች በአንድነት ከወለሉ ላይ ተነጥፈው ሲንጫጩ፥ ሲጮዋጮዋሁ፥ ቅዱስ ሳቅ ሲስቁና ሲነካኩ ይታያችሁ!" ብለዋል። እንደ እርሳቸው ምስክርነት፥ የሳቅ ሪቫይቫል አገልጋዮችም ሳይቀሩ ተቃቅፈውና ተደጋግፈው ይታያሉ። እንዲያውም፥ የሳቅ ሪቫይቫል ተሳታፊዎች እንዲህ ዓይነቱን ከሰው ጋር መደጋገፍ ችላ እንዳይሉ መሪዎቹ ይናገራሉ። ለዚህ ዶክተር ጀምስ የሚጠቅሱት ምሳሌ አላቸው።

*"ለምሳሌ፥ ራብዲ ክላርክ 'እሳቱን ያዙ' በተባለው ኮንፍረንስ ላይ ቅባቱ በሚመጣበት ጊዜ ሰዎቹ የሚይዙት ሰው እንዳላቸው ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ገልጸአል። ለዚህም አባባሉ በአስረጅነት ያቀረባት ይህንኑ ትእዛዝ የጣሰችውን የአንዲት የፍሎሪዳ ሴት ታሪክ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በእርሷ ላይ በወረደ ጊዜ ወደ ኋላ በመወድቋ፥ ጭንቅላቷ ከግድግዳ ጋር ተላተመ! ከዚያም ለአንድ ሳምንት ሆስፒታል ተኛች።"*

ዶክተሩ ይህንን ታሪክ ከጻፉ በኋላ፥ "እውን ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ሊባል ነው? ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው?" ሲሉ ጠይቀዋል። ለመሆኑ

እንዲያውም፥ የሳቅ ሪቫይቫል ተሳታፊዎች እንዲህ ዓይነቱን ከሰው ጋር መደጋገፍ ችላ እንዳይሉ መሪዎቹ ይናገራሉ። ለዚህ ዶክተር ጀምስ የሚጠቅሱት ምሳሌ አላቸው።

*"ለምሳሌ፥ ራብዲ ክላርክ 'እሳቱን ያዙ' በተባለው ኮንፍረንስ ላይ ቅባቱ በሚመጣበት ጊዜ ሰዎቹ የሚይዙት ሰው እንዳላቸው ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ገልጸአል። ለዚህም አባባሉ በአስረጅነት ያቀረባት ይህንኑ ትእዛዝ የጣሰችውን የአንዲት የፍሎሪዳ ሴት ታሪክ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በእርሷ ላይ በወረደ ጊዜ ወደ ኋላ በመወድቋ፥ ጭንቅላቷ ከግድግዳ ጋር ተላተመ! ከዚያም ለአንድ ሳምንት ሆስፒታል ተኛች።"*

ዶክተሩ ይህንን ታሪክ ከጻፉ በኋላ፥ "እውን ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ሊባል ነው? ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው?" ሲሉ ጠይቀዋል። ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ሲመጣ ታላቅ ፈውስ ያመጣል ወይስ ለሆስፒታል ይዳርጋል?

ጀኒስ የተባለችው ባለቤቱ ከሳቅ በስተቀር ምንም ነገር ለማድረግ ዓቅም ያጣችበትንም ሁኔታ ጸሐፊው በመጽሐፋቸው ውስጥ ዘግበዋል።

